In a few instances, there are two or three characters for the same Amharic syllable. These characters contrasted with each other in Geez, but are more or less interchangeable in Amharic.

To put it another way, there are alternative spellings for certain Amharic words.

1) 1, 3 and 13, i.e. ሀ , ሐ and ኀ are /ha/; ሁ , ሑ and ኁ are /hu/; ሂ , ሒ and ኂ are /hi/, etc.

2) 5 and 7, i.e. ሠ and ሰ are /se/; ሡ and ሱ are /su/, etc.

3) 16 and 20, i.e. አ and ዐ are /a/; ኡ and ዑ are /u/, etc.

4) 30 and 31, i.e. ጸ and ፀ are /Se/, ጹ and ፁ are /Su/, etc.

Note that the vowel of /gi'iz/ and that of /rabi/ in ሀ , ሐ , ኀ , አ and ዐ is the same, i.e.

ሀ or ሃ = /ha/
ሐ or ሓ = /ha/
ኀ or ኃ = /ha/
አ or ኣ = /a/
ዐ or ዓ = /a/

Note also that in modern Amharic character 18 ኸ is written in the first order /gi'iz/ only. Syllables /hu/, /hi/, /ha/, /he/, /hi/ and /ho/ are represented by 1, 3 or 13.

All symbols listed under the sixth order (/sadis/) may represent either a consonant followed by the vowel /i/, or a consonant only, e.g. may be /hi/ or /h/; ብ may be /bi/ or /b/; ን may be /ni/ or /n/, etc.

The doubling of consonants is not indicated in the writing system, e.g. the word አለ may be read /ale/ 'he said', or /alle/ 'there is'; አባይ /abay/ 'a liar' or /abbay/ 'Nile'; ገና /gena/ 'yet' or /genna/ 'Christmas', etc. The meaning is determined by the context.

A closer examination of the Amharic Syllabary shows that the majority of characters are predictable modifications of their basic form, i.e. from the first order /gı'ız/. Thus the second order /ka'ıb/ is characterized by a hooked dash /⁊/ usually attached to the center of the right side of the character, e.g.

I	II
/gı'ız/	/ka'ıb/
ሀ /ha/	ሁ /hu/
መ /me/	ሙ /mu/
በ /be/	ቡ /bu/

etc.

In /salıs/ (order III) a similar dash is attached to the bottom part of the right side of the character or to its extension, e.g.

I	III
/gı'ız/	/salıs/
ሀ /ha/	ሂ /hi/
መ /me/	ሚ /mi/
በ /be/	ቢ /bi/
አ /a/	ኢ /i/

Characters of the fourth order /rabı/ have three basic patterns:

a) The ones which are two- or three-legged in the basic form have the right leg extended, e.g.

I	IV
/gı'ız/	/rabı/
ለ /le/	ላ /la/
በ /be/	ባ /ba/

ዘ /ze/	ዛ /za/
ሐ /ha/	ሓ /ha/

etc.

b) One legged characters in the basic form acquire a kind of hook attached to the leg, e.g.

I /gı'ız/	IV /rabı/
ተ /te/	ታ /ta/
ገ /ge/	ጋ /ga/
ፐ /pe/	ፓ /pa/
ነ /ne/	ና /na/

etc.

c) A leg is attached to originally legless characters, e.g.

I /gı'ız/	IV /rabı/
ሀ /ha/	ሃ /ha/
ሠ /se/	ሣ /sa/
ወ /we/	ዋ /wa/
ፀ /Se/	ፃ /Sa/

etc.

The fifth order (/hamıs/) is characterized by a small semi circle attached to the right leg of the character or to its extension, e.g.

I /gı'ız/	V /hamıs/
በ /be/	ቤ /be/
ተ /te/	ቴ /te/
ነ /ne/	ኔ /ne/
ጠ /Te/	ጤ /Te/
ወ /we/	ዌ /we/

etc.

The characters of the sixth and seventh orders (i.e. /sadis/ and /sabi/) are less predictable. Thus /sadis/ may be characterized either by a zigzag, e.g.

I		VI	
/gi'iz/		/sadis/	
ሀ	/ha/	ህ	/hi/
አ	/a/	እ	/i/
ከ	/ke/	ክ	/ki/
ጠ	/Te/	ጥ	/Ti/
ፐ	/pe/	ፕ	/pi/

or by a hooked dash at the left side of the character, e.g.

I		VI	
/gi'iz/		/sadis/	
በ	/be/	ብ	/bi/
ሐ	/ha/	ሕ	/hi/
ዘ	/ze/	ዝ	/zi/

some characters of this order have the dash attached to the right side, e.g.

I		VI	
/gi'iz/		/sadis/	
ደ	/de/	ድ	/di/
ሸ	/Se/	ሽ	/Si/
ወ	/we/	ው	/wi/

Characters 20 and 31 have a vertical line attached to the top:

I		VI	
/gi'iz/		/sadis/	
ዐ	/a/	ዕ	/i/
ፀ	/Se/	ፅ	/Si/

A few characters change theır shape ın the sıxth order ın varıous unpredıctable ways, e.g.

I /gı'ız/	VI /sadıs/
ለ /le/	ል /lı/
መ /me/	ም /mı/
ሠ /se/	ሥ /sı/
ረ /re/	ር /rı/
ሰ /se/	ስ /sı/
የ /ye/	ይ /yı/
ገ /ge/	ግ /gı/
ፈ /fe/	ፍ /fı/

The seventh order /sabı/ may have eıther a longer left leg, e.g.

I /gı'ız/	VII /sabı/
ሐ /ha/	ሖ /ho/
ሰ /se/	ሶ /so/
በ /be/	ቦ /bo/
ደ /de/	ዶ /do/

etc.

or a small semı cırcle (or cırcle) attached to the upper or the mıddle part of the character, e.g.

I /gı'ız/	VII /sabı/
ሀ /ha/	ሆ /ho/
ለ /le/	ሎ /lo/
ረ /re/	ሮ /ro/
ቀ /Ke/	ቆ /Ko/

ተ /tə/	ቶ /to/
ነ /nə/	ኖ /no/
ገ /gə/	ጎ /go/
etc.	

or a leg inclined toward the left, e.g.

I	VII
/gı'ız/	/sabı/
ዐ /a/	ዖ /o/
ሠ /sə/	ሦ /so/
ወ /wə/	ዎ /wo/
ፀ /Sə/	ፆ /So/

Finally, the seventh order of the character የ /yə/ is ዮ /yo/ and that of the character መ /mə/ is ሞ /mo/.

አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጤና፡ ይስጥልኝ፡	ጤና፡ ይስጥልኝ፡ እንደምን፡ አደሩ።
ደህና፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን። እንደምን፡ አደሩ።	
አማርኛ፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ አውቃለሁ። የለም፡ አላውቅም። ትንሽ፡ አውቃለሁ።
ምን፡ አሉ?	ምንም፡ አላለሁ።

ቃላት

እንደገና
ይድገሙት
ልክ፡ ነው
ልክ፡ አይደለም
በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
እንረፍ።

ሁለተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

አባክዎ፣ ያሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ የት፡ ነው?	ፊት፡ ለፊት፡ ነው። ሩቅ፡ ነው። ያሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ በስተቀኝ፡ ነው። በስተግራዎ፡ ነው። ወደፊት፡ ይሂዱና፡ ወደ፡ ግራ፡ ይዞሩ። ቅርብ፡ ነው።
ባቡር፡ ጣቢያው፡ የት፡ ነው?	
ባቡር፡ ጣቢያው፡ ከዚህ፡ ሩቅ፡ ነው?	ሩቅ፡ አይደለም፡ ቅርብ፡ ነው።
ዳህና፡ ሆቴል፡ የት፡ አለ?	አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ፊት፡ ለፊት፡ ዳህና፡ ሆቴል፡ አለ። ሆቴሉ፡ እዚያ፡ ነው።

ቁጥሮች

አንድ (፩)፣ ሁለት (፪)፣ ሦስት (፫)፣ አራት (፬)፣ አምስት (፭)፣ ስድስት (፮)፣ ሰባት (፯)፣ ስምንት (፰)፣ ዘጠኝ (፱)፣ አሥር (፲)።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ጤና፡ ይስጥልኝ፡ እንደምን፡ አደሩ?	ደህና፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን።
እባክዎ፡ አንድ፡ ደህና፡ ሆቴል፡ የት፡ አለ?	ደህና፡ ሆቴል፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ፊት፡ ለፊት፡ አለ።
ሆቴሉ፡ ሩቅ፡ ነው?	የለም፡ ሩቅ፡ አይደለም።
አማርኛ፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ ትንሽ፡ አውቃለሁ።
ምን፡ አሉ?	ምንም፡ አላልሁ።
ባቡር፡ ጣቢያው፡ እዚያ፡ ነው?	የለም፡ እዚያ፡ አይደለም።
አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ከዚህ፡ ሩቅ፡ ነው?	ሩቅ፡ አይደለም፡ ቅርብ፡ ነው።
በጣም፡ ጥሩ፡ አማርኛ፡ ያውቃሉ?	የለም፡ በጣም፡ ጥሩ፡ አይደለም።
ከዚህ፡ በስተግራ፡ ምን፡ አለ?	አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ሆቴል፡ አለ።
ከዚህ፡ በስተቀኝ፡ ምን፡ አለ?	ከዚህ፡ በስተቀኝ፡ አንድ፡ ኤምባሲ፡ አለ።
ባቡር፡ ጣቢያው፡ ሩቅ፡ ነው?	አዎ፡ በጣም፡ ሩቅ፡ ነው።
ሆቴሉ፡ ትንሽ፡ ነው?	አዎ፡ በጣም፡ ትንሽ፡ ነው።
ባቡር፡ ጣቢያው፡ የት፡ አለ?	አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ፊት፡ ለፊት፡

	እንዴ፡ ገቡር፡ ግቢያ፡ እሱ።
ከዚህ፡ ሩቅ፡ ነው?	የለም፡ ሩቅ፡ አይደለም፡ ቅርብ፡ ነው።
አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ የት፡ ነው?	አላውቅም።

ሦስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ ስሜ፡ ዮሐንስ፡ ነው። የርስዎስ?

ከበደ

ከበደ፡ ነው። ኢትዮጵያዊ፡ ነዎ?

ዮሐንስ

አሜሪካዊ፡ ነኝ። ነገር፡ ግን፡ አቶ፡ ተሰማና፡ አቶ፡ ከማ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ ናቸው።

ከበደ

መቼ፡ መጡ?

ዮሐንስ

ትናንትና፡ መጣሁ።

ከበደ

እባክዎ፡ ስንት፡ ሰዓት፡ ነው?

ዮሐንስ

ሦስት፡ ሰዓት፡ ነው።

ካበደ

እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ።

ዮሐንስ

አብሮ፡ ይስጠን።

የክፍል፡ ውስጥ፡ ንግግር፡

መጽሐፎቻችሁን፡ ክፈቱ።

አብራችሁ፡ በሉ።

አሁን፡ መጽሐፎቻችሁን፡ ዝጉ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች፡

እኔ፡ አሜሪካዊ፡ ነኝ።

ኢትዮጵያዊ፡ ነህ?

አንቺ፡ ቆንጆ፡ ነሽ።

አስተዋይ፡ ነው። አስተዋይ፡ ነዎት።

ይህ፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?

ጥሩ፡ ሴት፡ ናት። ጥሩ፡ ሴት፡ ነች።

ተማሪዎች፡ ነን።

አስተማሪዎች፡ ናችሁ።

መጥፎ፡ ናቸው።

እርሳቸው፡ ትልቅ፡ ናቸው።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
ስሜ፡ ተሰማ፡ ነው። የርስዎስ?	ጆን፡ ነው።
እርስዎ፡ አሜሪካዊ፡ ነዎ?	እኔ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነኝ።
እዚህ፡ መቼ፡ መጡ?	ትናንት፡ መጣሁ። ትናንትና፡ መጣሁ።
አቶ፡ ለማና፡ አቶ፡ ካበደ፡	አላውቅም።

ጥያቄ	መልስ
መቼ፡ መጡ?	
እርስዎ፡ ተማሪ፡ ነዎ?	አዎ፡ ተማሪ፡ ነኝ።
አማርኛ፡ ያውቃሉ?	ትንሽ፡ አውቃለሁ።
እሷ፡ ቆንጆ፡ ሴት፡ ናት?	አዎ፡ በጣም፡ ቆንጆ፡ ናት።
አቶ፡ ተሰማ፡ ምን፡ ያውቃሉ?	በጣም፡ ጥሩ፡ አማርኛ፡ ያውቃሉ።
አቶ፡ ለማ፡ መጥፎ፡ ሰው፡ ነው?	የለም፤ እሱ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ሰው፡ ነው።
አስተዋይ፡ ነው?	አዎ፡ አስተዋይ፡ ነው።
ሁለትና፡ ሁለት፡ ስንት፡ ነው?	ሁለትና፡ ሁለት፡ አራት፡ ነው።
ሦስትና፡ አራት፡ ስንት፡ ነው?	ሰባት፡ ነው።
አቶ፡ ተሰማ፡ ጤና፡ ነው?	አዎ፡ ደህና፡ ነው።
እነሱ፡ እዚህ፡ ናቸው?	አዎ፡ እዚህ፡ ናቸው።
አስተማሪዎች፡ እዚህ፡ መቼ መጡ?	እኔ፡ አላውቅም።
እዚህ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ መጡ?	ሁለት፡ ሰዎች፡ መጡ።
አቶ፡ ከበደ፡ መጥፎ፡ ነው?	የለም፤ መጥፎ፡ አይደለም።
አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ለማ፡ ተማሪዎች፡ ናቸው?	አዎ፡ እነሱ፡ ተማሪዎች፡ ናቸው።
አቶ፡ ከበደ፡ እዚህ፡ ነው?	እዚህ፡ አይደለም።

ጥያቄ	መልስ
እርስዎ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነዎ?	አዎ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነኝ።
እርስዎስ?	እኔ፡ አሜሪካዊ፡ ነኝ።
አስተማሪ፡ ነዎ?	የለም፤ ተማሪ፡ ነኝ።
አቶ፡ ተሰማ፡ የት፡ ነው?	እዚህ፡ ነው።
መጽሐፉ፡ የት፡ አለ?	እዚህ፡ ነው።
እሷ፡ አስተማሪ፡ ነች?	አዎ፡ አስተማሪ፡ ነች።
እሱ፡ ትልቅ፡ ነው?	የለም፤ ትንሽ፡ ነው።
ስንት፡ ሰዓት፡ ነው?	አስር፡ ሰዓት፡ ነው።
አቶ፡ ከማ፡ ደህና፡ ነው?	አዎ፡ በጣም፡ ደህና፡ ነው።
እዚህ፡ ደህና፡ አስተማሪ፡ አለ?	አዎ፡ አንድ፡ ደህና፡ አስተማሪ፡ አለ።
ደህና፡ አማርኛ፡ ያውቃሉ?	በጣም፡ ጥሩ፡ አይደለም።
አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ጆን፡ እዚህ፡ መቼ፡ መጡ?	ትናንትና፡ መጡ።

አራተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

ዮሐንስ

እባክዎ፡ ደህና፡ ሆቴል፡ ሊያሳዩኝ፡ ይችላሉ?

ከበደ

አዎ፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ ደህና፡ ይመስለኛል።

ዮሐንስ

አድራሻው፡ የት፡ ነው?

ከበደ

በታክሲ፡ መሄድ፡ ይችላሉ።

ዮሐንስ

እሺ፡ ታክሲ፡ እጠራለሁ።

ታክሲ፡ ነጂ፡

አቤት፡

ዮሐንስ

እባክዎ፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ ያድርሱኝ። ስንት፡ ልክፈልዎት?

ታክሲ፡ ነጂ

አራት፡ ብር።

የክፍል፡ውስጥ፡ ንግግር፡

ይህ፡ ነገር፡ ባማርኛ፡ ምን፡ ይባላል?

እርሳስ፡ አለዎት?

የለኝም።

ብዙ፡ እርሳሶች፡ አለዎት?

የለኝም፡ አንድ፡ ብቻ፡ አለኝ።

ይድገሙልኝ።

ይህን፡ ቃል፡ ይድገሙት።

አማርኛ፡ ይችላሉ?

አዎ፡ እችላለሁ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች፡

ስሜ፡ ከበደ፡ ነው።
አገርህ፡ አሜሪካ፡ ነው።
አባትሽ፡ ረጅም፡ ነው።
ስምዎ፡ ማን፡ ነው?

መጽሐፉ፡ ቀይ፡ ነው።
እናትዎ፡ ቆንጆ፡ ናት።
ስማችን፡ ከበደና፡ ለማ፡ ነው።
አገራችሁ፡ የት፡ ነው?
መኪናቸው፡ ጥሩ፡ አይደለም።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
መጽሐፍ፡ አለዎት?	አዎ፡ አለኝ። የለኝም።
ይህ፡ ተማሪ፡ እርሳስ፡ አለው?	አዎ፡ አለው። የለውም።
ተማሪዎች፡ ብዙ፡ እርሳሶች፡ አላቸው?	አዎ፡ ብዙ፡ እርሳሶች፡ አላቸው። ብዙ፡ እርሳሶች፡ የሏቸውም።
አንተ፡ ብዙ፡ መጽሐፎች፡ አሉህ?	አዎ፡ ብዙ፡ መጽሐፎች፡ አሉኝ። ብዙ፡ መጽሐፎች፡ የሉኝም።
ትምህርት፡ ቤቱን፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ አውቃለሁ። የለም፡ አላውቅም።
መኪና፡ አላት?	አዎ፡ አላት። የላትም።
ሰዓት፡ አለዎት?	አዎ፡ አለኝ። የለኝም።
ጊዮን፡ ሆቴሉን፡ ሊያሳዩኝ፡	አዎ፡ እችላለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ይችላሉ?	
መኪናዎን፡ ሊያሳዩኝ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ እችላለሁ።
አቶ፡ ከበደ፡ መኪና፡ አለው?	አዎ፡ አለው። የለውም።
አባትና፡ እናት፡ አሉህ?	አዎ፡ አሉኝ። የሉኝም።
ጊዮን፡ ሆቴል፡ ለማም፡ ሩቅ፡ ነው?	አዎ፡ ለማም፡ ሩቅ፡ ነው። ለማም፡ ሩቅ፡ አይደለም።
ጊዮን፡ ሆቴል፡ መሄድ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ እችላለሁ።
አስር፡ ብር፡ አለዎት?	አዎ፡ አለኝ። አስር፡ ብር፡ የለኝም።
ቀይ፡ መኪና፡ አለህ?	አዎ፡ አለኝ። መኪና፡ የለኝም።
መኪናዎች፡ አሉዋችሁ?	አዎ፡ አሉን። መኪናዎች፡ የሉንም።
አስተማሪው፡ መኪና፡ አለው?	አዎ፡ አለው። አስተማሪው፡ መኪና፡ የለውም።
ብዙ፡ መኪናዎች፡ አሉት?	አዎ፡ ብዙ፡ መኪናዎች፡ አሉት። ብዙ፡ መኪናዎች፡ የሉትም።
እሷ፡ መጽሐፍ፡ አላት?	አዎ፡ አላት። መጽሐፍ፡ የላትም።
አስተማሪው፡ ደህና፡ ነው?	አዎ፡ ደህና፡ ነው። ደህና፡ አይደለም።

ጥያቄ	መልስ
እርስዎ፡ አማርኛ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ እችላለሁ።
ሰዓትህ፡ መጥፎ፡ ነው?	አዎ፡ መጥፎ፡ ነው። መጥፎ፡ አይደለም።
ጥሩ፡ እርሳስ፡ አለዎት?	አዎ፡ አለኝ። የለኝም።
ጥሩ፡ እርሳሶች፡ አሉዎችሁ?	አዎ፡ አሉን። የሉንም።
አቶ፡ ከበደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ ይችላሉ።
ቀይ፡ መኪና፡ አለህ?	አዎ፡ አለኝ። የለኝም።
እነሱ፡ መኪናዎች፡ አሉዋቸው?	አዎ፡ አሉዋቸው። የሉዋቸውም።
መኪናዎች፡ ጥሩ፡ ናቸው?	አዎ፡ ጥሩ፡ ናቸው።
አባትዎ፡ ጥሩ፡ ሰዓት፡ አላቸው?	አዎ፡ አላቸው። የላቸውም።
መኪናችሁ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው?	አዎ፡ ጥሩ፡ ነው። ጥሩ፡ አይደለም።
ተማሪዎች፡ አማርኛ፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ ያውቃሉ።
አገርህ፡ ሩቅ፡ ነው?	አዎ፡ ሩቅ፡ ነው። ሩቅ፡ አይደለም።
መኪናቸው፡ እዚህ፡ ነው?	አዎ፡ እዚህ፡ ነው። እዚህ፡ አይደለም።

ጥያቄ	መልስ
አስተማሪው፡ ብዙ፡ ተማሪዎች፡ አሉት?	አዎ፡ አሉት። የሉትም።
እኅትዎ፡ እኅቴን፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ ያውቃሉ።
ባቡር፡ ጣቢያው፡ ሩቅ፡ ነው?	አዎ፡ ሩቅ፡ ነው። ሩቅ፡ አይደለም።
አንተ፡ ተማሪ፡ ነህ?	አዎ፡ ተማሪ፡ ነኝ።
ረጅም፡ እርሳስ፡ አለህ?	አዎ፡ አለኝ።
አንድ፡ ረጅም፡ ተማሪ፡ ሊያሳዩኝ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ እችላለሁ።

አምስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ጤና፡ ይስጥልኝ?

እንግዳ፡ ተቀባይ

አዎ፡ አለኝ።

እንግዳ፡ ተቀባይ

ጤና፡ ይስጥልኝ።

ዮሐንስ

ኪራዩ፡ ስንት፡ ነው?

ዮሐንስ

በዚህ፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ ባዶ፡ ክፍል፡ አለዎት?

እንግዳ፡ ተቀባይ

በሳምንት፡ ከሁለት፡ እስካስር፡ ብር፡ ነው።

ዮሐንስ

ክፍሉን፡ ማየት፡ እፈልጋለሁ።

እንግዳ፡ ተቀባይ

እሺ፡ አሳይዎታለሁ።

ዮሐንስ

እባክዎም፤ ኪራዩን፡ ቢነግሩኝ፡
ይህን፡ ክፍል፡ እወስደዋለሁ።

እንግዳ፡ ተቀባይ

በሳምንት፡ ስምንት፡ ብር፡
ነው፤ ጌታዬ።

ዮሐንስ

ዕቃዬን፡ ያስገቡልኝ። ምግብ፡
ቤቱስ፡ የት፡ ነው?

እንግዳ፡ ተቀባይ

አንደኛው፡ ፎቅ፡ ላይ፡ ነው።

ዮሐንስ

እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች።

ወደ፡ ከተማ፡ ሄድሁ።

ቤት፡ ፈለግህ።

ገንዘብ፡ ፈለግሽ።

ሰውዬው፡ እገቶን፡ መኘሬት፡
ፈለገ።

ሴትዮዋ፡ እናትዋን፡ አየች።

ከጠበዳ፡ እንድ፡ ስኒ፡ ቡና፡ ሰጠን።

እናንተ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡
ሄዳችሁ።

ተማሪዎች፡ ምግብ፡ ቤቱን፡ አዩ።

ጥያቄና፡ መልስ።

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ ከበደ፡ እኅትና፡ እናቱን፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ጠሩቸው?	አዎ፡ እሱ፡ ሁለቱን፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ጠሩቸው።
አቶ፡ ተሰማ፡ ወዳሜሪካ፡ መቼ፡ ሄዱ?	ትናንት፡ ሄዱ።
አቶ፡ ተሰማ፡ የት፡ ሆቴል፡ አደሩ?	አጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ አደሩ።
አቶ፡ ከበደን፡ ወደ፡ ሆቴሉ፡ ማን፡ አደረሰው?	አቶ፡ ተሰማ፡ አደረሰው።
አስተማሪዎ፡ ምን፡ አሉኝ?	አስተማሪዎ፡ ተማሪዎቻን፡ ጠሩኝ።
አንተና፡ አቶ፡ ተሰማ፡ የት፡ አደራችሁ?	አጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ አደርን።
እንግዳ፡ ተቀባይ፡ ክፍሉን፡ አሳየሽ?	አዎ፡ ሁለት፡ ጥሩ፡ ክፍሎች፡ አሳየኝ።
ዕቃውን፡ ማን፡ አስገባው?	እንግዳ፡ ተቀባይ፡ አስገባው።
እርስዎ፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ አወቁ?	አስር፡ ሰዎች፡ አወቅሁ።
አስተማሪዎች፡ ለትምህርት፡	ስምንት፡ ተማሪዎች፡ አዩ።

ጥያቄ	መልስ
ቤት፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ተማሪዎች፡ አሉ?	
ተማሪዎች፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤታቸው፡ መሄድ፡ ቻሉ?	አዎ፡ አሁን፡ መሄድ፡ ቻሉ።
ቃሉን፡ ማን፡ ደገመው?	ተማሪዎችና፡ አስተማሪዎች፡ ደገሙት።
ወደ፡ ምግብ፡ ቤት፡ መሄድ፡ ማን፡ ፈለገ?	እነ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ለማ፡ ፈለጉ።
አቶ፡ ከበደ፡ መጽሐፉን፡ ከፈተው?	አዎ፡ ከፈተው።
ለቡና፡ ኪሎ፡ ስንት፡ ብር፡ ከፈሉ?	ለሳምንት፡ አስር፡ ብር፡ ከፈልሁ።
አስተማሪዋ፡ ከየት፡ አገር፡ መጣች?	ካሜሪካ፡ መጣች።
አቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ ነገረህ?	ወዳሜሪካ፡ መሄዱን፡ ነገረኝ።
ይህን፡ መጽሐፍ፡ ማን፡ ሰጣችሁ?	አስተማሪያችን፡ ሰጠችን።
ተማሪዎች፡ በጣም፡ ተመሰገኑ?	አዎ፡ በጣም፡ ተመሰገኑ።
አጎትሽ፡ ማን፡ ይባላል?	አቶ፡ ተሰማ፡ ይባላል።
መጽሐፉን፡ ወደ፡ ትምህርት፡	አስተማሪው፡ ወሰደው።

ጥያቄ	መልስ
ቤት፡ ማን፡ ወሰደው ?	
ትምህርት፡ ቤቱን፡ ማን፡ ዘጋው ?	አቶ፡ ካሣ፡ ዘጋው ።
ከተማውን፡ ማን፡ ዞረ ?	እገቴ፡ ዞረ ።
ሰውዬው፡ ካሜሪካ፡ መቼ፡ መጣ ?	ትናንት፡ መጣ ።
ሴትዮዋ፡ መቼ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ሄደች ?	ገሌት፡ ሰዓት፡ ሄደች ።
አቶ፡ ጆን፡ አንድ፡ ስኒ፡ ቡና፡ ሰጠህ ?	አዎ፡ ሰጠኝ ።
አቶ፡ ከበደ፡ ጥሩ፡ ትምህርት፡ አለው ?	አዎ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ትምህርት፡ አለው ።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ ፈለገ ?	አዎ፡ ፈለገ ።
እንግዳ፡ ተቀባዩ፡ ደህና፡ ክፍል፡ አለው ?	አዎ፡ አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ክፍል፡ አለው ።
ጌታሁ፡ ወዳሜሪካ፡ ሄደ ?	አዎ፡ ትናንት፡ ሄደ ።
እዚህ፡ አንድ፡ እንግዳ፡ መጣ ?	አዎ፡ አንድ፡ እንግዳ፡ መጣ ።
ተማሪዎች፡ ገዱ፡ ክፍሉ፡	አዎ፡ ስምንት፡ ገዱ፡ ክፍሎች፡

ጥያቄ	መልስ
ፈለጉ?	ፈለጉ።
ለክፍሉ፡ ስንት፡ ብር፡ ከፈለች?	አስር፡ ብር፡ ከፈለች።
ለመጽሐፉ፡ ስንት፡ ብር፡ ከፈለ?	ሁለት፡ ብር፡ ከፈለ።
አቶ፡ ከበደ፡ ዕቃውን፡ እንግዳ፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ አስገባ?	አዎ፡ አስገባ።
መጽሐፉን፡ ወደቤት፡ ማን፡ ወሰደው?	እኔና፡ እናቴ፡ ወሰድነው።
አቶ፡ ተሰማና፡ አቶ፡ ከበደ፡ አንደኛው፡ ፎቅ፡ ላይ፡ ምን፡ አዩ?	አንድ፡ ምግብ፡ ቤት፡ አዩ።
ገንዘብ፡ ማን፡ ሰጠሽ?	አስተማሪው፡ ሰጠኝ።
ባልሽ፡ የት፡ አለ?	ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አለ።
ሚስትህ፡ መቼ፡ መጣች?	ትናንት፡ ጠዋት፡ ሰዓት፡ መጣች።
ወንድም፡ አለሽ?	አዎ፡ ሦስት፡ ወንድሞች፡ አሉኝ።
እህትህ፡ ምን፡ ፈለገች?	አንድ፡ መጽሐፍ፡ ፈለገች።
አስተናጋጁ፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ከበደ፡ ነው።
አክስትሽ፡ አስተማሪ፡ ናት?	አዎ፡ አስተማሪ፡ ናት።

ድርሰት

ትናንት፡ ወዳጄ፡ ዮሐንስ፡ ቤት፡ ሄድሁና፡ አባቱና፡ እናቱን፡ አየሁ። አቶ፡ ዮሐንስ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ አባትና፡ እናት፡ አሉት። እነሱ፡ አስተማሪዎች፡ ናቸው። እሱ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ መኪና፡ አለው። እኛ፡ በመኪናው፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤቱ፡ ሄድንና፡ ምግብ፡ ቤቱን፡ አየን። ትምህርት፡ ቤቱ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው። አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ተሰማ፡ እዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አሉ። እነሱ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ ናቸው። ነገር፡ ግን፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ አሜሪካዊ፡ ነው።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ አለው?
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነው?
ወዳጄ፡ ዮሐንስ፡ አባትና፡ እናት፡ ቤት፡ መቼ፡ ሄድሁ?
አቶ፡ ዮሐንስ፡ መኪና፡ አለው?
በትምህርት፡ ቤቱ፡ ውስጥ፡ ኢትዮጵያዊያን፡
ተማሪዎች፡ አሉ?

ምግብ፡ ቤቱ፡ የት፡ ነው?
አገትና፡ እናቱ፡ ደና ፡ ናቸው?
አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ተሰማ፡ የት፡ አሉ?
እርስዎ፡ መኪና፡ አለዎ?

ስድስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከማ

አቶ፡ ከበደ፤ ነገ፡ ጥዋት፡ ምን፡ ትሠራለህ?

ከበደ

ነገ፡ ጥዋት፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ቀጠሮ፡ ስላለኝ፡ እዚያ፡ እሄዳለሁ።

ከማ

ቀጠሮው፡ ከማን፡ ጋር፡ ነው?

ከበደ

ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ ነው።

ከማ

ከዚያ፡ በኋላስ፡ ምን፡ ትሠራለህ?

ከበደ

ከዚያ፡ በኋላ፡ ሥራ፡ የለኝም። ነፃ፡ ነኝ።

ከማ

እንግዲያማ፡ እቴጌ፡ ሆቴል፡ ልክ፡ በስድስት፡ ሰዓት፡ እንገናኝ።

ከበደ

መልካም፤ እመጣለሁ። ጠብቀኝ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች፡

ወደ፡ ሱቅ፡ እሄዳለሁ።

ካሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ትመጣለህ?

ተማሪዎቹን፡ ታያለሽ?

እርስዎ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ መቼ፡ ይሄዳሉ?

ወደ፡ ከተማ፡ ከመሄዱ፡ በፊት፡ ቡና፡ ይጠጣል።

ሆቴል፡ ትፈልጋለች።

በሁለት፡ሰዓት፡ ውስጥ፡ ወደ፡ ቤት፡ እንመጣለን።

ቤቱን፡ ዛሬ፡ ታያላችሁ።

ካስተማሪያቸው፡ ጋር፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ይሄዳሉ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እቤት፡ ውስጥ፡ ማደር፡ ማን፡ ይፈልጋል?	አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ለማ፡ ይፈልጋሉ።
አቶ፡ ለማ፡ ነገ፡ የት፡ ይሄዳል?	ወደ፡ አገሩ፡ ይሄዳል።
ወደ፡ ቀጠሮህ፡ ነገ፡ ትሄዳለህ?	አዎ፡ በሶስት፡ ሰዓት፡ እሄዳለሁ።
ትምህርት፡ ቤቱን፡ መቼ፡ ይከፍታሉ?	ነገ፡ ይከፍታሉ።
ነገ፡ ጥዋት፡ የት፡ መሄድ፡ ይፈልጋሉ?	ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ እፈልጋለሁ።
ለክፍሉ፡ ኪራይ፡ ማን፡ ይከፍላል?	አቶ፡ ከበደና፡ እኅቱ፡ ይከፍላሉ።
ይህን፡ መጽሐፍ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ማን፡ ይወስዳል?	እኔ፡ እወስዳለሁ።

ጥያቄ	መልስ
እናንተ፡ የት፡ ማደር፡ ትፈልጋላችሁ?	ጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ ማደር፡ እንፈልጋለን።
አቶ፡ ከበደ፡ መኪናውን፡ ይከፍታል?	አዎ፡ ይከፍታል።
እናትህ፡ መቼ፡ ይመጣሉ?	ነገ፡ ይመጣሉ።
በውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ መሥራት፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
አስተማሪዎች፡ ተማሪዎቹን፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ መጥራት፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፡ ይፈልጋሉ።
አቶ፡ ከበደ፡ መኪናውን፡ ይዘጋል?	አዎ፡ ይዘጋል።
ለተማሪዎች፡ ስንት፡ መጽሐፎች፡ መስጠት፡ ትፈልጋለህ?	አስር፡ መጽሐፎች፡ እሰጣለሁ።
ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ማን፡ መምጣት፡ ይፈልጋል?	እኛ፡ መምጣት፡ እንፈልጋለን።

ጥያቄ	መልስ
ዕቃውን፡ በመኪናው፡ ውስጥ፡ ማስገባት፡ ትፈልጊያለሽ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
ቀይ፡ ነገር፡ ምን፡ ይገኛል?	መጽሐፍ፡ ይገኛል።
መቼ፡ ወደ፡ አንቺ፡ ይመጣል?	ዛሬ፡ ይመጣል።
መኪናውን፡ መቼ፡ ማየት፡ ትፈልጊያለሽ?	ነገ፡ ማየት፡ እፈልጋለሁ።
ኋላ፡ ምን፡ ትሠራለህ?	ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እሄዳለሁ።
እዚህ፡ ማንን፡ ትጠብቂያለሽ?	አቶ፡ ለማን፡ እጠብቃለሁ።
ለቤቱ፡ ስንት፡ ይከፍላሉ?	አስር፡ ብር፡ እከፍላለሁ።
መኪናህን፡ ለማን፡ መስጠት፡ ትፈልጋለህ?	ካገቴ፡ እሰጣለሁ።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩን፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ ማን፡ ያደርሳል?	ከበደ፡ ያደርሳል።
አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ የት፡ ታርፊያለሽ?	ጊዮን፡ ሆቴል፡ እርፋለሁ።

ድርሰት

አንድ፡ ሰው፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ከመሄዱ፡ በፊት፡ ስለ፡ አገሩ፡ ማወቅ፡ ይፈልጋል። አቶ፡ ለማ፡ በፊት፡ አሜሪካ፡ ነበር። አቶ፡ ከበደ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ ስለፈለገ፣ አቶ፡ ለማ፡ ቤት፡ ሄደና፡ ስለአሜሪካ፡ ጠየቀው።

ከበደ፡- አሜሪካ፡ መሄድ፡ ስለፈለግሁ፣ አንተን፡ ለማየት፡ መጣሁ።
ለማ፡- አሜሪካ፡ ለምን፡ ትሄዳለህ?
ከበደ፡- ለትምህርት፡ ነው።
ለማ፡- ጥሩ፡ ነው። ስንት፡ ጊዜ፡ ትቆያለህ?
ከበደ፡- ሁለት፡ ዓመት፡ ነው።
ለማ፡- በዋሽንግተን፡ ውስጥ፡ ትቆያለህ?
ከበደ፡- አዎ፡
ለማ፡- ዋሽንግተን፡ ጥሩ፡ ከተማ፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ ትንሽ፡ ብርድ፡ ነው።
ከበደ፡- ትምህርት፡ ቤቱስ፡ እንደምን፡ ነው?
ለማ፡- በጣም፡ ጥሩ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ።

ጥያቄዎች፡

በሌት፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ማን፡ ነበር?

አቶ፡ ከበደ፡ የት፡ ሄደ?

አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ለማን፡ ስለምን፡ ጠየቀው?

አቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ ፈለገ?

አቶ፡ ከበደ፡ ማን፡ ቤት፡ ሄደ?

አቶ፡ ከበደ፡ ወደ፡ አቶ፡ ለማ፡ ቤት፡ ለምን፡ ሄደ?

አቶ· ከበደ፡ አቶ፡ ለማን፡ ምን፡ አለው?

አቶ፡ ለማ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ምን፡ ጠየቀው?

አቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ አለ?

አቶ፡ ከበደ፡ በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ጊዜ፡
ይቆያል?

ሰባተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ እንደምን፡ አሉ?

መንገደኛ

እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና።

ከበደ

እባክዎ፣ ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ በየትኛው፡ አውቶቡስ፡ መሄድ፡ እችላለሁ?

መንገደኛ

በውነቱ፡ አላውቅም፤ ነገር፡ ግን፡ ያ፡ ፖሊስ፡ ምናልባት፡ ሊነግርዎት፡ ይችላል?

ከበደ

እሺ፡ እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ፤ እጠይቀዋለሁ።

(ለአንድ፡ ፖሊስ)

ጤና፡ ይስጥልኝ?

ፖሊስ

ጤና፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ለመሄድ፡ ፈልጌ፡ ነበርና፡ አውቶቡሱን፡ የት፡ እንደማገኘው፡ አላውቅም።

ፖሊስ

ከዚህ፡ መንገድ፡ ማዶ፡ ያንን፡ ያውቶቡስ፡ ማቆሚያ፡ ያያሉ?

ከበደ

አዎ፡ አያለሁ።

ፖሊስ

እዚያ፡ ይሂዱና፡ ይጠብቁት።

ከበደ	ጆሴስ
አመሰግናችኋለሁ።	ምንም፡ አይደል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ትምህርት፡ ቤቱን፡ አያችሁት?	አዎ፡ አየነው።
አስተማሪዎን፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ጠራችኋት?	አዎ፡ ጠራናት።
አንድ፡ መጽሐፍ፡ ትሰጡታላችሁ?	አዎ፡ እንሰጠዋለን።
እዚህ፡ ከተማን፡ ያውቁታል?	አዎ፡ አውቀዋለሁ።
ዛሬ፡ ትጠሪዋለሽ?	አዎ፡ እጠራዋለሁ።
መኪናህን፡ ትከፍታለህ?	አዎ፡ እከፍታለሁ።
እሷ፡ ከማን፡ ጠየቃችሁት?	አዎ፡ ጠየቅነው።
አስተማሪዎች፡ ትምህርት፡ ቤቱን፡ ዘጉት?	አዎ፡ ዘጉት።

ጥያቄ	መልስ
ያቶ፡ ከበደን፡ እኅት፡ ታውቋታላችሁ?	አዎ፡ እናውቀዋለን።
ገበሬ፡ ማሪያምን፡ ታዩታላችሁ?	አዎ፡ እናየዋለን።
ተማሪው፡ አስተማሪውን፡ አመሰገነው?	አዎ፡ አመሰገነው።
እህትህን፡ ለትምህርት፡ ቤት፡ አስገባሃት?	አዎ፡ አስገባኋት።
አቶ፡ ለማ፡ ያጁስ፡ አበገን፡ ገበሬ፡ ማሪያ፡ አወቀው?	አዎ፡ አወቀው።
አቶ፡ ከበደ፡ ለህፃ፡ እንዴ፡ ሰኔ፡ ሉና፡ ሰጣት?	አዎ፡ ሰጣት።
አቶ፡ ከበደ፡ ገንዘብ፡ ነበረው?	አዎ፡ ነበረው።
እኅትዎን፡ ጠየቋቸው?	አዎ፡ ጠየቅኋቸው።
ከበደን፡ ዛሬ፡ ያዩታል?	አዎ፡ አየዋለሁ።
አስተማሪው፡ መጽፍ፡ ይሰጡሃል?	አዎ፡ አንድ፡ መጽፍ፡ ይሰጡኛል።
አቶ፡ ከበደን፡ ታውቁታላችሁ?	አዎ፡ እናውቀዋለን።

ጥያቄ	መልስ
አስተማሪህን፡ ትጠራቸዋለህ?	አዎ፡ እጠራቸዋለሁ።
አውቶቡስ፡ ማቆሚያ፡ አገኘዋለሁ?	አዎ፡ ታገኘዋለህ።
ከመንገዱ፡ ማዶ፡ ያውቶቡሱን፡ ማቆሚያ፡ ታየዋለህ?	አዎ፡ አየዋለሁ።
ቤትሽን፡ ለኔ፡ ታሳይኛለሽ?	አዎ፡ አሳይዎታለሁ።
ወንድምህን፡ እትምህርት፡ ቤት፡ ታስገባዋለህ?	አዎ፡ አስገባዋለሁ።
ስለ፡ መኪናው፡ ከበደን፡ ታመሰግኚዋለሽ?	አዎ፡ አመሰግነዋለሁ።
ዛሬ፡ አባትና፡ እናትዎን፡ ይጠይቋቸዋል?	አዎ፡ እጠይቃቸዋለሁ።
እህትዎን፡ ወደ፡ ትምህርት ቤት፡ ይወስዷታል?	አዎ፡ እወስዳታለሁ።
ኢትዮጵያን፡ ያውቋታል?	አዎ፡ አውቃታለሁ።
ሚስትዎን፡ ይወስዷታል?	አዎ፡ እወስዳታለሁ።
እህትህን፡ አየሃት?	አዎ፡ አየሁዋት።
መጽሐፍ፡ ነበሬት?	አዎ፡ ነበሬች።

ጥያቄ	መልስ
ጆን፡ መኪና፡ ነበረህ?	አዎ፡ ነበረኝ።
መኪናዎች፡ ነበሩህ?	አዎ፡ ነበሩኝ።
ቤቶች፡ ነበሩዋችሁ?	አዎ፡ ነበሩን።
ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ወንድም፡ ነበረው?	አዎ፡ ነበረው።
ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ቤት፡ ነበረዎት?	አዎ፡ ነበረኝ።
ጆን፡ ተማሪዎች፡ ነበሩዋቸው?	አዎ፡ ነበሩዋቸው።

ድርሰት

የኢትዮጵያ፡ ዋና፡ ከተማ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ይባላል። እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ብዙ፡ ኤምባሲዎችና፡ ሚኒስቴሮች፡ አሉ። የከተማው፡ ሕዝብ፡ በጣም፡ ብዙ፡ ነው። በከተማው፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ አውቶቡሶችና፡ መኪናዎች፡ አሉ። የከተማው፡ ምልክቶችም፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ናቸው። አንድ፡ ሰው፡ አንድ፡ አዲስ፡ ነገር፡ ለማየት፡ ቢፈልግ፡ ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ባውቶቡስ፡ መሄድ፡ ይችላል።

በአዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ የመጽሐፍ፡ ሱቆች፣ ሆቴሎችና፡ ሲኒማ፡ ቤቶች፡ አሉ። እቴጌ፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ መልካም፡ ምግብ፡ አለ።

አንድ፡ ሰው፡ ያሜሪካን፡ ሲኒማ፡ ለማየት፡ ቢፈልግ፣ ወደ፡ አንዱ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ መሄድና፡ ማየት፡ ይችላል። የሲኒማው፡ ዋጋ፡ ብዙ፡ አይደለም።

ጥያቄዎች፡

የኢትዮጵያ፡ ዋና፡ ከተማ፡ ማን፡ ይባላል?

አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ምን፡ አለ?

ያዲስ፡ አበባ፡ ሕዝብ፡ ስንት፡ ነው?

ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ በምን፡ መሄድ፡ ይቻላል?

የከተማው፡ ጎዳኖች፡ መልካም፡ ናቸው?

አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ሲኒማ፡ ቤቶች፡ አሉ?

የሲኒማ፡ ዋጋ፡ ስንት፡ ነው?

እቴጌ፡ ሆቴል፡ የት፡ አለ?

በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ምን፡ አለ?

ጥሩ፡ ምግብ፡ የት፡ አለ?

አንድ፡ ሰው፡ ያሜሪካን፡ ሲኒማ፡ የት፡ ማየት፡ ይችላል?

ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ጥዋት፡ ጥዋት፡ ምን፡ ታደርጋለህ?

ዮሐንስ

ካልጋዬ፡ እነሳና፡ ፊቴን፡ እታጠባለሁ።

ከበደ

ከቁርስ፡ በፊት፡ ታጠናለህ?

ዮሐንስ

የለም፤ ከቁርስ፡ በኋላ፡ ነው።

ከበደ

ምን፡ ዓይነት፡ ቁርስ፡ ትበላለህ?

ዮሐንስ

ጥብስ፡ እንቁላልና፡ ዳቦ፡ በቅቤ፡ እበላለሁ።

የብርቱካን፡ ጭማቂና፡ ቡና፡ በወተት፡ እጠጣለሁ።

ከበደ

በስንት፡ ሰዓት፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ትሄዳለህ?

ዮሐንስ

በሁለት፡ ሰዓት፡ ተኩል፡ እሄዳለሁ።

ቁጥሮች

አስራ፡ አንድ፡	(፲፩)	አስራ፡ ስድስት፡	(፲፮)
አስራ፡ ሁለት፡	(፲፪)	አስራ፡ ሰባት፡	(፲፯)
አስራ፡ ሦስት፡	(፲፫)	አስራ፡ ስምንት፡	(፲፰)
አስራ፡ አራት፡	(፲፬)	አስራ፡ ዘጠኝ፡	(፲፱)
አስራ፡ አምስት፡	(፲፭)	ሀያ፡	(፳)

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
መኪናውን፡ ካቶ፡ ከበደ፡ መቼ፡ ሰጣችሁት?	ትናንት፡ ሰጠነው።
ሚስትዎን፡ አዲስ፡ አበባ፡ መቼ፡ አደረሱዋት?	ዛሬ፡ አደረስሁዋት።
አስተማሪዎቻችን፡ የት፡ አገር፡ አዩዋቸው?	አሜሪካ፡ ውስጥ፡ አየሁዋቸው።
የኔን፡ መጽሐፍ፡ ማን፡ ወሰደው?	አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወሰደው።
ለተማሪዋ፡ መኪና፡ ማን፡ ሰጣት?	አባትና፡ እናትዋ፡ ሰጡዋት።

ጥያቄ	መልስ
የኔን፡ ቤት፡ ማን፡ አሳየዎ?	ተማሪዎቹ፡ አሳዩኝ።
እገርህን፡ ማን፡ አወቀው?	እስተማሪዎቹ፡ አወቁት።
ያስተማሪዎን፡ መኪና፡ ማን፡ ፈለገ?	እስተማሪዎቹ፡ ፈለጉት።
አቶ፡ ከማንና፡ አቶ፡ ከበደን፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መቼ፡ ጠራችሁዋቸው?	ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ጠራናቸው።
ካስተማሪው፡ ገንዘቡን፡ መቼ፡ ከፈላችሁት?	ከሰዓት፡ በኋላ፡ ከፈልነው።
እዚህ፡ ማንን፡ ጠበቃችሁ?	አቶ፡ ከበደን፡ ጠበቅነው።
ቤቱን፡ መቼ፡ ሠራችሁት?	ትናንት፡ ሠራነው።
መጽሐፉን፡ መቼ፡ ሰጣችሁት?	ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በፊት፡ ሰጠነው።
እስተማሪዎቻችንና፡ ተማሪዎቻችን፡ የት፡ ተገናኛችሁዋቸው?	ጊዮን፡ ሆቴል፡ ተገናኘናቸው።
ተማሪዎቻችን፡ መቼ፡ ጠራችሁዋቸው?	ትናንት፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ጠራናቸው።

ጥያቄ	መልስ
ያቶ፡ ከበደን፡ ቡና፡ ማን፡ ጠጣው?	ተማሪዋ፡ ጠጣችው።
ያቶ፡ ከበደን፡ መኪና፡ የት፡ ወሰዳችሁት?	ወደ፡ አሜሪካ፡ ወሰድነው።
መኪናውን፡ ማን፡ ወሰደው?	አቶ፡ ከማ፡ ወሰደው።
መጽሐፉን፡ የት፡ አደረሱት?	ትምህርት፡ ቤት፡ አደረስሁት።
መኪናውን፡ ማን፡ ዘጋው?	ያቶ፡ ከበደ፡ ሚስት፡ ዘጋችው።
ትምህርት፡ ቤቱን፡ ማን፡ ዘረው?	አስተማሪዎች፡ ዘሩት።
መጽሐፉን፡ ከማን፡ ሰጠኸው?	ከተማሪው፡ ሰጠሁት።
አቶ፡ ከማ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መቼ፡ ይሄዳሉ?	ነገ፡ በስምንት፡ ሰዓት፡ ይሄዳሉ።
ቁርስ፡ መቼ፡ ትበላለህ?	ጥዋት፡ እበላለሁ።
ዛሬ፡ የት፡ ትሄዳላችሁ?	ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ እንሄዳለን።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ማን፡ መጣ?	ያቶ፡ ከማ፡ እኅት፡ መጡ።

ጥያቄ	መልስ
ቁርስ፡ ምን፡ ትበላለህ?	ጥብስ፡ እንቁላል፡ ቅቤና፡ ዳቦ፡ እበላለሁ።
ከቁርስ፡ ምን፡ ትጠጣለህ?	ወተትና፡ የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ እጠጣለሁ።
ቁርሳችሁን፡ የት፡ ትበላላችሁ?	ከቤታችን፡ ውስጥ፡ እንበላለን።
ዛሬ፡ ትምህርታችን፡ ማን፡ ያጠናል?	የኔ፡ ወንድም፡ ያጠናል።
ጥዋት፡ ጥዋት፡ የት፡ ትሄዳላችሁ?	ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንሄዳለን።
ስንት፡ አጎቶች፡ አሉዎት?	አስር፡ አጎቶች፡ አሉኝ።
ትምህርት፡ ቤቱን፡ ማን፡ አሳየህ?	እናቴ፡ አሳየችኝ።
አቶ፡ ካሳ፡ ስንት፡ መኪናዎች፡ ነበሩት?	ሦስት፡ መኪናዎች፡ ነበሩት።
ዛሬ፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ አገኙሻለሁ?	አዎ፡ ያገኙኛል።
መጽሐፉን፡ ከካሳ፡ መቼ፡ ትሰጡታላችሁ?	ነገ፡ እንሰጠዋለን።

ጥያቄ	መልስ
ገንዘብዎን፡ ለማን፡ ይሰጡታል?	ለሚስቴ፡ እሰጣታለሁ።
ሚስትህን፡ የት፡ ታያታለህ?	እትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አያታለሁ።
መጽሐፍሽን፡ የት፡ ትወስጂዋለሽ?	ወደ፡ ቤቴ፡ እወስደዋለሁ።
አዲስ፡ መኪና፡ ማን፡ ይሰጥሻል?	አጎቴ፡ ይሰጠኛል።
የኔን፡ መኪና፡ ማን፡ ይፈልገዋል?	እኔ፡ እፈልገዋለሁ።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ማን፡ ይጠራሃል?	አስተማሪዬ፡ ይጠራኛል።
ገንዘቡን፡ የት፡ ትከፍሉታላችሁ?	እዚህ፡ እንከፍለዋለን።
አዲስ፡ አበገን፡ ማን፡ አየው?	አቶ፡ ከበደና፡ አጎቴ፡ አዩት።
አቶ፡ ከበደን፡ ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ማን፡ አደረሰው?	ወንድሙ፡ አደረሰው።

ጥያቄ	መልስ
አድራሻሽን፡ ማን፡ አወቀው?	እኔ፡ አወቅሁት።
መጽሐፌን፡ የት፡ አገኘሽው?	እንታ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አገኘሁት።
አቶ፡ ለማን፡ መቼ፡ ይገናኘታል?	አሁን፡ እገናኘዋለሁ።
የት፡ አገኛችሁዋለሁ?	አዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ታገኘናለህ።
መቼ፡ ትነግራታለህ?	ዛሬ፡ እነግራታለሁ።
አስተማሪውን፡ ማን፡ ይፈልገዋል?	አቶ፡ ከበደ፡ ይፈልገዋል።
ከበደን፡ የት፡ ታገኚዋለሽ?	እትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አገኘዋለሁ።
አስተማሪዋን፡ ምን፡ ጠየቃችሁዋት?	ስለ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ጠየቅናት።
መኪናውን፡ ማን፡ ዘጋው?	አቶ፡ ለማ፡ ዘጋው።
እዚህ፡ ማን፡ ይጠብቅሃል?	ለማ፡ ይጠብቀኛል።
ቤቱን፡ መቼ፡ ትሠሩታላችሁ?	ነገ፡ እንሠራዋለን።
አስተማሪዋን፡ የት፡ ታዩዋታላችሁ?	አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ እናያታለን።

ጥያቄ	መልስ
መኪናውን፡ መቼ፡ ትሰጡኛላችሁ?	ነገ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ እንሰጥሃለን።
ተማሪዎቹን፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መቼ፡ ትጠሩዋቸዋላችሁ?	ነገ፡ እንጠራቸዋለን።
ቡና፡ የት፡ ትጠጣላችሁ?	እዚህ፡ እንጠጣለን።
መኪናውን፡ ማን፡ ይዘጋዋል?	ተማሪው፡ ይዘጋዋል።
ከተማውን፡ ማን፡ ይዞረዋል?	አስተማሪዎቹ፡ ይዞሩታል።
መኪና፡ ማን፡ ይሰጥሃል?	አጎቴ፡ ይሰጠኛል።
አስተማሪውን፡ ማን፡ ያመሰግነዋል?	እኔ፡ አመሰግነዋለሁ።
አቶ፡ ከበደ፡ ስንት፡ መኪናዎች፡ ይሰጥሃል?	ሁለት፡ መኪናዎች፡ ይሰጠኛል።
በስንት፡ ሰዓት፡ ተነሳችሁ?	በሦስት፡ ሰዓት፡ ተነሳን።
ዳቦ፡ በቅቤ፡ መቼ፡ በሉ?	ትናንት፡ በላሁ።
ካልጋችሁ፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ትነሳላችሁ?	በሁለት፡ ሰዓት፡ ተኩል፡ እንነሳለን።
ነገ፡ ምን፡ ያደርጋሉ?	ወደ፡ ከተማ፡ እሄዳለሁ።

ጥያቄ	መልስ
መኪናውን፡ እዚህ፡ ማን፡ አደረሰው?	አስተማሪዎች፡ አደረሱት።
ለትምህርት፡ የት፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።
ወደ፡ ቤታችሁ፡ ማንን፡ መጥራት፡ ትፈልጋላችሁ?	ጆን፡ ዮሐንስን፡ እናት፡ መጥራት፡ እንፈልጋለን።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስ፡ አሜሪካዊ፡ ተማሪ፡ ነው። እርሱ፡ አማርኛ፡ ያጠናል። ጥዋት፡ ጥዋት፡ ለአንድ፡ ሰዓት፡ ከአልጋው፡ ይነሳና፡ ፊቱን፡ ይታጠባል። በሁለት፡ ሰዓት፡ ለቁርስ፡ ወደ፡ ምግብ፡ ቤት፡ ይሄድና፡ የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ ይጠጣል።

ከአንድ፡ ሰዓት፡ በኋላ፡ እንቁላል፡ ጥብስና፡ ዳቦ፡ በቅቤ፡ ይበላና፡ ሻይ፡ በወተት፡ ይጠጣል።

በሁለት፡ ሰዓት፡ ተኩል፡ መጽሐፎቹን፡ ይይዝና፡

ከሌሎች፡ ተማሪዎች፡ ጋር፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ይሄዳል።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ ያደርጋል?

እርሱ፡ የት፡ ያጠናል?

ጎለጋው፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ይነሳል?

ፊቱን፡ የት፡ ይታጠባል?

ለቁርስ፡ የት፡ ይሄዳል?

ለቁርስ፡ ምን፡ ይበላል?

እርሱ፡ ከቁርስ፡ በፊት፡ ምን፡ ይጠጣል?

ከቁርስ፡ በኋላ፡ ምን፡ ይጠጣል?

ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ይሄዳል?

ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከመሄዱ፡ በፊት፡ ምን፡ ይይዛል?

ከእርሱ፡ ጋር፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ማን፡ ይሄዳል?

ዘጠነኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

ከበደ

ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከሄድህ፡ በኋላ፡ ምን፡ ትሠራለህ?

ዮሐንስ

አስተማሪው፡ እስኪመጣ፡ ድረስ፡ ያማርኛ፡ ጋዜጣ፡ እነባለሁ። ከመጣ፡ በኋላ፡ ትምህርት፡ እንጀምራለን።

ከበደ

አስተማሪው፡ ሁልጊዜ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ ይመጣሉ?

ዮሐንስ

የለም፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ አይመጡም፤ ነገር፡ ግን፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ ተኩል፡ እክፍል፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ።

ከበደ

ከመጣ፡ በኋላ፡ ምን፡ ትማራላችሁ?

ዮሐንስ

አማርኛ፡ ንባብ፡ ጽሕፈትና፡ ንግግር፡ እንማራለን።

ከበደ

በቀን፡ ስንት፡ ሰዓት፡ ትማራላችሁ?

ዮሐንስ

ከምሳ፡ በፊት፡ አራት፡ ሰዓት፤ ከምሳ፡ በኋላ፡ ደግሞ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ እንማርና፡ እንጨርሳለን።

ከበደ

በስንት፡ ሰዓት፡ ከክፍሉ፡
ትወጣላችሁ?

ዮሐንስ

በአሥር፡ ሰዓት፡ እንወጣለን።

ከበደ

አሁን፡ ገማርኛ፡ መጻፍ፡
ትችላለህ?

ዮሐንስ

አሁን፡ ጽሕፈቴ፡ ገና፡ ጥሩ፡
አይደለም።

ዐረፍት፡ ነገሮች፡

ወደ፡ ገበያ፡ አልሄድሁም።
ወደ፡ ገበያ፡ አልሄደም።
ቤተ፡ ክርስቲያኑን፡ አላየህም።
ቤተ፡ ክርስቲያኑን፡ አታዩም።
ወተት፡ አልገዛሽም።
ወተት፡ አትገዢም።
ሲጋራ፡ አላጨስም።
ሲጋራ፡ አያጨስም።
ሲጋራ፡ አልሸጠችም።
ሲጋራ፡ አትሸጥም።
ከበደን፡ አልረዳንም።
ከበደን፡ አንረዳም።
ባለፈው፡ ሳምንት፡ አላረፉ
ችሁም።
የዛሬ፡ ሳምንት፡ አታርፉም።
ትናንት፡ሌት፡ አልበሉም።
ዛሬ፡ ሌት፡ አይበሉም።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ትምህርታችሁን፡ ከሁለት፡ ሰዓት፡ እስከ፡ አስር፡ ሰዓት፡ ታጠናላችሁ?	አዎ፡ እናጠናለን። የለም፡ አናጠናም።
ጥዋት፡ ጥዋት፡ ፊትሽን፡ ትታጠቢያለሽ?	አዎ፡ እታጠባለሁ። የለም፡ አልታጠብም።
ነገ፡ ወደ፡ አገራችሁ፡ ትሄዳላችሁ?	አዎ፡ እንሄዳለን። የለም፡ አንሄድም።
ምሳቸውን፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ በሉ?	አዎ፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ በሉ። የለም፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ አልበሉም።
አባትና፡ እናትሽ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እስኪመጡ፡ ትጠብቂያቸዋለሽ?	አዎ፡ እጠብቃቸዋለሁ። የለም፡ አልጠብቃቸውም።
እዚህ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ትቆያላችሁ?	አዎ፡ እንቆያለን። የለም፡ አንቆይም።
ወንድምዎን፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ያደርሱታል?	አዎ፡ አደርሰዋለሁ። የለም፡ አላደርሰውም።
ትናንት፡ እኛ፡ ቤት፡ አደራችሁ?	አዎ፡ አደርን። የለም፡ አላደርንም።

ጥያቄ	መልስ
ትምህርትህን፡ ጀመርህ?	አዎ፡ ጀመርሁ። የለም፡ አልጀመርሁም።
ብዙ፡ ያማርኛ፡ መጽሐፎች፡ ታነባለህ?	አዎ፡ አነባለሁ። የለም፡ አላነብም።
አስተማሪው፡ ለአማርኛ፡ መጽሐፍ፡ ይጽፋል?	አዎ፡ ይጽፋል። የለም፡ አይጽፍም።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ አማርኛ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ ይችላሉ። የለም፡ አይችሉም።
እዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ የአማርኛ፡ አስተማሪዎች፡ ይገኛሉ?	አዎ፡ ይገኛሉ። የለም፡ አይገኙም።
እርስዋ፡ እንግሊዝኛ፡ ትማራለች?	አዎ፡ ትማራለች። የለም፡ አትማርም።
አቶ፡ ለማና፡ አቶ፡ ከበደ፡ ትምህርታቸውን፡ ጨረሱ?	አዎ፡ ጨረሱ። የለም፡ አልጨረሱም።
ተማሪዎች፡ አስተማሪዎቻቸውን፡ ያመሰግናሉ?	አዎ፡ ያመሰግናሉ። የለም፡ አያመሰግኑም።
እዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ታርፋላችሁ?	አዎ፡ እናርፋለን። የለም፡ አናርፍም።

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ ካሣ፡ ቤቱን፡ አሳየህ?	አዎ፡ አሳየኝ።
	የለም፡ አላሳየኝም።
አቶ፡ ካሣን፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ታስገባዋለህ?	አዎ፡ አስገባዋለሁ።
	የለም፡ አላስገባውም።
አገርዎን፡ ማየት፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
	የለም፡ አልፈልግም።
አማርኛ፡ ይችላል?	አዎ፡ ይችላል።
	የለም፡ አይችልም።
ወደ፡ ቤቱ፡ መሄድ፡ ይፈልጋል?	አዎ፡ ይፈልጋል።
	የለም፡ አይፈልግም።
ከመጽሐፉ፡ ገንዘብ፡ ከፈለች?	አዎ፡ ከፈለች።
	የለም፡ አልከፈለችም።
ነገ፡ ትከፍለዋለች?	አዎ፡ ትከፍለዋለች።
	የለም፡ አትከፍለውም።

ድርሰት።

ያሜሪካ፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ አንድ፡ የቋንቋ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ አለው። ተማሪዎቹ፡ በዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ የውጭ፡ አገር፡ ቋንቋዎች፡ ይማራሉ። ለምሳሌ፡ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጣልያንኛና፡ መስኮብኛ፡ ይማራሉ። በትምህርት፡ ቤቱ፡ ውስጥ፡ የሚገኙት፡ ተማሪዎቹ፡ አሜሪካውያን፡ ብቻ፡ ናቸው። ከአስተማሪዎቹ፡ አብዛኛዎቹ፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ናቸው።

በዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ተማሪዎቹ፡ ልክ፡ በሦስት፡ ሰዓት፡ ትምህርት፡ ይጀምራሉ። በአምስት፡ ሰዓት፡ ቡና፡ ለመጠጣት፡ ይወጣሉ። እንደገና፡ በአምስት፡ ተኩል፡ ወደ፡ ክፍል፡ ይገቡና፡ በሰባት፡ ለምሳ፡ ይወጣሉ። በስምንት፡ ሰዓት፡ ወደ፡ ክፍል፡ ይመለሱና፡ እስከ፡ አስር፡ ሰዓት፡ ይማራሉ። ከዚያ፡ በኋላ፡ ወደየቤታቸው፡ ይሄዳሉ።

ጥያቄዎች፡

የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ምን፡ ዓይነት፡
 ትምህርት፡ ቤት፡ አለው?

ትምህርት፡ ቤቱ፡ የት፡ ይገኛል?

እዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ምን፡ ያስተምራሉ?

ምን፡ ዓይነት፡ ቋንቋ፡ ትማራላችሁ?

የቋንቋ፡ አስተማሪያችሁ፡ ማን፡ ነው?

ተማሪዎች፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ትምህርት፡ ይጀምራሉ?

በስንት፡ ሰዓት፡ ሻይ፡ ይጠጣሉ?

ወደ፡ ክፍል፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ይመለሳሉ?

የምሳችሁ፡ ጊዜ፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ነው?

የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ የቋንቋ፡ ትምህርት፡
 ቤት፡ ስንት፡ ተማሪዎች፡ ያስተምራል?

አስተማሪዎቹ፡ ከየት፡ አገር፡ ናቸው?

እርስዎ፡ ስንት፡ የውጭ፡ አገር፡ ቋንቋ፡ ያውቃሉ?

አሥረኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ፤ እንደምን፡ ሰነበትሽ፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ?

ጥሩነሽ

እግዚአብሔር፡ ይመስገን፤ እንደምን፡ ሰነበቱ፡ አቶ፡ ከበደ? ከተለያየን፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሆኖናል።

ከበደ

አዎ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሆኖናል። ባለቤትሽን፡ ግን፡ በየጊዜው፡ ስለማገኛቸው፣ ደህንነትሽን፡ እጠይቃቸዋለሁ።

ጥሩነሽ

አዎ፡ እንዳገኘዎ፡ ነገሩኝ። በቀደምለት፡ ልጅዎን፡ ወይዘሪት፡ አለማዝን፡ በመንገድ፡ ላይ፡ አግኝቼአት፡ ደህንነታችሁን፡ ነገረችኝ።

ከበደ

አለማዝ፡ ታምማ፡ ለጥቂት፡ ቀኖች፡ እሐኪም፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ናት።

ጥሩነሽ

ምነው! ምን፡ ሆነች?

ከበደ

ረፍት፡ ስላልነበራት፡ ራስዋን፡ ያማታል።

ጥሩነሽ

አዝናለሁ። ብችል፡ እስቲ፡ ዛሬ፡ ማታ፡ እጠይቃታለሁ።

ቁጥሮች፡

ሀያ፡	(፳)	ስሳ፡/ስልሳ፡	(፷)
ሀያ፡ አንድ፡	(፳፩)	ሰባ፡	(፸)
ሀያ፡ ሁለት፡	(፳፪)	ሰማንያ፡	(፹)
ሰላሳ፡	(፴)	ዘጠና፡	(፺)
አርባ፡	(፵)	መቶ፡	(፻)
አምሳ፡/ሃምሳ፡	(፶)	ሺ/ሺህ፡	(ሺ)

ጥያቄና፡መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
መኪና፡ የምትፈልግ፡ አንተ፡ ነህ?	አዎ፡ እኔ፡ ነኝ።
ቤቱን፡ የገዙት፡ አባትሽ፡ ናቸው?	አዎ፡ አባቴ፡ ናቸው።
ክበቡን፡ የፈለጉት፡ አስተማሪው፡ ናቸው?	አዎ፡ አስተማሪው፡ ናቸው።
የምትፈልገው፡ አስተማሪሽን፡ ነው?	አዎ፡ አስተማሪዬን፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ሊትዮዋን፡ የጠየቋችው፡ እስዋ፡ ናት?	አዎ፡ እስዋ፡ ናት።
ከበደን፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ያደረሰህ፡ አንተ፡ ነህ?	አዎ፡ እኔ፡ ነኝ።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ የሄድህ፡ አንተ፡ ነህ?	አዎ፡ እኔ፡ ነኝ።
የተማራችሁት፡ አማርኛ፡ ነው?	አዎ፡ አማርኛ፡ ነው።
የጻፉት፡ መጽሐፍ፡ በአማርኛ፡ ነው?	አዎ፡ በአማርኛ፡ ነው።
ያየኸው፡ አገር፡ አሜሪካ፡ ነው?	አዎ፡ አሜሪካ፡ ነው።
የጠየቋችው፡ አንተን፡ ነው?	አዎ፡ እኔን፡ ነው።
የምትፈልጊት፡ ቀይ፡ መኪና፡ ነው?	አዎ፡ ቀይ፡ መኪና፡ ነው።
የያዙት፡ መጽሐፍ፡ ነው?	አዎ፡ መጽሐፍ፡ ነው።
የመጣው፡ ከበደ፡ ነበር?	አዎ፡ ከበደ፡ ነበር።
መጽሐፉን፡ የሰጠሽው፡ አንቺ፡ ነሽ?	አዎ፡ እኔ፡ ነኝ።

ጥያቄ	መልስ
ለትምህርት፡ቤት፡የገባህ፡ አንተ፡ነህ?	አዎ፡ እኔ፡ነኝ።
ቤቱን፡የሚገዛ፡አባትህ፡ናቸው?	አዎ፡ አባቴ፡ናቸው።
አማርኛ፡ የምትማረው፡ ኢትዮጵያ፡ውስጥ፡ነው?	አዎ፡ ኢትዮጵያ፡ውስጥ፡ነው።
የነገርሁህን፡ ለከበደ፡ ነገርህ?	አዎ፡ ነገርሁት።
የቋንቋ፡ተማሪዎች፡ አማርኛ፡ እንደሚማሩ፡ታውቃለህ?	አዎ፡ እንደሚማሩ፡አውቃለሁ።
ወደ፡አሜሪካ፡እንደምትመለሱ፡ነገራችሁት?	አዎ፡ እንደምንመለስ፡ነገርናው።
እንደ፡ለማ፡ያለ፡ሰው፡ እዚህ፡ከተማ፡ውስጥ፡ አየህ?	ትናንት፡ ከሰዓት፡በኋላ፡አየሁ።
ሰውዬውን፡እንዳየኸው፡ ወደ፡አሜሪካ፡ሄድህ?	አዎ፡ከሁለት፡ቀን፡በኋላ፡ ሄድሁ።

ጥያቄ	መልስ
ሲጃራውን፡ እንዲጨስ፡ የት፡ ሄደ?	ወደ፡ ቤቱ፡ ሄደ።
ከትምህርት፡ ቤት፡ ምን፡ ጊዜ፡ እንደሚወጣ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።
አስተማሪው፡ መኪናውን፡ እንደሚሸጥ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።
ሌታቸውን፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ እንደማያበሉ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ለአገራቸው፡ ንግግር፡ እንደሚያደርጉ፡ ታውቃላችሁ?	አዎ፡ እናውቃለን።
እንደ፡ አማርኛ፡ ጽሕፈት፡ ያለ፡ ነገር፡ ታውቃለህ?	የለም፡ አላውቅም።
ባለቤቱ፡ ካሜሪካ፡ እንደመጣች፡ ማን፡ ነገራችሁ?	የርስዎ፡ አባትና፡ እናት፡ ነገሩን።
ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደሄድሁ፡ ማን፡ ነገረህ?	ከርስዎ፡ ተማሪዎች፡ አንዱ፡ ነገረኝ።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደሚሄድና፡ እናቱን፡ እንደሚጠይቅ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።
ምሳውን፡ በውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ እንደሚበላ፡ ነገረዎ?	አዎ፡ ነገረኝ።
አማርኛ፡ እንደምንማር፡ ታውቃላችሁ?	የለም፡ አናውቅም።
ከመኪና፡ ስንት፡ እንደከፈለ፡ ታውቃላችሁ?	አዎ፡ እናውቃለን።
አባትና፡ እናትህ፡ ወደዚህ፡ እንደሚመጡ፡ ላስተማሪህ፡ ነገርሃት?	አዎ፡ ዛሬ፡ ነገርሁዋት።
አቶ፡ ከማን፡ እንደመጡ፡ ታውቃለህ?	የለም፡ አላውቅም።
ጋዜጣውን፡ ከጎረቤቱ፡ እንደሚያነብ፡ ነገሯችሁ?	የለም፡ አልነገረንም።
እሲኒማ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ እንድንገናኝ፡ ትፈልጊያለሽ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ቤቱን፡ እንደምትገዙት፡ አባታችሁ፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ ያውቃሉ።
ወደ፡ አገሬ፡ እንደምመለስ፡ ነገርሁህ?	አዎ፡ ነገርኸኝ።

ድርሰት፡

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽና፡ አቶ፡ ከበደ፡ አንድ፡ ቀን፡ በመንገድ፡ ላይ፡ ተገናኙ። አቶ፡ ከበደ፡ ለወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ሰላምታ፡ ሰጧት። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ ላቶ፡ ከበደ፡ ሰላምታ፡ አደረገች። አቶ፡ ከበደ፡ የወይዘሮ፡ ጥሩነሽን፡ ባለቤት፡ በየጊዜው፡ እንደሚያገኟቸውና፡ ደህንነትዎን፡ እንደሚጠይቁ፡ ነገሯት። እስዋም፡ ወይዘሪት፡ አለማዝን፡ እንዳገኘችና፡ ደህንነታቸውን፡ እንደጠየቀች፡ ላቶ፡ ከበደ፡ ነገረቻቸው። አቶ፡ ከበደም፡ ልጄ፡ ወይዘሪት፡ አለማዝ፡ እንደታመመችና፡ እሐኪም፡ ቤት፡ ውስጥ፡ እንደለች፡ ለወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ነገሯት። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ ወደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ መሄድና፡ ወይዘሪት፡ አለማዝን፡

መጠየቅ፡ መፈለግዎን፡ ነገሯቸው ።

ጥያቄዎች፡

በመንገዱ፡ ላይ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ ተገናኙ?
የተገናኙት፡ ሰዎች፡ ስም፡ ማን፡ ነው?
አቶ፡ ከበደ፡ ለወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ምን፡ ነገሯት?
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ላቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ ነገሯቸው?
አቶ፡ ከበደ፡ ስለ፡ ልጁ፡ ምን፡ አሉ?
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ምን፡ አለች?
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አልማዝን፡ መቼ፡ ጠየቀቻት?
የሆስፒታሉ፡ ሐኪሞች፡ ጥሩ፡ ናቸው?

አሥራ፡ አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆሩነስ

እግዚአብሔር፡ ይማርሽ፤
እንደምን፡ ዋልሽ፡ አልማዝ?

አልማዝ

እግዚአብሔር፡ ይመስገን፤
ዛሬ፡ ትንሽ፡ ተሽሎኛል።

ጆሩነስ

በሽታሽ፡ ምንድን፡ ነው?

አልማዝ

ጉንፋን፡ ይዞኝ፡ ነበር።

ጆሩነስ

አሁን፡ ትንሽ፡ ተሽሎሻል?

አልማዝ

አዎ፡ ሐኪሙ፡ መርፌ፡ መድኃኒት፡ ከሰጠኝ፡ በኋላ፡ በጣም፡ ተሽሎኛል።

ጆሩነስ

ከሐኪም፡ ቤት፡ መቼ፡ መውጣት፡ ትችያለሽ?

አልማዝ፡

ቶሎ፡ ለመውጣት፡ እፈልግ፡ ነበር፤ ነገር፡ ግን፡ ሐኪሙ፡ እስኪነግረኝ፡ ድረስ፡ መውጣት፡ አልችልም።

ጆሩነስ

እሺ፡ እግዚአብሔር፡ ይማርሽ።
እጠይቅሻለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ቤቱን፡ ገዝቶ፡ ለናቱና፡ ላጎቱ፡ ሰጣቸው?	አዎ፡ እንዴ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ቤት፡ ገዝቶ፡ ለናቱና፡ ላጎቱ፡ ሰጣቸው።
ቤቱን፡ ሸጦ፡ የት፡ አገር፡ መሄድ፡ ይፈልጋል?	ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ ይፈልጋል።
ለአንድ፡ ሳምንት፡ እዚህ፡ አርፎ፡ ወዳገሩ፡ መሄድ፡ ይፈልጋል?	አዎ፡ ይፈልጋል።
አቶ፡ ከበደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ሄዶ፡ ምን፡ ገዛ?	አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ቤት፡ ገዛ።
ልጅህ፡ ገማርኛ፡ ተምራ፡ ጨረሰች?	የለም፡ አልጨረሰችም።
ቤቱን፡ ዘግቶት፡ ሄደ?	አዎ፡ ዘግቶት፡ ሄደ።
ገንዘቡን፡ ከፍለው፡ መኪናውን፡ ወስደውታል?	አዎ፡ ወስደውታል።
ዛሬ፡ ጥዋት፡ መጥተኸ፡ ከተማ ለው፡ ምን፡ ነግረኸው፡ ነበር?	አዲስ፡ አበባ፡ እንደምሄድ፡ ነግሬው፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ ከበደ፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴሩን፡ ጠርተው፡ እመጣለሁ፡ አሉዋቸው?	የለም፡ አላሉዋቸውም።
አቶ፡ ዮሐንስና፡ ባለቤቱ፡ እዚህ፡ አገር፡ መጥተው፡ የት፡ አሉ?	እጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ አሉ።
ባለቤትዎ፡ ከትናንት፡ በፊት፡ የት፡ ሄደው፡ መጡ?	ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ሄደን፡ መጣን።
ያቶ፡ ለማ፡ ልጅ፡ መጽሐፉን፡ ይዞ፡ መጥቶ አለ?	አዎ፡ ይዞ፡ መጥቶአለ።
ጋዜጣውን፡ እንዣበቤ፡ ምን፡ ነገርሁህ?	ስላሜሪካ፡ ትንሽ፡ ነገርኸኝ።
ትምህርታቸውን፡ ተምረው፡ ይመጡ?	ወደዚህ፡ አይመጡም።
ምሳውን፡ ወስደው፡ ለተማሪው፡ ሰጡት?	አዎ፡ ለተማሪውና፡ ላስተማሪው፡ ሰጡዋቸው።
ዛሬ፡ ሄዳ፡ ትመለሳለች?	ምናልባት፡ የዛሬ፡ ሳምንት፡ ትመጣለች።

ጥያቄ	መልስ
ሐኪም፡ቤት፡ሄደው፡ማንን፡ጠየቁ?	ልጁን፡ጠየቅሁዋት።
ተማሪዎች፡ወደ፡ትምህርት፡ቤት፡መጥተው፡አስተማሪውን፡ጠየቁት?	የለም፡አልጠየቁትም።
ምሳህን፡በቤትህ፡ትመጣለህ?	አዎ፡እመጣለሁ።
ዛሬ፡ትምህርት፡ቤት፡ሄደህ፡ምን፡ትሠራለህ?	መጽሐፍ፡አነባለሁ።
የውጭ፡ጉዳይ፡ሚኒስትሩ፡ከመጡ፡በኋላ፡የት፡ሄደው፡ነበር?	ወደ፡ቤታቸው፡ሄደው፡ነበር።
ትምህርትህን፡ጨርሰህ፡የት፡ትሄዳለህ?	ወደገሬ፡እሄዳለሁ።
አስተማሪዎች፡መጥተው፡ምን፡ይሠራሉ?	ያስተምራሉ።
ገንዘቡን፡ወስዶ፡ምን፡ይገዛል?	አንድ፡ቤት፡ይገዛል።

ጥያቄ	መልስ
መኪናውን፡ ገዝተሽ፡ ለማን፡ ሰጠሽው?	ለከበደ፡ ሰጠሁት።
ሌታችሁን፡ በሌታችሁ፡ መጣችሁ?	አዎ፡ በሌታን፡ መጣን።
ጥሩነሽን፡ እየታህ፡ የት፡ ትሄዳለህ?	ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እሄዳለሁ።
እዚህ፡ ውላችሁ፡ የት፡ ትሄዳላችሁ?	ወደ፡ ቤታችን፡ እንሄዳለን።
እስተማሪው፡ መጻፉ፡ ዐማንን፡ ፈለገ?	ተማሪዎቹን፡ ፈለገ።
ቤቱን፡ ሸጦ፡ ገንዘቡን፡ ለማን፡ ሰጠው?	ለገቶና፡ ለናቱ፡ ሰጣቸው።
ከቤት፡ ወጥቶ፡ ምን፡ ያደርጋል?	ሲጃራ፡ ያጨሳል።
የዛሬ፡ ሳምንት፡ መጥታ፡ አየችህ?	አዎ፡ አየችኝ።

ድርሰት፡

አንድ፡ ቀን፡ የወይዘሪት፡ አልማዝ፡ እኅት፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽን፡ አገኟና፡ የልጇን፡ መታመም፡ ነገሯት። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ወደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ሄዳ፡ ወይዘሪት፡ አልማዝን፡ ጠየቀቻት። ወይዘሪት፡ አልማዝ፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ወደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ መጥታ፡ ስለ፡ ጠየቀቻት፡ በጣም፡ ደስ፡ አላት። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ ለወይዘሪት፡ አልማዝ፡ ብዙ፡ ነገሮች፡ አመጣችላት። ከሐኪም፡ ቤት፡ መቼ፡ እንደምትወጣ፡ ጠየቀቻት። ወይዘሪት፡ አልማዝም፡ ሐኪሙ፡ ገና፡ አልነገረኝም፡ ብላ፡ መለሰች። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ መጥቼ፡ እጠይቅሻለሁ፡ ብላ፡ ተመለሰች።

ጥያቄዎች፡

ለወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ያልማዝን፡ መታመም፡ ማን፡ ነገሯት?

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አልማዝን፡ የት፡ ጠየቀቻት?

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አልማዝን፡ ለምን፡ ጠየቀቻት?

ወይዘሪት፡ አልማዝ፡ ለምን፡ ደስ፡ አላት?

ወይዘሮ፡ ሞሪሰን፡ ለአልማዝ፡ ምን፡ አሉዋት?

አልማዝ፡ ከሐኪም፡ ቤት፡ መቼ፡ እንደምትወጣ፡ ታውቃለች?

ሐኪሙ፡ ለአልማዝ፡ መቼ፡ እንደምትወጣ፡ ነገሯት?

አልማዝ፡ ከሐኪም፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ቀን፡ ቆየች?

የአልማዝ፡ አባትና፡ እናት፡ ይጠይቋታል?

አስራ፡ ሁለተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

ዓለሙ

አቶ፡ ጆን፡ የኢትዮጵያ፡ የጊዜ፡ አቆጣጠር፡ ከአውሮፓው ዩን፡ ልዩ፡ መሆኑን፡ ታውቃለህ?

ጆን

የለም፡ አላውቅም። ልዩነቱ፡ እንዴት፡ ነው?

ዓለሙ

የቀኑም፡ የሌቱም፡ የወሩም፡ ያመቱም፡ የሰዓቱም፡ አቆጣጠር፡ ከናንተው፡ በጣም፡ ልዩ፡ ነው።

ድን

እባክህ፡ ልዩነቱን፡ ግለጽልኝ?

ዓለሙ

በኢትዮጵያ፡ የጊዜ፡ አቆጣጠርና፡ በአውሮፓ፡ የጊዜ፡ አቆጣጠር፡ መካከል፡ የስምንት፡ ዓመት፡ መካከል፡ አለ። ለምሳሌ፡ እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ አቆጣጠር፡ አሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ አምስት፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ሲሆን፡ እንደ፡ አውሮፓ፡ አቆጣጠር፡ አሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ስልሳ፡ ሦስት፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ይሆናል።

ዐረፍተ፡ ነገሮች

የጊዜ፡ አቆጣጠር

ከቀኑ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ነው።

ከምሽቱ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ካምስት፡ ደቂቃ፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ከሩብ፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ከአሥራ፡ አምስት፡ ደቂቃ፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ከሃያ፡ አምስት፡ ደቂቃ፡ ነው።

ሁለት፡ ተኩል፡ ነው።

ለሦስት፡ ሰዓት፡ ሃያ፡ አምስት፡ ደቂቃ፡ ጉዳይ፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ከሠላሳ፡ አምስት፡ ደቂቃ፡ ነው።

ከሦስት፡ ሰዓት፡ ሩብ፡ ጉዳይ፡ ነው።

ሁለት፡ ሰዓት፡ ከአርባ፡ አምስት፡ ደቂቃ፡ ነው።

በጥዋት፡ ሥራዬን፡ እሠራለሁ።

ጥዋት፡ በአራት፡ ሰዓት፡ መኪናዬን፡ አመጣለሁ።

ከጥዋቱ፡ በአራት፡ ሰዓት፡ መኪናዬን፡ አመጣለሁ።

ከሰዓት፡ በኋላ፡ በሰባት፡ ሰዓት፡ እመጣለሁ።

ማታ፡ እንመጣለን።

ከምሽቱ፡ በአራት፡ ሰዓት፡ እመጣለሁ።

ከሌቱ፡ በስምንት፡ ሰዓት፡ እመጣለሁ።

ከትናንትና፡ ወዲያ፡ አልመጣም።

ትናንት፡ ማታ፡ መጣች።

ገበሬው፡ ሳምንት፡ በየቀኑ፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ይሄዱ፡ ነበር።

ከነገ፡ ወዲያ፡ ይመጣል።

በሚመጣው፡ ሳምንት፡ ይመጣሉ።

ደብዳቤውን፡ ልከውታል።

አሜሪካ፡ ውስጥ፡ አምስት፡ ዓመት፡ ኖሬአለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
ጋዜጣ፡ እያነበብህ፡ ሲጃራ፡ ታጨሳለህ?	አዎ፡ አጨሳለሁ።
አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሆቴል፡ እየሄዱ፡ ቁርስ፡ ይበላሉ?	የለም፡ አይበላም።
ምን፡ እያደረገች፡ ገንዘብ፡ ታገኛለች?	ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ እየሠራች፡ ገንዘብ፡ ታገኛለች።
የት፡ እያረፍን፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ እንችላለን?	ከሆቴል፡ ውስጥ፡ እያረፍን፡ መሄድ፡ እንችላለን።
የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ እየጠጣ፡ ቁርሱን፡ ይበላል?	አዎ፡ የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ እየጠጣ፡ ቁርሱን፡ ይበላል።
የት፡ እየሄደ፡ ኪራዩን፡ ይከፍላል?	ወደ፡ ነጋዴው፡ እየሄደ፡ ይከፍላል።
ሥራዋን፡ እየሠራች፡ ዳቦ፡ ትበላለች?	አዎ፡ ትበላለች።
ሉና፡ እየጠጣች፡ ወተት፡ ሰጣት?	አዎ፡ ወተት፡ ሰጣት።

ጥያቄ	መልስ
ከከተማው፡ ውጭ፡ እየኖሩ፡ እከተማው፡ ውስጥ፡ ይሠራሉ?	ከከተማው፡ ውጭ፡ እየኖርሁ፡ እከተማው፡ ውስጥ፡ እሠራለሁ።
ቋንቋውን፡ እየገለጹ፡ ያስተምራሉ?	አዎ፡ ያስተምራሉ።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ ከተማ፡ እየሄዱ፡ እንቁላል፡ ይገዛሉ?	አዎ፡ እየሄዱ፡ እንቁላል፡ ይገዛሉ።
ጉንፋን፡ እያመመህ፡ ወደ፡ ውጭ፡ መሄድ፡ ትፈልጋለህ?	የለም፡ መሄድ፡ አልፈልግም።
ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ እየሄድሽ፡ ሲኒማ፡ ታያለሽ?	አዎ፡ አያለሁ።
እየተማሩ፡ ቁርሳቸውን፡ ይበላሉ?	አዎ፡ እየተማሩ፡ ይበላሉ።
ቶሎ፡ ቶሎ፡ እየተማሩ፡ ሄዱ?	አዎ፡ እየተማሩ፡ ሄዱ።
አብሮ፡ እየመጣ፡ ይጠይቃችኋል?	አዎ፡ ይጠይቀናል።

ጥያቄ	መልስ
ልጅዋን፡ እያመጣች፡ ወደ፡ ሥራ፡ ሄደች?	አዎ፡ እያመጣች፡ ሄደች።
ጀርመናዊው፡ እየሄደ፡ አሜሪካዊውን፡ ያጠያቅቃል?	አዎ፡ ያጠያቅቃል።
ደብዳቤውን፡ እያነበብህ፡ ለናትህ፡ ትነግራታለህ?	አዎ፡ እያነበብሁ፡ እነግራታለሁ።
ለምን፡ እዚህ፡ እየመጡ፡ እያደሩም?	ቤትዎ፡ በጣም፡ ሩቅ፡ ነው።
ብርዱ፡ እየሆነ፡ ሄደ?	አዎ፡ ሄደ።
ብዙ፡ ገንዘብ፡ ሊኖርህ፡ የት፡ ትሄዳለህ?	ወደ፡ ጀርመን፡ እሄዳለሁ።
ለምን፡ ጊዜ፡ ሊኖርህ፡ አትመጣም?	ወደፊት፡ እመጣለሁ።
ቁርስ፡ ሊበሉ፡ እየሃቾው?	አዎ፡ እየሁቆቾው።
ሥራችሁን፡ ስትጨርሱ፡ የት፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።
እኅቱ፡ ሊመጣ፡ እያችሁት?	አዎ፡ እየነው።
ጉንፋን፡ ሊያምዎት፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ይሄዳሉ?	የለም፡ አልሄድም።

ጥያቄ	መልስ
ቋንቋን፡ ለመማር፡ ስትፈልጉ፡ የት፡ ትሄዳላችሁ?	ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንሄዳለን።
እኅትህ፡ ወደ፡ እዚህ፡ ከተማ፡ ስትመጣ፡ የት፡ ታርፋለች?	ለጊዜው፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ ታርፋለች።
የቤቱን፡ ኪራይ፡ ስትከፍሉ፡ ምን፡ ታደርጋላችሁ?	ባለቤቱን፡ እንጠራዋለን።
ለካምታ፡ ሊሰጥህ፡ መልስህ፡ ትሰጠዋለህ?	አዎ፡ እሰጠዋለሁ።
ሲኒማ፡ ቤት፡ ሲሄዱ፡ አየሃቸው?	አዎ፡ አየሁዋቸው።
ከዕረፍት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ስትሄዱ፡ ምን፡ ማየት፡ ትፈልጋላችሁ?	ዋሽንግተንን፡ ማየት፡ እንፈልጋለን።
አቶ፡ ከማ፡ ገንዘብ፡ ሲኖረው፡ ምን፡ መሥራት፡ ይፈልጋል?	መማር፡ ይፈልጋል።
መኪና፡ ሊሰጡህ፡ ምን፡ ታደርገዋለህ?	ለእኅቴና፡ ለእናቴ፡ እሰጣቸዋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ገለቤትህ፡ ስትመጣ፡ የት፡ መሄድ፡ ትችላለህ?	ወደ፡ ቤቱ፡ መሄድ፡ እችላለሁ።
ከእኔ፡ ጋር፡ አብሮ፡ ሊመጣ፡ አያችሁት?	የለም፡ ሊመጣ፡ አላየነውም።
ገንዘቡን፡ ጎዩሰኞህ፡ የት፡ ሄደ?	የት፡ እንደሄደ፡ አላውቅም።
ገንዘብ፡ እቆጣጠር፡ ሳያውቅ፡ ሥራ፡ አገኘ?	አዎ፡ አገኘ።
ሥራ፡ ሳንጨርስ፡ ቁርስ፡ አንበላም?	የለም፡ አንበላም።
የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ ሳይጠጡ፡ ቁርስ፡ ይበላሉ?	የለም፡ አይበሉም።
ወንድምህን፡ ሳታይ፡ ተመለስህ?	አዎ፡ ተመለስሁ።
ወደ፡ አገራችን፡ ስንሄድ፡ እናታችንን፡ እንጠይቅ?	አዎ፡ እንጠይቅ።
ገንዘብ፡ ሳገኝ፡ ወደ፡ ከተማ፡ መሄድ፡ እችላለሁ?	የለም፡ አትችልም።

ድርሰት

የኢትዮጵያዊያን፡ የጊዜ፡ አቆጣጠር፡ ከአውሮፓዊያን፡ በብዙ፡ መንገድ፡ የተለየ፡ ነው። ልዩነቱም፡ ከሰዓቱ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ድረስ፡ ነው። ለምሳሌ፡ እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ አቆጣጠር፡ የመጀመሪያው፡ ወር፡ መስከረም፡ ሲሆን፤ የመጨረሻው፡ ወር፡ ደግሞ፡ ጳጉሜ፡ ነው። የሰዓት፡ አቆጣጠሩም፡ ከአውሮፓዊያን፡ አቆጣጠር፡ በጣም፡ የተለየ፡ ነው። ለምሳሌ፡ አውሮፓዊያን፡ አራት፡ ሰዓት፡ ሲሉ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ አስር፡ ሰዓት፡ ይላሉ።

ቀንና፡ ሌሊቱ፡ እኩል፡ በአስራ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ እያንዳንዱ፡ ተከፍሎአል። በአንድ፡ ቀን፡ ውስጥ፡ ሃያ፡ አራት፡ ሰዓቶች፡ አሉ። በአንድ፡ ሰዓት፡ ውስጥ፡ ስልሳ፡ ደቂቃዎች፡ አሉ። በአንድ፡ ደቂቃ፡ ውስጥ፡ ደግሞ፡ ስልሳ፡ ሴኮንዶች፡ አሉ። እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ አቆጣጠር፡ ቀንና፡ ሌሊቱ፡ እኩል፡ እርዝመት አላቸው። ፀሐይ፡ ከወጣች፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ጠለቀች፡ ድረስ፡ ቀን፡ ነው። ከጠለቀች፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ወጣች፡ ድረስ፡ ሌሊት፡ ነው።

ጥያቄዎች፡

በኢትዮጵያዊያንና፡ በአውሮጳዊያን፡ የጊዜ፡ አቆጣ
ጠር፡ ምን፡ ልዩነት፡ አለ?

ልዩነቱስ፡ እንዴት፡ ነው?

የኢትዮጵያ፡ የመጀመሪያው፡ ወር፡ ማን፡ ይባላል?

የኢትዮጵያ፡ የመጨረሻው፡ ወር፡ ማን፡ ይባላል?

ቀንና፡ ሌሊት፡ እኩል፡ ተካፍሎአል?

በአንድ፡ ቀን፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሰዓቶች፡ አሉ?

በአንድ፡ ደቂቃ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሴኮንዶች፡ አሉ?

እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ አቆጣጠር፡ ቀንና፡ ሌሊት፡
ልዩነት፡ አለው?

ቀኑ፡ መቼ፡ ይጀመራል?

ሌሊት፡ መቼ፡ ይጀመራል?

አሥራ፡ ሦስተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

ዓለሙ

ዋጋው፡ ስንት፡ ነው?

ከበደ

ሦስት፡ ብር፡ ከሃምሳ፡ ሳንቲም፡ ነው።

ዓለሙ

በጣም፡ ውድ፡ ነው?

ከበደ

የለም፤ ይህ፡ የገበያ፡ ዋጋ፡ ነው።

ዓለሙ

ቅናሽ፡ አያደርጉም?

ከበደ

ደንበኛዬ፡ ስለሆኑ፡ ሃምሳ፡ ሣንቲም፡ ቅናሽ፡ አደርግልዎታለሁ።

ዓለሙ

ይሁን፡ እወስደዋለሁ።

ደግሞ፡ ወረቀት፣ ቀለምና፡ ኤንቨሎፕ፡ ይሰጡኝ።

ጠቅላላው፡ ዋጋ፡ ስንት፡ ነው?

ከበደ

አምስት፡ ብር፡ ነው።

ይኸውና፡ ጌታዬ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች፡

ጠረጴዛው፡ አጠገብ፡ ባለው፡ ወንበር፡ ላይ፡ ልቀመጥ፡ ነው።

አንተ፡ በጥቁር፡ ቀለም፡ እየጻፍህ፡ አማርኛ፡ ጽሕፈት፡ ልትማር፡ ነው።

እርስዎ፡ ከወዳጅዎ፡ ጋር፡ ጨዎ፡ ሊሰጡ፡ ነው።

እስቸጋሪውን፡ ዐረፍት፡ ነገር፡ ወደ፡ እንግሊዝኛ፡ ልትተረጉሚ፡ ነው።

ቤቱን፡ ቢጫ፡ ቀለም፡ ሊቀባ፡ ነው።

ቆንጆዋ፡ ልጃገረድ፡ አቶ፡ ጆንን፡ አማርኛ፡ ለማስተማር፡ ልትፈቅድ፡ ነው።

እነቸው፡ ሰማያዊ፡ መኪና፡ ሊገዙ፡ ነው።

አረንጓዴ፡ ቀለም፡ ልንደፋ፡ ነው።

ልትናገሩ፡ ነው።

ዐረፍት፡ ነገሩን፡ በቀላሉ፡ ሊያስተውሉ፡ ነበር።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ ሊገቡ፡ ይፈልጋሉ?	በጣም፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ሊገቡ፡ ይፈልጋሉ።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ስለ፡ ቤቱ፡ ደስ፡ ሊለው፡ ቻለ?	አዎ፡ ደስ፡ ሊለው፡ ቻለ።
አባትና፡ እናትዎ፡ ሊመጡ፡ ይፈልጋሉ?	የለም፡ ሊመጡ፡ አይፈልጉም።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ሥራ፡ልትሄዱ፡ነው?	አዎ፡ልንሄድ፡ነው።
ለሙሉነሽ፡መጽሐፎቹን፡ልትሰጡዋት፡ነው?	ከሰዓት፡በኋላ፡ልንሰጣት፡ነው።
ትምህርታቸውን፡ሊያጠኑ፡ነው?	የለም፡ሊያጠኑ፡አይችሉም።
አማርኛ፡ማን፡ሊማር፡ነው?	ዮሐንስ፡ሊማር፡ነው።
ዛሬ፡ከሰዓት፡በኋላ፡የት፡ልትውሉ፡ነው?	እመጽሐፍ፡ቤት፡ውስጥ፡ልንውል፡ነው።
ለምሳቸው፡ምን፡ሊበሉ፡ነው?	ምን፡ሊበሉ፡እንደሚፈልጉ፡አናውቅም።
እቤትዎ፡በሰዓት፡ሊሄዱ፡ይፈልጋሉ?	አዎ፡እፈልጋለሁ።
ማታ፡ወደ፡ቤታቸው፡ሊወስዱን፡ይፈልጋሉ?	አዎ፡ይፈልጋሉ።
ልጆቻችን፡ሊያውቋችሁ፡አይፈልጉም?	አይፈልጉም።
ገንዘቡን፡እንዴት፡ልታመጡት፡ትችላላችሁ?	በመኪና፡ልናመጣው፡እንችላለን።

ጥያቄ	መልስ
የሰውየውን፡ ስም፡ እንዴት፡ ልታውቁት፡ ቻላችሁ?	አንድ፡ ሰው፡ ነገረኝ።
በሁለት፡ ሰዓት፡ ክለብ፡ የት፡ ልትሄድ፡ ትፈልጋለህ?	ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ልሄድ፡ እፈልጋለሁ።
አቶ፡ ካሳ፡ የት፡ ሊማር፡ ይችላል?	አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ሊማር፡ ይችላል።
እኛ፡ ገንዘብ፡ ወደ፡ አገራችን፡ ልንልክ፡ እንችላለን?	አዎ፡ ትችላላችሁ።
ደብዳቤ፡ ለእናታችሁ፡ ልትጽፉ፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፡ እንፈልጋለን።
ስለ፡ አገራችሁ፡ ልትገልጹላቸው፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፡ እንፈልጋለን።
ለዮናታን፡ ሊገልጹልኝ፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
በአንድ፡ ሰዓት፡ ውስጥ፡ እቤትዎ፡ ሊሄዱ፡ ይችላሉ?	የለም፡ አልችልም።
እህቴን፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ በየወሩ፡ ትጠይቅልኛለህ?	አዎ፡ እጠይቅልሃለሁ። የለም፡ አልጠይቅልህም።

ጥያቄ	መልስ
ለጋዜጣው፡ አስር፡ ሣንቲም፡ ትሰጭልኛለሽ?	አዎ፡ እሰጥልሃለሁ። የለም፡ አልሰጥልህም።
ውዱን፡ መጽሐፍ፡ ለአቶ፡ ለማ ሸጥሽለት?	አዎ፡ ሸጥሁለት። የለም፡ አልሸጥሁለትም።
ለቤቱ፡ ኪራይ፡ ቅናሽ፡ ታደርግላቸዋለህ?	አዎ፡ አደርግላቸዋለሁ። የለም፡ አላደርግላቸውም።
ደንበኛ፡ መሬቶች፡ ትገዙልኛላችሁ?	አዎ፡ እንገዛልሃለን። የለም፡ አንገዛልህም።
እንጀራውን፡ ላስተማሪው፡ ትሰጡለታላችሁ?	አዎ፡ እንሰጥለታለን። የለም፡ አንሰጥለትም።
ቢጫውን፡ ቀለም፡ ወደ፡ ቤትዋ፡ ትወስዱላታላችሁ?	አዎ፡ እንወስድላታለን። የለም፡ አንወስድላትም።
ጠረጴዛውን፡ ትሠሩለታላችሁ?	አዎ፡ እንሠራለታለን። የለም፡ አንሠራለትም።
ደብዳቤውን፡ ወደ፡ እንግሊዝኛ፡ ትተረጉሚለታለሽ?	አዎ፡ እተረጉምለታለሁ። የለም፡ አልተረጉምለትም።
ይህን፡ ዐረፍተ፡ ነገር፡ ታነቢልኛለሽ?	አዎ፡ አነብልሃለሁ። የለም፡ አላነብልህም።

ጥያቄ	መልስ
ለከበደ፡ ስለ፡ ትምህርት፡ ቤቱ፡ ትናገርለታለህ?	አዎ፡ እናገርለታለሁ። የለም፡ አልናገርለትም።
ከበደን፡ እስክታየው፡ ደረስ፡ መቆየት፡ ትፈልጋለህ?	ከእርስዎ፡ ጋር፡ መቆየት፡ እፈልጋለሁ።
ሥራውን፡ እስኪጨርስ፡ ደረስ፡ እዚህ፡ ይቆያል?	አዎ፡ እዚህ፡ ይቆያል።
ደብዳቤውን፡ እስክትጽፍ፡ ደረስ፡ እኔ፡ ቡና፡ ልጠጣ?	አዎ፡ መጠጣት፡ ትችላለህ።
በሉ፡ ኢትዮጵያ፡ እስክትገቡ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሄዳ፡ ትምጣ?	አዎ፡ ሄዳ፡ ትምጣ።
እስካሁን፡ ምን፡ ትሠሩ፡ ነበር?	እዚህ፡ ተቀምጠን፡ ነበር።
ቁርስ፡ እስክንበላ፡ ደረስ፡ የት፡ መሄድ፡ ይፈልጋል?	ወደ፡ ቡና፡ ቤት፡ መሄድ፡ ይፈልጋል።
ገንዘብ፡ እስክንሰጠው፡ ደረስ፡ ወደ፡ አገሩ፡ መሄድ፡ አይችልም?	የለም፡ አይችልም።
አስተማሪህ፡ እስኪጠይቅህ፡ ደረስ፡ አትናገርም?	የለም፡ አልናገርም።

ጥያቄ	መልስ
ደብዳቤውን፡ እስካነበበው፡ ዶሪስ፡ ከየት፡ እንደመጣ፡ አውቆ፡ ነበር?	አዎ፡ አውቆ፡ ነበር።
ቤት፡ እስክታገኚ፡ ዶሪስ፡ የት፡ መቆየት፡ ትፈልጊያለሽ?	እጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ እቆያለሁ።
ገንዘቡን፡ እስክታገኙ፡ ዶሪስ፡ ዋሽንግተን፡ አትሄዱም?	እስክናገኝ፡ አንሄድም።
መኪናዎን፡ እስኪያመጡ፡ ዶሪስ፡ የእኔን፡ መኪና፡ መውሰድ፡ ትፈልጋለሽ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
ከበደ፡ እስኪመጣ፡ ዶሪስ፡ የት፡ ትቆያላችሁ?	እሆቴል፡ ውስጥ፡ እንቆያለን።
ሌሉን፡ እስኪጠመመው፡ ዶሪስ፡ ይሠራ፡ ነበረ?	አዎ፡ ይሠራ፡ ነበረ።
ጋዜጣውን፡ እስኪያነቡ፡ ዶሪስ፡ አንተ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ትፈልጋለህ?	ወደ፡ ከተማ፡ ሄጄ፡ መመለስ፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ክፍሉን፡ እስኪያገኙልሽ፡ ድረስ፡ ምግ፡ መግዛት፡ ትፈልጊያለሽ?	አዎ፡ አፈልጋለሁ።
ቁርሱን፡ በቤቶ፡ እስኪጨርስ፡ አንድ፡ ነገር፡ ማድረግ፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፡ ቡና፡ መጠጣት፡ እንፈልጋለን።

ድርሰት፡

አቶ፡ ዓለሙ፡ ዕቃ፡ ለመግዛት፡ ወደ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ሱቅ፡ ሄደ። በአቶ፡ ከበደም፡ ሱቅ፡ ብዙ፡ ጥሩ፡ ነገሮች፡ ነበሩ። አቶ፡ ዓለሙ፡ ለጥቂት፡ ደቂቃዎች፡ ከተመለከቱ፡ በኋላ፡ አንድ፡ ቦርሳ፡ ለመግዛት፡ ፈለገ። አቶ፡ ዓለሙ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ይህ፡ ቦርሳ፡ ምን፡ ያህል፡ ይሸጣል፡ ብሎ፡ ጠየቀው። አቶ፡ ከበደም፡ አምስት፡ ብር፡ ከሃምሳ፡ ሳንቲም፡ ነው፡ ብሎ፡ መለሰለት። አቶ፡ ዓለሙ፡ ገንዘቡን፡ ለመክፈል፡ ኪሱን፡ ቢዳብስ፤ ገንዘቡን፡

እቤቱ፡ ከንጺሬኀው፡ አወቀና፡ ሰውስ፡ ወዲያው፡ እርሱ፡ መንቹ፡ ከወሰጸቀከሁ፡ ሰሎሙ፡ ሄደ።

ጥያቄዎች፡

አቶ፡ ዓክሊሉ፡ ምን፡ ከመግዛት፡ ወደ፡ ሱቅ፡ ሄደ?

አቶ፡ ዓክሊሉ፡ ከማን፡ ሱቅ፡ ገባ?

በአቶ፡ ካበዴ፡ ሱቅ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ነበር?

አቶ፡ ዓክሊሉ፡ አቶ፡ ካበዴን፡ ምን፡ ጠየቀው?

አቶ፡ ዓክሊሉ፡ የርኅውን፡ ከምን፡ እስገዛውም?

አቶ፡ ዓክሊሉ፡ የርኅውን፡ ከመግዛት፡ መቼ፡ ከመ ማከሁ፡ ሰሎሙ፡ ሄደ?

በሳምንት፡ ውስጥ፡ የኬትን፡ የቀናቶች፡ ለምን፡ ንገሬኝ?

አስራ፡ አራተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

ዓለሙ

መኪናዬ፡ ውስጥ፡ ቤንዚን፡ ጨምርልኝ።

ለማ

ምን፡ ያህል፡ ልጨምርልዎት?

ዓለሙ

አስር፡ ሊትር፡ ጨምርልኝ።

ለማ

ቢፈልጉ፡ ዘይቱን፡ ልይልዎት?

ዓለሙ

እሺ። ደግሞም፡ ጎማዬ፡ ሊፈነዳብኝ፡ ነውና፡ እባክህ፡ እዳስልኝ።

ለማ

ጥቂት፡ ከመቆየት፡ በኋላ፡ እዳስልዎታለሁ።

ዓለሙ

አሁን፡ ሥራ፡ ስላለብኝ፡ መኪናውን፡ ትቼው፡ ልሄዳለሁ።

ዐረፍተ፡ ነገሮች፡

ይህ፡ ገርጂም፡ ነው።

ይቺ፡ ላም፡ ናት።

ይህኛው፡ ውሻ፡ ነው።

ይቺኛዋ፡ ድመት፡ ናት።

እነዚህ፡ ሸሚዞች፡ ናቸው።

እኚህ፡ አገሬ፡ ናቸው።

እነኚህ፡ ወንድሞችዎ፡ ናቸው።

ያ፡ ኮት፡ ነው።

ያቺ፡ አህያ፡ ናት።

ያኛው፡ ፈረስ፡ ነው።

ያቺኛዋ፡ በቅሎ፡ ናት። እኒያ፡ አስሰቦቹ፡ ናቸው።

እነዚያ፡ ካሌጎቶች፡ ናቸው። እነኛ፡ አጎቶቹ፡ ናቸው።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
ገንዘብ፡ ቢኖርህ፡ ኖሮ፡ የት፡ ትሄድ፡ ነበር?	ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እሄድ፡ ነበር።
ስልክ፡ ብትደውል፡ ኖሮ፡ እቤትህ፡ ታገኘህ፡ ነበር?	አዎ፡ ታገኘኝ፡ ነበር።
ከበር፡ ብር፡ ቢሰጥሽ፡ ኖሮ፡ ካምሽን፡ ትሰጭው፡ ነበር?	አዎ፡ እሰጠው፡ ነበር።
ምሳዎን፡ ቢበሉ፡ ኖሮ፡ የት፡ ይሄዱ፡ ነበር?	ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ እሄድ፡ ነበር።
እዚህ፡ መምጣታችሁን፡ አጎታችሁ፡ ቢያውቅ፡ ኖሮ፡ ምን፡ ትሉት፡ ነበር?	ሁለታችን፡ እንሄድም፡ እንለው፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
ስለውጭው፡ ደንበኞችሁ፡ ቢሆን፡ ድሮ፡ ቅናሽ፡ ታደርጉላት፡ ነበር?	ያስር፡ ብር፡ ቅናሽ፡ እናደርግላት፡ ነበር።
ከገውን፡ እቤትህ፡ ወስደህ፡ ብታገኘው፡ ድሮ፡ ምን፡ ትከው፡ ነበር?	ምንም፡ አላከው፡ ነበር።
ወረቀት፡ ቢኖርሽ፡ ድሮ፡ ደብዳቤ፡ ትጽፊለት፡ ነበር?	አዎ፡ እጽፍለት፡ ነበር።
አዲስ፡ አበባ፡ ወስደህ፡ ቤት፡ ቢኖራችሁ፡ ድሮ፡ ምን፡ ታደርጉት፡ ነበር?	እንሸጠው፡ ነበር።
ገንዘብ፡ ቢኖርህ፡ ድሮ፡ ፈረስ፡ ትገዛ፡ ነበር?	አዎ፡ እገዛ፡ ነበር።
በመኪናህ፡ ወስደህ፡ ቤንዚን፡ ቢኖርህ፡ ድሮ፡ የት፡ ትሄድ፡ ነበር?	ወደ፡ ኒውዮርክ፡ እሄድ፡ ነበር።
ቅናሽ፡ ብታገኙ፡ ድሮ፡ አህያና፡ በቅሎ፡ ትገዙዋቸው፡ ነበር?	አዎ፡ እንገዛቸው፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
ብዙ፡ ተማሪዎች፡ ቢኖሩህ፡ ኖሮ፡ ምን፡ ሥራ፡ ትሰጣቸው፡ ነበር?	አማርኛ፡ አስተምራቸው፡ ነበር።
ብዙ፡ ገንዘብ፡ ባይኖራቸው፡ ኖሮ፡ ከየት፡ ያመጡ፡ ነበር?	ከወንድሞቻቸው፡ ያገኙ፡ ነበር።
እያንዳንዱ፡ ተማሪ፡ እንዳንድ፡ ብር፡ ቢያገኝ፡ ኖሮ፡ ምን፡ ያደርገው፡ ነበር?	ወረቀትና፡ እንቦልስ፡ ይገዛ፡ ነበር።
አስር፡ ብር፡ ቢሰጥሽ፡ ኖሮ፡ ምን፡ ትገዢ፡ ነበር?	ሸማ፡ እገዛ፡ ነበር።
ዛሬ፡ ቅዳሜ፡ ቢሆን፡ ኖሮ፡ ምን፡ እንሠራ፡ ነበር?	ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ እንሄድ፡ ነበር።
መኪና፡ ባይኖረው፡ ኖሮ፡ ወደ፡ ከተማ፡ እንዴት፡ ይሄድ፡ ነበር?	በእግሩ፡ ይሄድ፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
አሜሪካ፡ በሄዳችሁበት፡ ጊዜ፡ ዋሽንግተንን፡ አያችሁ?	አዎ፡ አየነው። የለም፡ አላየነውም።
ከበደ፡ በሚማርበት፡ ጊዜ፡ ቆሠሎ፡ ነበር?	አዎ፡ ቆሠሎ፡ ነበር። የለም፡ አቆሠሎም፡ ነበር።
ሴትዮዎ፡ እዚህ፡ በመጣችበት፡ ጊዜ፡ ከልጅዎ፡ ቤት፡ አረፈች?	አዎ፡ ከልጅዎ፡ ቤት፡ አረፈች። የለም፡ ከልጅዎ፡ ቤት፡ አላረፈችም።
ደብዳቤውን፡ በጻፈበት፡ ጊዜ፡ አብረኸው፡ ነበርህ?	አዎ፡ አብሬው፡ ነበርሁ። የለም፡ አብሬው፡ አልነበርሁም።
ባለፈው፡ ሳምንት፡ አባትና፡ እናትህን፡ አየህ?	አዎ፡ አየሁ። የለም፡ አላየሁም።
በሚመጣው፡ ማክሰኞ፡ አብረኸን፡ ወደ፡ ኒውዮርክ፡ መሄድ፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ። የለም፡ አልፈልግም።
በሚመጣው፡ ታህሳስ፡ አማርኛ፡ ለማስተማር፡ ይፈልጋል?	አዎ፡ ይፈልጋል። የለም፡ አይፈልግም።

ጥያቄ	መልስ
አስተማሪዎ፡ አሜሪካዊት፡ ናት?	አዎ፡ አሜሪካዊት፡ ናት። የለም፡ አሜሪካዊት፡ አይደለችም።
በሚመጣው፡ ሳምንት፡ ለትዮዋን፡ ታመጡዋታላችሁ?	አዎ፡ እናመጣታለን። የለም፡ አናመጣትም።
ለትዮዋ፡ መጣች?	አዎ፡ መጣች። የለም፡ አልመጣችም።
ሥራቸውን፡ በሚሠሩበት፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ ትሄዳለህ?	አዎ፡ እሄዳለሁ። የለም፡ አልሄድም።
ባለፈው፡ ቅዳሜ፡ ወደ፡ ሱቅ፡ ሄዳችሁ፡ ነበር?	አዎ፡ ሄደን፡ ነበር። የለም፡ አልሄድንም።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ወደ፡ እናንተ፡ አገር፡ ይመጣል?	አዎ፡ ይመጣል። የለም፡ አይመጣም።
ሥራህን፡ ከአምስት፡ ሰዓት፡ በፊት፡ ብትጨርስ፡ ወደ፡ ቤትህ፡ አብረን፡ እንሄዳለን?	አዎ፡ እንሄዳለን። የለም፡ አንሄድም።

ጥያቄ	መልስ
እያንዳንዱ፡ሰው፡ሦስት፡ሦስት፡ብር፡በየወሩ፡ቢከፍል፡በጣም፡ጥሩ፡ነው?	አዎን፡ ጥሩ፡ ነው። የለም፡ጥሩ፡አይደለም።
ጋዜጣውን፡ከእንግሊዝኛ፡ወደ፡አማርኛ፡ቢተረጉሙት፡በጣም፡ጥሩ፡ነው?	አዎን፡ በጣም፡ጥሩ፡ነው። የለም፡ ጥሩ፡አይደለም።
ልጃገረድዋ፡ወደ፡ትምህርት፡ቤት፡ለመሄድ፡ብትፈልግ፡መሄድ፡ትችላለች?	አዎ፡መሄድ፡ትችላለች፡ የለም፡ አትችልም።
ሁለት፡የመኪና፡ጐማዎች፡ቢኖሩህ፡አንዱን፡መውሰድ፡እችላለሁ?	አዎን፡ ይችላሉ። የለም፡ አይችሉም፡
የሁለት፡ብር፡ቤንዚን፡ለመኪናው፡ውስጥ፡ቢጨምሩለት፡ዋሽንግተን፡ያደርሰዋል?	አዎን፡ያደርሰዋል። የለም፡አያደርሰውም።
በሚመጣው፡እሁድ፡ወደ፡ሲኒማ፡ቤት፡ትሄዳላችሁ?	አዎን፡እንሄዳለን። የለም፡አንሄድም።

ጥያቄ	መልስ
ወንበርዋን፡ወሰዷቸው?	እዎን፡ወሰዷቸው። የለም፡አልወሰዷቸውም።
ደብዳቤውን፡በሚያነቡበት፡ ጊዜ፡ እንታ፡ ቡና፡ ትጠጣ፡ ነበር?	እዎን፡ እጠጣ፡ ነበር። የለም፡ አልጠጣም፡ ነበር።
የቤቷን፡ኪራይ፡በከፈሉ፡ጊዜ፡ ቦርሳውን፡ ትሰጡታላችሁ?	እዎን፡ እንሰጠዋለን። የለም፡አንሰጠውም።
እንታ፡ቤት፡በሚመጡበት፡ ቀትር፡ምሳውን፡ይበላል?	እዎን፡ ይበላል። የለም፡ አይበላም።
አማርኛ፡በማንበቡ፡ብዙ፡ አዲስ፡ ቃሎች፡ አወቀ?	እዎ፡ ብዙ፡ ቃሎች፡ አወቀ። የለም፡ ብዙ፡ ቃሎች፡ አላወቀም።
ሥራ፡ በሚሠሩበት፡ ቀትር፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ያገኛሉ?	እዎን፡ ያገኛሉ። የለም፡ አያገኙም።
በወንበር፡ ላይ፡ በሚቀመጡበት፡ ጊዜ፡ መጽሐፍ፡ ያነብባሉ?	እዎን፡ ያነብባሉ። የለም፡ አያነብቡም።

ጥያቄ	መልስ
ከሆቴሉ፡ ባለቤት፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ በመክፈሉ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ስፍራ፡ አገኘ?	አዎን፡ አገኘ። የለም፡ አላገኘም።
ዕዳ፡ ባለበት፡ ቁጥር፡ ቶሎ፡ ይከፍላል?	አዎ፡ ቶሎ፡ ይከፍላል። የለም፡ አይከፍልም።
ዕዳውን፡ በመክፈሉ፡ ምክንያት፡ ደስ፡ አለው?	አዎ፡ ደስ፡ አለው። የለም፡ ደስ፡ አላለውም።
በሰዓቱ፡ በመድረስሽ፡ ደስ፡ አለሽ?	አዎን፡ ደስ፡ አለኝ። የለም፡ ደስ፡ አላለኝም።
ስንቃችሁን፡ ሌባ፡ መሰደባችሁ?	አዎን፡ መሰደብን። የለም፡ አልመሰደብንም።
በየጊዜው፡ ስልክ፡ ትደውልላታለህ?	አዎን፡ እደውልላታለሁ። የለም፡ አልደውልላትም።
እንደ፡ ገርፎጣና፡ እንደ፡ ሸሚዝ፡ ብትመጣለህ፡ ደስ፡ ይለሃል?	አዎ፡ ደስ፡ ይለኛል። የለም፡ ደስ፡ አይለኝም።
ከእርጎሉ፡ ሦስት፡ ሣንቲም፡ ብሰጣት፡ መልካም፡ ነው?	አዎ፡ መልካም፡ ነው። የለም፡ መልካም፡ አይደለም።

ጥያቄ	መልስ
ሰማያዊ፡ መኪናውን፡ ከወሰደበት፡ ይፈልጋል?	አዎን፡ ይፈልጋል። የለም፡ አይፈልግም።
ጎማቸውን፡ ሸጠገቸው?	አዎን፡ ሸጠገቻው። የለም፡ አልሸጠገቻውም።
በመኪናው፡ ውስጥ፡ ዘይት፡ ጨመረ?	አዎን፡ ጨመረ። የለም፡ አልጨመረም።
ከበደ፡ የመኪናው፡ ጎማ፡ ፈነዳበት?	አዎን፡ ፈነዳበት። የለም፡ አልፈነዳበትም።
አህያቸውን፡ ዓለሙ፡ ወሰደባቸው?	አዎን፡ ወሰደባቸው። የለም፡ አልወሰደባቸውም።
ዓለሙ፡ የከበደን፡ ዘይት፡ ጨረሰበት?	አዎን፡ ጨረሰበት። የለም፡ አልጨረሰበትም።
አስር፡ ሣንቲም፡ ብትሰጥህ፡ ቡና፡ ትጠጣለህ?	አዎን፡ እጠጣለሁ። የለም፡ አልጠጣም።
ወደ፡ ሱቅ፡ ብትሄድ፡ ሰሬባት፡ ትገዛልሃለች?	አዎን፡ ትገዛልኛለች። የለም፡ አትገዛልኝም።
ቁርስ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ቢበሉ፡ መልካም፡ ይመስልሃል?	አዎን፡ ይመስለኛል። የለም፡ አይመስለኝም።

ጥያቄ	መልስ
የእህትህ፡ ድመትና፡ ውሻ፡ እዚህ፡ ቢመጡ፡ ትወስድላታለህ?	አዎን፡ እወስድላታለሁ። የለም፡ አልወስድላትም።
እሱ፡ ዮሐንስ፡ ኪሱን፡ ይዳብሳል?	አዎን፡ ይዳብሳል። የለም፡ አይዳብስም።
መጽሐፉን፡ ከአማርኛ፡ ወደ፡ እንግሊዝኛ፡ ቢተረጉም፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ይችላል?	አዎን፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ይችላል። የለም፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ አይችልም።
ሦስት፡ ሰዎች፡ በመንገድ፡ ላይ፡ ብታይ፡ ትጠራቸዋለህ?	አዎን፡ እጠራቸዋለሁ። የለም፡ አልጠራቸውም።
ፀሐይ፡ ብትወጣ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ትሄዳለህ?	አዎን፡ እሄዳለሁ። የለም፡ አልሄድም።
ደንበኛህ፡ ብትሆን፡ እሬንጊድውን፡ ሜማ፡ ትሰጣታለህ?	አዎን፡ እሰጣታለሁ። የለም፡ አልሰጣትም።

ጥያቄ	መልስ
የቤት፡ኪራይ፡ቅናሽ፡ ብታደ ርግላቸው፡ በቤቱ፡ውስጥ፡ ይቆዩበት፡ ይመስልሃል?	አዎን፡ ይመስለኛል። የለም፡ አይመስለኝም።
አህያና፡ ፈረስ፡ በመግዛቱ፡ ደስ፡ አለው?	አዎን፡ ደስ፡ አለው። የለም፡ ደስ፡ አላለውም።
መኪና፡ ስላገኘህ፡ ታዝናለ ህ?	የለም፡ አላዝንም።
ኮከብ፡ ስለወጣች፡ ደስ፡ አለህ?	አዎ፡ ደስ፡ አለኝ።
ፊታና፡ ስላላፉችሁ፡ ወደ፡ እዚህ፡ እበግ፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	የለም፡ አንፈልግም።
እያታችን፡ ስለምታነብን፡ ወ ደ፡ እዚህ፡ ከተማ፡ እየ ሊኽን፡ ትሄዳለህ?	አዎ፡ እሄዳለሁ።
በዝናብ፡ ውስጥ፡ መሮጥ፡ ስለማትችል፡ ምን፡ ማ ድረግ፡ ትፈልጋለህ?	ታክሲ፡ ከመኪናዬት፡ እፈልጋ ለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ገርዶማና፡ ሸሚዝ፡ ለመግዛት፡ ስለምትፈልግ፡ በዚህ፡ አውቶቡስ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ትሄዳለህ?	እሺ፡ እሄዳለሁ። የለም፡ አልሄድም።
ወንድምህ፡ አርብ፡ ስለሚመጣ፡ ስልክ፡ ትደውልለታለህ?	ሐሙስ፡ ከቀኑ፡ በአራት፡ ሰዓት፡ ልደውልለት፡ አስቤአለሁ።
መሬት፡ ስለምትዘር፡ እኛም፡ አብረን፡ እንዘራለን?	የለም፡ አንዘርም።
ከህያ፡ ነፍስ፡ እንዳለው፡ ታውቃለህ?	በውነቱ፡ አላውቅም።
ክረምት፡ ስለሚመጣ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ትፈልጋለህ?	ለዕረፍት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ እሄዳለሁ።
ስለ፡ አዲሱ፡ ከተማ፡ ምን፡ ትነግረኛለህ?	የምነግርህ፡ ነገር፡ የለኝም።
ስለ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ እዚህ፡ መምጣት፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ። የለም፡ አላውቅም።

ጥያቄ	መልስ
በሬ፡ ስለሰጡሽ፡ ካሳም፡ ትሰጫቸዋለሽ?	አዎን፡ እሰጣቸዋለሁ።
አልማዝ፡ ስልክ፡ ስለምትደውል፡ አንተም፡ ትደውላለህ?	አዎን፡ እደውላለሁ። የለም፡ አልደውልም።
አጎታችሁ፡ መጥተው፡ ስለጠየቁዋችሁ፡ ደስ፡ አላችሁ?	በጣም፡ ደስ፡ አላለንም።
በንቅ፡ ስላገኘች፡ እዚህ፡ ትቆያለች?	የለም፡ አትቆይም። አዎ፡ ትቆያለች።
ስለ፡ እህትህ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ ታውቃለህ?	የለም፡ አላውቅም።
አጎትህ፡ ገንዘብ፡ ስላገኙ፡ ደስ፡ አለህ?	አዎን፡ ደስ፡ አለኝ። የለም፡ ደስ፡ አላለኝም።
ስለ፡ ወንድሙ፡ ተናገረ?	የለም፡ ስለ፡ ሴት፡ ልጁ፡ ተናገረ።
ስለ፡ ጥያቄው፡ ምን፡ መለሰ?	ምንም፡ አልመለሰም።
ብዙ፡ ስለሠራች፡ ራስዋን፡ አመማት?	የለም፡ ብዙ፡ ስለሠራች፡ ራስዋን፡ አላመማትም።

ጥያቄ	መልስ
ስለ፡ አዲሱ፡ ነቃወማ፡ ምን፡ ትነግረኛለህ?	ምንም፡ ነገር፡ አልነገርኸኝም።
ስለ፡ አውቶቡስ፡ መምጣት፡ ታውቃለህ?	የለም፡ አላውቅም።
ካም፡ ስለሰጠሃቸው፡ ምን፡ የሰጡሃል?	ምናልባት፡ አንድ፡ ሌሊት፡ ያስጡኛል።
ስለ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴሩ፡ ምን፡ ታስባላችሁ?	አሁን፡ ምንም፡ ማሰብ፡ አንችልም።
ብዙ፡ ስንቅ፡ እዚህ፡ ስለሌለ፡ ወደ፡ አገራቸው፡ መሄድ፡ አይፈልጉም?	ወደ፡ አገራቸው፡ መሄድ፡ በጣም፡ ይፈልጋሉ።
ቋንቋ፡ ለማወቅ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ያገኛል?	የለም፡ አያገኝም።
ስለ፡ ጥያቄው፡ ምን፡ መለስህ?	ምንም፡ አልመለስሁም።
ስለ፡ ንግግሩ፡ ምን፡ ታስባለህ?	ምንም፡ አላስብም።
ስለ፡ ምን፡ መናገር፡ ትፈልጋለህ?	ስለ፡ ትምህርት፡ ቤቱ፡ መናገር፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ስለ፡ አማርኛ፡ ቋንቋ፡ መናገር፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፡ እፈልጋለሁ።
ስለ፡ ትናንቱ፡ ሌት፡ ለባለቤትህ፡ ነገርሃት?	የለም፡ አልነገርሁዋትም።
ጥዋት፡ ቡና፡ ስላልጠጣች፡ አሁን፡ መጠጣት፡ ትፈልጋለች?	አላውቅም።
ለማ፡ ስለሌላት፡ ትገዛላታለህ?	የለም፡ አልገዛላትም።
መኪናው፡ አረንጓዴ፡ ስላልሆነ፡ መግዛት፡ አትፈልግም?	አዎን፡ አልፈልግም።

ድርሰት።

ጊዜው፡ በጋ፡ ስለሆነ፡ ፀሐይ፡ ወጥታለች። አቶ፡ ከበደም፡ ወንድሙን፡ ከማየት፡ ስለፈለገ፣ ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ለአሥራ፡ አምስት፡ ቀን፡ ፈቃድ፡ ተቀበለ።

የአቶ፡ ከበደ፡ ወንድም፡ የሚኖረው፡ በሐረር፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ስለሆነ፣ በመኪና፡ ከመሄድ፡ አሰበ። አቶ፡ ከበደ፡ ሚማውን፣ ከታን፣ ሽሚዜንና፡ ከሌገታን፡ ካዘጋጀ፡ በኋላ፡ ከመኪናው፡ ውስጥ፡ ቤንዚንና፡ ዘይት፡ ጨመረ። ጉዞውን፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፣ ልጁ፡ ፈተናውን፡ ጨርሶ፡ ስለነበር፣ ካጎቱ፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ አብሮ፡ ከመሄዱና፡ አጎቱን፡ ከማየት፡ ፈለገ።

አጎትና፡ ልጁ፡ አብረው፡ አምስት፡ ሰዓት፡ ከተጓዙ፡ በኋላ፡ በመንገዳቸው፡ ላይ፡ በሚገኘው፡ ጣቢያ፡ አርፈው፡ ምሳቸውን፡ በሉ። ምሳቸውን፡ እስኪበሉ፡ ድረስ፡ የመኪናቸው፡ ጎማ፡ ኪፈነዳ፡ ስለነበር፣ የመኪናውን፡ ጎማ፡ አሳድሰው፡ መንገዳቸውን፡ እንደገና፡ ጀመሩ።

እስከ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ያህል፡ ከተጓዙ፡ በኋላ፡ በሁለተኛው፡ ቀን፡ ሐረር፡ ከተማ፡ ደረሱ። በደረሱበት፡ ሰዓት፡ ፀሐይ፡ ጠልቃ፡ ስለነበር፣ ኮከቦችን፡ ከማየት፡ ቻሉ።

ጥያቄዎች፡

አቶ፡ ከበደ፡ ማንን፡ ለማየት፡ ፈለገ?

ፈቃዱ፡ ከየት፡ ተቀበለ?

አቶ፡ ከበደ፡ ወንድሙን፡ በየትኛው፡ ወራት፡ ማየት፡ ፈለገ?

ፈቃዱ፡ ለስንት፡ ቀን፡ ተቀበለ?

የአቶ፡ ከበደ፡ ወንድም፡ የሚኖረው፡ የት፡ ነው?

አቶ፡ ከበደ፡ ከማን፡ ጋር፡ ሄደ?

አቶ፡ ከበደና፡ ልጁ፡ በምን፡ ተጓዙ?

ከመሄዱ፡ በፊት፡ ምን፡ አዘጋጀ?

አጎቱና፡ ልጁ፡ አብረው፡ ስንት፡ ሰዓት፡ ተጓዙ?

የአቶ፡ ከበደ፡ ልጁ፡ ለምን፡ ከአጎቱ፡ ጋር፡ ሄደ?

ምሳቸውን፡ የት፡ በሉ?

የመኪናቸውን፡ ጎማ፡ ምን፡ አደረጉት?

ሐረር፡ መቼ፡ ደረሱ?

ሐረር፡ ሲደርሱ፡ ምን፡ አዩ?

በሳምንት፡ ውስጥ፡ ያሉትን፡ የቀኖች፡ ስም፡ ንገረኝ?

የአመቱን፡ ወራት፡ ስሞች፡ ንገሩኝ?

አስራ፡ አምስተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

አጎላሌ

ምን፡ ላቅርብ፡ ጌታዬ?
ምን፡ ላምጣ፡ ጌታዬ?

ጃን

ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ አላችሁ?

አጎላሌ

የዶሮ፡ አልጫ፣ ፓስታ፡ ሹታ፣ አትክልት፣ ጥብስ፡ ሥጋ፣ የዶሮ፡ ወጥ፡ ከነእንቁላሉም፣ ነጭ፡ እንጀራና፡ ዳቦ፡ አለን።

ጃን

ለእኔ፡ የዶሮ፡ ወጥ፡ ከነጭ፡ እንጀራ፡ ጋር፡ እፈልጋለሁ።

አጎላሌ

ከመጠጡስ፡ ምን፡ ላምጣ?

ጃን

የጾም፡ ምግብ፡ ምን፡ አላችሁ?

አጎላሌ

ከዓሣና፡ ከአትክልት፡ የተሠራ፡ የጾም፡ ምግብ፡ አለን። ሌላም፡ ዓይነት፡ ከፈለጉ፡ መሥራት፡ እንችላለን።

ጃን

ዓሣ፡ ስለምትወድ፡ የዓሣ፡ ወጡን፡ አምጣልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
ፈቃዱ፡ ብታገኙ፡ ትመጣላችሁ?	አዎ፡ ካገኘን፡ እንመጣለን።
ውድ፡ ከሆነ፡ ለምን፡ እሪያን፡ ሆቴል፡ ትቆያለህ?	በከተማው፡ ውስጥ፡ ሌላ፡ ሆቴል፡ የለም።
እንዴ፡ ሰዓት፡ ካለፈ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ይሄዱ?	አዎ፡ ይሄዱ።
ለማ፡ ከበሶ፡ ትበላለህ?	አዎ፡ ከበሶ፡ እበላለሁ።
ሌሊት፡ ከጠፋህ፡ ትሄዳለህ?	ከጠፋኝ፡ እሄዳለሁ።
ዝናብ፡ ከመጣ፡ ወደ፡ ቤትሽ፡ አትሄጂም?	ዝናብ፡ ከመጣ፡ ወደ፡ ቤቴ፡ እሄዳለሁ።
ጉማሙን፡ ካደሉት፡ ገንዘብ፡ ትሰጡዋቸዋላችሁ?	ገንዘብ፡ ካለን፡ እንሰጣቸዋለን።
አሁን፡ ከመጡ፡ ደብዳቤ፡ ትሰጣቸዋለህ?	አዎ፡ እሰጣቸዋለሁ።
እሆቴሉ፡ ውስጥ፡ የዶሮ፡ ወጥ፡ ከነእንቁላሉ፡ ካገኘህ፡ ትበላለህ?	ካገኘሁ፡ እበላለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ፓስታ፡ ሹታ፡ ቢያቀርብላችሁ፡ ትበላላችሁ?	ካቀረበልን፡ እንበላለን።
ፀሐይ፡ ስትገባ፡ ጨረቃ፡ ትወጣለች?	አዎ፡ ፀሐይ፡ ከገባች፡ ጨረቃ፡ ትወጣለች።
ወንድምህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከገባ፡ ትገባለህ?	ከገባ፡ እገባለሁ።
አሜሪካ፡ ከመጣችሁ፡ ስንት፡ ዓመት፡ ሆነ?	አሥር፡ ዓመት፡ ሆነ።
አማርኛ፡ መማር፡ ከፈለግ፡ ለምን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ አትሄድም?	ከአንድ፡ ሳምንት፡ በኋላ፡ ይሄዳል።
የዛሬ፡ ሳምንት፡ ከመጣች፡ ወደ፡ እኛ፡ ታመጣታለህ?	አዎ፡ ከመጣች፡ አመጣታለሁ።
ፍቃድ፡ ከጠየቃችሁ፡ ታገኛላችሁ?	አዎ፡ ከጠየቅን፡ እናገኛለን።
ገንዘብ፡ ካለው፡ ወደ፡ ሐረር፡ በመኪና፡ መሄድ፡ ይችላል?	አዎ፡ ገንዘብ፡ ካለው፡ መሄድ፡ ይችላል።

ጥያቄ	መልስ
ቤታችሁን፡ ካሳደሳቹ፡ ስንት፡ ዓመት፡ ሆነው?	ሁለት፡ ዓመት፡ ሆኖታል።
አባትና፡ እናትህን፡ ካየህ፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ሆነ?	አንድ፡ ዓመት፡ ሆነ።
መኪና፡ ካለህ፡ ለምን፡ አንድ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ እዚህ፡ አትመጣም?	ጊዜ፡ የለኝም።
ካሜሪካ፡ ከመጣ፡ አቶ፡ ሮቢንሰን፡ ማን፡ አየው?	አቶ፡ ለማ፡ አየው።
ወንድምህ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከሄደ፡ ደብዳቤ፡ ጻፈ?	አንድ፡ ጊዜ፡ ብቻ፡ ጻፈ።
መጽሐፉን፡ ከጠየቀች፡ ለምን፡ አልሰጠሃትም?	እስዋ፡ መጽሐፉን፡ መውሰድ፡ አልፈለገችም።
ብዙ፡ ገንዘብ፡ ካላቸው፡ ለምን፡ መኪና፡ አልገዙም?	መኪና፡ አያስፈልጋቸውም።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ቢያገኙ፡ ይሄዳሉ?	አዎ፡ ደህና፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ካገኙ፡ ይሄዳሉ።
ምሳዎን፡ ከበላቹ፡ ማንበብ፡ አትፈልጉም?	የምትፈልጉ፡ አይመስለኝም።

ጥያቄ	መልስ
እናትህና፡ አባትህ፡ ከመጡ፡ ትመጣለህ?	ከመጡ፡ እመጣለሁ።
በጥዋት፡ ብመጣ፡ አብሬህ፡ መሄድ፡ እችላለሁ?	አዎ፡ ጥዋት፡ ከመጣህ፡ እብረን፡ እንሄዳለን።
መሄድ፡ ካልቻልሁ፡ ትመልስልኛለህ?	መሄድ፡ ካልቻልህ፡ እመልስልሃለሁ።

ድርሰት፡

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለምሳ፡ ወደ፡ አንድ፡ ሆቴል፡ ሄዱ። በዚህ፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የኢትዮጵያ፡ ምግብ፡ ነበር።

የሆቴሉ፡ አሳላፊ፡ እንግዳውን፡ እንዳየ፡ ሄዶ፡ ምን፡ ላቅርብ፡ ጌታዬ፡ ብሎ፡ ጠየቀው። አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለጥቂት፡ ጊዜ፡ ከቆዩ፡ በኋላ፤ ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ አላችሁ፡ አሉና፡ አሳላፊውን፡ ጠየቀው። አሳላፊውም፡ የዶሮ፡ አልጫ፤ ፓስታ፡ ሾርባ፤ አትክልት፤ ጥብስ፡ ሥጋ፤ የዶሮ፡ ወጥ፤ ሩዝ፡ እንጀራና፡ ዳቦ፡ አለን፡ አለው። አቶ፡ ዮሐንስም፡

ለራሱ፡ የዶሮ፡ ወጥ፡ ከነእንቁላሉም፤ ለጋበዛት፡ ዓሣ፡ ወጥ፡ አዘዘ።

ጥያቄዎች፡

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለምሳ፡ የት፡ ሄዱ?

እሱ፡ በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ከማን፡ ጋር፡ ተነጋገረ?

ለምሳው፡ ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ አዘዘ?

ለጋበዛት፡ ምን፡ አዘዘላት?

እሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ ይገኛል?

ለምግቡ፡ ስንት፡ ገንዘብ፡ ከፈለ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከየት፡ አገር፡ መጡ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ እህትና፡ ወንድም፡ አሉት?

እንግዳው፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ምን፡ ብሎ፡ ጠየቀው?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ አሉና፡ መለሱለት?

አስራ፡ ስድስተኛ፡ ትምህርት፡

ንግግር

አሳካው

ከማዘጋጀት፡ ትንሽ፡ ጊዜ፡ ስለሚፈጅ፡ ሩብ፡ ሰዓት፡ ያህል፡ ታገሱኝ።

ጆን

ግድ፡ የለም፤ እንቆያለንም።

አሳካው

እስከዚያ፡ ድረስ፡ ከመቀነሻ፡ ምን፡ ዓይነት፡ መጠጥ፡ ላቅርብ?

ጆን

በጣም፡ ጥሩ፡ አሳብ፡ ነው። ምን፡ ዓይነት፡ መጠጥ፡ አላችሁ?

አሳካው

የውጭ፡ አገር፡ ወይም፡ ያገር፡ ውስጥ፡ መጠጥ፡ ይፈልጋሉ?

ጆን

ምን፡ ዓይነት፡ ያገር፡ ውስጥ፡ መጠጥ፡ አለ?

አሳካው

ቪኖ፣ ቢራ፣ አረቄ፣ ጠላና፡ ጠጅ፡ አለን።

ጆን

ከእኔ፡ አንድ፡ ጠርሙስ፡ ቢራ፣ ከእስዋ፡ ደግሞ፡ አንድ፡ ጠርሙስ፡ ጠጅ፡ እንጠጣለን።

ሚስስ፡ ጆን

ውሃ፡ እንጂ፡ ጠጅ፡ እንዲያመጣልኝ፡ አልፈልግም።

አሳካው

እሺ።

ጆን

ስንት፡ እከፍልሃለሁ?

አሳላፊ	ጆን
አምስት፡ብር፡ከሃምሳ፡ሣንቲም፡ነው።	የሃምሳ፡ብር፡ምንዛሪ፡አለህ?
	አሳላፊ
	አዎን፡ አለኝ።

ጥያቄና፡መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
አሳላፊው፡ምን፡ዓይነት፡ምግብ፡እንዲሰጥህ፡ትፈልጋለህ?	ዓሣ፡ወጥና፡ዳቦ፡እንዲሰጠኝ፡እፈልጋለሁ።
ጋዜጣ፡እንድገዛላችሁ፡ትፈልጋላችሁ?	ከአሥራ፡አምስት፡ደቂቃዎች፡በኋላ፡ግዛን።
ገንዘብ፡እንድትሰጪው፡አልነገረሽም?	የለም፡ አልነገረኝም።
ጋዜጣውን፡ሊያነብ፡እንድታዶች፡ፈለገ?	አዎን፡ እንድናነበው፡ ፈለገ።

ጥያቄ	መልስ
ስንት፡ ሰዎች፡ እንዲመጡ፡ ነገርሃቸው?	ሃምሳ፡ ሰዎች፡ እንዲመጡ፡ ነገርሁዋቸው።
ጥቂት፡ ጊዜ፡ እንድትታገሡት፡ ነገሩችሁ?	አዎን፡ ነገሩን።
የዱሮ፡ አለቃ፡ እንድንሠራላችሁ፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎን፡ እንፈልጋለን።
ፓስታ፡ ሹታ፡ እንዲበላ፡ ጠየቅኸው?	የለም፡ አልጠየቅሁትም።
ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ እንድትበሉ፡ ትፈልጋላችሁ?	ጥብስ፡ ሥጋ ፡ እንድንበላ፡ እንፈልጋለን።
የቱን፡ ምግብ፡ እንዲያቀርብልሽ፡ ትፈልጋለሽ?	የዱሮ፡ ወጡን፡ እንዲያቀርብልኝ፡ እፈልጋለሁ።
ከመቤቱ፡ ምን፡ እንዲመጣላቸው፡ ይፈልጋሉ?	ቢራ፡ እንዲመጣላቸው፡ ይፈልጋሉ።
ከበደና፡ ከማ፡ እንዲመጡ፡ አትፈልጉም?	የለም፡ አንፈልግም።
ወደ፡ አሜሪካ፡ ለሄዱ፡ እንዲመስዱሽ፡ ነገርሃቸው?	አዎን፡ ነገርሁዋቸው።

ጥያቄ	መልስ
ከኢትዮጵያዊያን፡ ጋር፡ ሲሆን፡ አማርኛ፡ እንዲናገር፡ ማን፡ ነገረው?	አባትና፡ እናቱ፡ ነገሩት።
ብዙ፡ ገንዘብ፡ እንዲያገኝ፡ የት፡ እንሥራ?	ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ እንሥራ።
ምን፡ ዓይነት፡ ምሳሌ፡ እንዲነገርዎ፡ ያስፈልጋል?	እኔ፡ ምሳሌ፡ አልፈልግም።
እቤትዎ፡ መኝታው፡ እንዲሠሩ፡ ነገሩዋቸው?	አዎን፡ ነገርሁዋቸው።
ጋዜጣውን፡ እንድትተረጉመው፡ ማን፡ ነገረህ?	አስተማሪዬ፡ ነገሩኝ።
ደብዳቤውን፡ ዛሬ፡ እንዲደርስለው፡ ነገራችሁት?	አዎን፡ ነገርናው።
ምሳቸውን፡ አብረው፡ እንዲበሉ፡ ጠሩዋቸው?	አዎን፡ እቤቴ፡ ድረስ፡ ጠራሁዋቸው።
ወደ፡ ሥራው፡ እንዲሮጥ፡ ማን፡ ነገረው?	ወንድሙ፡ የነገረው፡ ይመስለኛል።
ከቤቱ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ እንዲንከፈለ፡ ያውቃል?	አዎን፡ ያውቃል።

ጥያቄ	መልስ
ከማና፡ ጥሩነሽ፡ አባትህን፡ እንዲጠይቋቸው፡ ትፈልጋለህ?	እሺ፡ በጣም፡ እፈልጋለሁ።
በምን፡ እንዲመጣ፡ ትፈልጊያለሽ?	በመኪና፡ እንዲመጣ፡ እፈልጋለሁ።
እናትሽ፡ እዚህ፡ እንዲመጡ፡ ነገርሺያቸው?	አዎን፡ ነገርሁዋት።
በኣምስት፡ ሰዓት፡ ከሥራ፡ እንዲወጡ፡ ነገርሃቸው?	አዎን፡ ነገርሁዋቸው።
ከበደና፡ ከማ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ቡና፡ እንዲጠጡ፡ ነገርሃቸው?	አዎን፡ ነገርሁዋቸው።
ሰዓት፡ እንዲሰጡሽ፡ ትፈልጊያለሽ?	አዎን፡ እፈልጋለሁ።
ነገ፡ ማን፡ እንዲመጣ፡ ትፈልጋለህ?	አስተማሪው፡ እንዲመጣ፡ እፈልጋለሁ።
ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ከመሄድ፡ አባትና፡ እናትህ፡ እንዲፈቅዱልህ፡ ትፈልጋለህ?	እሺ፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ምሳህን፡ እንዲያዘጋጁልህ፡ ትፈልጋለህ?	አሣን፡ እንዲያዘጋጁልኝ፡ እፈልጋለሁ።
ጋዜጣ፡ እንድታነብ፡ ትፈልጋለህ?	የለም፡ አልፈልገውም።

ድርሰት፡

ትናንትና፡ እኔና፡ ባለቤቴ፡ ወደ፡ ሆቴል፡ ሄደን፡ ነበር። ሆቴሉ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነበር። ብዙ፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ አገኘን። ከፓስታ፡ ሹታው፡ የዶሮው፡ ወጥ፡ ጣዕም፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው። መጠጥ፡ በየዓይነቱ፡ ይገኛል። ጠጅ፡ የሚባለው፡ መጠጥ፡ ከምግብ፡ ጋር፡ ይስማማል። ነገር፡ ግን፡ ጥቂት፡ ጠንካራ፡ ነው። ባለቤቴ፡ ቢራውን፡ በጣም፡ ስለወደደችው፡ ሁለት፡ ጠርሙስ፡ ያህል፡ ጠጣች።

በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ የነበረው፡ አሳላፊ፡ ትሁት፡ ነበር። የሆቴሉ፡ ባለቤት፡ ጥቁር፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ በሆቴሉ፡ መግቢያ፡ ላይ፡ ቆሞ፡ ነበር።

ከሆቴሉ፡ ስንገባ፡ ወደ ምንቀመጥበት፡ ቦታ፡ መሩን

ና፡ ከመተከክሎ፡ የሚሆን፡ ነገር፡ አቀረበልን። ከዚያም፡ በኋላ፡ አሳላፊውን፡ መጠጥ፡ እንዲያቀርብልን፡ አዘዘው።

ምግቡን፡ ስንበላ፡ የኢትዮጵያና፡ የአውሮፓ፡ ሙዚቃ፡ ስለሰማን፡ የደስታ፡ ምሽት፡ ሆኖልን፡ ነበር። ምግባችንን፡ ጨርሰን፡ ሰላሳ፡ ደቂቃ፡ ከቆየን፡ በኋላ፡ አሳላፊው፡ የምግቡን፡ ዋጋና፡ ጉርሻ፡ ከፍለን፡ ወደ፡ ቤታችን፡ ተመለስን።

ምግቡ፡ በጣም፡ እርካሽ፡ ነው። የአገር፡ ውስጥ፡ መጠጥም፡ እርካሽ፡ ነው። ግን፡ የውጭ፡ አገር፡ መጠጥ፡ ውድ፡ ነው።

ጥያቄዎች፡

ትናንት፡ አቶ፡ ከበደ፡ ከባለቤታቸው፡ ጋር፡ የት፡ ሄደው፡ ነበር?

በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ምግብና፡ መጠጥ፡ አገኙ?

ጠጅ፡ የሚባለው፡ መጠጥ፡ ከምን፡ ጋር፡ ይስማማል?

የአቶ፡ ከበደ፡ ባለቤት፡ ስንት፡ ጠርሙስ፡ ቢራ፡ ጠጣች?

የሆቴሉ፡ ባለቤት፡ የት፡ ቆሞ፡ ነበር?

የሆቴሉ፡ ባለቤት፡ ምን፡ ዓይነት፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ ነበር?

እንግዳው፡ ትሁት፡ ነበር?

አቶ፡ ከበደና፡ ባለቤታቸው፡ ምን፡ ዓይነት፡ ምሽት፡ ነበራቸው?

እሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ሙዚቃ፡ ሰሙ?

ከመነሳቃቸው፡ ለሴት፡ እንግዳው፡ ምን፡ ሰጡት?

ለኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የታወቀ፡ መጠጥ፡ ምን፡ ይባላል?

እርስዎ፡ ወደ፡ ሆቴል፡ እየሄዱ፡ ይበላሉ?

እርስዎ፡ መጠጥ፡ ይጠጣሉ?

አስራ፡ሰባተኛ፡ትምህርት፡

ንግግር

በመኪና፡ሰፊ፡ቤት፡ውስጥ፡

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ አቶ፡ ለማ። ከተያየን፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሆነን።

መኪና፡ሰፊ

አዎን፡ ከተያየን፡ ሁለት፡ ወር፡ አለፈን። አሁን፡ ምን፡ ላድርግልዎ?

ከበደ

አንድ፡ ሙሉ፡ ልብስ፡ ለማሰፋት፡ እፈልጋለሁ።

መኪና፡ሰፊ

መልካም፤ ለመቼ፡ እንዲደርስልዎት፡ ይፈልጋሉ?

ከበደ

ለዛሬ፡ ሳምንት፡ ቢያደርሱልኝ፡ እወድ፡ ነበር።

መኪና፡ሰፊ

ይቻላል። አሁን፡ ልብሱ፡ እንዲለካልዎት፡ ይፈልጋሉ?

ከበደ

አዎን፡ ይለኩልኝ። እጄ፡ ረጅም፡ ስለሆነ፡ እጅጌውን፡ ረጅም፡ ያድርጉልኝ። ደግሞ፡ የኮቱ፡ ትከሻ፡ ሰፊ፡ እንዲሆን፡ እፈልጋለሁ።

መኪና፡ሰፊ

ሱሪው፡ ጠባብ፡ ይሁንልዎ?

ከበደ

ጠባብ፡ ሱሪ፡ ስለማልወድ፣ ግርጌውን፡ ሰፊ፡ ያድርጉልኝ።

መኪና፡ሰፊ

ኮቱን፡ አጭር፡ ላድርግልዎት?

ከበደ	ከበደ
በግም፡ እንኳር፡ እይሁን፤ መንከከኛ፡ ሊያደርጉት፡ ጥሩ፡ ነው።	ዋጋውን፡ አሁን፡ ልክፈልዎት?
መኪና፡ ሰሪ	**መኪና፡ ሰሪ**
እንግዲያስ፡ በሚመጣው፡ አርብ፡ በስምንት፡ ሰዓት፡ ይዘጋጅልዎታል።	ግዴ፡ የለም። ለብሱን፡ ሲወስ ዱ፡ ይከፍሉኛል።
	ከበደ
	እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ። ደህና፡ ዋሉ።

ጥያቄና፡ መልስ፡

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ አገራችሁ፡ ስትመለሱ፡ ምን፡ መሥራት፡ ታስባላችሁ?	ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ እንሠራለን።
ከአሜሪካ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደተመለሳችሁ፡ የት፡ ታርፋላችሁ?	እጊዮን፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ ማረፍ፡ እንፈልጋለን።

ጥያቄ	መልስ
ይህ፡ መኪና፡ እንዲሠራ፡ ለማን፡ ልንገር?	ለለማ፡ ንገረው፡
ለማ፡ የፈለገውን፡ መጽሐፍ፡ መቼ፡ ትሰጠዋለህ?	ከመጣ፡ ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ እሰጠዋለሁ።
አባትህን፡ ለማየት፡ መቼ፡ ወደ፡ አገርህ፡ ትሄዳለህ?	ገንዘብ፡ እንዳገኘሁ፡ እሄዳለሁ።
ስንት፡ ገንዘብ፡ ትሰጣታለህ?	የምትፈልገውን፡ ያህል፡ እሰጣታለሁ።
የሚነግሩሽን፡ ነገር፡ ትነግሪኛለሽ?	አዎ፡ እነግርሃለሁ።
ለማ፡ ከአሜሪካ፡ ከተመለሰ፡ በኋላ፡ ከማን፡ ጋር፡ ይሠራ፡ ነበር?	ከአባቱ፡ ጋር፡ ይሠራ፡ ነበር።
ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ከሚሄዱት፡ ሰዎች፡ ጋር፡ ትሄጃለሽ?	የለም፡ አልሄድም።
ይህን፡ ነገር፡ ስላየሽው፡ በጣም፡ ደስ፡ አለሽ?	አዎ፡ ስላየሁት፡ ደስ፡ አለኝ።

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ ስለመጣው፡ ሰውዬ፡ ምን፡ ታውቃለህ?	እርሱ፡ ተማሪ፡ እንደነበር፡ ብቻ፡ አውቃለሁ።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለምን፡ ወደዚህ፡ እንደመጣ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ እናቱን፡ ለማየት፡ ነው።
ስለ፡ ጠየቀህ፡ ጥያቄ፡ አሁን፡ ምን፡ ትመልሳለህ?	አሁን፡ መልስ፡ የለኝም።
ለሚወዱህ፡ ሰዎች፡ ምን፡ ማድረግ፡ ትፈልጋለህ?	እንዴ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ መኪና፡ መስጠት፡ እፈልጋለሁ።
በሁለት፡ ሰዓት፡ ቢመጡ፡ አብረሃቸው፡ ትሄዳለህ?	ብችል፡ አብሬአቸው፡ እሄዳለሁ።
አቶ፡ ለማ፡ ሁልጊዜ፡ ለምን፡ ይተክዛሉ?	በእውነቱ፡ ለምን፡ እንደሆነ፡ አላውቅም።
አቶ፡ ዮሐንስና፡ ገለፀቷ፡ ጠላ፡ ሲጠጡ፡ አየሃቸው?	የለም፡ አላየሁዋቸውም።
ቡና፡ ከመጠጣትህ፡ በፊት፡ ወደ፡ እኛ፡ መምጣት፡ ትችላለህ?	የለም፡ አልችልም።

ጥያቄ	መልስ
ገንዘቡን፡ እስኪያገኙ፡ ድረስ፡ እዚህ፡ ይቆያሉ?	አዎ፡ እዚህ፡ ይቆያሉ።
መኪናውን፡ ሊያጸዳው፡ ገንዘብ፡ ትሰጠዋለህ?	አዎ፡ አምስት፡ ብር፡ እሰጠዋለሁ።
ያገርህ፡ ሕዝብ፡ ቢማር፡ በጣም፡ ትወዳለህ?	አዎ፡ በጣም፡ እወዳለሁ።
የቤተ፡ ክርስቲያኑን፡ መግቢያ፡ የሚያውቀው፡ ማን፡ ነው?	የአቶ፡ ዮሐንስ፡ አጎት፡ ነው።
በጠቅላላው፡ ሊሸጠው፡ በስንት፡ ትገዛዋለህ?	በሃምሳ፡ ብር፡ ሊሸጠው፡ እገዛዋለሁ።
ነገሩን፡ በቀላሉ፡ ለእምቶስ፡ ተውከው፡ ከእስዎ፡ መንገር፡ ጥሩ፡ ይመስልሃል?	አዎ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ይመስለኛል።
ሌባውን፡ በእጁ፡ ሊዳብሰው፡ ጥሩ፡ መሆኑን፡ ማወቅ፡ ይችላል?	አዎ፡ ይችላል።
ከኪሱ፡ ውስጥ፡ የነበረውን፡ ቦርሳ፡ ማን፡ ወሰደው?	ተማሪዎ፡ ወሰዳቸው።

ጥያቄ	መልስ
የአቶ፡ ዮሐንስ፡ ልጅ፡ የምትማረውን፡ ትምህርት፡ ታውቃለህ?	አማርኛ፡ ቋንቋ፡ ነው።
አምስት፡ ብር፡ ያህል፡ ቢሰጥህ፡ አንተ፡ ምን፡ ትሰጠዋለህ?	አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ልብስ፡ እሰጠዋለሁ።
ሁልጊዜ፡ በአማርኛ፡ ቢናገር፡ አማርኛው፡ ይሻሻል፡ ይመስልሃል?	አዎ፡ በጣም፡ ሊሻሻል፡ ይችላል።
ወደዚህ፡ መምጣት፡ ቢሬጉ፡ እንጂ፡ ወደ፡ እርሱ፡ ትሄጃለሽ?	አዎ፡ እሄዳለሁ።
አቶ፡ ከማ፡ ደህንነቱን፡ ቢነግርህ፡ መልሰህ፡ ትነግረኛለህ?	አዎ፡ መልሼ፡ እነግርሃለሁ።
አስተማሪያችን፡ እረፍት፡ መቼ፡ የሚኖረው፡ ይመስልሃል?	ከአንድ፡ ወር፡ በኋላ፡ ይኖረዋል።
በሽታው፡ እየተሻለው፡ ሄደ?	አዎ፡ በጣም፡ ተሻሽሎታል።

ጥያቄ	መልስ
ጉንፋን፡ ሲሸንፋቸው፡ ይመጣሉ?	የለም፡ አይመጡም።
ፀሐይ፡ እስክትጠልቅ፡ ድረስ፡ ምን፡ ትሠራለህ?	መጽሐፍ፡ እነብባለሁ።
የገንዘብ፡ ቅናሽ፡ ባደርግልሽ፡ እልጋውን፡ ትገዢዋለሽ?	አዎን፡ እገዛዋለሁ።
ይህን፡ ነገር፡ እርካሽ፡ ሲያደርጉት፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይገዙዋቸዋል?	በእውነቱ፡ አላውቅም።
ጠረጴዛውና፡ ወንበሩ፡ ውድ፡ ካልሆኑ፡ ልግዛቸው?	በጣም፡ ውድ፡ ከሆኑ፡ አትግዛቸው።
ከስንቅ፡ የሚሆን፡ ዳቦ፡ ከመግዛት፡ የት፡ መሄድ፡ ያስፈልጋል?	ወደ፡ ሆቴሉ፡ መሄድ፡ ያስፈልጋል።
እዳውን፡ ከመክፈሉ፡ ማን፡ መጣ?	ከበደ፡ መጣ።
ዛሬ፡ ሌቱና፡ የሚወስደ፡ ማን፡ ነው?	ከበደ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ሌተናውን፡ የሚቀበሉት፡ ሰዎች፡ መጡ?	የለም፡ አልመጡም።
መኮንኑን፡ የሚፈልግ፡ ሰው፡ የሚገኝ፡ ይመስልሃል?	የለም፡ መኮንኑን፡ የሚወዱ፡ የለም።
የምትፈልጉትን፡ ስንቅ፡ አገኛችሁ?	የለም፡ አላገኘንም።
ሰው፡ የሚሞትበትን፡ ጊዜ፡ ያውቀዋል?	የሚሞትበትን፡ ጊዜ፡ አያውቅም።
ውሀ፡ ስንቅ፡ ሲያልቅ፡ ሌላ፡ ከየት፡ ታመጣላችሁ?	ከአገራችን፡ እናመጣለን።
ለሰበረችው፡ ሰዓት፡ ስንት፡ ገንዘብ፡ ከፈለች?	አሥራ፡ አምስት፡ ብር፡ ከፈለች።
ወንበሩን፡ ማን፡ ሲሰብረው፡ አየህ?	የወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ትንሽዋ፡ ልጅ፡ ስትሰብረው፡ አየሁ።
የጠፋውን፡ መኪና፡ የት፡ አገኛት?	እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ አገኘሁት።
ሰላዩ፡ ለፖሊስ፡ የመከሰሰ፡ ማን፡ ነው?	ሰላዩን፡ የመከሰስሁ፡ እኔ፡ ነኝ።

ጥያቄ	መልስ
የምትፈልገውን፡ የስልክ፡ ቁጥር፡ ሰጠሃት?	አዎ፡ ሰጠሁዋት።
አሁን፡ ያጣኸውን፡ ነገር፡ የምታገኘው፡ ይመስልሃል?	የለም፡ አይመስለኝም።
ምክንያቱን፡ የሚነግረኝ፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?	አስተማሪው፡ ነው።
የምታስቡትን፡ ከማወቅ፡ ጠየቃችሁ?	ምን፡ ታስገኛችሁ፡ ብሎ፡ ጠየቀን።
በቦርሳው፡ የሚወስደውን፡ ገንዘብ፡ ከማን፡ ይሰጠዋል?	ከናቱ፡ ይሰጣታል።
የሚያስፋውን፡ ልብስ፡ ዓይነት፡ አየህ?	አዎን፡ ነጭ፡ ነው።
መዝና፡ ሰዉ፡ ቤት፡ የት፡ ይገኛል?	ገጹስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ይገኛል።
ከበደ፡ እንደ፡ ሙሉ፡ ልብስ፡ ከማሰፋት፡ ማታ፡ ማታ፡ ይሠራል?	ከሁለት፡ ሳምንት፡ ያህል፡ ከመሥራት፡ አስቦአል።

ጥያቄ	መልስ
ልብሱን፡ መቼ፡ ለማሰፋት፡ እንደሚፈልግ፡ ታውቃለህ?	ለጊዜው፡ አላውቅም። ግን፡ ከማን፡ ጠይቄ፡ ልነግርዎት፡ እችላለሁ።
ረጅም፡ ሰው፡ እንደምወድ፡ ማን፡ ነገረህ?	ትንሹዋ፡ እህትሽ፡ ነገረችኝ።
በጠባብ፡ መንገድ፡ ከመሄድ፡ ካወደድህ፡ ለምን፡ በዚህ፡ መንገድ፡ መጣህ?	ለሥራዬ፡ ቅርብ፡ ስለሆነ፡ ነው።
ልብስዎን፡ የሚሰፋልዎት፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?	ጎረቤቴ፡ ጆሩ፡ ልብስ፡ ሰፊ፡ ስለሆነች፡ የእኔንና፡ የልጆቼን፡ ልብስ፡ ትሰፋለች።
ለምን፡ ያገራችሁ፡ ሴቶች፡ ረጅም፡ ልብስ፡ ይለብሳሉ?	ረጅም፡ ልብስ፡ ስለሚወዱ፡ ነው።
አሜሪካ፡ ብትሄዱ፡ ምን፡ ታያላችሁ?	መንገድና፡ ቤት፡ ብቻ፡ እናያለን።
ክረምት፡ ሲያልፍ፡ ቤት፡ ለመሥራት፡ አስባችሁዋል?	እኔና፡ ወንድሜ፡ አብር፡ ፎቅ፡ ቤት፡ ለመሥራት፡ ተዘጋጅተናል።

ጥያቄ	መልስ
በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ረጅም፡ ሰው፡ ያገኛል?	አዎ፡ ያገኛል። እጅረም፡ ሰው፡ በብዙ፡ ያገኛል።
ትልቅ፡ መኪና፡ ትወዳለህ?	መካከለኛ፡ መኪና፡ እወዳለሁ።

ድርሰት

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ወደ፡ መኪና፡ ሰፊ፡ ቤት፡ መሄድ፡ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው። የተሰፋ፡ ልብስ፡ ከመግዛት፡ የተለመደ፡ ስለሆነ፣ አብዛኛው፡ ሰው፡ ልብሱን፡ ወደ፡ መኪና፡ ሰፊ፡ ቤት፡ ይወስዳል።

የፋሲካን፡ በዓል፡ ለከደረስ፡ አቶ፡ ከበደ፡ አንድ፡ ሙሉ፡ ልብስ፡ ለማሰፋት፡ ወደ፡ መኪና፡ ሰፊ፡ ቤት፡ ሄደ። አቶ፡ ለማ፡ በከተማው፡ የታወቀ፡ ልብስ፡ ሰፊ፡ በመሆኑ፣ ብዙ፡ ሰዎች፡ ልብሳቸውን፡ ወደ፡ እርሱ፡ ሉቅ፡ ስለሚያመጡ፣ አቶ፡ ከበደ፡ ቀደም፡ ብሎ፡ ልብሱን፡ ወደ፡ ለማ፡ ሉቆ፡ አመጣው።

አቶ፡ ለማ፡ ደግ፡ ከበደን፡ ልብስ፡ ከመስፋቱ፡ በፊት፡ እንዴት፡ ሆኖ፡ እንዲሰፋለት፡ ጠየቀው። አቶ፡ ከበደም፡ ሱሪው፡ ሰፊ፡ እንዲሆን፤ እጅጌው፡ ረጅም፡ እንዲሆንና፡ ኮቱ፡ መካከለኛ፡ እንዲሆን፡ ነገረው።

በዚሁ፡ ስምምነት፡ መሠረት፡ አቶ፡ ለማ፡ ልብሱን፡ ለአቶ፡ ከጨረሰ፡ በኋላ፡ በሚመጣው፡ ሳምንት፡ መጥቶ፤ የተሰፋውን፡ ልብስ፡ እንዲወስድ፡ ነገረው።

ከፋሲካ፡ በዓል፡ አቶ፡ ከበደ፡ አዲሱን፡ ልብስ፡ ለብሶ፤ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሄደ፡ በአንበር፤ የቅርብ፡ ጓደኞች፡ አዲሱ፡ ልብስ፡ በጣም፡ እንደተስማማው፡ ስለነገሩት፡ እጅግ፡ ደስ፡ ብሎት፡ በዓሉን፡ አሳለፈ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ከበደ፡ የት፡ ሄደ?

አቶ፡ ከበደ፡ ወደ፡ መዚና፡ ሰፊ፡ ቤት፡ ለምን፡ ሄደ?

ለምን፡ እንደ፡ ሙሉ፡ ልብስ፡ ለማሰፋት፡ ፈለገ?

አቶ፡ ለማ፡ በከተማው፡ የታወቀ፡ ልብስ፡ ሰፊ፡ ነው?

አቶ፡ ከበደ፡ ከምን፡ ወደ፡ አቶ፡ ካሣ፡ ሱቅ፡ ቅዳሜ፡ ጠዋት፡ ሄደ?

አቶ፡ ካሣ፡ የአቶ፡ ከበደን፡ ልብስ፡ ከመለካቱ፡ በፊት፡ ምን፡ አለ?

አቶ፡ ከበደ፡ ሱሪው፡ ጠባብ፡ እንዲሆን፡ ፈለገ?

ኮቱ፡ ረጅም፡ እንዲሆን፡ ይወዳል?

አቶ፡ ከበደ፡ ልብሱን፡ መቼ፡ ከመውሰድ፡ ተስማማ?

ከፋሪካ፡ በኋላ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ አደረገ?

የቅርብ፡ ጓደኞቹ፡ ለአቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ አሉት?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ወደ፡ መኪና፡ ሰፊ፡ ቤት፡ መሄድ፡ የተለመደ፡ ነው?

የልብስ፡ ማሰፊያ፡ ዋጋ፡ ውድ፡ ነው?

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ አብዛኛው፡ ሕዝብ፡ የተሰፋ፡ ልብስ፡ ይገዛል?

አሥራ፡ ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

እንደምን፡ አደሩ፡ አቶ፡ ዮሐንስ?

ጆን

እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፤ እርስዎስ?

ከበደ

በማለዳ፡ የት፡ ይሄዳሉ?

ጆን

ቢሮ፡ ከመግባቴ፡ በፊት፡ ትንሽ፡ ሽርሽር፡ ስለምፈልግ፤ ወደ፡ መናፈሻ፡ እሄዳለሁ።

ከበደ

ዛሬ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ቀን፡ ስለሆነ፡ እኔም፡ ወደ፡ ተለለው፡ ከመሄድ፡ እዘጋጃለሁ።

ጆን

ሰማዩ፡ ደመና፡ ስለሆነ፡ ዝናብ፡ ይዘንብ፡ ይመስልዎታል?

ከበደ

የለም፤ የሚዘንብ፡ አይመስለኝም። ምናልባት፡ ነገ፡ ይዘንብ፡ ይሆናል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ ትሄዳለህ?	አርብ፡ ስለሆነ፡ ምናልባት፡ እሄድ፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ነገ፡ ማለዳ፡ ወደ፡ ቢሮ፡ ይሄዳሉ?	ምናልባት፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ነገ፡ ጥዋት፡ አንተና፡ ባለቤትህ፡ ምን፡ ትሠራላችሁ?	ምናልባት፡ እንሸራሸር፡ ይሆናል።
ወደ፡ መናፈሻ፡ መሄድ፡ ማን፡ ይፈልጋል?	ተማሪዎች፡ መናፈስ፡ ስለሚፈልጉ፣ አብረውህ፡ ይሄዱ፡ ይሆናል።
ከዚህ፡ በፊት፡ ተራራ፡ አይተሃል?	ከዚህ፡ በፊት፡ አላየሁም፤ ወደፊት፡ አይ፡ ይሆናል።
ትናንት፡ እዚህ፡ ዝናብ፡ ዘነበ?	ትናንት፡ አልዘነበም፤ ምናልባት፡ ዛሬ፡ ይዘንብ፡ ይሆናል።
ትናንትና፡ ለምሳ፡ የበላችሁት፡ ወጥ፡ ጥሩ፡ ነበር?	አዎ፣ ጥሩ፡ ነበር። ነገር፡ ግን፡ የዛሬው፡ የተሻለ፡ ጣዕም፡ ይኖረው፡ ይሆናል።
አቶ፡ ለማን፡ ታውቀዋለህ?	እኔ፡ አላውቀውም፤ ምናልባት፡ ወይዘሮ፡ አልማዝ፡ ታውቀው፡ ይሆናል።
ተማሪዎች፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ይስማሙ፡ ይመስልሃል?	ምናልባት፡ ይስማሙ፡ ይሆናል።
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ለምን፡ ያሜሪካን፡ መኪና፡ ገዛች?	ገንዘብ፡ ይኖራት፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ብትገባ፡ ጥሩ፡ ይመስልሃል?	ምናልባት፡ ጥሩ፡ ይሆናል።
ከዚህ፡ በፊት፡ እዚህ፡ ቦታ፡ መጥታችሁ፡ ነበር?	ምናልባት፡ መጥተን፡ ይሆናል።
ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ትሄዳላችሁ?	ምናልባት፡ ልብሳችንን፡ ለብሰን፡ እንሄድ፡ ይሆናል።
ዶ.ቶ፡ ዮሐንስን፡ ገለቤት፡ ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ትወስዱዋታላችሁ?	ምናልባት፡ እንወስዳት፡ ይሆናል።
ዛሬ፡ ማታ፡ ወደ፡ ሆቴል፡ ትሄዳላችሁ?	ምናልባት፡ ሄደን፡ ሙዚቃ፡ እንሰማ፡ ይሆናል።
ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ ለምን፡ ሄዱ?	ምናልባት፡ ሲኒማውን፡ ወደውት፡ ይሆናል።
እነካሌው፡ ለምን፡ ለማን፡ ወደደው?	ጉርሻ፡ ሰጥቶት፡ ይሆናል።
አስተማሪዎች፡ በገንዘባቸው፡ ምን፡ ያደርጉበታል?	በጣም፡ ጥሩ፡ ቤት፡ ይገዙበት፡ ይሆናል።
ጥሩ፡ ሥራ፡ በመሥራት፡ ምን፡ ታገኛላችሁ?	ምናልባት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ እንሄድ፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
መኪናውን፡ ለምን፡ ሰጣት?	ምናልባት፡ ለምምንት፡ እንድርገው፡ ይሆናል።
እናትና፡ አባትህን፡ ለማየት፡ ወደ፡ አገርህ፡ መቼ፡ ትሄዳለህ?	ለፋሲካ፡ በዓል፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ገንዘብ፡ ለምን፡ ያስፈልጋታል?	ለልጇ፡ ኮት፡ ለማሰፋት፡ ይሆናል።
አሜሪካ፡ በጣም፡ ብርድ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ ብርድ፡ ነው፤ ግን፡ ይለመድ፡ ይሆናል።
ተማሪዎች፡ ለምን፡ እቤታቸው፡ አልነበሩም?	ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ሄደው፡ ይሆናል።
ሲኒማው፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ያልቅ፡ ይመስልሃል?	ገሌት፡ ሰዓት፡ ያልቅ፡ ይሆናል።
አቶ፡ ለማ፡ ሚስት፡ አገባ?	የለም፣ እስካሁን፡ አላገባም፤ ምናልባት፡ በዚህ፡ ዓመት፡ ያገባ፡ ይሆናል።
አስተማሪዎች፡ የት፡ አሉ?	ዕቃ፡ ለማምጣት፡ ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ሄደው፡ ይሆናል።
ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ መሄዴን፡ ለወንድሜ፡ ልንገረው?	ምናልባት፡ ለሰዎች፡ ይነግር፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ለምን፡ አዲስ፡ መኪና፡ ለመግዛት፡ ትፈልጋለች?	ምናልባት፡ አስፈለጋት፡ ይሆናል።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ለምን፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ አይሄዱም?	ለመታወቅ፡ አይፈልጉም፡ ይሆናል።
አለማዝ፡ ዛሬ፡ በስልክ፡ ለምን፡ አልጠራችኝም?	ስልኩን፡ አላስቀጠለችም፡ ይሆናል።
ተማሪዎች፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ልብሳቸውን፡ ይለብሳሉ?	እስከ፡ ስምንት፡ ሰዓት፡ ልብሶቻቸውን፡ ይለብሳሉ፡ ይሆናል።
አለማዝ፡ በጥሩነሽ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ብትሠራ፡ ምን፡ ታገኛለች?	ጥሩነሽ፡ ሙሉ፡ ልብስ፡ ትገዛላት፡ ይሆናል።
አለማዝ፡ እቤት፡ ውስጥ፡ ምን፡ ትሠራለች?	ወደ፡ ሲኒማ፡ ለመሄድ፡ ትዘጋጅ፡ ይሆናል።
ከበደን፡ ለምን፡ አሁን፡ አትጠሩውም?	በቤት፡ ውስጥ፡ አይኖር፡ ይሆናል።
ወደ፡ ቤታችሁ፡ ለመሄድ፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ትዘጋጃላችሁ?	ከሀያ፡ ደቂቃዎች፡ በኋላ፡ እንዘጋጅ፡ ይሆናል።
ትምህርት፡ ሚኒስቴርን፡ ማን፡ ያውቃል?	መካከለኛው፡ ልጅ፡ ያውቀው፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ ወደ፡ አገርዎ፡ ደብዳቤ፡ ይጽፋሉ?	ምናልባት፡ አንድ፡ አጭር፡ ደብዳቤ፡ እጽፍ፡ ይሆናል።

ድርሰት

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ ያመት፡ ረፍታቸውን፡ ለቅርብ፡ ቀኖች፡ ውስጥ፡ ስለሚያገኙ፣ ተገናኝተው፡ ምን፡ እንደሚሠሩ፡ መነጋገር፡ ፈለጉ።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ በረፍቱ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ አንድ፡ የቆላ፡ ቦታ፡ ሄጄ፡ መቆየት፡ እፈልጋለሁ፡ አለ። አቶ፡ ከበደ፡ ግን፡ ወደ፡ አንድ፡ ተራራ፡ ላይ፡ ከልጆቹ፡ ጋር፡ መውጣትና፡ የረፍቱን፡ ጊዜ፡ እዚያ፡ ማሳለፍ፡ ፈለገ። ሁለቱም፡ የረፍታቸውን፡ ጊዜ፡ አብረው፡ ለማሳለፍ፡ የሚፈልጉት፡ ነገር፡ ተመሳሳይ፡ ስላልሆነ፣ ወደየመረጡት፡ ቦታ፡ ሄዱ።

ሁለቱም፡ የረፍታቸውን፡ ጊዜ፡ ጨርሰው፡ ሲመለሱ፣ ያዩትንና፡ የሰሙትን፡ ነገር፡ ለመነጋገር፡ ሊጠቀሙ፡ ይችሉ፡ ይሆናል።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የረፍታቸውን፡ ጊዜ፡ መቼ፡ ያገኛሉ?

የረፍታቸውን፡ ጊዜ፡ ከማግኘታቸው፡ በፊት፡ ምን፡ ማድረግ፡ ፈለጉ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ በረፍቱ፡ ጊዜ፡ የት፡ መሄድ፡ ፈለገ?

አቶ፡ ከበደ፡ በረፍቱ፡ ጊዜ፡ የት፡ መሄድ፡ ፈለገ?

ለምን፡ ለረፍታቸው፡ አብረው፡ ወደ፡ አንድ፡ ቦታ፡ አልሄዱም?

የረፍቱን፡ ጊዜ፡ ከልጆቹ፡ ጋር፡ ማሳለፍ፡ የፈለገ፡ ማን፡ ነው?

ያዩትንና፡ የሰሙትን፡ ነገር፡ ለመነጋገር፡ ለምን፡ ፈለጉ?

አንተ፡ የረፍትህን፡ ጊዜ፡ ለተሌሌ፡ ነፃ፡ አሳልፈሃል?

የናንተ፡ የረፍት፡ ጊዜ፡ መቼ፡ ነው?

በከተማው፡ ውስጥ፡ የዋና፡ ቦታ፡ አለ?

አሥራ፡ ዘጠነኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ይቅርታ፡ ጌታዬ፤ የዋሽንግተን፡ ዓየር፡ እንዴት፡ ነው?

ጆን

ዋሽንግተን፡ በበጋው፡ ወራት፡ በጣም፡ ይሞቃል።

ከበደ

አዲስ፡ አበባ፡ ብዙ፡ አይሞቅም፡ እንዲያውም፡ ማታ፡ ማታ፡ ትንሽ፡ ይበርዳል።

ጆን

አዲስ፡ አበባ፡ ባለፉት፡ ወራት፡ ሙቀት፡ ነበር?

ከበደ

አዎ፤ ባለፈው፡ ወር፡ አዲስ፡ አበባ፡ በጣም፡ ሙቀት፡ ስለነበር፤ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ወንዝ፡ እየሄዱ፡ በመዋኘት፡ ጊዜአቸውን፡ አሳለፉ።

ጆን

ባለፈው፡ ዓመት፡ ዋሽንግተን፡ በጣም፡ ሙቀት፡ ስለነበር፣ እኔና፡ ባለቤቴ፡ ከሁለት፡ ልጆቻችን፡ ጋር፡ ለዋና፡ ወደ፡ ባሕር፡ ሄደን፡ ነበር።

ከበደ

በባሕሩ፡ ዳር፡ ከቤተ፡ ሰብዎ፡ ጋር፡ ጥሩ፡ ጊዜ፡ ነበርዎ?

ጆን

አዎን፣ በደስታ፡ ጊዜያችንን፡ አሳለፍን።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የኔ፡ መጽሐፍ፡ ከሌላው፡ መጽሐፍ፡ ቀይ፡ ነው?	አዎ፤ ያንተ፡ መጽሐፍ፡ ከሌላው፡ መጽሐፍ፡ ቀይ፡ ነው።
የፕሬዚዳንቱ፡ ቤት፡ ከቤቶች፡ ሁሉ፡ እጅግ፡ በጣም፡ ነጭ፡ ነው?	አዎ፤ ከቤቶች፡ ሁሉ፡ እጅግ፡ በጣም፡ ነጭ፡ ነው።
አዲሱ፡ ቤትህ፡ ከሌሎቹ፡ ቤቶች፡ በጣም፡ ሰፊ፡ ነው?	አዎ፤ ሰፊ፡ ነው። የለም፤ ሰፊ፡ አይደለም።
የኢትዮጵያ፡ ዓየር፡ ከዚህ፡ አገር፡ ዓየር፡ ጥሩ፡ ነው?	አዎ፤ ከዚህ፡ አገር፡ ዓየር፡ ጥሩ፡ ነው። የለም፤ ከዚህ፡ አገር፡ ዓየር፡ ጥሩ፡ አይደለም።
ከዚህ፡ እርሳስና፡ ከዚያ፡ እርሳስ፡ የቱን፡ ትወዳለህ?	ይህኛውን፡ እወዳለሁ።
ከዚህኛውና፡ ከዚያኛው፡ ሰው፡ የትኛው፡ እጅግ፡ በጣም፡ አስተዋይ፡ ነው?	ያኛው፡ ሰው፡ እጅግ፡ በጣም፡ አስተዋይ፡ ነው።
ከሁለቱ፡ ቤቶች፡ በጣም፡ ሰፊውን፡ ትወዳለህ?	አዎን፡ በጣም፡ ሰፊውን፡ እወዳለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ይህኛው፡ ተማሪ፡ ከዚያኛው፡ በጣም፡ አስተዋይ፡ ነው?	አዎ፤ በጣም፡ አስተዋይ፡ ነው። የለም፤ አስተዋይ፡ አይደለም።
ከሁለቱ፡ ተራራዎች፡ የትኛው፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው?	ያኛው፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው።
ከሦስቱ፡ ተማሪዎች፡ የትኛውን፡ እጅግ፡ በጣም፡ ትወዳለህ?	ሁለተኛውን፡ ተማሪ፡ እጅግ፡ በጣም፡ እወዳለሁ።
ከትልቆቹና፡ ከትንሾቹ፡ መናፈሻዎች፡ የትኞቹን፡ በጣም፡ ትወዳላችሁ?	ትልቆቹን፡ በጣም፡ እንወዳለን።
ከአዲስ፡ አበባ፡ ዋሽንግተን፡ ይሞቃል?	አዎ፤ ዋሽንግተን፡ ይሞቃል። የለም፤ ዋሽንግተን፡ አይሞቅም።
የናንተ፡ አገር፡ ከኛ፡ አገር፡ በጣም፡ ሞቃ፡ ነው?	አዎ፤ የኛ፡ አገር፡ በጣም፡ ሞቃ፡ ነው።
ከትልቁ፡ ትንሹን፡ ቢሮ፡ ትወዳለህ?	አዎ፤ ትንሹን፡ እወዳለሁ።
የዛሬው፡ ዓየር፡ ከትናንቱ፡ ሞቃ፡ ነው?	አዎ፤ የዛሬው፡ ከትናንቱ፡ ሞቃ፡ ነው። የለም፤ የዛሬው፡ ከትናንቱ፡ ሞቃ፡ አይደለም።

ጥያቄ	መልስ
ከቅዳሜና፡ ከእሁድ፡ የትኛው፡ በጣም፡ ይሞቅ፡ ነበር?	ቅዳሜ፡ በጣም፡ ይሞቅ፡ ነበር።
ጥዋት፡ ከማታው፡ ይበርዳል?	አዎ፤ ጥዋት፡ ይበርዳል። የለም፤ ጥዋት፡ አይበርድም።
ከሙቀትና፡ ከብርድ፡ የቱን፡ ትወዳለህ?	ብርድ፡ እወዳለሁ።
ከወንዙና፡ ከገደሉ፡ የትኛው፡ ሩቅ፡ ነው?	ወንዙ፡ በጣም፡ ሩቅ፡ ነው።
ካንተ፡ ልጅ፡ ይልቅ፡ ያቶ፡ ካሣ፡ ልጅ፡ ረጅም፡ ነው?	አዎ፤ ረጅም፡ ነው። የለም፤ ረጅም፡ አይደለም።
ከዚያኛው፡ ይልቅ፡ ይህኛው፡ ሰው፡ ወጣት፡ ነው?	አዎ፤ ወጣት፡ ነው። የለም፤ ወጣት፡ አይደለም።
ካቶ፡ ዮሐንስና፡ ከወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አማርኛ፡ የማን፡ ጥሩ፡ ነው?	ያቶ፡ ዮሐንስ፡ ጥሩ፡ ነው።
ያንተ፡ ክፍል፡ ከዚህኛው፡ በጣም፡ ውድ፡ ነው?	አዎ፤ የኔ፡ ክፍል፡ ከዚህኛው፡ በጣም፡ ውድ፡ ነው።
የጥሩነሽ፡ ጠረጴዛ፡ ከኔ፡ ጠረጴዛ፡ ይሻላል?	የለም፤ አይሻልም።

ጥያቄ፡	መልስ
ካረንጓዴው፡ መጽሐፍ፡ ሌላውን፡ ይመርጣል?	አዎ፣ ሌላውን፡ ይመርጣል።
ከቀዩ፡ መኪና፡ ይልቅ፡ ነጩን፡ በጣም፡ ትፈልገዋለህ?	የለም፣ በጣም፡ አልፈልገውም።
ከዛሬና፡ ከነገ፡ ወደ፡ አገራችሁ፡ መቼ፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ከነገ፡ ይልቅ፡ ዛሬ፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።
ከእርስዎ፡ አማርኛ፡ ይልቅ፡ የባለቤትዎ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው?	የለም፣ በጣም፡ ጥሩ፡ አይደለም።
ከልብስ፡ ይልቅ፡ ጫማ፡ ትመርጣለህ?	ጫማ፡ በጣም፡ እመርጣለሁ።
ከቢራ፡ ይልቅ፡ ጠጅ፡ ለመጠጣት፡ ትፈልጋለህ?	የለም፣ ጠጅ፡ ለመጠጣት፡ አልፈልግም።
ከዶሮ፡ ወጥ፡ ይልቅ፡ የሥጋ፡ ወጥ፡ ትወዳለህ?	አዎ፣ የሥጋ፡ ወጥ፡ እወዳለሁ።
ከውሻው፡ ይልቅ፡ ድመቷን፡ ትወዳለህ?	ሁለቱንም፡ አልወድም።

ድርሰት

በሳምንት፡ ውስጥ፡ ከሥራ፡ ከምናርፍባቸው፡ ከሁለቱ፡ ቀኖች፡ አንዱ፡ ትናንት፡ እሁድ፡ ስለነበር፤ እኔና፡ ባለቤቴ፡ ከመኝታችን፡ አርፍደን፡ ተነሣን።

እኔ፡ ፊቴን፡ እስክታጠብና፡ ጢሜን፡ እስክላጭ፤ ልብሴንም፡ እስክለብስ፡ ድረስ፤ ባለቤቴ፡ ቁርስ፡ አዘጋጅታ፡ ወደ፡ ምግብ፡ ቤት፡ ጠራችኝ። እኔም፡ ገብቼ፡ ምግቤን፡ ከበላሁ፡ በኋላ፡ ባለቤቴ፡ ልብሷን፡ ለብሳ፡ እስክትወጣና፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እስክንሄድ፡ ድረስ፡ በበረንዳዬ፡ ላይ፡ እንሸራሸር፡ ነበር። በግቢዬ፡ ውስጥ፡ ያሉትን፡ ለምለምና፡ አስደሳች፡ አበባዎችና፡ ዛፎች፡ ስመለከት፤ ባልንጀሬዬ፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ ዋና፡ ለመሄድ፡ ተዘጋጅቶ፡ ሲመጣ፡ አየሁትና፡ ሰላምታ፡ ሰጠሁት።

እኔም፡ ለዋና፡ ወደ፡ የትኛው፡ ወንዝ፡ እንደሚሄድ፡ ብጠይቀው፤ ወደ፡ አንድ፡ ሩቅ፡ ወንዝ፡ እንደሚሄድ፡ ነገረኝ። ምክንያቱም፡ በቅርቢያው፡ ያለውን፡ ወንዝ፡ ስለማያውቅ፡ ነው። በኋላ፡ ግን፡ አቅጣጫውን፡ አሳይቼው፡ ወደ፡ ወንዙ፡ ሲሄድ፡ እኔ፡ ከባለቤቴ፡ ጋር፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሄድሁ።

ጥያቄዎች

ከሥራ፡ የምታርፉባቸው፡ ቀኖች፡ ስንት፡ ናቸው?

የቀኖቹስ፡ ስም፡ ማን፡ ማን፡ ይባላል?

ለማና፡ ባለቤቱ፡ ከመኝታቸው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ተነሱ?

ለምን፡ በጣም፡ አርፍደው፡ ተነሱ?

ያቶ፡ ለማ፡ ባለቤት፡ ቁርስ፡ ስታዘጋጅ፡ እሱ፡ ምን፡ ይሠራ፡
ነበር?

ቁርሳቸውን፡ ከበሉ፡ በኋላ፡ አቶ፡ ለማ፡ ምን፡ አደረገ?

አቶ፡ ለማ፡ ለበረንዳው፡ ላይ፡ ሲንሸራሸር፡ ማንን፡ አየ?

ከገሴንጀሬው፡ ጋር፡ ስለምን፡ ተነጋገሩ?

ንግግራቸውን፡ ከጨረሱ፡ በኋላ፡ ገሴንጀሬው፡ የት፡ ሄደ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከባለቤቱ፡ ጋር፡ የት፡ ሄዱ?

ሀያኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

የሚመጣው፡ ሳምንት፡ ጃሩ፡ ቀን፡ ቢሆን፡ ወደ፡ ተሌሌው፡ እንባሬን፡ እንሄድ።

ከበደ

እንዳጋጣሚ፡ በሚመጣው፡ ሳምንት፡ ወደ፡ ትግሬ፡ ስለምሄድ፣ ከርስዎ፡ ጋር፡ ወደ፡ ተሌሌሌው፡ ከመሄድ፡ አልችልም።

ጆን

ወደ፡ ትግሬ፡ ለምን፡ ይሄዳሉ?

ከበደ

አጎቴ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከመምጣት፡ ስንሰሙ፡ እርሳቸውን፡ ከማምጣት፡ መሄድ፡ አለብኝ።

ጆን

ትግሬ፡ በየት፡ አቅጣጫ፡ ይገኛል?

ከበደ

ትግሬ፡ በስተ፡ ሰሜን፡ ይገኛል።

ጆን

በአዲስ፡ አበባ፡ ዙሪያ፡ የሚገኙት፡ ከሌቹ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ እነማን፡ ናቸው?

ከበደ

በስተ፡ ምሥራቅ፡ ሐረርጌ፣ በስተ፡ ምዕራብ፡ ወለጋና፡ በስተ፡ ደቡብ፡ አሩሲ፡ ናቸው።

ጆን

ከትግሬ፡ መቼ፡ ይመለሳሉ?

ከበደ

ከአሥር፡ ቀን፡ በኋላ፡ እመለሳለሁ።

ጆን

መልካም፡ ጉዞ፡ እመኝልዎታለሁ። ካገኙዎ፡ ሰላምታዬን፡ ያቅርቡልኝ።

ከበደ

እሺ፡ አቀርባለሁ።

ጆን

ጤና፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

አሜን፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ ብርድ፡ ይሰማሃል?	አዎ፡ ይሰማኛል። የለም፡ አይሰማኝም።
የፈለግሽው፡ መኪና፡ ተሰጠሽ?	አዎ፡ ተሰጠኝ። የለም፡ አልተሰጠኝም።
የዛሬ፡ ቀን፡ ይሞቃችኋል?	አዎ፡ በጣም፡ ይሞቀናል። የለም፡ አይሞቀንም።
አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ይበርዳችኋል?	አዎ፡ ይበርደናል። የለም፡ አይበርደንም።
ሲጋራ፡ ስታጨስ፡ ራስህን፡ ያምሃል?	አዎ፡ ያመኛል። የለም፡ አያመኝም።

ጥያቄ	መልስ
ለማ፡ የነገረህ፡ ይገባሃል?	አዎ፣ ይገባኛል። የለም፣ አይገባኝም።
ያነበበው፡ መጽሐፍ፡ ይገባቸዋል?	አዎ፣ ይገባቸዋል። የለም፣ አይገባቸውም።
ቡና፡ ስትጠጣ፡ ራስህን፡ ይሻልሃል?	አዎ፣ ይሻለኛል። የለም፣ አይሻለኝም።
በሰዓት፡ ስንት፡ ብር፡ ይከፈልሃል?	ሁለት፡ ብር፡ ይከፈለኛል።
ደብዳቤ፡ መቼ፡ ይደርስሃል?	ከአንድ፡ ቀን፡ በኋላ፡ ይደርሰኛል።
ይህ፡ መኪና፡ ለማን፡ ይገባዋል?	ለጥሩነሽ፡ ይገባታል።
ወደ፡ አገራችን፡ መሄድ፡ ይገባናል?	አዎ፣ መሄድ፡ ይገባችኋል። የለም፣ መሄድ፡ አይገባችሁም።
አዲሱን፡ ቤት፡ ለማን፡ ይሰጠዋል?	ለኔ፡ ይሰጠኛል።
አባትና፡ እናትህን፡ ካየህ፡ ስንት፡ ዓመት፡ ሆነህ?	ሦስት፡ ዓመት፡ ሆነኝ።
ይህ፡ አጭር፡ ጠረጴዛ፡ ለማን፡ ይገባዋል?	ለሱ፡ ይገባዋል።

ጥያቄ	መልስ
የኛ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ጥሩ፡ ይመስልሃል?	ወደፊት፡ በጣም፡ ጥሩ፡ የሚሆን፡ ይመስለኛል።
ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ እንደምትሄድ፡ መቼ፡ ይነገርሃል?	ከሁለት፡ ቀኖች፡ በኋላ፡ ይነገረኛል።
ወደ፡ ሩሲያ፡ ብትሄድ፡ ይበርድሃል፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይበርደኛል።
ከትናንት፡ ዛሬ፡ ይበርዳል?	አዎ፣ ይበርዳል። የለም፣ አይበርድም።
ሌሊቱን፡ ትንሽ፡ ተኛለህ?	አዎ፣ ትንሽ፡ ተኛሁኝ። የለም፣ አልተኛሁኝም።
ከኒው፡ ዮርክና፡ ከዋሽንግተን፡ የቱ፡ ከተማ፡ ደስ፡ ይሎችዋል?	ዋሽንግተን፡ በጣም፡ ደስ፡ ይሎችዋል።
አማርኛ፡ ቋንቋ፡ ይገባሃል?	አዎ፣ ትንሽ፡ ይገባኛል። የለም፣ አይገባኝም።
በመኪናው፡ ውስጥ፡ ሙቀት፡ ወይስ፡ ብርድ፡ ይሰማሃል?	ብርድ፡ ይሰማኛል።
አሥር፡ ሰዓት፡ ብትሠሩ፡ ስንት፡ ብር፡ ይሰጣችኋል?	ሀያ፡ ብር፡ ይሰጡናል።

ጥያቄ	መልስ
የሚናገሩው·ቋንቋ·ይገባሃል?	የለም፣ አይገባኝም።
ሐኪም·ቤት·ብትሄድ·ይሻልሃል?	አዎ፣ ይሻለኛል።
አቶ·ዮሐንስና·ወይዘሮ·ጥሩነሽ·ሲነጋገሩ·ይሰማሃል?	አዎ፣ ይሰማኛል። የለም፣ አይሰማኝም።
ከማ·የመጣ·ይመስልሃል?	አዎ፣ የመጣ·ይመስለኛል። የለም፣ የመጣ·አይመስለኝም።

ድርሰት

ያቶ·ከማና፡ ያቶ·ዮሐንስ፡ የረፍታቸው·ጊዜ፡ ባለፈው·ሳምንት፡ ስለነበር፣ ወደ·ገጠር፡ ከዋና፡ ሄደው·ነበር። ለዚህም፡ ገጠር፡ዳር፡ ከዋና፡ የሄዱ· ለብዙ·መቶ·የሚቆጠሩ·ሰዎች፡ አገኙ። ከነሱም፡ ጋር·ለመዋኘትና፡ ለመጨዋወት፣ እንዲሁም፡ ያላቸውን፡ ምግብና፡ መጠጥ፡ ተካፍለው·ለመብላት·በጣም፡ ተደስተው፡ ነበር። አንዳንድ፡ ጊዜም፡ መዋኘት፡ ሲደክማቸው፡ ተቀምጠው·ስለ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ጨዋታዎች፡ እየተጨዋወቱ፣ ስለ፡ ዓለም·ፖለቲካና፡ሁኔታ፡ ይነጋገሩኩ። ባለቤቶቻቸውም፡ ከስ

ጆቻቸው፡ ጋር፡ ከቆዩ፡ በኋላ፤ ምግብ፡ ሠርተው፡ ራታቸውን፡ በሉ። ድንኳኖቻቸውን፡ በገላጣ፡ ሜዳ፡ ተክለው፡ አንድ፡ ሳምንት፡ ያህል፡ ከቆዩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ ተመለሱ።

ጥያቄዎች

ከቆና፡ ወደ፡ ገጠር፡ የሄዱ፡ እነማን፡ ናቸው?

ከምን፡ ወደ፡ ቆና፡ ሄዱ?

ማንን፡ ይዘው፡ ሄዱ?

ከቆና፡ ከሄዱ፡ በኋላ፡ እዚያ፡ ምን፡ አገኙ?

እዚያ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ አገኙ?

ከምን፡ ተደሰቱ?

ቆናው፡ ሊደክማቸው፡ ምን፡ አደረጉ?

እዚያ፡ ቦታ፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ቆዩ?

እዚያ፡ በቆዩበት፡ ጊዜ፡ የት፡ ይኖሩ፡ ነበር?

ገከበቶቻቸው፡ ጊዜያቸውን፡ እንዴት፡ አሳለፉ?

ካንድ፡ ሳምንት፡ በኋላ፡ ወዴት፡ ሄዱ?

ከምን፡ ወደ፡ አገራቸው፡ ተመለሱ?

ቆና፡ ከመኪና፡ ይጠቀማል?

ሀያ፡ አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከማ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ ጌታዬ፤ ስሜ፡ ከማ፡ ይባላል።

የቪዛ፡ ሹም

እባክዎ፡ ይግቡና፡ ይቀመጡ።

ከማ

እሺ፡ አመሰግናለሁ።

የቪዛ፡ ሹም

ምን፡ ላደርግልዎ፣ አቶ፡ ከማ?

ከማ

ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ስለምፈልግ፡ ቪዛ፡ እንዲሰጡኝ፡ እፈልጋለሁ።

የቪዛ፡ ሹም

ለምን፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ ይፈልጋሉ?

ከማ

ትምህርቴን፡ እዚያ፡ ለመቀጠል፡ ስለምፈልግ፡ ነው።

የቪዛ፡ ሹም

የትኛው፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ ለመማር፡ ይፈልጋሉ?

ከማ

ዋሽንግተን፡ ውስጥ፡ ለሚገኘው፡ ለአሜሪካን፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ ነው።

የቪዛ፡ ሹም

ይህ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ይቀበልዎታል?

ከማ

አዎ፡ ጌታዬ፤ ዩኒቨርሲቲው፡ እንደሚቀበለኝ፡ ደብዳቤ፡ አለኝ፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ ደርሶኛል።

የቪዛ፡ ሹም

እስቲ፡ ደብዳቤውን፡ ልየው?

ከማ

በደስታ፡ ጌታዬ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
በስንት፡ መቶ፡ የሚቆጠሩ፡ ሰዎች፡ አገኘህ?	ምናልባት፡ በሁለትና፡ በሦስት፡ መቶ፡ የሚቆጠሩ፡ ሰዎች፡ አገኘሁ።
በመቶ፡ የሚቆጠሩ፡ ተማሪዎች፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ሲሄዱ፡ አየህ?	አዎ፤ ብዙ፡ ተማሪዎች፡ አየሁ።
ዛሬ፡ ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ የሚመጣው፡ ሰው፡ ማን፡ ይባላል?	ምናልባት፡ አቶ፡ ለማ፡ ያውቁ፡ ይሆናል።
አስተማሪያችሁ፡ ከተማሪዎች፡ ጋር፡ ስለፖለቲካ፡ መወያየት፡ ይፈልጋል?	የለም፤ አይፈልግም።
እነዚህ፡ ሰዎች፡ ከየት፡ አገር፡ መጡ?	እነዚህ፡ ከአሜሪካ፡ መጡ፤ እንዲሁም፡ ሌሎች፡ ከእንግሊዝ፡ አገር፡ ይመጣሉ።
ምግብህን፡ ከመንገደኞች፡ ጋር፡ መካፈል፡ ትወዳለህ?	አዎ፤ በጣም፡ እወዳለሁ።
በረፍታችሁ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ለመሄድ፡ የምትፈልጉት፡ ለመደሰት፡ ነው?	በረፍታችን፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የምንሄደው፡ የሚያስደስቱ፡ ነገሮችን፡ ለማየት፡ ነው።
ዛሬ፡ ማታ፡ ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ መሄድና፡ መደሰት፡ የሚፈልግ፡ ማን፡ ነው?	እኛ፡ መሄድና፡ መደሰት፡ እንፈልጋለን።

ጥያቄ	መልስ
እሲጆው፡ ወደ፡ ከተማ፡ ብትሄድ፡ ይደክምሃል?	አዎ፣ በጣም፡ ይደክመኛል።
ከአዲስ፡ አበባ፡ ወደዚህ፡ አገር፡ ስትመጪ፡ በጣም፡ ደከመሽ?	አዎ፣ በጣም፡ ደከመኝ፡
ወደ፡ ከተማ፡ ሄዳችሁ፡ ጠዋት፡ አታደርም?	ከሰዓት፡ በኋላ፡ ሄደን፡ እናያለን።
ከእናንተ፡ መካከል፡ ፖለቲካ፡ የሚማሩ፡ እነማን፡ ናቸው?	ከበደና፡ ለማ፡ ናቸው።
ምግብ፡ ማን፡ ይሠራላችኋል?	እህቶቻችን፡ ይሠሩልናል።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ምግብ፡ ይሠራል?	የለም፣ አይሠራም።
ቀን፡ ቀን፡ እናቶቻችሁ፡ ወደ፡ ሥራ፡ ሲሄዱ፡ ልጆቻችሁን፡ ወዴት፡ ይልካሉ?	ምናልባት፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ይልኩ፡ ይሆናል።
ውሻውን፡ አበልተህ፡ የት፡ ትሄዳለህ?	ወደ፡ አዲስ፡ ከተማ፡ እሄዳለሁ።
ድንኳን፡ የተከላችሁበት፡ ቦታ፡ የት፡ ነበር?	ከወንዙ፡ ዳር፡ ነበር።
ጓደኞችህ፡ ድንኳናቸውን፡ የት፡ እንደተከሉ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
እናታችሁ፡ ሁልጊዜ፡ እየመጣች፡ ታያችኋለች?	አዎ፣ በሳምንት፡ አንድ፡ ጊዜ፡ እየመጣች፡ ታየናለች።

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ ለማ፡ ሁልጊዜ፡ ወደ፡ አገሩ፡ ስለሄደ፡ እናቱን፡ ያያል?	አንዳጋጣሚ፡ ሁልጊዜ፡ አይሄድም።
ከቅሽንግታን፡ ለአቶ፡ ለሜን፡ ያለውን፡ ከተማ፡ ታውቀዋለህ?	አዎን፣ አውቀዋለሁ።
ፀሐይ፡ በምስራቅ፡ ስትወጣም፡ ያለ፡ ማን፡ ነው?	አንድ፡ ተማሪ፡ ነው። ስሙን፡ ግን፡ አላውቀውም።
በቤትህ፡ ዙሪያ፡ የሚገኙት፡ ለምለም፡ ዛፎችና፡ አበባዎች፡ የት፡ አሉ?	በክረምት፡ እንጂ፡ በበጋ፡ አይታዩም።
የቢሮው፡ ሹም፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ለሚሠሩት፡ ሰዎች፡ ምን፡ ሰጣቸው?	ብዙ፡ ገንዘብ፡ ሰጣቸው።
በቅርብ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ወደ፡ እኛ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ የመጡ፡ እነማን፡ ናቸው?	የኢትዮጵያ፡ ተማሪዎች፡ ናቸው።
ጢሞን፡ ተጎምቶ፡ የት፡ መሄድ፡ እንደሚፈልግ፡ ታውቃላችሁ?	ምናልባት፡ ወደ፡ ሥራው፡ ይሄድ፡ ይሆናል።
በዚህ፡ አቅጣጫ፣ ስገሕሩ፡ አቅራቢያ፡ ቤቶች፡ አሉ?	አዎ፣ አምስት፡ ቤቶች፡ አሉ።
አቶ፡ ለማ፡ ጥያቄ፡ ሲጠየቅ፡ ማን፡ መለሰ?	በእውነቱ፡ አላውቅም።
አውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ግቢ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ለምለም፡ ዛፎች፡ አሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ ዛፎች፡ አሉ።

ጥያቄ	መልስ
በቦርድ፡ ለምን፡ መጣህ?	በጣም፡ የምፈልገው፡ ነገር፡ ስላለኝ፡ ነው።
ለምን፡ አርፍደህ፡ ትመጣለህ?	አውቶቡስ፡ ስጠብቅ፡ ነው።

ድርሰት

አቶ፡ ለማ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚሰጠውን፡ ትምህርት፡ ከጨረሰ፡ በኋላ፡ ለከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ አሰበ።

አንድ፡ ቀን፡ በጥዋት፡ ተነስቶ፡ ስለ፡ ቪዛው፡ ለመነጋገር፡ ወደ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ሄደ። እዚያም፡ የቪዛውን፡ ሹም፡ አግኝቶ፡ ሰላምታ፡ ከሰጠው፡ በኋላ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ መፈለጉን፡ ገለጸለት። የቪዛው፡ ሹም፡ የሚገባበትን፡ የዩኒቨርሲቲና፡ እንዲሁም፡ ከዩኒቨርሲቲው፡ ባለሥልጣኖች፡ ደብዳቤ፡ ማግኘቱን፡ ጠየቀው። አቶ፡ ለማ፡ ከዩኒቨርሲቲው፡ ባለሥልጣኖች፡ የደረሰውን፡ ደብዳቤ፡ ባቀረበለት፡ ጊዜ፡ የቪዛው፡ ሹም፡ ማናቸውም፡ ነገር፡ የተሟላ፡ መሆኑን፡ ካረጋገጠ፡ በኋላ፡ ቪዛውን፡ ላቶ፡ ለማ፡ ሊሰጠው፡ ፈለገ።

ማናቸውም፡ ሰው፡ ለትምህርት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ሲፈልግ፡ በመጀመሪያ፡ የሚገባውን፡ ደንብ፡ መፈጸም፡ አለበት። ይህ፡ ደንብ፡ በሚገባ፡ ካልተፈጸመ፡ ቪዛ፡ ማግኘት፡ አስቸጋሪ፡ መሆኑ፡ የታወቀ፡ ነው።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ለምን፡ ፈለገ?

መቼ፡ ወደ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ሄደ?

ለምን፡ ወደ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ለመሄድ፡ ፈለገ?

በአሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ውስጥ፡ ማንን፡ አገኘ?

ለቪዛው፡ ሹም፡ ምን፡ ገለጸለት?

የቪዛው፡ ሹም፡ አቶ፡ ለማን፡ ምን፡ ጠየቀው?

አቶ፡ ለማ፡ ለቪዛው፡ ሹም፡ ምን፡ አሳየው?

የቪዛው፡ ሹም፡ ላቶ፡ ለማ፡ ምን፡ ሊሰጠው፡ ፈለገ?

አንድ፡ ተማሪ፡ ለትምህርት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ሊሄድ፡ ምን፡
ማድረግ፡ ይገባዋል?

አንድ፡ ሰው፡ የሚገባውን፡ ደንብ፡ ከፈጸመ፣ ቪዛ፡ ማግኘት፡
አስቸጋሪ፡ ነው?

ሀያ፡ ሁለተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

የቪዛ፡ ሹም

አሜሪካ፡ አገር፡ በሚማሩበት፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ገንዘብ፡ ማን፡ ይከፍልዎታል?

ካሣ

አባቴና፡ እናቴ፡ ናቸው።

የቪዛ፡ ሹም

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ሄደው፡ እንዲማሩ፡ ፈቅዶልዎታል?

ካሣ

አዎ፡ ፈቅዶልኛል።

የቪዛ፡ ሹም

ቤተሰቦችዎ፡ በወር፡ ስንት፡ ያሜሪካን፡ ብር፡ ይከፍልዎታል?

ካሣ

ሦስት፡ መቶ፡ ያሜሪካን፡ ብር፡ ይከፍሉኛል።

የቪዛ፡ ሹም

ሦስት፡ መቶ፡ ብር፡ እንደሚከፍልዎ፡ የሚያስረዳ፡ ደብዳቤ፡ አለዎት?

ካሣ

አዎ፡ አለኝ።

የቪዛ፡ ሹም

እስቲ፡ ልየው?

ካሣ

እሺ፡ ይኸውና!

የቪዛ፡ ሹም

እንግዲያስ፡ ይህንን፡ የማመልከቻ፡ ፎርም፡ ቢፈልጉ፡ እዚህ፡ ባይፈልጉ፡ ቤትዎ፡ ይውሰዱና፡ ሞልተው፡ ይላኩልኝ።

ካሣ

ብዙ፡ ጊዜ፡ ስለሌለኝ፡ እዚሁ፡ ብጨርስ፡ ፍቃዴ፡ ነው።

የቪዛ፡ ሹም

ጥሩ። ማመልከቻው፡ ላይ፡ የሚያስቸግሩዎ፡ ጥያቄዎች፡ ቢኖሩ፡ እኔን፡ ወይም፡ ጸሐፊዬን፡ ሊጠይቁ፡ ይችላሉ።

ካሣ

እሺ፡ ጌታዬ።

የቪዛ፡ሹም

ቪዛው፡ ሊዘጋጅ፡ እንጠራዎታለን።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ሚኒስትሩ፡ ለመጡ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋል?	ሚኒስትሩ፡ ለመጡ፡ ሠላምታ፡ መስጠት፡ ያስፈልጋል።
በብዙ፡ ሺ፡ የሚቆጠሩ፡ ሰዎች፡ አየህ?	ለማየት፡ ፈልጌ፡ ነበር፤ ግን፡ ለማየት፡ አልቻልኩም።
እናታችሁ፡ በቅርብ፡ ቀን፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ እንደሚመጣ፡ ነገረችሁ?	በስልክ፡ ጠርታ፡ ነገረን።
ሰውዬው፡ እየሄደ፡ እንዲያስተምር፡ አዘዝከው?	አዝዤው፡ ነበር፤ ነገር፡ ግን፡ ከመሄድ፡ አልቻለም።
የማመልከቻው፡ ፎርም፡ ሊመጣልህ፡ ወደ፡ ከሚኒስቴር፡ ለትምህርት፡ ትሄዳለህ?	ምናልባት፡ ሊመጣልኝ፡ እሄዳ፡ ይሆናል።
የቢሮው፡ ሹም፡ ጥዋት፡ ልክ፡ በሦስት፡ ሰዓት፡ በቢሮአቸው፡ ተገኝተው፡ ሥራቸውን፡ መሥራት፡ አለባቸው?	አዎ፣ በሦስት፡ ሰዓት፡ ገብተው፡ መሥራት፡ አለባቸው።

ጥያቄ	መልስ
ቤትህ፡ ሁለት፡ ክፍል፡ ስላለው፡ አንዱን፡ ክፍል፡ ለጓደኛህ፡ ከመስጠት፡ ትፈቅዳለህ?	እርሱ፡ ከፈለገ፡ ከመስጠት፡ እፈቅዳለሁ።
የከተማው፡ ፖሊስ፡ ወደምፈልገው፡ ሰው፡ ሊመራኝ፡ ይችላል?	አዎ፣ ሊመራዎ፡ ይችል፡ ይሆናል።
አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ እንዲሄድ፡ ፈቅደውለታል?	አዎ፣ ፈቅጄለታለሁ።
የተገኘው፡ ገንዘብ፡ በሠራተኞች፡ ሌት፡ ተቆጠረ?	ሹሙ፡ ስላዘዘ፡ በሠራተኞች፡ ሌት፡ ተቆጠረ።
አስተማሪው፡ ክፍሉ፡ ውስጥ፡ እንደገባ፡ ትምህርት፡ ይጀምራል?	አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ይጀምራል። አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡ አይጀምርም።
ጋዜጣውን፡ እንዳነበበ፡ ያባቱን፡ መሄድ፡ አረጋገጠ?	አዎ፣ ሊያረጋግጥ፡ ቻለ።
መንግሥት፡ ቢፈቅድልኝ፡ ገንዱ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ መሥራት፡ እችላለሁ?	መንግሥት፡ ከፈቀደልህ፡ መሥራት፡ ትችላለህ።
ወንዙ፡ ቢሞላ፡ ወደ፡ ዋና፡ ትሄዳለህ?	ምናልባት፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ከቤታችሁ፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ መኝታችሁ፡ ምን፡ ትሠራላችሁ?	ጋዜጣውን፡ እናነባለን።
ወደ፡ ቤቴ፡ እንድትመጪ፡ ብጠይቅሽ፡ ትመጫለሽ?	አዎ፣ በደስታ፡ እመጣለሁ።

ጥያቄ	መልስ
አማርኛ፡ ቢያስተምሩህ፡ በወር፡ ስንት፡ ብር፡ ትለማቸዋለህ?	ሁለት፡ መቶ፡ ብር፡ እለማቸዋለሁ።
በውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ ሥራ፡ ትሰጡታላችሁ?	አዎ፡ እንሰጠዋለን።
ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ወደ፡ ቢሮ፡ መሄድ፡ አልነበረብህም?	አዎ፡ መሄድ፡ ነበረብኝ።
ወዳገርህ፡ ስመጣ፡ እንድጠይቅህ፡ አድራሻህ፡ የት፡ ነው?	አድራሻዬ፡ ትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ነው።
ስለ፡ አገሬ፡ ብነግራችሁ፡ እናንተም፡ ስለ፡ አገራችሁ፡ ትነግሩኛላችሁ?	አንተ፡ ስለ፡ አገርህ፡ ከነገርከን፡ እኛም፡ ስለ፡ አገራችን፡ እንነግርሃለን።
በዚህ፡ ወር፡ ውስጥ፡ ዝናብ፡ ስለሚዘንብ፡ ብርድ፡ የሚሆን፡ ይመስለሃል?	ሁልጊዜ፡ ዝናብ፡ ከዘነበ፡ ይበርድ፡ ይሆናል።
ወይዘሪት፡ አለማዝ፡ የጠየቅሻትን፡ ነገረችህ?	የማውቀው፡ ነገር፡ የለም፡ አለችና፡ ነገረችኝ።
እመጣለሁ፡ ስለሆነ፡ ትጠብቀኛለህ?	አዎ፡ እኔን፡ ለማየት፡ ስለምትመጣ፡ እጠብቅሃለሁ።
ዛሬ፡ ጓደኛህ፡ ወደ፡ ቢሮ፡ ለምን፡ አልመጣችም?	ሌሊቱን፡ ስላመማት፡ ወደ፡ ሐኪም፡ ሄዳለች።
ስለ፡ ወንድምህ፡ ካሜሪካ፡ መምጣት፡ ሰማህ?	አዎ፡ ትናንትና፡ አንድ፡ ሰው፡ ነገረኝ።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ከተማ፡ ከማን፡ ጋር፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ከባልንጀሮቻችን፡ ጋር፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።
ከዚህ፡ በፊት፡ የት፡ ሄዳችሁ፡ ነበር?	ወዳዲስ፡ ከተማ፡ ሄደን፡ ነበር።
እቤት፡ ካሉት፡ ሰዎች፡ ማንን፡ ጠራህ?	አቶ፡ ለማንና፡ አጎቴን፡ ጠራሁዋቸው።
ገንዘቡን፡ ሲያገኝ፡ ሽርሽር፡ የሚሄድ፡ ይመስልሃል?	አዎ፤ ምናልባት፡ ወዳዲስ፡ አበባ፡ ለአንድ፡ ሳምንት፡ ይሄድ፡ ይሆናል።
ክረምቱ፡ ሳይመጣ፡ ወደ፡ አገራችሁ፡ ትሄዳላችሁ?	አዎ፤ ካንድ፡ ወር፡ በኋላ፡ ወደ፡ አገራችን፡ እንሄዳለን።
ከሥራ፡ ስትመጣ፡ ወደ፡ እኛ፡ ቤት፡ ትመጣለህ?	ወደ፡ ከተማ፡ ስለምሄድ፤ መምጣት፡ አልችልም።
ወይዘሪት፡ አለማዝ፡ ስትመጣ፡ የት፡ ትቆያለች?	ምናልባት፡ ካቶ፡ ዮሐንስ፡ ጋር፡ ትቆይ፡ ይሆናል።
ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ስትሄዱ፡ በመንገድ፡ ላይ፡ ምን፡ አያችሁ?	ምንም፡ አላየንም።
እንግሊዝ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ስላየኸው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ልትነግረን፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፤ የምትፈልጉትን፡ ብትጠይቁኝ፡ እነግራችኋለሁ።
አለማዝ፡ ትናንት፡ ምን፡ እንድትነግራት፡ ጠየቀችህ?	ስለ፡ አሜሪካ፡ ትምህርት፡ ቤቶችና፡ ተማሪዎች፡ እንድነግራት፡ ጠየቀችኝ።

ጥያቄ	መልስ
ለማና፡ ሚስቱ፡ እንደመጡና፡ ወደ፡ ወንዝ፡ ሄደን፡ እንድንዋኝ፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ ቶሎ፡ ሲመጡ፡ ሄደን፡ እንድንዋኝ፡ እፈልጋለሁ።
ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ሄዳችሁ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ እንድትሠሩ፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፣ እዚያ፡ ሄደን፡ እንድንሠራ፡ በጣም፡ እንፈልጋለን።
አማርኛ፡ ቋንቋ፡ እንድትማር፡ የነገረህ፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?	አማርኛ፡ ቋንቋ፡ እንድማር፡ ወንድሜ፡ ነገረኝ።

ድርሰት

አቶ፡ ለማ፡ የሚባለው፡ ኢትዮጵያዊ፡ ተማሪ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድና፡ ትምህርቱን፡ ለመቀጠል፡ ስለፈለገ፣ ወደ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ መሄድና፡ ቪዛ፡ መጠየቅ፡ ግዴታው፡ ሆነ። አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ለቪዛ፡ ከመሄዱ፡ በፊት፡ ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ መፈጸም፡ የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ ከጨረሰ፡ በኋላ፣ ወደ፡ ኤምባሲ፡ ሄዶና፡ የቪዛውን፡ ሹም፡ አቶ፡ ጆን፡ የሚባሉትን፡ አሜሪካዊ፡ ተገናኘ። አቶ፡ ጆንም፡ አቶ፡ ለማን፡ ለምን፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ እንደሚፈልግ፣ የት፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንደሚገባ፣ ስንት፡ ዓመት፡ እንደሚቆይ፣ ለትምህርቱ፡ ማን፡ እንደሚከፍልለት፡ ከጠየቁት፡ በኋላ፡ አንድ፡ ፎርም፡ ሰጡትና፡ እንዲሞላ፡ አዘዙት።

አቶ፡ ለማም፡ ፎርሙን፡ ሞልቶ፡ ሲጨርስ፡ ላቶ፡ ጆን፡ ሰጣቸውና፡

ቢዛውን፡ ተቀበሉ። አቶ፡ ጆን፡ ቪዛውን፡ ላቶ፡ ለማ፡ ሊሰጡት፣ ስላስጠበቅሁ፡ አዝናለሁ፡ አሉ። አቶ፡ ለማም፡ ምንም፡ አይደል፡ እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ፡ አሉና፡ ወደ፡ ቤት፡ ሄዱ።

ጥያቄዎች

ወደ፡ አሜሪካ፡ የሚሄደው፡ ተማሪ፡ ስሙ፡ ማን፡ ይባላል?

አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለምን፡ ይሄዳል?

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ አቶ፡ ለማ፡ ስንት፡ ዓመት፡ ይቆያል?

ለትምህርቱ፡ ማን፡ ይከፍልለታል?

ያቶ፡ ጆን፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ቪዛውን፡ ለማግኘት፡ ምን፡ አደረገ?

አቶ፡ ለማ፡ ቪዛውን፡ ለማግኘት፡ ወዴት፡ ሄደ?

ቪዛውን፡ ተቀብለው፡ ላቶ፡ ጆን፡ ምን፡ አሉት?

አንድ፡ ኢትዮጵያ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ምን፡ ማድረግ፡ አለበት?

ሀያ፡ ሦስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

እባክዎ፡ እዚህ፡ ሰፈር፡ ባንክ፡ አለ?

ከበደ

አሁን፡ ክፍት፡ አይደለም፡ እንጂ፡ መኖሩን፡ አለ።

ዮሐንስ

ምን፡ ጊዜ፡ ይከፈታል?

ከበደ

ይህ፡ እኛ፡ ሰፈር፡ ያለው፡ ባንክ፡ የሚከፈተው፡ ጥዋት፡ ብቻ፡ ነው። ሌሎቹ፡ ግን፡ ቀኑን፡ በሙሉ፡ ክፍት፡ ናቸው።

ዮሐንስ

አሁን፡ ገንዘብ፡ እፈልጋለሁና፡ ወደ፡ ሌላ፡ ባንክ፡ ሄጄ፡ ግዴታ፡ ቼክ፡ መመንዘር፡ አለብኝ።

ከበደ

እንግዲያስ፡ ለቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አደባባይ፡ ያለው፡ ባንክ፡ ይቀርብዎታልና፡ እዚያኛው፡ ቢሄዱ።

ዮሐንስ

አዎ፣ አድራሻውን፡ ባውቀው፡ እዚያ፡ መሄድና፡ መመንዘር፡ ይቻለኛል።

ከበደ

ባንኩን፡ ለማግኘት፡ በጣም፡ አስቸጋሪ፡ አይደለም። ከዚህ፡ በፊት፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አደባባይ፡ ሄደው፡ የለም?

ዮሐንስ

አዎ፣ መጽሐፍ፡ ለመዋስና፡ ለመመለስ፡ ወደሜሪካን፡ ቤተ፡ መጻሕፍት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሄጃለሁ።

ከበደ

የሜሪካንን፡ መጽሐፍ፡ ቤት፡ ካወቁት፡ ባንኩ፡ ከሱ፡ ጎን፡ ነው።

ዮሐንስ

እሱንስ፡ አላጣውም፤ ቶሎ፡ ደርሼ፡ እመጣለሁ።

ከበደ

እሺ፡ ይቅናዎ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የት፡ ሰፈር፡ ባንክ፡ ይገኝ፡ ይመስለሃል?	እዚሁ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ሁለት፡ ባንኮች፡ እንዳሉ፡ አውቃለሁ።
የቱን፡ መዝገብ፡ ተከፍቶ፡ አየኸው?	እኔ፡ ስመጣ፡ ቀዩ፡ መዝገብ፡ ክፍቱን፡ ሆኖ፡ አየሁት።
የትኛውን፡ ቤት፡ መክፈትና፡ መዝጋት፡ ትችላለህ?	ሁለቱን፡ ቤቶች፡ ብቻ፡ መክፈትና፡ መዝጋት፡ እችላለሁ።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሠራተኞች፡ በሙሉ፡ የት፡ እንደሄዱ፡ ታውቃላችሁ?	ዛሬ፡ ሥራ፡ ስለማይሠሩ፡ ወደ፡ መሥሪያ፡ ቤታቸው፡ አልመጡም።
እዚሁ፡ ከተማ፡ ወዳለው፡ ቤተ፡ መጽሐፍት፡ የሚሄድ፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ከበደ፡ ነው።
እዚህ፡ ካሉት፡ ሰዎች፡ ወንድምዎ፡ ማንኛው፡ ነው?	እሴቶች፡ መካከል፡ የተቀመጠው፡ ረጅሙ፡ ሰው፡ ነው።
እዚህ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ የትኛዋን፡ ሴትዮ፡ አይተሃት፡ ነበር?	ቀይ፡ ልብስ፡ የለበሰችዋን፡ ሴት፡ አይቻት፡ ነበር።
ስለ፡ ማንኛው፡ ነገር፡ ትነግረኛለህ?	ስለ፡ ምንም፡ ነገር፡ አልነግርህም።
የሰጠኸኝን፡ ገንዘብ፡ ለማን፡ እንድሰጠው፡ ትፈልጋለህ?	ለእናቴ፡ እንድትሰጥልኝ፡ እፈልጋለሁ።
እዚህ፡ ጠረጴዛ፡ ላይ፡ ካሉት፡ መጽሐፎች፡ የትኛውን፡ ማንበብ፡ ይፈልጋሉ?	ቢጫውንና፡ አረንጓዴውን፡ መጽሐፎች፡ ማንበብ፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ስለ፡ የትኛው፡ አገር፡ መናገር፡ ትፈልጋለህ?	ስለ፡ አሜሪካ፡ መናገር፡ እፈልጋለሁ።
የትኛውን፡ መኪና፡ መዋስ፡ ትፈልጋለህ?	ትንሽዋን፡ መኪና፡ መዋስ፡ እፈልጋለሁ።
የትኞቹ፡ አስተማሪዎች፡ ከእረፍት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ይሄዳሉ?	ሁሉም፡ በሙሉ፡ ይሄዳሉ።
እነማን፡ አማርኛ፡ እንዲማሩ፡ ትፈልጋለህ?	ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሠራተኞች፡ አንድ፡ ወይም፡ ሁለት፡ ሰዎች፡ እንዲማሩ፡ እፈልጋለሁ።
እሱ፡ ከየትኛው፡ ገንዘብ፡ ሹም፡ ነው?	ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ገንዘብ፡ ሹም፡ ነው።
የትኛውን፡ ጠረጴዛ፡ ተዋሰ?	አዲሱን፡ ጠረጴዛ፡ ተዋሰ።
ምሳቸውን፡ ለምን፡ እዚህ፡ መብላት፡ አስፈለጋቸው?	እዚህ፡ ምሳ፡ ለመብላት፡ በጣም፡ ውድ፡ ነው።
ይህን፡ ደብዳቤ፡ ለማንኛው፡ ሰው፡ መስጠት፡ አለብኝ?	ለትምህርት፡ ቤቱ፡ ሹም፡ መስጠት፡ አለብህ።
ስትመጡ፡ ማንም፡ ሰው፡ አላያችሁም?	የለም፣ ማንም፡ ሰው፡ አላየንም።
ማንም፡ ቢጠይቃችሁ፡ ስለ፡ ሠራነው፡ አትናገሩም?	የለም፣ አንናገርም።

ጥያቄ	መልስ
አልማዝ፡ ወደ፡ ዋና፡ ስትሄድ፡ የምትበላው፡ ምንም፡ አልወሰደች?	የለም፣ ምንም፡ አልወሰደች።
ስለ፡ ቤቱ፡ ሰባችህ፡ ምንም፡ አልሰማህ?	የለም፣ እስካሁን፡ ምንም፡ አልሰማሁም።
አገራችሁ፡ መቼ፡ ደርሳችሁ፡ ተመለሳችሁ?	ከአንድ፡ ወር፡ በፊት፡ ደርሰን፡ ተመለስን።
ማንኛውን፡ ሰው፡ መጎብኘት፡ ፈልጋችሁ፡ ነበር?	ያቶ፡ ዮሐንስን፡ አባት፡ መጎብኘት፡ ፈልገን፡ ነበር።
የትኞቹን፡ ቤቶች፡ ሊገዙ፡ ይፈልጋሉ?	በስተቀኝ፡ ያሉትን፡ ሁለት፡ ቤቶች፡ መግዛት፡ ይፈልጋሉ።
የትኞቹን፡ ጋዜጦች፡ አንብበህ፡ ጨረስህ?	አጠረጴዛ፡ ላይ፡ ያሉትን፡ አንብቤ፡ ጨረስሁ።
ስለ፡ ማንኛዎቹ፡ አገሮች፡ ማስተማር፡ ትችላለህ?	ስለ፡ ኢትዮጵያና፡ አሜሪካ፡ ማስተማር፡ እችላለሁ።
ወደ፡ አገራችሁ፡ ከማን፡ ጋር፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ከነ፡ አልማዝ፡ ጋር፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ኑሮ፡ ከጀመሩበት፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ላገሩ፡ እንግዳ፡ ለሰው፡ ባዳ፡ ነበር። በዚሁ፡ ምክንያት፡ የከተማውን፡ መውጫና፡ መግቢያ፡ አያውቁትም። እንዳጋጣሚ፡ አንድ፡ ቀን፡ ወደ፡ ባንክ፡ ለመሄድና፡ ቼክ፡ ለመመንዘር፡ ፈልገው፤ መንገዱ፡ ጠፋባቸና፡ ቆሞ፡ ሲያመነቱ፡ አቶ፡ ከበደን፡አየው። አቶ፡ ከበደም፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ መንገድ፡ የተሳሳታቸው፡ መሆኑን፡ ስላወቁ፤ ጠጋ፡ ብለው፡ "ልረዳዎት፡ እችላለሁ?" አለና፡ ዮሐንስን፡ ጠየቀው። ዮሐንስም፡ ፈጠን፡ ብለው፡ "ገቅሌሊያ፡ ያለው፡ ባንክ፡ የት፡ ነው፡" አለው። ከበደም፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥትን፡ ባንክ፡ አድራሻ፡ ነገረውና፡ ጉዞውን፡ ቀጠለ። ዮሐንስም፡ ቼኩን፡ ሊመነዝር፡ ወደ፡ ባንኩ፡ ሄደ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስን፡ ላገሩ፡ እንግዳ፡ ለሰው፡ ባዳ፡ ያደረጋቸው፡ ምንድን፡ ነው?

አንተ፡ ወደ፡ አንድ፡ አዲስ፡ አገር፡ ስትሄድ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ይሰማሃል?

ዮሐንስ፡ ቼክ፡ ለመመንዘር፡ የፈለገው፡ ለምንድን፡ ነው?

መንገዱ፡ በጠፋበት፡ ጊዜ፡ ምን፡ አደረገ?

ዮሐንስ፡ አመንገድ፡ ላይ፡ ቆሞ፡ ለምን፡ አመነታ?

አቶ፡ ከበደ፡ ላቶ፡ ዮሐንስ፡ የየትኛውን፡ ባንክ፡ አድራሻ፡ ሰጠው?

ከበደ፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ምን፡ አደረገ?

ዮሐንስስ፡ ምን፡ ሠራ?

አንተ፡ ከሃገሩ፡ እንግዳ፡ የሆንክበት፡ ጊዜ፡ አለ?

ሀያ፡ አራተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

እባክዎ፡ ይህን፡ ቼክ፡ እንዲመነዝሩልኝ፡ እፈልጋለሁ?

የባንክ፡ ሠራተኛ

እሺ፡ እመነዝርልዎታለሁ። ለመሆኑ፡ የመታወቂያ፡ ወረቀት፡ ይዘዋል?

ዮሐንስ

አዎ፣ አሜሪካ፡ ኤምባሲ፡ የምሠራ፡ አሜሪካዊ፡ መሆኔን፡ የሚገልጽ፡ ወረቀት፡ አለኝ።

የባንክ፡ ሠራተኛ

እሱ፡ በቂ፡ ነው። ግን፡ ማየት፡ እፈልጋለሁ።

ዮሐንስ

ይኸው፡ ጌታዬ።

የባንክ፡ ሠራተኛ

እሺ፡ እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ። በቼኩ፡ ጀርባ፡ ላይ፡ ስምዎን፡ ይጻፉበት።

ዮሐንስ

ይኸው፡ ጻፍኩበት።

የባንክ፡ ሠራተኛ

ታዲያ፡ እንዴት፡ እንድመነዝርልዎ፡ ይፈልጋሉ?

ዮሐንስ

ገኪ፡ ኣምስትና፡ ገኪ፡ አሥር፡ ያድርጉልኝ።

የባንክ፡ ሠራተኛ

ይኸው፡ ጌታዬ። ለመሆኑ፡ ከባንክ፡ ገንዘብ፡ መበደር፡ ይፈልጋሉ?

ዮሐንስ

ለጊዜው፡ ብድር፡ አያስፈልገኝም። ከሁለት፡ ወር፡ በኋላ፡ ግን፡ ለመበደር፡ እመጣለሁ።

የባንክ፡ ሠራተኛ

መልካም፡ እንደፈለጉ።

ዮሐንስ

በጣም፡ አመሰግናለሁ።

የባንክ፡ ሠራተኛ

ምንም፡ አይደል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እባንክ፡ ውስጥ፡ ገንዘብ፡ ለማስቀመጥ፡ መታወቂያ፡ ወረቀት፡ ያስፈልጋል?	የለም፣ አያስፈልግም።
ከባንኩ፡ ቤቱ፡ ገንዘብ፡ አወጣህ?	አንድ፡ አሥራ፡ አምስት፡ ብር፡ አውጥቻለሁ።
ከባንኩ፡ ጀርባ፡ ያለውን፡ ሱቅ፡ መግዛት፡ ትችላለህ?	በሦስት፡ ሺ፡ ብር፡ ቢሸጠው፡ እገዛዋለሁ።
ቼክ፡ ለመመንዘር፡ ስምህን፡ መፈረም፡ ያስፈልጋል?	አዎ፣ ከሱም፡ በላይ፡ ዋስ፡ ያስፈልጋል።
ከባንክ፡ ማውጣት፡ የፈለግኸው፡ ባለ፡ አምስትና፡ ባለ፡ አሥር፡ ብር፡ ነው?	አዎ፣ ባለ፡ አሥርና፡ ባለ፡ አምስት፡ ብር፡ ነው።
ከባንክ፡ ከተበደርከው፡ ገንዘብ፡ ስንት፡ ትሰጠኛለህ?	ሁለት፡ ባለ፡ አሥር፡ ብር፡ እሰጥሃለሁ።
የገንዘብ፡ ብድር፡ ብፈልግ፡ ባንኩ፡ ስንት፡ ይሰጠኝ፡ ይመስልሃል?	የምትፈልገውን፡ ያህል፡ ይሰጥሃል።
ባንኩ፡ ካለበት፡ ሰፈር፡ የኪራይ፡ ቤት፡ ማግኘት፡ ይቻላል?	አዎ፣ ሁለት፡ የሚከራዩ፡ ቤቶች፡ ማግኘት፡ ይቻላል።
ከባንኩ፡ ሠራተኞች፡ ቤት፡ ለመከራየት፡ የሚፈልጉትን፡ ሰዎች፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ባንኮች፡ ጥዋት፡ ጥዋት፡ የሚከፈቱ በትን፡ ሰዓት፡ ማወቅ፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ ማወቅ፡ እፈልጋለሁ።
የባንኩ፡ ሠራተኞች፡ ቀኑን፡ በሙሉ፡ ይሠራሉ?	የለም፣ ቀኑን፡ በሙሉ፡ አይሠሩም።
ገንዘቡን፡ እዚሁ፡ ከተማ፡ ባለው፡ ባንክ፡ ውስጥ፡ ማስቀመጥ፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ ቢቻል፡ እዚያ፡ ማስቀመጥ፡ ይፈልጋል።
ከበደ፡ እባንክ፡ ውስጥ፡ ያስቀመጠውን፡ ገንዘብ፡ ማውጣትና፡ ለጎረቤቱ፡ ማበደር፡ ይፈልጋል?	ግማሹን፡ እውነቱ፡ ማበደር፡ ይፈልጋል።
ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ገሰሰ፡ የተበደረውን፡ ገንዘብ፡ መለሰ?	ገና፡ አልመለሰም።
ካገሩ፡ ገዴ፡ ከሆነ፡ ባንኩ፡ ገንዘብ፡ እንዴት፡ አበደረው?	በእውነቱ፡ እንዴት፡ እንደሆነ፡ አላውቅም።
ገንዘብዎን፡ ኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ባንክ፡ ውስጥ፡ ለማስቀመጥ፡ አመንትተው፡ ነበር?	አዎ፣ በጣም፡ አመንትቼ፡ ነበር።
ወደ፡ አገራችሁ፡ ከመሄድ፡ ከምን፡ ታመነታላችሁ?	ምናልባት፡ ሥራ፡ አናገኝም፡ ይሆናል።
እባንክ፡ ውስጥ፡ ካለህ፡ ገንዘብ፡ ወለድ፡ ስንት፡ ታገኛለህ?	በመቶ፡ ሦስት፡ መቶ፡ ብር፡ አገኛለሁ።

ጥያቄ	መልስ
እባንክ፡ ውስጥ፡ ያስቀመጥኸውን፡ ገንዘብ፡ ማውጣት፡ ትችላለህ?	አዎ፤ ስፈልግ፡ አወጣለሁ።
ነጋዴዎች፡ ሁሉ፡ እባንክ፡ ውስጥ፡ ገንዘብ፡ አላቸው?	ሁሉም፡ አላቸው።
ባንኩ፡ በወር፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ትርፍ፡ ያገኛል?	በእውነቱ፡ አላውቅም።
አንተ፡ ባንክ፡ መክፈት፡ ትፈልጋለህ?	ገንዘብ፡ ስለሌለኝ፡ መክፈት፡ አልችልም።
የባንኩን፡ ገንዘብ፡ የሚያበድረው፡ ሰው፡ ስም፡ ማን፡ ነው?	ዮሐንስ፡ ይባላል።
ወደ፡ ሲኒማ፡ መሄድ፡ ግዴታ፡ አለብኝ?	ካልፈለግህ፡ ሲኒማ፡ መሄድ፡ ግዴታ፡ የለብህም።
ይህን፡ ቤት፡ ካገቱ፡ ግዴታ፡ መግዛት፡ አለበት?	አዎ፤ ይህን፡ ቤት፡ ገዝቶ፡ ካገቱ፡ መስጠት፡ ግዴታው፡ ነው።
ያን፡ ከማን፡ ቤት፡ በግዴታ፡ ከፍተህ፡ ገባህ?	የለም፤ በግዴታ፡ አልከፈትሁም።
በግዴታ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ሥራ፡ መሥራት፡ ትችላለህ?	በግዴታ፡ ምንም፡ መሥራት፡ አልችልም።
አቶ፡ ዮሐንስና፡ ባለቤቱ፡ በግዴታ፡ ይመጡልሃል?	የለም፤ እኔ፡ በግዴታ፡ እንዲመጡ፡ አልፈልግም።
ለምን፡ ገንዘቡን፡ በግዴታ፡ መውሰድ፡ ትፈልጋለህ?	ገንዘቡን፡ በግዴታ፡ ለመውሰድ፡ አልፈለግሁም።
ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መሄድና፡ አገሩን፡ ማየት፡ ግዴታ፡ አለብህ?	አዎ፤ መሄድና፡ አገሩን፡ ማየት፡ ግዴታ፡ አለብኝ።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ኢትዮጵያ፡ ከመሄዴ፡በፊት፡ በግዴታ፡ አማርኛ፡ ማወቅ፡ አለብኝ?	አዎ፣ አማርኛ፡ መማር፡ አለብህ።
ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ በግዴታ፡ ወደ፡ሐኪም፡ መሄድ፡ አለባት?	አዎ፣ በግዴታ፡ መሄድ፡ አለባት።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ ባልፈልግ፡ ግዴታ፡ መሄድ፡ አለብኝ?	አዎ፣ ባትወድም፡ ወደ፡ ትምህርት፡ ግዴታ፡ መሄድ፡ አለብህ።
ከበደ፡ ግዴታ፡ መሄድ፡ አለበት?	ካልፈለገ፡ ግዴታ፡ መሄድ የለበትም።
ወደ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ ነበረበት?	በተለይ፡ ዛሬ፡ ግዴታ፡ መሄድ፡ ነበረበት።
ልብሱን፡ እዚህ፡ ማስቀመጥ፡ ግዴታ፡ ነበረበት?	አዎ፣ ልብሱን፡ ግዴታ፡ ማስቀመጥ፡ ነበረበት።
ልጁን፡ ግዴታ፡ ከትምህርት፡ ቤት፡ ማውጣት፡ ነበረበት?	አዎ፣ ማውጣት፡ ነበረበት።
ይህ፡ ኦርጎስ፡ ከዚያኛው፡ መብለጥ፡ ነበረበት?	አዎ፣ መብለጥ፡ ነበረበት።
ስንት፡ ዮሐንስ፡ ዋስ፡ ማግኘት፡ ግዴታ፡ ሆነበት?	አዎ፣ ሁለት፡ ዋሶች፡ ማግኘት፡ ግዴታ፡ ሆነበት።
መኪና፡ መከራየት፡ ግዴታ፡ ነበረባት?	የለም፣ ግዴታ፡ መከራየት፡ አልነበረባትም።
መኪና፡ መከራየትና፡ ወደ፡ አገሩ፡ መሄድ፡ ነበረበት?	አዎ፣ መኪና፡ ተከራይቶ፡ ወደ፡ አገሩ፡ መሄድ፡ ነበረበት።
ለመሆኑ፡ አማርኛ፡ መማር፡ ግዴታ፡ ነበረባት?	አዎ፣ ግዴታ፡ አማርኛ፡ መማር፡ ነበረባት።

ጥያቄ	መልስ
ከመሆኑ፡ መታወቂያ፡ ወረቀት፡ ግዴታ፡ ማውጣት፡ አለብሽ?	አዎ፤ ማውጣት፡ አለብኝ።
ወደ፡ አሜሪካ፡ ከመሄድ፡ በቂ፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ግዴታ፡ ሆነብዎ?	አዎ፤ በቂ፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ግዴታ፡ ሆነብኝ።
አቶ፡ ለማ፡ ጀርባውን፡ ለሚያመው፡ መድኃኒት፡ መፈለግ፡ ግዴታ፡ ሆነበት?	አዎ፤ ግዴታ፡ ሆነበት።
ቼኩን፡ ከመውሰዳቸው፡ በፊት፡ መፈረም፡ ግዴታ፡ ሆነባቸው?	አዎ፤ ግዴታ፡ ሆነባቸው።
ወደ፡ አገርህ፡ ስትሄድ፡ ገንዘብ፡ ግዴታ፡ መበደር፡ አለብህ?	አዎ፤ ደሞዜን፡ ስላላገኘሁ፡ መበደር፡ አለብኝ።
ብድር፡ ከባንክ፡ መበደር፡ አለብህ?	አዎ፤ መበደር፡ አለብኝ።
ገንዘብ፡ መበደርና፡ ለናትህ፡ መላክ፡ ግዴታ፡ ሆነብህ?	አዎ፤ ደሞዜን፡ እስካገኝ፡ ድረስ፡ መበደር፡ ግዴታ፡ ሆነብኝ።
ግማሽ፡ ደሞዝህን፡ ለቤት፡ ኪራይ፡ መክፈል፡ ግዴታ፡ ሆነብህ?	የደሞዜን፡ ግማሽ፡ ለቤት፡ ኪራይ፡ መክፈል፡ ግዴታ፡ ሆነብኝ።
አዲስ፡ አበባን፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ታውቀዋለህ?	አዎ፤ አውቀው፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ ካየሁት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ስለሆነ፡ ግዴታ፡ መሄድና፡ እንደገና፡ ማየት፡ አለብኝ።
ፈጠን፡ ብዬ፡ ከቤት፡ መውጣት፡ ነበረብኝ?	አዎ፤ ፈጠን፡ ብለህ፡ መውጣት፡ ነበረብህ።

ጥያቄ	መልስ
ባንኩ፡ ቋሀን፡ ስሌር፡ መግዛት፡ ነበረበት?	እዎ፣ መግዛት፡ ነበረበት።
እዚህ፡ ሥራ፡ ለማግኘት፡ ግዴታ፡ እንግሊዝኛ፡ መቻል፡ ነበረበት?	እዎ፣ እንግሊዝኛ፡ መቻል፡ ነበረበት።
ወደ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አደባባይ፡ መሄድ፡ ግዴታ፡ ሆነብህ?	ካቶ፡ ለማ፡ ጋር፡ ቀጠሮ፡ ስላለኝ፣ መሄድ፡ ግዴታ፡ ሆነብኝ።

ድርሰት

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከሚገኙት፡ ባንኮች፡ ሁሉ፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ ባንክ፡ ከሁሉም፡ ከፍ፡ ያለ፡ ነው። የሚገኘውም፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ነው። በዚህ፡ ባንክ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሠራተኞች፡ ይገኛሉ። በትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ሁሉ፡ ቅርንጫፎች፡ አሉት። ከኢትዮጵያ፡ ውጭም፡ በአንዳንድ፡ አገሮች፡ ውስጥ፡ ቅርንጫፍ፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ ከፍቶአል። ለምሳሌ፡ ባለፉት፡ ሦስት፡ ዓመታት፡ ውስጥ፡ አንድ፡ ትልቅ፡ ቅርንጫፍ፡ በሱዳን፡ ውስጥ፡ ከፍቶአል።

የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ ባንክ፡ ብድር፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ያበድራል። ነጋዴዎችና፡ የመንግሥት፡ ሠራተኞች፡ እንዲሁም፡ የከተማ፡ ነዋሪዎች፡ ሁሉ፡ ኑሮአቸውን፡ ለማሻሻልና፡ ንግዳቸውን፡ ለማስፋፋት፡ ገንዘብ፡ ይበደራሉ። ነጋዴዎችም፡ ከባንክ፡ በሚያገኙት፡ ገንዘብ፡ ወለድ፡ ይከፍላሉ። ከዚህም፡ በላይ፡ ባንኩ፡ የገሩን፡ ኢኮኖሚ፡ ለማበልጸግና፡ የሕዝቡን፡ የኑሮ፡ ደረጃ፡ ለማንሣት፡ ብዙ፡ ጥረት፡ ያደርጋል።

ባለፉት፡ ዓመታት፡ ውስጥ፡ ይህ፡ ባንክ፡ ከማናቸውም፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤቶች፡ ብዙ፡ መሻሻል፡ አድርጐአል።

ጥያቄዎች

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከሁሉ፡ ባንኮች፡ የሚበልጥ፡ የትኛው፡ ነው?
የዚህ፡ ባንክ፡ ቅርንጫፎች፡ የሚገኙት፡ የት፡ ነው?
በዚህ፡ ባንክ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሠራተኞች፡ ይገኛሉ?
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ቅርንጫፎች፡ አሉት?
ይህ፡ ባንክ፡ ብድር፡ ለማን፡ ይሰጣል?
ለምን፡ ዓይነት፡ ጉዳይ፡ ያበድራቸዋል?
ገንዘቡን፡ የተበደሩት፡ ሰዎች፡ ስንት፡ ወለድ፡ ይከፍላሉ?
ባንኩ፡ በተለይ፡ የሚያደርገው፡ ጥረት፡ ለምንድን፡ ነው?
ገንዘብ፡ ለማስቀመጥ፡ በወር፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ባንክ፡ ትሄዳለህ?
እባንክ፡ ውስጥ፡ ካስቀመጥኸው፡ ገንዘብ፡ በመቶ፡ ስንት፡ ገንዘብ፡ ታገኛለህ?
ገንዘብ፡ በባንክ፡ ውስጥ፡ ማስቀመጥ፡ ለምን፡ ይጠቅማል?
በሱዳን፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ቅርንጫፎች፡ አሉ?

ሀያ፡ አምስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ አቶ፡ ጆን።

ዮሐንስ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ አቶ፡ ከበደ።

ከበደ

እባክዎ፡ ይግቡ።

ዮሐንስ

እሺ፡ እግዜር፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

ብዙ፡ ጊዜ፡ በመዘግየትዎ፡ አይመጡም፡ በማለት፡ እኔና፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አዝነን፡ ነበር።

አሁን፡ ግን፡ ስለመጡ፡ በጣም፡ ደስታ፡ ይሰማናል።

ዮሐንስ

በውነቱ፡ አዝናለሁ። ቀደም፡ ብዬ፡ እደርሳለሁ፡ በማለት፣ ከቤቴ፡ ልክ፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ ተነስቼ፡ ነበር።
የሆነው፡ ሆኖ፡ ራስ፡ ገለቻ፡ ሆስፒታል፡ አጠገብ፡ ስደርስ፡ የመኪናዬ፡ ጐማ፡ ስለፈነዳ፣ እስክለውጠው፡ (እስክቀይረው)፡ ድረስ፡ መቆየት፡ ግዴታ፡ ሆኖብኝ፡ ነው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ቅዳሜ፡ ቅዳሜና፡ እሁድ፡ እሁድ፡ የት፡ ትሄዳላችሁ?	ቀን፡ ቀን፡ ሁልጊዜ፡ ወደ፡ መጽሐፍ፡ ቤት፡ እንሄዳለን፤ ማታ፡ ማታ፡ ግን፡ ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ እንሄዳለን።

ጥያቄ	መልስ
ትልልቅ፡ ቤቶች፡ ሠርቶ፡ መሸጥ፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ መሸጥ፡ ይፈልጋል።
አንዳንድ፡ ነጋዴዎች፡ ዓመት፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ትርፍ፡ ማግኘት፡ ይችላሉ?	አንድ፡ ሺ፡ ብር፡ ትርፍ፡ ማግኘት፡ ይችላሉ።
ሰኞ፡ ሰኞ፡ የት፡ ትሄዳለህ?	ወደ፡ ዋና፡ እንሄዳለን።
ቀን፡ ቀን፡ ትተኛላችሁ?	የለም፣ አንተኛም።
የሆነው፡ ሆኖ፡ ወንድምህን፡ ማታ፡ ማታ፡ ታየዋለህ?	አዎ፣ ማታ፡ ማታ፡ አየዋለሁ።
እሁድ፡ እሁድ፡ ወደ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ትሄዳላችሁ?	የለም፣ እሁድ፡ የረፍት፡ ቀን፡ ስለሆነ፣ ወደ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ አንሄድም።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ እያለ፡ ሄደ?	አዎ፣ በጣም፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ብሏል።
ሰፋፊ፡ ቤቶች፡ አገኛችሁ?	አዎ፣ አገኘን።
አንዳንድ፡ ነጋዴዎች፡ ብዙ፡ ትርፍ፡ ያገኛሉ?	አዎ፣ ያገኛሉ።
ነጫጭ፡ ድመቶች፡ አሉሽ?	አዎ፣ ሁለት፡ ነጫጭ፡ ድመቶች፡ አሉኝ።
ረጃጅም፡ እርሳሶች፡ አሉህ?	አዎ፣ አሉኝ።
ልጆችህ፡ ለምን፡ ቀጫጭኖች፡ ናቸው?	እኔም፡ ቀጭን፡ ስለሆንኩ፡ ነው።
ጥቋቁር፡ በቅሎዎች፡ አይተዋል?	አዎ፣ አይቻለሁ።
ቀያይ፡ ሰዎች፡ መጥተው፡ ነበር?	አዎ፣ ሁለት፡ ሰዎች፡ መጥተው፡ ነበር።
ማታ፡ ማታ፡ መሥራትና፡ ቀን፡ ቀን፡ ቀን፡ መማር፡ ይችላል?	ምናልባት፡ ይችል፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ጥቋቁሮቹን፡ ውሾች፡ ለማን፡ ሰጠሃቸው?	ለልጆቹ፡ ሰጠሁዋቸው።
በጣም፡ ደጋግ፡ ሰዎች፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ብዙ፡ ደጋግ፡ ሰዎች፡ አውቃለሁ።
መኪና፡ አለህ?	አዎ፣ ሁለት፡ ቆንጆ፡ መኪናዎች፡ አሉኝ።
አጫጭር፡ ሰዎች፡ ፖሊስ፡ መሆን፡ ይችላሉ?	የለም፣ አይችሉም።
ሆቴሉ፡ ሰፋፊ፡ ክፍሎች፡ አሉት?	አዎ፣ አምስት፡ ሰፋፊ፡ ክፍሎች፡ አሉት።
ቀይ፡ ልብስ፡ ገዛኸ?	አዎ፣ ሦስት፡ ቀያይ፡ ልብሶች፡ ገዛኹ።
ቀያይ፡ ገርጂጣዎች፡ ትገዛለህ?	አሁን፡ ገንዘብ፡ ስለሌለኝ፡ መግዛት፡ አልችልም።

ድርሰት

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ በወዳጅነት፡ ከብዙ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ ስለሚተዋወቁ፣ አንድ፡ ቀን፡ አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ለራት፡ አቤቱ፡ ጋበዘው። አቶ፡ ዮሐንስም፡ ግብዣውን፡ አክብሮ፡ በሦስት፡ ሰዓት፡ ገዶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ እንዲገኝ፡ ቃሉን፡ ሰጠ።

ልክ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ ሲሆን፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ መኪናውን፡ አስነስቶ፡ እያነዱ፡ ንዘውን፡ ወደ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ ቀጠለ። ዳሩ፡ ግን፡ ግማሽ፡ መንገድ፡ እንደ

ተጓዘ፡ የመኪናው፡ ጐማ፡ ስለፈነዳበት፣ ጐማውን፡ ለማስቀየር፡ ሠላሳ፡ ደቂቃ፡ አጠፋ።

ጐማውን፡ ካሳደሰ፡ በኋላ፡ መኪናውን፡ አስነስቶ፡ እየነዳ፡ ሲሄድ፣ በድንገት፡ ፖሊስ፡ አቁሞት፡ የትራፊክን፡ ሕግ፡ ስለጣሰ፡ በማግሠቱ፡ ወደ፡ ፖሊስ፡ ጣቢያ፡ እንዲቀርብ፡ ወረቀት፡ አገኘ። በዚህ፡ ምክንያት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ስላባከነ፣ አቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ ከሰዓቱ፡ አሳልፎ፡ ደረሰ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ለምን፡ ጋበዘው?

አቶ፡ ከበደ፡ ግብዣውን፡ አክብሮ፡ መጣ?

በስንት፡ ሰዓት፡ አቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ እንዲገኙ፡ ቃሉን፡ ሰጠ?

ጉዞውን፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ጀመረ?

መኪናውን፡ አስነስቶ፡ ወዴት፡ ሄደ?

ግማሽ፡ መንገድ፡ እንደተጓዘ፡ የመኪናው፡ ጐማ፡ ምን፡ ሆነ?

ጐማውን፡ ካሳደሰ፡ በኋላ፡ ምን፡ አደረገ?

አቶ፡ ዮሐንስን፡ በመንገድ፡ ላይ፡ ማን፡ አቆመው?

ፖሊሱ፡ ለምን፡ አቆመው?

በማግሥቱ፡ ወዴት፡ መቅረብ፡ ነበረበት?

ወደ፡ ግብዣ፡ መሄድ፡ ለምን፡ ይጠቅማል?

በወር፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ግብዣ፡ ትሄዳለህ?

ሀያ፡ ስድስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጥሩነሽ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ አቶ፡ ዮሐንስ፣ እንደምን፡ ሰነበቱ?

ዮሐንስ

ደህና፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን። እርስዎስ?

ጥሩነሽ

አቶ፡ ከበደ፣ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ከእንግዶቻችን፡ ጋር፡ አስተዋውቃቸው።

እንዲሁም፡ የሚበላና፡ የሚጠጣ፡ ነገር፡ ወዳለበት፡ ውሰዷቸው።

ከበደ

ጥሩ፡ ሃሳብ፡ ነው፣ ጥሩነሽ። ይምጡ፡ ከእንግዶቹ፡ ጋር፡ ላስተዋውቅዎት፣ አቶ፡ ዮሐንስ።

ዮሐንስ

እሺ፣ ነገር፡ ግን፡ ከእንግዶቹ፡ ጋር፡ ከመተዋወቄ፡ በፊት፡ እጄን፡ መታጠብ፡ እፈልጋለሁ።

ከበደ

እንግዲያስ፡ መታጠቢያ፡ ቤቱን፡ ላሳይዎ።

ሳሙናና፡ ፎጣ፡ በመታጠቢያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ይገኛል።

ዮሐንስ

አመሰግናለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የሆነው፡ ሆኖ፡ ወንድምህን፡ ሃይሉን፡ አየኸው?	አዎ፣ ባለፈው፡ ወር፡ ሃረር፡ አየሁት።
ቀደም፡ ማለትና፡ መምጣት፡ ያስፈልገዋል?	አዎ፣ በሁለት፡ ሰዓት፡ እዚህ፡ መገኘት፡ አለበት።

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ ቆመህ፡ ምን፡ ትሠራለህ?	አውቶቡስ፡ ይመጣል፡ በማለት፡ እጠብቃለሁ።
አሁን፡ ወደ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ትሄዳላችሁ?	ምናልባት፡ እንሄድ፡ ይሆናል።
ሥራ፡ ለማግኘት፡ ብዙ፡ ጥረት፡ አድርገህ፡ ነበር?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ ጥረት፡ አድርጌ፡ ነበር።
ያቶ፡ ለማ፡ ደረጃ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ነው?	አዎ፣ የትምህርት፡ ቤት፡ ሹም፡ ነው።
ልጅህ፡ የቤቱን፡ ደረጃ፡ መውጣት፡ ትችላለች?	የለም፣ ገና፡ ትንሽ፡ ናት።
አስተማሪ፡ መሆን፡ አያበለጽግም?	በጣም፡ ያበለጽጋል።
ትምህርት፡ ቤቱን፡ ለማስፋፋት፡ ገንዘብ፡ የት፡ አገኘህ?	የትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ሰጠኝ።
ንግድ፡ የሚያበለጽግ፡ ሥራ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ የሚያበለጽግ፡ ይመስለኛል።
አቶ፡ ከበደ፣ አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ነዋሪ፡ ናቸው?	አዎ፣ እዚያ፡ ያስተምራሉ።
ባንክ፡ ብዙ፡ ቅርንጫፎች፡ አሉት?	ሁለት፡ ቅርንጫፎች፡ ብቻ፡ አሉት።
ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ወደዚህ፡ አገር፡ መቼ፡ ይመጣሉ?	ከሁለት፡ ወር፡ በኋላ፡ ይመጣሉ።
ንጉሠ፡ ነገሥቱን፡ ከዚህ፡ በፊት፡ አይተሃቸዋል?	የለም፣ አላየሁዋቸውም።
እንደ፡ ሰው፡ በሥራ፡ ከፍ፡ ማለት፡ ቢፈልግ፡ ምን፡ ማድረግ፡ አለበት?	ትምህርቱን፡ ማሻሻል፡ ያስፈልገዋል።

ጥያቄ	መልስ
የወር· ደምወዝህ· ስንት· ነው?	አራት· መቶ· ብር· ነው።
ደምወዝህ· ሊያበለጽግህ· ይችላል?	ነገሩን· ግልጽልሁ· ደምወዜ· ሊያበለጽገኝ· አይችልም።
የመኪናውን· መስኮት· የዘጋኸው· አንተ· ነህ?	የለም፤ እቶ· የሐጎስ· ነው።
ቤትህ· ስንት· መስኮቶች· አሉት?	ስድስት· መስኮቶች· አሉት።
መዝጊያህን· በምን· ዘጋኸው?	በቁልፍ· ዘጋሁት።
የመኪናው· መዝጊያ· ሰፊ· ነው?	በጣም· ሰፊ· አይደለም።
የበሩን· መዝጊያ· የከፈተው· ማን· ነበር?	ያች· የሐጎስ· ሴት· ልጅ· ነበረች።
አንተ· የመኪናህን· በር· ዘግተኸው· ነበር?	አዎ፤ ዘግቼው· ነበር።
የእናንተ· ባንክ· ለወር· ስንት· ወለድ· ይሰጣል?	ስድስት· ብር· ከመቶው· ማትረፊያ· ይሰጣል።
ወደ· ውጭ· አገር· መሄድ· ትርፍ· አለው?	ይህ· በጣም· አስቸጋሪ· ጥያቄ· ነው።
እናንተ· ከተማ· ውስጥ· ስንት· ነጋዴዎች· ይገኛሉ?	ሃምሳ· የሚሆኑ· ነጋዴዎች· አሉ።
ሉቃ· መኪኖችን· የሚሸጡ· ነጋዴዎች· ታውቃለህ?	አዎ፤ አውቃለሁ።
የዚህ· ሱቅ· ከሌላ· ከዚያኛው· ይበልጣል?	አዎ፤ በአሥር· ብር· ይበልጣል።

ጥያቄ	መልስ
ሁለት፡ ውሾች፡ ብሰጥህ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ብር፡ ታበድረኛለህ?	እሺ፣ አበድርሃለሁ።
ዋስህ፡ ስንት፡ መቶ፡ ብር፡ ሊከፍል፡ ነው?	አንድ፡ መቶ፡ ብር፡ ሊከፍል፡ ነው።
መኪናው፡ ስንት፡ አወጣ?	ሁለት፡ ሺ፡ አምስት፡ መቶ፡ ብር፡ አወጣ።
ከባንክ፡ ስንት፡ ብር፡ እንዲወጣልህ፡ ትፈልጋለህ?	ሀያ፡ ብር፡ አውጣልኝ።
ቀጣሪው፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ገንዘብ፡ ከማን፡ ተበደረ?	ከባንክ፡ ተበደረ።
ባንኩ፡ ስንት፡ ገንዘብ፡ አበደረው?	የገንዘቡን፡ ቁጥር፡ በትክክል፡ አላውቅም።
ገንዘቡን፡ ሲበደር፡ ለባንኩ፡ ፈረመ?	እሺ፣ ፈረመ።
ለመሆኑ፡ መታወቂያ፡ ወረቀት፡ ቢኖርህ፣ በዋስ፡ ፋንታ፡ እሱን፡ መስጠት፡ ይቻላል?	እሺ፣ ይቻላል።
ገንዘብ፡ ከባንክ፡ ለመበደር፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ይፈጃል?	አንድ፡ ሳምንት፡ ይፈጃል።
የሰማን፡ ብዐር፡ ለካበዴ፡ አልሰጠኸውም?	የለም፣ አልሰጠሁትም።
እሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ለምን፡ መተኛት፡ አትፈልግም?	ምክንያቱም፡ እሆቴሉ፡ ውስጥ፡ መተኛት፡ ደስ፡ ስለማይለኝ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የነበረኽን፡ አንድ፡ ሳጥን፡ ብርጭቆ፡ ለማን፡ ሸጥኸው?	ገና፡ አልሸጥሁትም።
አስተማሪው፡ ጠመኔ፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ ይፈልጋል።
ቀጭን፡ መሆን፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ ቀጭን፡ መሆን፡ እፈልጋለሁ።
ቤቱን፡ በቁልፍ፡ ከፍተህ፡ ሳጥኑንና፡ ብርጭቆውን፡ አስገባኸው?	የለም፣ አላስገባሁትም። ምክንያቱም፡ ቁልፍ፡ አልነበረኝም።
ልብስሽን፡ የምትሰፊበት፡ መርፌ፡ አለሽ?	አሁን፡ የለኝም፤ ወደፊት፡ ግን፡ አገኝ፡ ይሆናል።
ሎሚ፡ ለመግዛት፡ ወደ፡ ገበያ፡ ማን፡ ይሄዳል?	የቶ፡ ተሰማ፡ ባለቤት፡ ትሄዳለች።
ሳሙና፡ ገዝተሽ፡ ሎሚውን፡ ማጠብ፡ ትፈልጊያለሽ?	የለም፣ ዛሬ፡ ወደ፡ ገበያ፡ መሄድ፡ አልችልም።
ከመታጠቢያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ምን፡ ታደርጋላችሁ?	ቆሻሻውን፡ ሎሚ፡ እናጥባለን።
ወደ፡ ገበያ፡ ስትሄድ፡ ምንም፡ ልትገዛልኝ፡ ትችላለህ?	ገንዘብ፡ የለኝም፡ እንጂ፡ እገዛልህ፡ ነበር።
ወፍራሙ፡ በሬ፡ የማነው?	ያቶ፡ ዮሐንስ፡ ፆመስከኛል።
ምንም፡ እንኳን፡ ደሀ፡ ቢሆን፡ ደግ፡ ሰው፡ አይመስልህም?	አዎ፣ በጣም፡ ደግ፡ ሰው፡ ነው።
የጥሩነሽና፡ የከማ፡ ወዳጅነት፡ ምሥጢሩ፡ ይገባሃል?	አዎ፣ ይገባኛል።
ከማ፡ ካገሩ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ለመተዋወቅ፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ ለመተዋወቅ፡ በጣም፡ ይፈልጋል።

ጥያቄ	መልስ
አገሬ፡ ገዢው፡ እንግዶችን፡ መጋበዝ፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፣ ይፈልጋሉ።
ያገሬ፡ ገዢው፡ ግብዣ፡ እንዴት፡ ነበር?	በጣም፡ ጥሩ፡ ነበር።
ሰውን፡ ማክበር፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነገር፡ አይመስልህም?	አዎ፣ በጣም፡ ጥሩ፡ ነገር፡ ነው።
አቶ፡ ለማን፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ታስነሳዋለህ?	ገሌት፡ ሰዓት፡ ገደማ፡ አስነሳዋለሁ።
መኪናውን፡ አስነስቶ፡ ወዴት፡ አገር፡ ሄደ?	ወዳዲስ፡ ከተማ፡ ሲነዳ፡ አየሁት።
የነበረህን፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ የት፡ አጠፋኸው?	ብዙ፡ ነገር፡ ገዛሁበት።
በድንገት፡ ከመኝታው፡ ይነሳል?	አዎ፣ አንዳንዴ፡ ይነሳል።
አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ትራፊክ፡ አለ?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ ትራፊክ፡ አለ።
እዚህ፡ በመጣህ፡ በማግሥቱ፡ የት፡ ሄደህ፡ ነበር?	ለማን፡ ለማየት፡ ወዳዲስ፡ ከተማ፡ ሄጄ፡ ነበር።
ልጅህን፡ ከልጄ፡ ጋር፡ እናስተዋውቃቸው?	በጣም፡ ጥሩ፡ ሃሳብ፡ ነው።
ይህ፡ ምግብ፡ ሁሉ፡ ዛሬ፡ ማታ፡ መበላት፡ አለበት?	አዎ፣ ሁሉም፡ ማለቅ፡ አለበት።
ወተቱስ፡ መጠጣት፡ አለበት?	ወተቱ፡ ገንድ፡ ቀን፡ መጨረስ፡ የለበትም።

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ ካልሄድህ፡ እንግዲያስ፡ መቼ፡ ትሄዳለህ?	ምናልባት፡ ነገ፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ጨለማ፡ የብርሃን፡ ተቃራኒ፡ እንደሆነ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
እዚህ፡ አገር፡ ብዙ፡ ሀብታም፡ ሰዎች፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ሀብታሞች፡ አሉ።
ገዢው፡ በጣም፡ ሀብታም፡ ሰው፡ ነው?	አዎ፣ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ አለው።
በጣም፡ ጌታ፡ ብትሆን፡ በገንዘብህ፡ ምን፡ ታደርግበታለህ?	አንድ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እሠራበታለሁ።
በለማና፡ በዮሐንስ፡ ፋንታ፡ ወደ፡ ካሊፎርኒያ፡ ማን፡ ማን፡ ሄዱ?	ያቶ፡ ከበደ፡ ሁለቱ፡ ልጆች፡ ሄዱ።
ቆሻሻውን፡ ከቤት፡ ማን፡ አወጣው?	ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አወጣችው።
ዛሬ፡ ቆሻሻ፡ ልብስህን፡ ታጥባለህ?	ምናልባት፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ አጥብ፡ ይሆናል።
ልብሴ፡ ንጹሕ፡ ነው?	አዎ፣ ልብስህ፡ ሁሉ፡ ንጹሕ፡ ነው።
እቤት፡ የነበረውን፡ ንጹሕ፡ ፎጣ፡ ማን፡ ወሰደው?	ልጆች፡ ወደ፡ ዋና፡ ይዘውት፡ ሄዱ።
ሀብታም፡ ሰው፡ በገንዘቡ፡ ምን፡ ያደርግበታል?	የፈለገውን፡ ነገር፡ ይገዛበታል።
አንድ፡ ሰው፡ ጌታ፡ ለመሆን፡ ቢፈልግ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልገዋል?	ቤትና፡ ቀን፡ መሥራትና፡ ገንዘብ፡ ማስቀመጥ፡ ያስፈልገዋል።
የጥሩነሽ፡ አባትና፡ እናት፡ ገብጋቦች፡ ናቸው?	አዎ፣ በጣም፡ ገብጋቦች፡ ናቸው።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ቤትህ፡ ለምን፡ በጨለማው፡ ሄድህ?	መሄድ፡ ግዴታዬ፡ ነበር።
እቤት፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ጨለማ፡ ነው?	የለም፣ በጣም፡ ጨለማ፡ አይደለም።
እቤቱ፡ በቂ፡ ብርሃን፡ አለው?	አዎ፣ አለው።
የጨለማ፡ ተቃራኒ፡ ምንድን፡ ነው?	የጨለማ፡ ተቃራኒ፡ ብርሃን፡ ነው።
የዋሽንግተን፡ ባንኮች፡ በመቶ፡ ስንት፡ ወለድ፡ ይሰጣሉ?	በመቶ፡ ሦስት፡ ወይም፡ አራት፡ ይሰጣሉ።
በመቶ፡ ሰባት፡ ወለድ፡ ትፈልጋለህ?	የለም፣ አልፈልግም።
አስተማሪያችሁ፡ ክፉ፡ ነው፣ ወይስ፡ ደግ?	በጣም፡ ደግ፡ ሰው፡ ነው።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የመኪናውን፡ ጎማ፡ ካስለወጡ፡ በኋላ፡ ትንሽ፡ ዘግይተው፡ እናቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ ደረሱ። እርሳቸው፡ እንደደረሱ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ደስታ፡ ሆነ። ከዚያ፡ በኋላ፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ከሌሎቹ፡ እንግዶች፡ ጋር፡ እንዲያስተዋውቋቸው፡ ነገሯቸው። አቶ፡ ዮሐንስም፡ እጃቸው፡ በጣም፡ ቆሽሾ፡ ስለ ነበር፣ ከመተዋወቃቸው፡ በፊት፡ መታጠብ፡ ፈለጉ። አቶ፡ ከበደም፡ ላቶ፡ ዮሐንስ፡ መታጠቢያ፡ ቤቱን፡ አሳይተው፡ ሳሙናና፡ ፎጣ፡ አቀረቡላቸው።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ እጃቸውን፡ ታጥበው፡ በፎጣ፡ ካደረቁ፡ በኋላ፡ ወደ፡ እንግዳ፡ ቤት፡ ሄደው፡ ከሌሎቹ፡ እንግዶች፡ ጋር፡ ተዋወቁ። ከዚያ፡ በኋላ፡ ምግብ፡ ቀረበላቸውና፡ ተመገቡ። እንግዳው፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ጊዜ፡ ነበራቸው።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስ፡ እናቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ ምን፡ ጊዜ፡ ደረሱ?

ከምን፡ ትንሽ፡ ዘግይተው፡ ደረሱ?

እሳቸው፡ እጥረው፡ ቦታ፡ እንደደረሱ፡ ምን፡ ሆነ?

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ላቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ ነገሯቸው?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ እጃቸውን፡ ከምን፡ መታጠብ፡ ፈለጉ?

አቶ፡ ከበደ፡ ላቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ አቀረቡላቸው?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ እጃቸውን፡ ታጥበው፡ ምን፡ አደረጉ?

እጃቸውን፡ በፎጣ፡ ካደረቁ፡ በኋላ፡ ምን፡ አደረጉ?

ከእንግዶቹ፡ ከተቀመጡ፡ በኋላ፡ ምን፡ ሠሩ?

እጥረው፡ ቤት፡ ውስጥ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ጊዜ፡ አሳለፉ?

ሀያ፡ ሰባተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

(ዮሐንስ፡ወደ፡እንግዳ፡ክፍል፡ይገባል፡)

እንግዶች

ኖር፡ (ይኑሩ)፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡

ዮሐንስ

ባእግዚአብሔር፡ በእግዚአብሔር፡ ይቀመጡ፤ ወይም፡ ይክበሩ።

ከበደ

እዚህ፡ያሉትን፡ሰዎች፡ ሁሉ፡ ያውቃሉ። የሆነው፡ ሆኖ፡ አቶ፡ ለማና፡ አቶ፡ ተሰማ፡ ከጓደኛም፡ አሁን፡ስለመጡ፤ ከእነሱ፡ ጋር፡ ላስተዋውቅዎት።

ዮሐንስ

እሺ፡

ከበደ

አቶ፡ ዮሐንስ፣ እርሳቸው፡ አቶ፡ ለማ፡ ይባላሉ። እርሳቸው፡ ደግሞ፡ አቶ፡ ተሰማ፡ ይባላሉ።

ዮሐንስ

እንደምን፡ ናችሁ፤ እንኳን፡ ደህና፡ ገባችሁ።

ለማና፡ ተሰማ

እንኳን፡ ደህና፡ ቆዩን።

ከበደ

አቶ፡ ዮሐንስ፡ምን፡ ዓይነት፡ መጠጥ፡ ልስጥዎት?

ዮሐንስ

ጠላ፡ ቢሰጡኝ፡ በጣም፡ ፍቃዴ፡ ነው።

ከበደ

በደስታ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ዮሐንስ፡መጥቶ፡ የት፡ ገባ?	ከመጣ፡ በኋላ፡ ወደ፡ እንግዳ፡ ክፍል፡ ገባ።

ጥያቄ	መልስ
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ እንግዳ፡ ክፍሉ፡ ሲገባ፡ እንግዶቹ፡ ምን፡ አሉት?	እንግዶቹ፡ ሁሉ፡ ኖር፡ አሉት።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ አለ?	አቶ፡ ዮሐንስ፡ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር፡ አለ።
ከጎጃም፡ የመጡትን፡ ሰዎች፡ ካቶ፡ ዮሐንስ፡ ጋር፡ ማን፡ አስተዋወቃቸው?	አቶ፡ ከበደ፡ አስተዋወቃቸው።
ከእንግዶቹ፡ ጋር፡ ከተዋወቀ፡ በኋላ፡ ምን፡ አላቸው?	እንኳን፡ በደህና፡ ገባችሁ፡ አላቸው።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ እንኳን፡ ደህና፡ ገባችሁ፡ ያለው፡ እነማንን፡ ነው?	ከጎጃም፡ የመጡትን፡ እንግዶች፡ ነው።
እንግዶቹ፡ እንኳን፡ ደህና፡ ቆያችሁ፡ ያሉት፡ ማንን፡ ነው?	አቶ፡ ዮሐንስን፡ ነው።
አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ምን፡ ጠየቀው?	ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ ትወዳለህ፡ ብሎ፡ ጠየቀው።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ መለሰ?	አቶ፡ ዮሐንስም፡ ጠላ፡ እፈልጋለሁ፡ ብሎ፡ መለሰ።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ ለምን፡ መጣ?	አቶ፡ ከበደን፡ ለመጠየቅ፡ መጣ።
አንድ፡ አምስት፡ ብር፡ የሚሆን፡ ልታበድረኝ፡ ትችላለህ?	የለም፥ ገና፡ ደሞዝ፡ አልተቀበልሁም።
ከውሾችህ፡ ክፉው፡ የትኛው፡ ነው?	ነጩ፡ ውሻዬ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
እቤት፡ ውስጥ፡ ለማንበብ፡ በቂ፡ ብርሃን፡ አለ?	አዎ፣ መስኮቱ፡ ሲከፈት፡ በቂ፡ ብርሃን፡ ታገኛለህ?
አንዳንድ፡ ለሊት፡ ወደ፡ ሆቴል፡ ትሄዳለህ?	አዎ፣ እሄዳለሁ።
የናንተ፡ ጠቅላይ፡ ገዢ፡ ማን፡ ናቸው?	አቶ፡ ለማ፡ ናቸው።
እናንተ፡ ሠፈር፡ ገደማ፡ ባንክ፡ አለ?	የለም።
ምንም፡ እንኳን፡ ወንድምህ፡ ባይኖር፡ ለምን፡ እኛን፡ አትጠይቀንም?	ጊዜ፡ ስለሌለኝ፡ ነው።
የባለቤትህ፡ ወላጆች፡ ባለጸጎች፡ ናቸው?	አዎ፣ በጣም፡ ሃብታሞች፡ ናቸው።
ድሆችን፡ በምን፡ ዓይነት፡ መንገድ፡ መርዳት፡ ይቻላል?	ሥራ፡ በመስጠት፡ መርዳት፡ ይቻላል።
ልብስህን፡ ወደ፡ መኪና፡ ሰፌ፡ ቤት፡ መውሰድ፡ ትፈልጋለህ?	የለም፣ አልፈልግም።
ቆሻሻ፡ ልብስህን፡ እንዲያጥብልህ፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ እፈልጋለሁ።
ለማ፡ ልብሱን፡ ዛሬ፡ ማጠብ፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ ይፈልጋል።
አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የት፡ ይተዋወቁ፡ ነበር?	በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ይተዋወቁ፡ ነበር።
ከግብዣው፡ በኋላ፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የት፡ ሄደ?	ተመልሶ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ሄደ።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰው፡ በመሆኑ፣ አቶ፡ ከበደ፡ አገር፡ ሊያላምደው፡ ፈለገ። አንድ፡ ቀን፡ ወደ፡ ቤቱ፡ መጥቶ፡ እንዲጋበዝ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ጠየቀው። አቶ፡ ዮሐንስም፡ በአቶ፡ ከበደ፡ ሃሳብ፡ ስለተስማማ፣ ግብዣውን፡ በደስታ፡ ተቀበለ።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ቤት፡ እንደደረሰ፡ እንግዶቹ፡ ሁሉ፡ በደስታ፡ ተቀበሉት። ወዲያው፡ ካቶ፡ ለማና፡ ካቶ፡ ተሰማ፡ ጋር፡ ከተዋወቀ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ተዘጋጀለት፡ ቦታ፡ ሄደ፡ ተቀመጠ።

ከዚያም፡ በኋላ፡ አቶ፡ ከበደ፡ የሚፈልገውን፡ መጠጥ፡ አቅርቦለት፡ መጠጣቸውን፡ እየጠጡ፡ ጨዋታቸውን፡ ጀመሩ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ከበደ፡ ምን፡ ፈለገ?

አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ ለመጋበዝ፡ ለምን፡ ፈለገ?

አቶ፡ ከበደ፡ አቶ፡ ዮሐንስን፡ የት፡ ጋበዘው?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ በምን፡ ተስማማ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለግብዣው፡ ወዴት፡ ሄደ?

አቶ፡ ዮሐንስን፡ እንግዶቹ፡ እንግዶቹ፡ እንዴት፡ ተቀበሉት?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከማን፡ ጋር፡ ተገናኘ?

አቶ፡ ከበደ፡ ላቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ አቀረበለት?

ኢትዮጵያዊ፡ ወዳጅ፡ አለህ?

በኢትዮጵያ፡ ቤተ፡ሰብ፡ ውስጥ፡ ለመጋበዝ፡ ትፈልጋለህ?

ሀያ፡ ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ተሰማ

አቶ፡ ዮሐንስ፣ እርስዎ፡ አሜሪካዊ፡ እንደሆኑ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ነገሩኝ። ስለዚህ፡ ትንሽ፡ ስላገርዎ፡ ለጠይቅ፡ እወዳለሁ።

ዮሐንስ

ለማወቅ፡ የሚፈልጉትን፡ ሁሉ፡ ልገልጽልዎ፡ ፈቃደኛ፡ ነኝ።

ተሰማ

ያሜሪካን፡ ወጣቶች፡ ሁሉ፡ እንደ፡ እርስዎ፡ ረዣዥሞች፡ ናቸው?

ዮሐንስ

የለም፣ ሁሉም፡ አይደሉም። ነገር፡ ግን፡ አብዛኛዎቹ፡ ረዣዥሞች፡ ናቸው።

ተሰማ

ያገሩ፡ ዓየር፡ እንዴት፡ ነው?

ዮሐንስ

ባንዳንድ፡ ቦታዎች፡ ዓየሩ፡ መጥፎ፡ ነው። ባብዛኛዎቹ፡ ግን፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።

ተሰማ

በአሜሪካን፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ተማሪዎች፡ ይገኛሉ?

ዮሐንስ

በውነቱ፡ ስንት፡ እንደሆኑ፡ አላውቅም። ዳሩ፡ ግን፡ በብዙ፡ ሚሊዮን፡ የሚቆጠሩ፡ ተማሪዎች፡ እንዳሉ፡ አምናለሁ።

ተሰማ

ሽማግሌ፡ ባልሆን፡ ኖር፡ ወዳሜሪካ፡ መሄድና፡ መማር፡ በወደድሁ፡ ነበር?

ዮሐንስ

ወንድ፡ ወይም፡ ሴት፡ ልጆች፡ እንዳሉዎ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መላክ፡ ይችላሉ።

ተሰማ

ልጆች፡ የሉኝም፤ ነገር፡ ግን፡ ትምህርት፡ መማር፡ በጣም፡ ጠቃሚ፡ መሆኑን፡ አስተውለዋለሁ።

ገቶክዩ፡ ስለ፡ እርሻና፡ ስለ፡ መድኃኒት፡ ደግሞ፡ ስለ፡ መሐንዲስነት፡ የሚያጠኑ፡ ሰዎች፡ በጣም፡ ይጠቀማሉ።

ጥሩነሽ

የሚበላ፡ ነገር፡ ተዘጋጅቷልና፡ ወደ፡ ምግብ፡ ቤት፡ እንሂድ።

ተሰማ

በጣም፡ ጥሩ፡ አሳብ፡ ነው። ካሉስ፡ ትንሽ፡ ርቦኛል።

ዮሐንስ

እኔም፡ እርቦኛል፡ ጠምቶኛልም።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ከተማ፡ ከመሄድ፡ ፈቃደኛ፡ ነህ?	ራሴን፡ አሞኛል፡ እንጂ፡ ከመሄድስ፡ ፈቃደኛ፡ ነበርሁ።
ሬጃጅም፡ ወንድሞች፡ አሉዎችሁ?	ሁሉም፡ ሬጃጅሞች፡ አይደሉም።
ርቦህ፡ እንደሆን፡ ሄደን፡ ምሳችንን፡ እንብላ?	መልካም፡ ርቦኛል፤ ግን፡ አሁን፡ ሥራ፡ አለብኝ።
መሐንዲስ፡ መሆን፡ ትወዳለህ?	አዎን፤ በጣም፡ እወዳለሁ።
ውሃ፡ ሲጠማን፡ ምን፡ እናደርጋለን?	ወደ፡ ሆቴል፡ ቤት፡ እንሄዳለን።
የርሻ፡ ትምህርት፡ በጣም፡ ጠቃሚ፡ ይመስላችኋል?	አዎን፤ በጣም፡ ጠቃሚ፡ ነው።
ከበደ፡ ለምን፡ በጊዜ፡ ሄደ?	ስለ፡ራበው፡ ራቱን፡ ሊበላ፡ ሄደ።
ራሳችሁን፡ አሟችኋል?	የለም፤ አላመመንም።
እግርህን፡ ቢያምህ፡ ምን፡ ታደርጋለህ?	አዲስ፡ መኪና፡ እገዛለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ሽማግሌ፡ አጎት፡ አሉሽ?	አዎን፣ አጎቴ፡ ሽማግሌ፡ ናቸው።
አገሩ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ወጣቶች፡ አሉ?	የለም፣ ወጣቶች፡ ብዙ፡ አይገኙም።
ተሰማ፡ ምን፡ አለህ?	ጠምቶኛል፡ አለኝ።
ሬጆጅም፡ ልጆች፡ ለምን፡ ወደዚህ፡ መጡ?	ሲኒማ፡ ለማየት፡ መጡ።
ወጣት፡ መሆን፡ ትወዳለህ?	እንደሌሎቹ፡ ሁሉ፡ ወጣት፡ መሆን፡ እወዳለሁ።
ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ለምን፡ ትፈልጋለህ?	አንድ፡ ለርሻ፡ የሚሆን፡ መሬት፡ ለመግዛት፡ አስቤአለሁ።
የሰማኸውን፡ ነገር፡ ልታምነው፡ ቻልህ?	ለማመን፡ አስቸገረኝ።
ኢትዮጵያን፡ ለማየት፡ ፈቃደኛ፡ ነህ?	አዎን፣ በጣም፡ ፈቃደኛ፡ ነኝ።
እርሻቸውን፡ ሲያስፋፉ፡ ጥሩ፡ ይመስልሃል?	አዎን፣ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
ልጅሽ፡ ምን፡ ይማራል?	መሐንዲስነት፡ ይማራል።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ መሐንዲሶች፡ አሉ?	ጥቂቶች፡ በየቦታው፡ ይገኛሉ።
ዮሐንስ፡ ለምን፡ ተኛ?	ታምሜአለሁ፡ ብሎ፡ ተኛ።
ብዙ፡ ብርጭቆ፡ ጠላ፡ ለምን፡ ጠጣ?	ውሃ፡ ስለጠማው፡ ነው።

ድርሰት

ግብዣ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የተለመደ፡ ነገር፡ ነው። በዓል፡ በሚሆንበት፡ ጊዜ፡ ሁሉ፤ ግብዣ፡ በየቤቱ፡ ወይም፡ በየሰፈሩ፡ ይደረጋል። የግብዣውም፡ ዓይነት፡ ባንዳንድ፡ ነገር፡ የተለያየ፡ ቢሆንም፤ በጠቅላላው፡ የተመሳሰለ፡ ነው።

አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ግብዣ፡ ትልቅ፡ ዝግጅትን፡ ይጠይቃል። ምክንያቱም፡ ጋባዦቹ፡ እንግዶቻቸውን፡ ለማስደሰት፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ ምግብና፡ መጠጥ፡ ስለሚያዘጋጁ፡ ነው።

የግብዣው፡ ጥሪ፡ ለተጋባዦቹ፡ ቀደም፡ ብሎ፡ ይነገራቸዋል። ጥሪው፡ የደረሳቸው፡ ሰዎችም፡ ልክ፡ በጥሪው፡ መሠረት፡ በተጠየቁበት፡ ቦታና፡ ሰዓት፡ መገኘት፡ ይገባቸዋል።

ግብዣው፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ እንግዶቹ፡ መምጣት፡ ሲጀምሩ፡ ባለቤቶቹ፡ ወጥተው፡ እንግዶቻቸውን፡ ይቀበላሉ።

የተለመደውን፡ ሰላምታ፡ ከተሰጣጡ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ማረፊያ፡ ቤት፡ እንዲሄዱ፡ ይጠየቃሉ። በተወሰነው፡ ሰዓት፡ ግብዣው፡ ሲጀመር፡ እንግዶቹ፡ ባንድነት፡ ምግብና፡ መጠጡን፡ መጋበዝ፡ ይጀምራሉ።

ብዙ፡ ጊዜ፡ ለግብዣው፡ የተዘጋጀው፡ ምግብና፡ መጠጥ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ከመሆኑ፡ የተነሳ፡ የግብዣው፡ ጊዜ፡ ረጅም፡ ነው።

ምግብ፡ እንደተፈጸመ፤ ጥቂት፡ ንግግር፡ ከተደረገ፡ በኋላ፡ ጭፈራ፡ ወይም፡ ዳንስ፡ ይጀመራል። በዚህ፡ ሰዓት፡ መኳንንትና፡ ወይዛዝርት፡ ከየሥፍራቸው፡ እየተነሱ፡ ይደንሳሉ። አንዳንድ፡ ጊዜም፡ ተጋባዦች፡ በመነጋገርና፡ ሐሳብ፡ በመከፋፈል፡ ብቻ፡ ሳይደንሱ፡ ይመለሳሉ። ዳንሱ፡ ከተፈጸመ፡ በኋላ፡ እንግዶቹ፡ ምሥጋናቸውን፡ እያቀረቡና፡ ባለቤቶቹን፡ እየተሰናበቱ፤ ወደየቤታቸው፡ ይሄዳሉ።

ጥያቄዎች

ግብዣ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ይጠይቃል?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ስለሚደረገው፡ ግብዣ፡ ተናገር።

አሜሪካዊያን፡ እንግዶቻቸውን፡ እንዴት፡ ይቀበላሉ?

ተጋባዦቹ፡ ግብዣው፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ የት፡ ያርፋሉ?

ግብዣው፡ ከተጀመረስ፡ በኋላ፡ ምን፡ ያደርጋሉ?

ተጋባዦች፡ በሰዓቱ፡ እግብዣው፡ ቦታ፡ ይመጣሉ?

ዳንስ፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ የሚደረገውን፡ አስረዳ።

በዳንሱ፡ ውስጥ፡ እንግዶቹ፡ ምን፡ እንደሚያደርጉ፡
በጠቅላላው፡ ግለጽ።

ዳንስ፡ መደነስ፡ ያውቃሉ?

ከዚህ፡ በፊት፡ ኢትዮጵያዊ፡ ቤት፡ ተጋብዘው፡ ነበር?

ሀያ፡ ዘጠነኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ለማ

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፤ ካገርሽ፡ መቼ፡ መጣሽ?

ጥሩነሽ

እንደ፡ ሳምንት፡ ያህል፡ ሆኖኛል። አንተስ?

ለማ

እኔ፡ ረጅም፡ ጊዜ፡ ሆኖኛል። ለመሆኑ፡ የኔን፡ ወላጆች፡ ታውቂያቸዋለሽ?

ጥሩነሽ

እንዴታ፣ ለምን፡ አላውቃቸውም። እንዲያውም፡ ያንተና፡ የኔ፡ ወላጆች፡ በጣም፡ የተቀራረቡ፡ ወዳጆች፡ መሆናቸውን፡ ረሳህ?

ለማ

ዘንግቼው፡ ነው። ለመሆኑ፡ ከተማው፡ እየተሻሻለ፡ ሄዶአል?

ጥሩነሽ

አዎ፣ በጣም፡ እንጂ። የምታውቃቸው፡ አሮጌ፡ ቤቶች፡ ሁሉ፡ ፈርሰው፡ አዳዲስ፡ ቤቶች፡ ተሠርተዋል።

ለማ

በትምህርት፡ ቤታችን፡ አጠገብ፡ የነበረው፡ ቆንጆ፡ ሰፈር፡ ፈርሶአል?

ጥሩነሽ

አዎ፣ እሱ፡ ፈርሶ፡ ለተማሪዎች፡ መጫወቻ፡ ሜዳ፡ ሆኖአል።

ለማ

የከተማው፡ መንገዶች፡ አሁን፡ ንጹሕ፡ ሆነዋል?

ጥሩነሽ

አዎ፣ ጨለማ፡ የነበሩት፡ መንገዶች፡ በኤሌትሪክ፡ ብርሃን፡ አጊጠዋል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ እንዳተኛ፡ ማን፡ ነገረህ?	ወንድሜ፡ ነገረኝ።
ለከበደ፡ አንድ፡ ሳጥን፡ እንቁላል፡ እንደሰጠሁት፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ጠመኔ፡ የት፡ እንዳለ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
አባትና፡ እናትዎ፡ ከእኔ፡ ጋር፡ እንደሚኖሩ፡ ነገርሃት?	አዎ፣ ነገርሁዎት።
ፎጣውን፡ መቼ፡ እንዲያጥበው፡ ትፈልጋለህ?	አሁን፡ እንዲያጥበው፡ እፈልጋለሁ።
ልብሱ፡ በጣም፡ ንጹህ፡ እንዲሆን፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ በጣም፡ ንጹህ፡ ይሁን።
እዚህ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ደሃ፡ ሰው፡ እንዳለ፡ ማወቅ፡ የሚፈልግ፡ ማን፡ ነው፧	አቶ፡ ከበደ፡ ነው።
ሳይነግርህ፡ በድንገት፡ እንዲመጣ፡ ትፈልጋለህ?	የለም፣ አልፈልግም።
መኪናይን፡ እንዲነዳው፡ ትፈቅድለታለህ?	አዎ፣ እፈቅድለታለሁ።
እጁን፡ በፎጣ፡ እንዲያደርቅ፡ ነገርኸው?	አዎ፣ ነገርሁት።
አባትዎ፡ ሰፊ፡ እርሻ፡ እንዳለው፡ ከየት፡ ሰማችሁ?	ወንድሜ፡ ነገረኝ።
ወፍራም፡ እንደሚሆን፡ ታውቅ፡ ነበር?	አዎ፣ አውቅ፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
እንደሚመጣ፡ ነግሮሃል?	አዎ፣ ነግሮኝ፡ ነበር።
ወዳገሩ፡ ሊመለስ፡ እዚህ፡ እንደሚያርፍ፡ ነገረህ?	አዎ፣ ነገረኝ።
ቀለሙን፡ እንዲያመጣው፡ ነገርኸው?	የለም፣ አልነገርሁትም።
ምግቡን፡ የት፡ እንዲበላ፡ ትፈልጋለህ?	እዚህ፡ እንዲበላ፡ እፈልጋለሁ።
አባትና፡ እናትህ፡ እንደሚመጡ፡ ትነግረዋለህ?	አዎ፣ እነግረዋለሁ።
ሬዲውን፡ ከጠረጴዛ፡ ላይ፡ እንዲያስቀምጠው፡ ነገርኸው?	አዎ፣ ነገርሁት።
ፊቱን፡ በሳሙና፡ እንዲታጠብ፡ ልንገረው?	አዎ፣ ንገረው።
በድንገት፡ እንደመጣ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ እንደመጣ፡ አውቃለሁ።
ብርሃን፡ ቢሆን፡ ወደ፡ ቤትህ፡ ትሄዳለህ?	አዎ፣ እሄድ፡ ይሆናል።
ሽማግሌው፡ ከቤት፡ እንደገባ፡ ቡና፡ ሰጠኸው?	አዎ፣ ሰጠሁት።
ሰውዬው፡ እንደገባ፡ መደነስ፡ ጀመረ?	የለም፣ አልጀመረም።
ጥሩነሽ፡ እዚህ፡ እንዳለች፡ ጠየቃችኋት?	አዎ፣ ጠየቅናት።
አልማዝን፡ አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ እንዳያችኋት፡ ለጌታዎ፡ ነገራችሁት?	አዎ፣ ነገርነው።

ጥያቄ	መልስ
ተማሪዎች፡ እንዲመጡ፡ ትመኛለህ?	አዎ፣ እመኛለሁ።
ገንዘብ፡ እንዳገኛችሁ፡ የት፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ወደ፡ ካናዳ፡ መሄድ፡ እንፈልጋለን።
ከአዲስ፡ አበባ፡ መቼ፡ ተመለስክ?	ለማን፡ እንዳየሁት፡ ተመለስኩ።
ሰዎችን፡ መቼ፡ አያችኋቸው?	ማረፊያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ እንደገቡ፡ አየናቸው።
ሥራችሁን፡ እንደፈጸማችሁ፡ ቡና፡ ትጠጣላችሁ?	አዎ፣ እንጠጣለን።
ተማሪዎች፡ ቡና፡ እንደቆሙ፡ ጠጡ?	አዎ፣ እንደቆሙ፡ ጠጡ።
ልጆቹ፡ ካባታቸው፡ እንደተሰናበቱ፡ የት፡ ሄዱ?	ወደ፡ እናታቸው፡ ሄዱ።
አሮጌው፡ መኪና፡ እጋራዥ፡ ውስጥ፡ እንዳለ፡ አዲስ፡ መኪና፡ ገዛ?	አዎ፣ ገዛ።
ገንዘብ፡ ያላገኘህበት፡ ምክንያት፡ ምንድን፡ ነው?	ስላልሠራሁ፡ ነው።
የለማን፡ ወንጆች፡ የምትጠይቅበት፡ ምክንያት፡ ለምንድን፡ ነው?	ጠይቅልኝ፡ ስላለኝ፡ ነው።
ወንድምህ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ የሄደበት፡ ምክንያቱ፡ ለምንድን፡ ነው?	ምክንያቱ፡ ትምህርት፡ ስለፈለገ፡ ነው።
ትናንት፡ ማታ፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ ለምን፡ ሄዳችሁ?	መደነስ፡ ስለፈለግን፡ ነው።
አስተማሪው፡ ትናንት፡ ለምን፡ አል መጣም?	ምክንያቱ፡ ስለዘነጋው፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ቤት፡ የመጣችሁበት፡ ምክንያት፡ምንድን፡ ነው?	ምክንያቱ፡ እናቱን፡ ለማየት፡ ስለፈለግን፡ ነው።
ለምን፡ እቤት፡ አልገባህም?	ጨለማ፡ ስለሆነ፡ ነው።
ለማና፡ ገለቤቱ፡ ለምን፡ አብረው፡ አልመጡም?	ምክንያቱ፡ ስለተለያዩ፡ ነው።
መኪናህን፡ ለምን፡ ቀይ፡ ቀለም፡ ቀባሃት?	ቀይ፡ ቀለም፡ ስላስደሰተኝ፡ ነው።
አስተማሪውን፡ ለምን፡ ትፈልጋላችሁ?	ምክንያቱ፡ መሰናበት፡ ስለፈለግን፡ ነው።
አሜሪካዊያን፡ አማርኛ፡ ለምን፡ ይማራሉ?	ምክንያቱ፡ በጣም፡ ጠቃሚ፡ ስለሆነ፡ ነው።
አሁን፡ ወደ፡ ሆቴሉ፡ መሄድ፡ ለምን፡ ትፈልጋላችሁ?	ምሳ፡ ለመብላት፡ ስለፈለግን፡ ነው።
አሁን፡ ወደ፡ቤታችሁ፡ መሄድ፡ የፈለጋችሁ፡ ለምንድን፡ ነው?	ምክንያቱ፡ ሥራችንን፡ ስለፈጸምን፡ ነው።
ብዙ፡ ተማሪዎች፡ ለምን፡ ስለ፡ እርሻና፡ ስለ፡ መሐንዲስነት፡ ይማራሉ?	በጣም፡ ጠቃሚ፡ ስለሆነ፡ ነው።
እነዚህ፡ ሰዎች፡ ለምን፡ እዚህ፡ መጡ?	ስለተጋበዙ፡ ይመስለኛል።

ድርሰት

አቶ፡ ለማና፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ በተለያዩ፡ በሁለት፡ ዓመታቸው፡ ዋሽንግተን፡ ውስጥ፡ ስለተገናኙ፡ በጣም፡ ደስ፡ አላቸው። አቶ፡ ለማም፡ ወዳጆቹን፡ በጣም፡ ስለሚወዷቸውና፡ ስለጤንነታቸው፡ ማወቅ፡ ስለፈለጉ፡ ወዲያውኑ፡ ስለነሱ፡ ጠየቃት። እሷም፡ ከመነሳትዋ፡ በፊት፡ እንደጠየቋቸውና፡ ደብዳቤም፡ እንደመጣችላት፡ ነገሯቸው። አቶ፡ ለማ፡ በጣም፡ ደስ፡ አላቸውና፡ ስለሌላ፡ ነገር፡ መጠየቅ፡ ጀመሩ። ከጥያቄዎች፡ አንዱ፡ ስላገሩና፡ ሕዝቡ፡ ኑሮ፡ መሻሻል፡ ነበር። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ በጣም፡ እንደተሻሻለ፡ ስትነግረው፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለ፡ ደስታ፡ ተሰማው። አቶ፡ ለማም፡ እንደኛ፡ አገር፡ ለማሻሻል፡ ከባድ፡ ሸክም፡ መሆኑን፡ ስለሚያውቁ፡ ሃላፊነቱን፡ የወሰዱትን፡ ሰዎች፡ በጣም፡ አመሰገናቸው። ወይዘሮ፡ ጥሩነሽም፡ በምሥጋናው፡ ተስማማች።

ከዚያ፡ በኋላ፡ ሁለቱም፡ ወዳገራቸው፡ ተመልሰው፡ ሕዝባቸውን፡ ለማገልገል፡ ግዴታቸው፡ መሆኑን፡ ተነጋገሩና፡ ለማታ፡ ሂሳቡን፡ ሆቴል፡ ድረስ፡ ተቀጣጥረው፡ ተለያዩ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ለማና፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ከየት፡ አገር፡ ናቸው?

አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መቼ፡ መጣ?

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽስ፡ መቼ፡ መጣች?

ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ የት፡ አረፈች?

ሁለቱ፡ ሰዎች፡ ስለምን፡ ተጨዋወቱ?

አቶ፡ ለማ፡ በመጀመሪያ፡ ስለምን፡ ጠየቁት?

ጥሩነሽ፡ ላቶ፡ ለማ፡ ምን፡ አመጣችለት?

ሁለተኛ፡ ጊዜ፡ ምን፡ ጠየቁት?

እሷስ፡ ምን፡ መልስ፡ ሰጠችው?

ስላገሩና፡ ሕዝቡ፡ መሻሻል፡ ምን፡ ነገረችው?

ወደ፡ አገራቸው፡ ተመልሰው፡ ምን፡ መሥራት፡ ይፈልጋሉ?

አቶ፡ ለማና፡ ጥሩነሽ፡ ለመገናኘት፡ ቀጠሮ፡ የት፡ አደረጉ?

አቶ፡ ለማ፡ ወይዘሮ፡ ጥሩነሽን፡ ከጠየቁት፡ ጥያቄዎች፡ አንዱ
ምን፡ ነበር?

ለጥያቄው፡ ምን፡ መልስ፡ ሰጠችው?

ሠላሳኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

እባክህ፡ ወንድሜ፣ የዚህ፡ ቦታ፡ ስም፡ ማን፡ ይባላል?

ከበደ

አዋሽ፡ ይባላል።

ጆን

በከተማው፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይኖሩበታል?

ከበደ

አዎ፣ የሰው፡ ቁጥር፡ በርከት፡ ያለ፡ ነው።

ጆን

እባክህ፡ የመኪናችን፡ ጎማ፡ ተንፍሶ፡ ነበርና፣ የት፡ ማስነፋት፡ እንችላለን?

ከበደ

ከዚህ፡ ትንሽ፡ ራቅ፡ ብሎ፡ አንድ፡ ትልቅ፡ ጋራዥ፡ አለ። ደግሞም፡ አንድ፡ የመኪና፡ ጎማ፡ የሚነፋና፡ ትንንሽ፡ ነገሮችን፡ የሚያድስ፡ ከዚህ፡ ቤት፡ ጋር፡ አለ።

ሜሪ

መጀመሪያ፡ የምናርፍበት፡ ቦታ፡ ማግኘት፡ ደህና፡ አይመስልህም፣ ጆን?

ጆን

አዎ፣ እውነትሽን፡ ነው። አቶ፡ ከበደ፣ ደህና፡ ምግብና፡ መኝታ፡ ቤት፡ ያለው፡ ሆቴል፡ የት፡ ይገኛል?

ከበደ

ከከተማው፡ መካከል፡ ወይስ፡ ከዚህ፡ ሰፈር፡ ይፈልጋሉ?

ጆን

ቢቻል፡ ከዚህ፡ ሰፈር፡ ቢሆን፡ አይከፋም።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ከቤቱ፡ ጋር፡ ጥሩ፡ መጫወቻ፡ ሜዳ፡ አላችሁ?	አዎ፣ ከተማሪዎቹ፡ የተሠራ፡ አለ።
አሮጌዎቹ፡ ቤቶች፡ መፍረስ፡ አለባቸው?	አዎ፣ መፍረስ፡ አለባቸው።
በንጽሕና፡ ትምህርት፡ በኩል፡ ይተባበራሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ይተባበራሉ።
ጤንነትዎ፡ ከትናንትና፡ ዛሬ፡ እንዴት፡ ነው?	ዛሬ፡ በጣም፡ ደህና፡ ነኝ።
ከዚህ፡ ወደ፡ አገርዎ፡ መቼ፡ መነሣት፡ ይፈልጋሉ?	ከአንድ፡ ሳምንት፡ በኋላ፡ እነሣለሁ።
ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ መተማከር፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፣ እፈልጋለሁ።
ለጂህና፡ እንዴት፡ ትመሰግናላችሁ?	በጣም፡ እንመሰግናለን።
የትምህርት፡ ቤቱን፡ ኃላፊነት፡ ወሰድህ?	አዎ፣ ወሰድሁ።
ወደ፡ ኒውዮርክ፡ መቼ፡ መነሣት፡ ትፈልጋላችሁ?	ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ እንነሣለን።
መቼ፡ ትመለሳላችሁ?	በማግስቱ፡ እንመለሳለን።
ከዚህ፡ ገደማ፡ ሆቴል፡ አለ?	አዎ፣ ሁለት፡ ጥሩ፡ ሆቴሎች፡ አሉ?
ስለ፡ አሁን፡ የመንግሥቱ፡ ሕግ፡ ያውቃሉ?	በውነቱ፡ አላውቅም።

ጥያቄ	መልስ
እንዴ·ገብረው·በጣም·ሃብታም·ነው?	አዎ፣ በጣም·ሃብታም·ነው።
ማንኞቹና·ዘፋኙ·ጋር·መተዋወቅ·ያስፈልግሃል?	አዎ፣ ያስፈልገኛል።
እጠብቁ·ቤት·ውስጥ·ስንት·ተቀመጥሁ?	ወርሃን·ለስለስ·ነው።
ራስ·ሆቴል·ገደማ·ሌላ·ሆቴል·ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ትናንትና·ከነባለቤታቸው·ቦታ·ሄዳችሁ·ነበር?	አዎ፣ ሄደን·ነበር።
ከሐኪሙ·ጋር·የቀረበው·ማን·ነው?	ወንድሙ·ነው።
ዛሬ·ለምሳ·የጋበዝሁትን·ሰው·ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቀውም።
እዚህ·አገር·የመጣሁ·በድንገት·ነው?	የለም፣ በድንገት·አይደለም።
ከትምህርት·ሚኒስትሩ·ጋር·ተዋወቃችሁ?	አዎ፣ ተዋወቅን።
የዚህ·መደብር·መንገድ·ትፈልጋለህ?	የለም፣ አልፈልግም።
በቀን·ጊዜው·ያደረገው·ማን·ነው?	የኔ·ጓደኛ·ነኝ።
ወደ·ኒውዮርክ·ለመሄድህ·ደስ·አለህ?	አዎ፣ በጣም·ደስ·አለኝ።
ቀድሞ·ብሎ·የመጣው·የማን·ሽጉጥ·ነው?	የሠራተኞቹ·ሽጉጥ·ነው።

ጥያቄ	መልስ
ቆም፡ ብላ፡ ጋዜጣ፡ የምታነበው፡ ሴት፡ ማን፡ ናት?	አስተማሪያችን፡ ናት።
ከመጽሐፍ፡ ቤት፡ ፈጠን፡ ብላችሁ፡ ወጥታችሁ፡ ምን፡ ሠራችሁ?	ካስተማሪያችን፡ የምስጋና፡ ደብዳቤ፡ ጻፍን።
ለማ፡ ጠጋ፡ ብሎ፡ ምን፡ ነገረሽ?	ራበኝ፡ ብሎ፡ ነገረኝ።
መሐንዲሶቹ፡ ከሐኪሞቹ፡ ራቅ፡ ብለው፡ ተቀመጡ?	የለም፣ አብረው፡ ተቀመጡ።
ሠራተኞቹ፡ በርከት፡ ብለው፡ ቢመጡ፡ ሥራውን፡ ዛሬ፡ የምትጨርሱት፡ ይመስላችኋል?	ምናልባት፡ እንጨርሰው፡ ይሆናል።
እዚህ፡ ቤት፡ ለመሥራት፡ ደስ፡ አለው?	አዎ፣ በጣም፡ ደስ፡ አለው።
ፈጠን፡ ብላ፡ ሄዳ፡ ምን፡ ይዛ፡ መጣች?	ምንም፡ ይዛ፡ አልመጣችም።
ነጋዴዎቹ፡ በስንት፡ ሰዓት፡ መጡ?	ከሰዓቱ፡ ቀደም፡ ብለው፡ መጡ።
ቆም፡ ብለሽ፡ ተናገርሽ?	አዎ፣ ቆም፡ ብዬ፡ ተናገርሁ።
ካባቱና፡ ከናቱ፡ ጋር፡ ይናፈሳል?	የለም፣ ትንሽ፡ ራቅ፡ ብሎ፡ ብቻውን፡ ይናፈሳል።
ቀደም፡ ብሎ፡ ከነጋዴን፡ ሸክም፡ ወሰደ?	የለም፣ አልወሰደም።
ቀደም፡ ብላ፡ ከማን፡ ጋር፡ ተቀጣጠረች?	ከወንድሟ፡ ጋር፡ ተቀጣጠረች።

ጥያቄ	መልስ
ቁጭ፡ ብሎ፡ ምን፡ አየ?	ምንም፡ አላየም።
ገንዘቡን፡ ከየሰንበቱ፡ ሊሰጠው፡ ፕሬዚዶ፡ ምን፡ አሉኝ?	መለስ፡ ብሎ፡ እፎታው፡ ሄዱኝ።
ቁጭ፡ ብሎ፡ ግቢህ፡ በኋላ፡ ምን፡ አለህ?	ነገ፡ ከመጣሁ፡ ብሎ፡ ሄደ።
ቀድሞ፡ ብላችሁ፡ ሄዳችሁ፡ ምን፡ ትሠራላችሁ?	ወደ፡ ሊረዳ፡ ብቻ፡ እንሄዳለን።
ጸሉ፡ ብሎኛል፡ ብሎ፡ የነገረህ፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?	ያጎቱ፡ ልጅ፡ ናት።
ራቅ፡ ብሎ፡ የተቀመጠውን፡ ሰው፡ ታውቀዋለህ?	አዎ፣ አውቀዋለሁ።
ጠጋ፡ ብለው፡ ቢያናግሩህ፡ ትሰማለህ?	አዎ፣ እሰማለሁ።
የብርቱካን፡ ጭማቂውን፡ ራቅ፡ አድርጎ፡ ያስቀመጠው፡ ማን፡ ነው?	ከማ፡ ነው።
እከጋው፡ ጎዶ፡ ቁጭ፡ ብሎ፡ ምን፡ ያደርጋል?	አማርኛ፡ መጽሐፍ፡ ያነባል።
ከጥሩነሽ፡ ቀረብ፡ ብለህ፡ ነገርካት?	አዎ፣ ቀረብ፡ ብዬ፡ ነገርሁዋት።
ይህን፡ ወረቀት፡ ነገር፡ ሄዶ፡ አድርጎ፡ የሰጣችሁ፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ከማ፡ ነው።
ትንሽ፡ አረፍ፡ ጠጭ፡ ማድረግ፡ ትፈልጋለህ?	ካገኘሁ፡ ደስ፡ ይለኛል።
እርሷ፡ ለትያ፡ ቀድሞ፡ ብላ፡ መጣች?	አዎ፣ ቀድሞ፡ ብላ፡ መጣች።

ጥያቄ	መልስ
ያቺ፡ ከሚ፡ ልጅ፡ ገና፡ ብዙ፡ ምን፡ ነገረቻችሁ?	እናትዎን፡ ከማየት፡ መሄዷን፡ ነገረችኝ።
አዲሱን፡ ልብስ፡ ለብሶ፡ አድርጎ፡ የት፡ ሊሄድ፡ ይፈልጋል?	ወደ፡ ሥራው፡ ሊሄድ፡ ይፈልጋል።
እጁን፡ ታጥቦ፡ አድርጎ፡ ምን፡ ሊሠራ፡ ነው?	ምሳውን፡ ሊበላ፡ ነው።
ወደ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ መቼ፡ መሄድ፡ ትፈልጋለህ?	ቡናዬን፡ ጠጥ፡ አድርጌ፡ እሄዳለሁ።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስና፡ ወይዘሮ፡ ማሬ፡ ኢትዮጵያን፡ በመኪናቸው፡ እየዞሩ፡ ለማየት፡ ተስማሙ። ወይዘሮ፡ ማሬ፡ ለጉዞአቸው፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ አስቀድማ፡ ማዘጋጀት፡ ጀመረች። አቶ፡ ዮሐንስም፡ በበኩሉ፡ ሥራውን፡ ጨርሶ፡ ለጉዞው፡ ተዘጋጀ።

ዝግጅቱ፡ ካለቀ፡ በኋላ፣ ዕቃቸውን፡ በመኪናቸው፡ ጭነው፡ ወደ፡ አዋሽ፡ ጉዞአቸውን፡ ጀመሩ። አዋሽ፡ ከተማ፡ እንደደረሱ፡ የመኪናቸው፡ ጐማ፡ በድንገት፡ ተነፈሰባቸው። የተነፈሰውን፡ ጐማ፡ ለማስጠገን፡ ወደ፡ አንድ፡ ትንሽ፡ ጋራዥ፡ ለመሄድ፡ ፈለጉ።

በመንገዳቸው፡ ላይ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ስለትንሿ፡ ጋራዥ፡ የሚገኝበትን፡ ቦታ፡ ጠየቁት። አቶ፡ ከበደም፡ በቀጥታ፡ ወደ፡ ጋራዡ፡ ስለመሯቸው፡ መኪናቸውን፡ ወስደው፡ ጐማውን፡ አስነፉ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ የሐንስና፡ ወይዘሮ፡ ማሬ፡ ምን፡ ለማየት፡ ተስማሙ?

ወይዘሮ፡ ማሬ፡ ምን፡ አዘጋጁ?

አቶ፡ የሐንስ፡ ምን፡ አደረጉ?

ከዝግጅቱ፡ በኋላ፡ ምን፡ አደረጉ?

ዕቃቸውን፡ በምን፡ ጫኑ?

በመኪናቸው፡ ወዴት፡ ሄዱ?

አዋሽ፡ ከተማ፡ ሊደርሱ፡ ምን፡ ነገር፡ አገኛቸው?

ጎማቸውን፡ከማሳለስ፡ወዴት፡ ሄዱ?

በመንገዳቸው፡ ላይ፡ ማንን፡ አገኙ?

አቶ፡ ከበደን፡ ምን፡ ጠየቁት?

በመጨረሻ፡ ምን፡ አደረጉ?

በመኪና፡ መጓዝ፡ ትወዳለህ?

ሠላሳ፡ አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

ከነገርኋችሁ፡ ገሬዥ፡ አጠገብ፡ ደህና፡ ሆቴል፡ አለ።

ሜሪ

እሱ፡ ከሁሉም፡ የተሻለ፡ ነው። ለመሆኑ፡ በቀን፡ ስንት፡ ያስከፍላል?

ከበደ

ለመኝታ፡ ቤቱ፡ በቀን፡ ሦስት፡ ብር፡ ከሃምሳ፡ ሳንቲም፡ ይመስለኛል። ለምግብ፡ ግን፡ አላውቅም።

ጆን

ላንድ፡ ቀን፡ ምንም፡ አይደለ። ታክሲ፡ እንጥራና፡ እንሂድ።

ከበደ

ተሸካሚ፡ ካልተገኘ፡ በስተቀር፡ ገዋሽ፡ ውስጥ፡ ታክሲ፡ አይገኝም።

ጆን

የኔ፡ ወንድም፣ እስቲ፡ እባክህ፡ ተሸካሚ፡ ጥራልን።

ከበደ

ስንት፡ ተሸካሚዎች፡ ትፈልጋላችሁ?

ሜሪ

ሁለት፡ ይበቃሉ። የቀረውን፡ እኛ፡ በጃችን፡ እናንጠለጥለዋለን። በዚህ፡ ሳጥን፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ነገር፡ ተሰባሪ፡ ስለሆነ፣ ተጠንቅቀሁ፡ ተሸከመው።

ሜሪ

ዕቃውን፡ አውርደና፡ ካልጋው፡ ግርጌ፡ አስቀምጠው።

ጆን

ስንት፡ ልክፈላችሁ?

ተሸካሚ

በጠቅላላው፡ ሁለት፡ ብር፡ ከሃምሳ፡ ሳንቲም፡ ነው።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ደግ፡ ሰው፡ ነው፡ ያልኸው፡ ማንን፡ ነበር?	የወይዘሪት፡ አልማዝን፡ እናት፡ ነበር።
ከገንዘብ፡ ሚኒስቴሩ፡ ስልክ፡ ከደወለ፡ በኋላ፡ ምን፡ አለ?	ሚኒስትሩን፡ አገኘሁ፡ አለ።
በጥሩነሽ፡ ፈንታ፡ ፎርሙን፡ ከመፈረም፡ የፈቀደ፡ ማን፡ ነው?	የጥሩነሽ፡ ባለቤት፡ ነው።
ፈጠን፡ ብለህ፡ ከፎቁ፡ ላይ፡ ፎጣና፡ ሳሙና፡ ልታመጣልን፡ ትችላለህ?	አዎ፣ ላመጣላችሁ፡ እችላለሁ።
ጋዜጣ፡ የሚጽፉትን፡ ሰዎች፡ ግብዣ፡ የጋበዝህ፡ አንተ፡ ነህ?	አዎ፣ እኔ፡ ነኝ።
በግንቦት፡ ወር፡ ደሞዙ፡ ከገበያ፡ ምን፡ ነገር፡ ገዛ?	በግማሹ፡ የመኪና፡ ጐማ፡ ገዛ። በግማሹ፡ ግን፡ ምን፡ እንደገዛበት፡ ገና፡ አልገለጸልኝም።
ከጎኔ፡ ተቀምጦ፡ እንጀራ፡ በወጥ፡ የበላው፡ ማን፡ ነው?	በውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ የሚሠራው፡ ሰው፡ ነው።
ባለጸጋ፡ ባልንጀራ፡ አለህ?	የለም፣ የኔ፡ ባልንጀሮች፡ ሁሉ፡ ደሆች፡ ናቸው።
የገንዘብ፡ ብድር፡ የምትጠይቅ፡ ምን፡ ለመግዛት፡ ነው?	አንድ፡ በሬና፡ ሁለት፡ ላሞች፡ ለመግዛት፡ ነው።
ዛሬ፡ ቼካችሁን፡ ተቀብላችሁ፡ ምን፡ ታደርጋላችሁ?	መንዝረን፡ አዳዲስ፡ ዕቃዎች፡ እንገዛበታለን።

ጥያቄ	መልስ
መኪናህን፡ የትኛው፡ ጋራዥ፡ ውስጥ፡ አስገብተህ፡ ትሄዳለህ?	ባንት፡ ቤት፡ አጠገብ፡ ባለው፡ ጋራዥ፡ ውስጥ፡ አስገብቻት፡ እሄዳለሁ።
ላሳላፊው፡ ስንት፡ ሳንቲም፡ ጉርሻ፡ ሰጠኸው?	አሥራ፡ አምስት፡ ሳንቲም፡ ሰጠሁት።
ጉንፋን፡ ሲይዝህ፡ ምን፡ ታደርጋለህ?	ወደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ እሄዳለሁ።
ለማ፡ በየጊዜው፡ እየመጣ፡ ይጎበኛችኋል?	አዎ፣ ሁልጊዜ፡ ሐሙስ፡ ሐሙስ፡ እየመጣ፡ ይጎበኘናል።
ብድሩን፡ መቼ፡ ትከፍለኛለህ?	እሁድ፡ እከፍልሃለሁ።
እመቤትህ፡ ካሜሪካ፡ ብዙ፡ ነገር፡ መግዛት፡ ትፈልጋለች?	አዎ፣ መግዛት፡ ትፈልጋለች።
ከዚህ፡ አገር፡ የመጣኸው፡ የኢኮኖሚ፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ ነው?	የለም፣ የመሐንዲስነት፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ ነው።
ዳቦና፡ ፓስታ፡ ሹታ፡ ለመብላት፡ ትፈልጋለህ?	እንጀራ፡ በወጥ፡ እንጂ፡ ሌላ፡ አልፈልግም።
አከፍላለሁ፡ ያልኸውን፡ ገንዘብ፡ ለባለሱቁ፡ ከፈልኸው?	ወደፊት፡ እከፍለዋለሁ፡ እንጂ፡ ከዚህ፡ በፊት፡ አልከፈልሁትም።
እህትህ፡ ወደ፡ ቤትዋ፡ የሄደችው፡ በእግርዋ፡ ነው?	የለም፣ በለማ፡ መኪና፡ ነው።
ለቁርስ፡ እንቁላል፡ የበሉ፡ እነማን፡ ናቸው?	ለማ፡ ከነወንድሞቹ፡ ነው።
ዛሬ፡ ጥዋት፡ እርሻው፡ ውስጥ፡ ምን፡ ይሠሩ፡ ነበር?	አበባዎችና፡ ዛፎች፡ ይተክሉ፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከፍተኛው፡ ተራራ፡ ማን፡ ይባላል?	ራስ፡ ዳሽን፡ ይባላል።
ቀን፡ ኮከብ፡ ማየት፡ ይቻላል?	የለም፣ አይቻልም።
እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ አለ?	አዎ፣ ሁለት፡ ከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ።
ዛሬ፡ ቀጠሮህ፡ ከማን፡ ጋር፡ ነው?	ካንዲት፡ ቆንጆ፡ ልጃገረድ፡ ጋር፡ ነው፡
መሥሪያ፡ ቤታችሁ፡ ሌላ፡ ቅርንጫፍ፡ አለው?	አዎ፣ አንድ፡ ቅርንጫፍ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ አለው።
ብቻህን፡ ወደ፡ ጓሮ፡ መሄድና፡ አትክልቱን፡ ማጠጣት፡ ትችላለህ?	እሺ፣ ከራት፡ በኋላ፡ እሄዳለሁ።
ልጅህንና፡ ባለቤትህን፡ አስቀድመህ ወዳገርህ፡ ትልካቸዋለህ?	የለም፣ ብቻቸውን፡ አልካቸውም።
እጓሮ፡ ብቻውን፡ ያለው፡ መኪና፡ የማን፡ ነው?	የለማ፡ ይመስለኛል።
ብቻዋን፡ በቅሎዋን፡ መጫን፡ ትችላለች?	አዎ፣ እንዴታ። የምትጫናት፡ ብቻዋን፡ ነው።
የመኪናውን፡ ዋጋ፡ ብቻህን፡ ከሰከፈለህ?	አዎ፣ ሁሉንም፡ ብቻዬን፡ ከፈልኩ።
ዕቃውን፡ ከመኪናው፡ ላይ፡ ብቻውን፡ አወረደው?	አዎ፣ አወረደው።
ጠረጴዛውን፡ ብቻህን፡ ከመኪናው፡ ላይ፡ መጫን፡ ትችላለህ?	አዎ፣ እጭነዋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
እዚያ፡ ትልቅ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ የምትኖሩ፡ ብቻችሁን፡ ነው?	አዎ፤ ብቻችንን፡ ነው።
እሲኒማ፡ ቤት፡ የሄዱ፡ ብቻዎን፡ ነበር?	የለም፤ ከጓደኞቼ፡ ጋር፡ ነበርኩ።
ብቻዎን፡ መኖር፡ የምትፈልጉ፡ ለምንድን፡ ነው?	አላውቅም።
ብቻህን፡ አንድ፡ ጠርሙስ፡ አረቄ፡ መጠጣት፡ ትችላለህ?	የለም፤ አልችልም።
ሥራህን፡ ብቻህን፡ ጀምረህ፡ ብቻህን፡ ጨረስከው?	የለም፤ ወንድሜ፡ ረዳኝ።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስና፡ ወይዘሮ፡ ሜሪ፡ የመኪናቸው፡ ጐማ፡ እስኪታደስላቸው፡ ድረስ፡ ወዳንድ፡ ሆቴል፡ ሄደው፡ ማደር፡ ፈለጉ።

ገዋሽ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ የሚያውቁት፡ ሰው፡ አቶ፡ ከበደ፡ ብቻ፡ ስለሆነ፤ ወደ፡ ሆቴል፡ እንዲወስዳቸው፡ ጠየቁት። አቶ፡ ከበደ፡ ከሁሉ፡ የተሻለ፡ ሆቴል፡ ፈልጎ፡ ስላገኘ፡ ወደዚያ፡ ይዟቸው፡ ሄደ።

በከተማው፡ ውስጥ፡ ታክሲ፡ ስለሌለ፤ ዕቃቸውን፡ በሁለት፡ ተሸካሚዎች፡ አስይዘው፡ ወደ፡ ሆቴሉ፡ ደረሱ።

እሆቴሉ፡ እንደደረሱ፡ የተሸከሙለትን፡ ዋጋ፡ ለተሸካሚዎቹ፡ ከፍለው፡ ዕቃቸውን፡ ካልጋቸው፡ ግርጌ፡ አስቀመጡት። ሌሊቱን፡ እዚያ፡ አድረው፡ በማግስቱ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ተመለሱ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስና፡ ወይዘሮ፡ ሜሪ፡ ለምን፡ ከሆቴሉ፡ አደሩ?

አዋሽ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ የሚያውቋት፡ ሰው፡ ማን፡ ነው?

አቶ፡ ከበደ፡ ወዴት፡ ወሰዷቸው?

በከተማው፡ ውስጥ፡ ታክሲ፡ አለ?

ዕቃቸው፡ እንዴት፡ ወደ፡ ሆቴሉ፡ አደረሱት?

ከተሸካሚዎች፡ ምን፡ ከፈሉዋቸው?

ዕቃቸውን፡ የት፡ አስቀመጡት?

በማግስቱ፡ ወዴት፡ ሄዱ?

በመኪና፡ መጓዝ፡ ትወዳለህ፡ ወይስ፡ በባቡር፡
መጓዝ፡ ትወዳለህ?

ሠላሳ፡ ሁለተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ሜሪ

እሰት፡ ውስጥ፡ እንደት፡ ዓለም፡ ነው፡ ከገበሀ። ወጥወጥ፡ አለት፡ አይደለም፡ እንደ።

ከበደ

ምን፡ አይተው። እንዴሳት፡ የሚያቀም ስጦ፡ ወሬት፡ ገና፡ ይመጣል።

ሜሪ

ከዚህ፡ የሚለበስ፡ ጊዜ፡ እሱ፡ ማለትህ፡ ነው?

ከበደ

በጣም፡ እንጂ።

ሜሪ

ታዲያ፡ ሰው፡ እንዴት፡ መኖር፡ ይችላል?

ከበደ

በዚህ፡ ወቅት፡ ውስጥ፡ ሕዝቡ፡ ለሉ፡ ሰብስ፡ መሰብሰብ፡ ይጀምራል።

ሜሪ

በእስ፡ ሰብስ፡ ብቻ፡ የሙቀቱን፡ ጊዜ፡ ካሳለፉትስ፡ ደህና፡ ነው። ክፉስ፡ ከውሃ፡ ውስጥ፡ የሚወጣ፡ አይደለለንም።

ከበደ

ከቀዩበት፡ ማዕጆቹ፡ ነገር፡ ይለውጫል። እምነለሁ፡ እኛ፡ ለአዲሱቱ፡ አገር፡ ጠርዝ፡ ለዓለም፡ እንዴት፡ እንደምትኖሩ፡ ይገለፃል።

ሜሪ

አወነትም፡ የለምድ፡ ነገር፡ ነይሆኑ፡ አይቀርም። ከመሆኑ፡ ወገውስ፡ እንዴት፡ ነው።

ከበደ

እንዲ፡ ጊዜ፡ በጣም፡ መቀርሬ፡ ነበር፡ ይላሉ። እሁን፡ ግን፡ ደህና፡ ነው።

ሜሪ

አቶ፡ ከበደ፥ ለሉ፡ አርዳታህ፡ ሁሉ፡ በጣም፡ አመሰግንሃለሁ።

ጆን

ምናልባት፡ ወደ፡ እዚሁ፡ አገር፡ ብቆ፡ የምትል፡ እንደሆነ፥ እደሌሎቹ፡ አማሪካን፡ አምባሲ፡ ነው።

ካሳዬ

ለቅርብ፡ ጊዜ፡ ወለጋ፡ ለመሄድ፡ እለ
ማሰብህ፡ እደርጌልሃሁ፡ ለመምጣት
ችኳለሁ።

ጆን

እንደታረጋ። ለኔ፡ አሁን፡ ጤና፡ ይስጥ
ልኝ።

ካሳዬ

መልካም፡ ጉዞ።

ጥያቄና፡ መልስ

ካሳዬ፡ ዛሬ፡ የመጣ፡ እንደሆነ፡ የት፡ ያርፋል?	እዚያው፡ ሆቴል፡ ሊያርፍ፡ ይችላል።
ባለፈው፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ የሄደ፡ እንደሆነ፣ ስንት፡ ዓመት፡ ሊቆይ፡ ይፈልጋል?	ሦስት፡ ዓመት፡ ያህል፡ ነው።
እንበሉና፡ ማበደ፡ ለንደን፡ ያማችሁ፡ እንደሆነ፡ የት፡ ተገናኛችሁ?	ወደ፡ ከተማ፡ መመለስ፡ አለብን።
ፈረንሳይኛ፣ የተማሩ፡ እንደሆነ፡ ወደ፡ ፈረንሳይ፡ አገር፡ መሄድ፡ ይችላሉ?	አዎ፣ ገንዘብ፡ ወር፡ ወለጋ፡ መሄድ፡ እችላለሁ።
መኪናዋ፡ ጥሩ፡ የሆነች፡ እንደሆነ፡ ትገዛታለህ?	አዎ፣ እገዛታለሁ።
እንግዳው፡ ስትገርህ፡ የጠየቁህ፡ እንደሆነ፡ ትነግረዋለህ?	አዎ፣ እነግርሃለሁ።
ጥሩነሽ፡ ገንዘብ፡ የምትፈልግ፡ እንደሆነ፡ ገንዘብ፡ ትሰጣታለህ?	የለም፣ አልሰጣትም።

ጥያቄ	መልስ
ገንዘብን፡ ትመነዝራለህ፡ እንደሆን፡ ትጠይቃለህ?	አዎ፣ ለመጠየቅ፡ እፈልጋለሁ።
ለትዴዋ፡ ቤቷን፡ ታከራይ፡ እንደሆን፡ ጠየቃችኋት?	አዎ፣ ለመጠየቅ፡ እፈልጋለሁ።
ነገ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ የመጣሁ፡ እንደሆን፡ ዝርዝሩን፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?	አዎ፣ እነግርሃለሁ።
እነዚህ፡ ሰዎች፡ የመጡ፡ እንደሆን፡ ትነግሩኛላችሁ?	አዎ፣ እንነግርሃለን።
መዝገቡ፡ የቆሸሸ፡ እንደሆን፡ ትጠብቃለህ?	አዎ፣ እጠብቃለሁ።
መኪናዬ፡ በተሀን፡ የሰጠሁህ፡ እንደሆነ፡ ለጂሉን፡ እድሬሳን፡ ትነግረናለህ?	አዎ፣ እነግራችኋለሁ።
እዚስ፡ ልብስ፡ የገዛሁ፡ እንደሆነ፡ እርግጤን፡ ከሆንኝ፡ ትሰጣለህ?	አዎ፣ እሰጣለሁ።
ማመልከቻ፡ የደሉ፡ እንደሆን፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
ለትዴዋ፡ ማርቴል፡ ቤት፡ ተኛታ፡ እንደሆን፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
መሥሪያ፡ ቤቱን፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ የዘጋው፡ እንደሆን፡ ማን፡ ያውቃል?	ከኛ፡ ማንም፡ አያውቅም።

ጥያቄ	መልስ
መድኃኒት፡ የገዛህ፡ እንደሆነ፡ ከዚ፡ ሱቅ፡ ትገዛለህ?	አዎ፣ እገዛለሁ።
መታወቂያ፡ ወረቀት፡ ያለኝ፡ እንደሆነ፡ ቼክ፡ መመንዘር፡ እችላለሁ?	አዎ፣ የፈለግኸውን፡ ቼክ፡ መመንዘር፡ ትችላለህ።
ከሞ፡ አለቃ፡ ገበያ፡ እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ?	የለም፣ አናውቅም።
ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ንግግር፡ ያደርጉ፡ እንደሆነ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ሚስትዎ፡ ምሥጢሩን፡ ታውቃ፡ እንደሆነ፡ ጠየቋት?	የለም፣ አልጠየቅኋትም።
ቤቱ፡ ምቹ፡ እንደሆነ፡ አየኸው?	የለም፣ አላየሁትም።
ዕቃውን፡ እንደጠበቅኸው፡ የመጣ፡ እንደሆነ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
መድኃኒቱን፡ ከመድኃኒት፡ ቤት፡ መግዛትህ፡ ነው?	አዎ፣ መግዛቴ፡ ነው።
ወጡን፡ ለዘሮቹ፡ መሥራትህ፡ ነበር?	አዎ፣ መሥራቴ፡ ነበር።
አሁን፡ ዝናብ፡ መዝነቡ፡ ነው?	አዎ፣ መዝነቡ፡ ነው።
አባቱ፡ ዘመድ፡ ዘመዶ፡ ብር፡ መላካቸው፡ ነበር?	አዎ፣ መላካቸው፡ ነበር።
ዕቃውን፡ አሁን፡ መግዛታቸው፡ ነበር?	አዎ፣ መግዛታቸው፡ ነበር።
እነሱም፡ ሊመጡ፡ እንዳሉ፡ የመከሩበትን፡ ጉዳይ፡ ማስነሳታቸው፡ ነበር?	የለም፣ ማስነሳቱ፡ አልነበረም።

ጥያቄ	መልስ
እነቱ፡ ግብጋቸው፡ ጋር፡ ለትምህርት፡ [illegible] ሁ፡ ያን፡ መሥራታቸው፡ ነበር?	ከልጁ፡ ጋር፡ መማሯ፡ ነበር።
እኚ፡ የሐኪሞች፡ ለሮገናው፡ ወዲገሩ፡ መሄዱ፡ ነበር?	አዎ፤ መሄዱ፡ ይመስለኛል።
ዛሬ፡ ከባንክ፡ ገንዘብ፡ መበደርህ፡ ነው?	አዎን፤ መበደሬ፡ ነው።
ዕቃችሁን፡ ይዛችሁ፡ ለሽርሽር፡ መሄዳችሁ፡ ነው?	አዎ፤ መሄዳችን፡ ነው።
ለትምህርት፡ ገንዘብ፡ ከመንግሥት፡ መቀበልህ፡ ነው?	አዎን፤ መቀበሌ፡ ነው።
እነቱ፡ ከባንክ፡ ለትወጣ፡ ሌላ፡ መንገድ፡ ነበር?	የለም፤ ከእኛም፡ መውጫ፡ ነበር።
እናንተ፡ ለትላላ፡ ክፍ፡ መቀመጥዎ፡ ነበር?	አዎ፤ መቀመጥዎ፡ ነበር።
ቤቱን፡ መከራየታችሁ፡ ነበር?	አዎ፤ መከራየታችን፡ ነበር።
እኚ፡ ወዲ፡ ሥራ፡ ለንግድ፡ ሌላ፡ ክፍል፡ መጠምጧ፡ ነበር?	ግንፉ፡ ይመስለኛል።
ጥፋኒስ፡ ዛሬ፡ ጥቂት፡ ለወንዝ፡ አጠገብ፡ ያን፡ መሥራታቸው፡ ነበር?	መሽርሽርዎ፡ ነበር።
የሐኪሙ፡ መድሐኒቱን፡ ካማርኛ፡ ወደ፡ እንግሊዝኛ፡ መተርጐሙ፡ ነው?	አዎ፤ መተርጐሙ፡ ነው።
ከምግባደሬቻችሁ፡ ጋር፡ መተዋወቃችሁ፡ ነበር?	አዎ፤ መተዋወቃችን፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ወንዝ፡ ስንመጣ፡ ምን፡ ማድረጋችሁ፡ ነበር?	መዋኘታችን፡ ነበር።
ወደ፡ ገበር፡ ማበያ፡ መሄዳችሁ፡ ነበር?	አዎ፥ መሄዳችን፡ ነበር።
ጥብስ፡ ሥጋ፡ መብላታችሁ፡ ነው?	አዎ፥ መብላታችን፡ ነው።
ከወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ጋር፡ መዋኘታችሁ፡ ነው?	አዎ፥ መዋኘታችን፡ ነው።
ወረቀቱን፡ ከወጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ መስጠታችሁ፡ ነው?	አዎን፥ ዛሬ፡ መስጠታችን፡ ነው።
የኢትዮጵያ፡ ወይዛዝርት፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መምጣታቸው፡ ነው?	አዎን፥ መምጣታቸው፡ ነው።
የዛሬ፡ ሳምንት፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ መሄዳችሁ፡ ነው?	አዎ፥ መሄዳችን፡ ነው።
ዕቃችሁን፡ ከመኪናው፡ ላይ፡ መጫናችሁ፡ ነው?	አዎ፥ መጫናችን፡ ነው።

ድርሰት

ከለታት፡ አንድ፡ ቀን፡ አቶ፡ ጆን፡ ገለበቶን፡ ወይዘሮ፡ ሜሪን፡ ይዞ፡ ወደ፡ አዋሽ፡ ሄደ። አዋሽ፡ እንደደረሱ፡ ያቶ፡ ጆን፡ የመኪናው፡ ጐማ፡ ስለፈነዳበት፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ተመልሰው፡ መሄድ፡ አልቻሉም።

የመኪናውን፡ ጐማ፡ ለማሳደስ፡ ጋራዥ፡ ሲፈልጉ፡ እንዳጋጣሚ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ስላገኘው፥ የጐማ፡ ማደሻ፡ ቦታ፡ ጠየቁት። አቶ፡ ከበደም፡ ለበ፡ ቀን፡ ሰው፡ ስለነበር፥ የጐማ፡ ማደሻ፡ ቦታ፡ ፈለጉ፥ ጐማውን፡ እንዲታደስ፡ አደረጉላቸው።

ጊዜው፡ በጣም፡ መሽቶ፡ ከመሆኑ፡ የተነሳ፣ ወይዘሮ፡ ሜሪና፡ አቶ፡ ጆን፡ በጣም፡ ስለደከማቸው፡ አዋሽ፡ ውስጥ፡ ለማደር፡ ቆረጡ።

ነገሩ፡ እንግዲህ፡ ስለሆነ፣ አቶ፡ ከበደ፡ ዕቃቸውን፡ በተሸካሚ፡ አስይዞ፡ ወደ፡ አንድ፡ ደህና፡ ሆቴል፡ መራቸው።

ከሆቴሉ፡ እንደደረሱ፡ ተሸካሚው፡ ዕቃቸውን፡ ወደ፡ ክፍላቸው፡ አስገብቶ፡ የተሸከመበትን፡ ዋጋ፡ ተቀብሎ፣ ወደ፡ ቤቱ፡ ሄደ።

አቶ፡ ጆንና፡ ወይዘሮ፡ ሜሪ፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ ጥቂት፡ ከተነጋገሩ፡ በኋላ፣ አቶ፡ ከበደ፡ ተሰናብቶ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ መሄድ፡ ፈለገ።

እነሱም፡ ስላደረገላቸው፡ መልካም፡ እርዳታ፡ ካመሰገኑት፡ በኋላ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሲመጣ፡ እንዲጠይቃቸው፡ አድራሻቸውን፡ ሰጡት። እሱም፡ አድራሻውን፡ ተቀብሎ፡ ተሰነባብተው፡ ተለያዩ።

ጥያቄዎች

ተሸካሚዎች፡ የንግዶቹን፡ ዕቃ፡ የት፡ አስገቡ?

አቶ፡ ከበደ፡ ተሸካሚዎቹን፡ ከየት፡ አመጣቸው?

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ጆን፡ የት፡ ተዋወቁ?

ወይዘሮ፡ ሜሪና፡ አቶ፡ ጆን፡ ወዴት፡ ይሄዱ፡ ነበር?

አቶ፡ ከበደ፡ ከመሄዱ፡ በፊት፡ ካቶ፡ ዮሐንስ፡ ጋር፡ ምን፡ ተነጋገረ?

አቶ፡ ዮሐንስና፡ ወይዘሮ፡ ሜሪ፡ ለምን፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ መመለስ፡ አልቻሉም?

ሠላሳ፡ ሦስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበበ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ ጌታዬ፣ ስሜ፡ ከበበ፡ ይባላል?

ዓለሙ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ አቶ፡ ከበበ። ስሜ፡ ዓለሙ፡ ነው?

ከበበ

መልካም። አቶ፡ ዓለሙ፡ ምን፡ ላድርግልዎት?

ዓለሙ

እንደምመለከተው፡ ዕቃዎችዎ፡ ሁሉ፡ በጣም፡ ውድ፡ ይመስሉኛል፤ ነገር፡ ግን፡ መጠየቅ፡ አይከፋም።

ከበበ

በውነቱ፡ ውድ፡ አይደሉም። ብዙ፡ ሰዎች፡ ከርካሽ፡ ነው፡ እያሉ፡ ጓደኞቻቸውን፡ ወደኛ፡ ሱቅ፡ ይልኩዋቸዋል።

ዓለሙ

ላዲስ፡ ቤት፡ የሚያስፈልጉ፡ ብዙ፡ ዕቃዎች፡ ለመግዛት፡ ስለምፈልግ፣ ለዚህ፡ ወረቀት፡ ላይ፡ ዘርዝሬያቸዋለሁ።

ከበበ

እስቲ፡ ሌስዎ፡ የሚፈልጉትን፡ ዕቃ፡ ለመቀመና፡ ለአቀጋመና፡ ለኩፄናቶ፡ እንነጋገርበታለን።

ዓለሙ

እኔ፡ ሌላ፡ የምፈልገው፡ ከዚህ፡ የሚቀጥሉትን፡ ዕቃዎች፡ ነው። የቤተ፡ ሰብ፡ አልጋ፡ ከነፍራሹና፡ ከነትራሱ፣ ሁለት፡ ትንንሽ፡ አልጋዎች፡ ከነፍራሾቻቸውና፡ ከነትራሶቻቸው፣ አንድ፡ ሰፊ፡ የምግብ፡ ጠረጴዛ፡ ከስድስት፡ ወንበሮች፡ ጋር።

አራት፡ ፎቴዎች።

ጌጥ፡ ያላቸው፡ የጠረጴዛ፡ መብራቶች።

ከበበ

መልካም፣ መጀመሪያ፡ አልጋዎቹን፡ ላሳይዎት።

ዓለሙ	አበበ
እሺ፣ እንዲሁም፡ አሌት፡ የሲኒማ፡ መተርጐሚያዎች፡ ያስፈልጉናል።	አዎን፣ ሳያስፈልጉዎት፡ አይቀሩም። የሆነው፡ ሆኖ፡ በኔ፡ ቢሮ፡ ውስጥ፡ አይገኙም። ነገር፡ ግን፡ አናቶ፡ ከበደ፡ ቢሮ፡ ማግኘት፡ ይቻላል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከመሄዳችን፡ በፊት፡ ለማን፡ የምናገኘው፡ ይመስልሃል?	ምናልባት፡ ሳታገኙት፡ አትቀሩም።
እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ወባ፡ ያለ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ሳይኖር፡ አይቀርም።
አባትህ፡ ለትምህርት፡ ቤቱ፡ እርዳታ፡ ለመስጠት፡ ቆረጡ?	አዎን፣ ሳይቆርጡ፡ አይቀሩም።
ዕቃውን፡ ከመኪናው፡ ላይ፡ አወረዱት?	ሳያወርዱት፡ አይቀሩም።
እናቱን፡ ለማየት፡ እመጣለሁ፡ ብሎ፡ ሳይመጣ፡ ቀረ?	የለም፣ አልመጣም።
እንመጣለን፡ ካሉ፡ ሳይመጡ፡ ይቀራሉ?	ካንድ፡ ሰዓት፡ በኋላ፡ ሳይመጡ፡ አይቀሩም።
በዚህ፡ ዓመት፡ ልጅህ፡ መጥታ፡ ሳትጠይቅህ፡ ትቀራለች?	ምናልባት፡ ሳትጠይቀኝ፡ አትቀርም።

ጥያቄ	መልስ
አለማዝ፡ ወንድሟን፡ ሳትጠይቅ፡ ቀረች?	የጠየቀች፡ አይመስለኝም።
አሜሪካ፡ውስጥ፡ቤት፡ውድ፡ነው?	አዎ፣ ውድ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።
ወንድምህ፡ እቤት፡ ውስጥ፡ ነው?	አዎ፣ ሳይሆን፡ አይቀርም።
ውኃውን፡ ሐኪም፡ቤት፡ ወሰዳችሁት?	አለማዝ፡ ሳትወስደው፡ አልቀረችም።
ያቺ፡ ሴት፡ ሁልጊዜ፡ እቤታችሁ፡ ትመጣለች?	አንድ፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ሳትመጣ፡ አልቀረችም።
አሜሪካዊ፡ ሰውዬ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ መጥቶ፡ ነበር?	ትናንት፡ ከሰዓት፡ በፊት፡ ሳይመጣ፡ አልቀረም።
አስተማሪህ፡ ምን፡ ዓይነት፡ መጠጥ፡ ይጠጣል?	ጠጅ፡ ሳይጠጣ፡ አይቀርም።
መኪናዬ፡ የት፡ እንደሆነች፡ ታውቃለህ?	ባቡር፡ ጣቢያ፡ ሳትሆን፡ አትቀርም።
ፈረሱ፡ ወደ፡ ወንዝ፡ ለምን፡ ሄደ?	ውሃ፡ ሳይጠማው፡ አልቀረም።
እርሳስና፡ ወረቀት፡ ለምን፡ ገዛ?	ገንዘብ፡ ሳያገኝ፡ አልቀረም።
እናታቸውን፡ ለማየት፡ ልጆቹ፡ እንዴት፡ ሄዱ?	ካባታቸው፡ መኪና፡ ሳይወስዱ፡ አልቀሩም።
እህትህ፡ ለምን፡ የኔን፡ መጽሐፍ፡ ወሰደች?	ሳትሳሳት፡ አልቀረችም።
ካንድ፡ ዓመት፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መሄድና፡ ማስተማር፡ ትፈልጋለች?	አዎ፣ ሳትፈልግ፡ አትቀርም።
የዚህ፡ ሰው፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?	መሐንዲስነት፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።

ጥያቄ	መልስ
እቤት፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ሰውዬ፡ ማን፡ ነው?	ተጋባዥ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ የሰጣቸውን፡ ገንዘብ፡ ምን፡ አደረጉት?	ሳይከፋፈሉት፡ አልቀሩም።
የኛ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ተማሪዎች፡ የት፡ ሄዱ?	ሲኒማ፡ ቤት፡ ሳይሄዱ፡ አይቀሩም።
የገዛቻት፡ መኪና፡ ቀለም፡ ምን፡ ዓይነት፡ ነው?	ሰማያዊ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።
ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ይሄዳሉ?	በአራት፡ ሰዓት፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።
ዕቃውን፡ እቤት፡ ውስጥ፡ ማን፡ አገባው?	ሠራተኞች፡ ሳይሆኑ፡ አይቀሩም።
ለሴትዮዋ፡ የሰጡዋት፡ ምንድን፡ ነው?	የአሥር፡ ብር፡ ምንዛሪ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።

ድርሰት

አንድ፡ ቀን፡ አበበ፡ በሱቅ፡ ውስጥ፡ ሳለ፣ ዓለሙ፡ መኮንን፡ ሊሊን፡ ከአበበ፡ ጋር፡ አስተዋወቀ።

ዓለሙ፡ አዲስ፡ ቤት፡ ስለገዛ፣ ቤቱን፡ በልዩ፡ ልዩ፡ ዕቃዎች፡ ሊያጌጠው፡ ፈለገ። የቤት፡ ዕቃዎች፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በጣም፡ ውድ፡ ናቸው። ግን፡ ኑሮን፡ ስለሚያስደስቱና፡ ብዙ፡ ጥቅም፡ ስለሚሰጡ፣ ዓለሙ፡ ለመግዛት፡ ቆረጠ።

ወደ፡ ሱቅ፡ እንደገባ፡ ከሱቁ፡ ባለቤት፡ ጋር፡ አበበ፡ የሚፈልጋቸውን፡

የቃዎች፡ ዝርዝር፡ አሳየው። የቃዎቹም፡ ዝርዝር፡ ፍራሽ፣ ትራስ፣ የቤት፡ ሰብ፡ አለጋ፣ ትንንሽ፡ አለጋዎች፣ የምግብ፡ ጠረጴዛ፣ ስድስት፡ ወንበሮች፣ አራት፡ ፎቶዎችና፡ ጌጥ፡ ያላቸው፡ የጠረጴዛ፡ መብራቶች፡ ነበሩ።

አቶ፡ ዓለሙ፡ ዕቃዎቹን፡ አንድ፡ በአንድ፡ ከተመለከተ፡ በኋላ፡ በሌላ፡ ቀን፡ መጥቶ፡ የቤት፡ ዕቃዎቹን፡ ለመግዛት፡ ተስማምቶ፡ ወደ፡ ቤት፡ ተመለሰ።

ጥያቄዎች

ከበበ፡ የት፡ ነበር?

ዓለሙ፡ የት፡ ሄደ?

ዓለሙ፡ ለምን፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ ለመግዛት፡ ፈለገ?

የቤት፡ ዕቃዎች፡ ውድ፡ ናቸው?

የቤት፡ ዕቃዎች፡ የሚሰጡት፡ ጥቅም፡ ምንድን፡ ነው?

አቶ፡ ዓለሙ፡ ላቶ፡ ከበበ፡ ምን፡ አሳየው?

የዕቃዎችን፡ ዝርዝር፡ ጻፍ።

አቶ፡ ዓለሙ፡ ዕቃዎቹን፡ ሳይገዛ፡ ለምን፡ ተመለሰ?

ምን፡ ዓይነት፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ ለመግዛት፡ ይፈልጋሉ?

ምን፡ ዓይነት፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ እንዲኖሩህ፡ ትፈልጋለህ?

ሠላሳ፡ አራተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዓለሙ

እስቲ፡ አልጋውን፡ እንየው?

አበበ

ይህ፡ አልጋ፡ አዲስና፡ ዘመናዊ፡ ከመሆኑም፡ በላይ፣ ለልጅ፡ ልጅ፡ የሚተላለፍ፡ ጠንካራ፡ አልጋ፡ ነው።

እንዲሁም፡ ፍራሹ፡ በጥንካሬው፡ የታወቀና፡ ምቹ፡ ነው።

ዓለሙ

ስላልጋና፡ ፍራሹ፡ ጥንካሬ፡ ገጽታውም፡ እንዳነጋገርዎ፡ ጥሩ፡ ይመስለኛል።

እስቲ፡ ስለዋጋው፡ እንነጋገርበት።

አበበ

እንደሚመለከቱት፡ ዋጋው፡ አንድ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ የኢትዮጵያ፡ ብር፡ ነው።

ዓለሙ

አንድ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ የኢትዮጵያ፡ ብር፡ ላንድ፡ አልጋ፡ ውድ፡ ነው።

እርግጠኛውን፡ ዋጋ፡ ይንገሩኝና፡ ልግዛው።

አበበ

ዕቃው፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ስለሆነ፡ ውድ፡ አይደለም። በውነቱ፡ እርካሽ፡ ነው።

ዓለሙ

ምንም፡ እንኳን፡ ብልጭልጭ፡ ቢልና፡ ጥሩ፡ መስሎ፡ ቢታየኝም፣ ላንድ፡ አልጋ፡ አንድ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ ብር፡ መክፈል፡ ካቅሜ፡ በላይ፡ ነው።

አበበ

በዋጋው፡ የተጐዱ፡ አይመስለኝም። የሆነው፡ ሆኖ፡ ደንበኞቼን፡ ማስደሰት፡ ስለምፈልግ፣ ባንድ፡ መቶ፡ አርባ፡ ብር፡ እሸጥልዎታለሁ።

ዓለሙ

እሺ፡ አሁንም፣ አንድ፡ መቶ፡ አርባ፡ ብር፡ ይበዛብኛል።

አበበ

ለመሆኑ፡ በስንት፡ ለመግዛት፡ ይፈልጋሉ?

ዓለሙ	ከበ
መቶ፡ ሠላሳ፡ ብር፡ ይበቃዎታል።	በጣም፡ ጉዳት፡ ነው። ሆኖም፡ የወደፊት፡ ደንበኛዬ፡ ስለሚሆኑ፣ ገለት፡ ዋጋ፡ እሸጥልዎታለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እንግዶች፡ ገንዘብ፡ ለሰዎች፡ ሰጡ?	አዎ፣ ትንሽ፡ ገንዘብ፡ ሰጥተው፡ ሄዱ።
እዚህ፡ እየዟዟርኩ፡ እስክትመጡ፡ ስጠብቃችሁ?	በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
ቡና፡ ደጋግሞ፡ ከጠጣ፡ መተኛት፡ ይቻላል?	ሊተኛ፡ የሚችል፡ አይመስለኝም።
ዕቃቸውን፡ ከሆቴሉ፡ አደራርሰው፡ የት፡ ሄዱ?	ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ ሄዱ።
ለማ፡ ጥሩነሽን፡ እየጠራራ፡ ስለ፡ አገርዋ፡ ይጠያይቃታል?	አዎ፣ አንዳንዴ፡ ይጠያይቃታል።
ገንዘቡን፡ ከቀፍሉ፡ ለማን፡ ሰጠው?	ለሁለቱ፡ ልጆች፡ ሰጣቸው።
ቤታቸውን፡ ዘጋግተው፡ የት፡ የሄዱ፡ ይመስልሃል?	ምናልባት፡ ወደ፡ እናታቸው፡ ቤት፡ ሄደው፡ ይሆናል።
መኪናቸውን፡ ከቀፍታው፡ ምን፡ ይሠራሉ?	ዕቃውን፡ ያስገባሉ።

ጥያቄ	መልስ
ምሳችሁን፡ በላልታችሁ፡ ዋና፡ ትሄዳላችሁ?	አዎን፣ ምናልባት፡ እንሄድ፡ ይሆናል።
መጽሐፉን፡ ፈላልገህ፡ አገኘኸው?	አዎን፣ አገኘሁት።
ገንዘብ፡ ከተማሪዎች፡ ወሳሰዱና፡ ምን፡ ገዙ?	ዕቃዎች፡ ገዙ።
አስተማሪው፡ ተማሪዎቹን፡ ሊያመሰጋግን፡ እቀበሌህ፡ ነበር?	የለም፣ እቀበሌ፡ አልነበርሁም።
ገንዘብን፡ መመንዛዘር፡ ለምን፡ ትፈልጋለህ?	ምንዛሬ፡ በጣም፡ ስለምፈልግ፡ ነው።
ወንድሞችህን፡ አያይተህ፡ ተመለስክ?	አዎ፣ አያይቼ፡ ተመለስኩ።
ነገሩን፡ ሰማምቶ፡ የት፡ ሄደ?	ወደ፡ መሥሪያ፡ ቤቱ፡ ሄደ።
እነከበደ፡ የት፡ ሄዱ?	ምሳቸውን፡ በልተው፡ ወጡ።
ትንሽ፡ ሠራርተን፡ ወደ፡ ቤታችን፡ መሄድ፡ አንችላለን?	አዎን፣ ትንሽ፡ ሠራርታችሁ፡ መሄድ፡ ትችላላችሁ።
ሥራውን፡ ጀማምረህ፡ ለምን፡ ተውከው?	ጊዜ፡ ስለሌለኝ፡ ነው።
ሥራ፡ መፈላለግ፡ ከጀመርክ፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ሆነህ?	አንድ፡ ሳምንት፡ ሆኖኛል።
ለማ፡ ሁልጊዜ፡ ይጠይቃችኋል?	አንዳንዴ፡ እየመጣጣ፡ ይጠያይቀናል።
የገዛኋቸውን፡ መኪናዎች፡ አይተሃል?	አዎ፣ አይቻለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ስለ፡ ግብዣው፡ ያመሰጋገኑዎችሁ፡ ሰዎች፡ ስም፡ ማን፡ ማን፡ ይባላል?	አቶ፡ ከማና፡ ወይዘሪት፡ ጥሩነሽ፡ ይባላሉ።
ቡና፡ ደጋግሞ፡ የጠጣው፡ ሰውዬ፡ ወንድምዎ፡ ነው?	አዎን፡ ወንድሜ፡ ነው።
ቡናህን፡ ጠጣጥተህ፡ የት፡ ሄደህ፡ ነበር?	መኝታ፡ ቤት፡ ስልክ፡ ልደውል፡ ነበር።
ከሰጀቹ፡ ገንዘብ፡ ለማጥፉ፡ ወደገሩ፡ ተመለሰ?	አዎን፡ ትናንትና፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ተመለሰ።
ሁልጊዜ፡ ገንዘብ፡ ትበዳደራላችሁ?	የለም፡ አንበዳደርም።
ከማና፡ ገለበቱ፡ በጣም፡ እንደሚመሰጋገኑ፡ ታውቃለህ?	የለም፡ አላውቅም።
አንተና፡ ወንድምህ፡ ትተማመናላችሁ?	አዎን፡ እንተማመናለን።
እጃቸውን፡ ተጣጥበው፡ ምሳቸውን፡ በሉ?	አዎ፡ ተጣጥበው፡ በሉ።
ዮሐንስና፡ ጥሩነሽ፡ ባልና፡ ሚስት፡ ለመሆን፡ ይፈቃቀዳሉ?	በውነቱ፡ አላውቅም።
ጥሩነሽና፡ እናትዎ፡ አበታ፡ ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ ይፈላለጉ፡ ነበር?	አዎ፡ ተፈላልገው፡ ተገናኙ።
ስለ፡ በቶ፡ ኪሎፍ፡ ዛሬ፡ ትፈላለጋለህ?	አዎ፡ እፈላለጋለሁ።
አስተማሪዎች፡ ባመት፡ ስንት፡ ጊዜ፡ ይገባበዛሉ?	እንደ፡ አሥር፡ ጊዜ፡ ያህል፡ ይገባበዛሉ።

ጥያቄ	መልስ
አገኘሁና፡ አንተ፡ ነገሩን፡ ተገነዘባችሁ?	አዎ፣ ተገነዘብን።
ወደ፡ አሜሪካ፡ የምትሄዱበትን፡ ምክንያት፡ ተጨዋወታችሁ?	የለም፣ ገና፡ አልተጨዋወትንም።
ለስንት፡ ሰዓት፡ ለመገናኘት፡ ተቀጣጠራችሁ?	ገሌት፡ ሰዓት፡ ገደማ፡ ነው።
ከባለቤትሽ፡ ጋር፡ ተገናኘሽ?	አዎ፣ ተገናኘሁ።
ገንዘቡን፡ መቼ፡ ተከፋፈላችሁ?	ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ እንከፋፈላለን።
ከማና፡ ዮሐንስ፡ ተቀራርበው፡ ይኖራሉ?	የለም፣ ተራርቀው፡ ይኖራሉ።
አንተና፡ እህትህ፡ ለምን፡ ተራራቃችሁ?	እኔ፡ እዚህ፡ ከተማ፡ መኖር፡ ስለፈለግሁ፡ ነው።
ጥሩነሽና፡ ወንድሟ፡ ለምን፡ ተለያዩ?	እሱ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ለመሄድ፡ ስለፈለገ፡ ነው።
ከማና፡ አገኘ፡ በጣም፡ ይመሳሰላሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ይመሳሰላሉ።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩና፡ የትምህርት፡ ሚኒስትሩ፡ ስለምን፡ ተነጋገሩ?	ስለ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ተነጋገሩ።
አለማዝና፡ ጥሩነሽ፡ ተሰነባበቱ?	አዎን፣ ተሰነባበቱ።
ጥሩነሽና፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ ተሰጣጡ?	በጣም፡ ጥሩ፡ ልብሶች፡ ተሰጣጡ።
አገኘና፡ ሚኒስትሩ፡ ተዋወቁ?	የለም፣ አልተዋወቁም።

ጥያቄ	መልስ
አንተና፡ ወንድምህ፡ ትጠላላላችሁ?	አዎ፤ እንጠላላለን።
ለማና፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ ይሰጣጣሉ?	ኮትና፡ ከረባት፡ ይሰጣጣሉ።
ገንዘብ፡ ተመነዛዘራችሁ?	አዎ፤ ተመነዛዘርን።
እነከበደ፡ ብዙ፡ ነገር፡ ተሻሻጡ?	አዎ፤ ብዙ፡ ተሻሽጠዋል።
ከሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ተጋባበዛችሁ?	ቡና፡ ብቻ፡ ነው።
ተማሪዎች፡ ራሳቸውን፡ ተዋወቁ?	የለም፤ ገና፡ ናቸው።

ድርሰት

አቶ፡ ዓለሙ፡ ከየዘሬ፡ በሱቁ፡ ውስጥ፡ ያሉትን፡ እቃዎች፡ ሁሉ፡ ከተመለከቱ፡ በኋላ፤ አንደኛውን፡ እቃ፡ ለመግዛት፡ ፈለገ። ይህ፡ እቃ፡ ጠንካራና፡ ምቹ፡ ከመሆኑም፡ በላይ፡ እጅግ፡ ዘመናዊ፡ ነበር።

ያቃው፡ ዋጋ፡ አንድ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ ብር፡ ስለነበረና፡ ላቶ፡ ዓለሙ፡ በጣም፡ ውድ፡ መስሎ፡ ስለታየው፤ በዚህ፡ ዋጋ፡ ለመግዛት፡ አልፈለገም። በዋጋው፡ ካቶ፡ አበበ፡ ጋር፡ ከተከራከሩ፡ በኋላ፤ አቶ፡ ዓለሙ፡ እቃውን፡ ባንድ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ ብር፡ ለመግዛት፡ ፈለገ።

በየትም፡ ቦታ፤ የዕቃው፡ ዓይነት፡ ከዋጋው፡ ጋር፡ የተመሳሰለ፡ ነው። ዕቃው፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ከሆነ፤ ዋጋው፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለ፡ ይሆናል። ዕቃው፡ ዝቅተኛ፡ ከሆነ፤ ዋጋው፡ እንደዚሁ፡ ያንሳል። አቶ፡ ዓለሙ፡ ለገዛው፡ እቃ፡ አንድ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ ብር፡ የከፈለበት፡ ምክንያቱ፡ ያቃው፡ ዓይነት፡ ጥሩ፡ መሆኑ፡ በማወቅ፡ ነው።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዓለሙ፡ እየዞረ፡ ምን፡ ተመለከተ?

አቶ፡ ዓለሙ፡ ምን፡ ለመግዛት፡ ፈለገ?

ለምን፡ አልጋውን፡ ለመግዛት፡ ፈለገ?

ያልጋው፡ ዋጋ፡ ስንት፡ ነበር?

አቶ፡ ዓለሙ፡ ካልጋው፡ ስንት፡ ከፈለ?

አቶ፡ አበበና፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ በዋጋው፡ ተከራከሩ?

የዕቃው፡ ዓይነት፡ ከዋጋው፡ ጋር፡ ይመሳሰላል?

አቶ፡ ዓለሙ፡ ካልጋው፡ አንድ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ ብር፡ የከፈለበት፡
 ምክንያቱ፡ ምንድን፡ ነው?

የቤት፡ ዕቃ፡ ለመግዛት፡ ስትፈልግ፡ ወዴት፡ ትሄዳለህ?

በቤትህ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ አሉህ?

ሠላሳ፡ አምስተኛ፡ ትምህርት

ዓለሙ

ዕቃውን፡ መች፡ ይልኩልናል?

ከበበ

አሁን፡ ሰው፡ ስለላክሁ፡ ነገ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ሳስረክብዎት፡ እችላለሁ። ከሁሉም፡ ነገር፡ ስልክ፡ እደውልልዎታለሁ።

ዓለሙ

እንግዲያስ፡ ግማሹን፡ ዋጋ፡ እንደ፡ ቀብድ፡ አሁን፡ እሰጥዎታለሁ። የቀረውን፡ ግን፡ ዕቃውን፡ ስረከብ፡ እከፍልዎታለሁ።

ከበበ

እሺ፤ ደረሰኙ፤ ከመሄዴ፡ በፊት፡ ከካ፡ የሚፈልጓቸው፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ እንደ፡ ሰሐን፤ ቢላዋ፤ ሹካ፤ ማንኪያ፤ ስኒ፤ ብርጭቆ፤ መክከያ፡ እንዲሁም፡ ሌሎች፡ ዕቃዎች፡ ማየት፡ ይፈልጋሉ?

ዓለሙ

እነዚህን፡ የወጥ፡ ቤት፡ ዕቃዎች፡ ቀደም፡ ብዬ፡ ገዝቻለሁ።

ግን፡ ስላስታወሱኝ፡ አመሰግናለሁ። ወደፊት፡ ሌሎች፡ ደንበኞች፡ አመጣልዎታለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
አባትህ፡ ስንት፡ የልጅ፡ ልጆች፡ አሉዋቸው?	አሥራ፡ አምስት፡ ወንድና፡ ሴት፡ የልጅ፡ ልጆች፡ አሏቸው።
ይችን፡ መኪና፡ ብገዛት፡ ጥንካሬ፡ ያላት፡ ይመስልሃል?	አዎ፤ በጣም፡ ጥንካሬ፡ ያላት፡ ይመስለኛል።
ወደ፡ ባንክ፡ ለመሄድ፡ ምቹ፡ ጊዜ፡ አለዎ?	ነገ፡ እንደሆን፡ ነው፡ እንጂ፡ ዛሬ፡ የለኝም።

ጥያቄ	መልስ
ነገ፡ እርግጠኛ፡ ወዳገርሽ፡ የምትሄጂ፡ ይመስልሻል?	ምናልባት፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ከእኛ፡ ጋር፡ ወደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ መሄድ፡ ትፈልጋለች?	አሁን፡ የምትሄድ፡ አይመስለኝም።
መኪናህን፡ ስትሸጥ፡ ተጎዳህ?	የለም፤ አልተጎዳሁም።
አዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ዱንገኞች፡ አሉ?	ሁለት፡ ብቻ፡ ናቸው።
ያዲስ፡ አበባ፡ ሕዝብ፡ ብዛት፡ ስንት፡ ነው?	ቁጥሩን፡ አላውቅም።
ከነዚህ፡ መኪናዎች፡ መካከል፡ የትኛው፡ ጠንካራ፡ ይመስልሃል?	አላውቅም።
ከለማ፡ ጋር፡ ስለምን፡ ተከራከራችሁ?	ስለ፡ መኪና፡ ዋጋ፡ ተከራከርን።
እዝቅተኛው፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ተማሪዎች፡ አሉዋችሁ?	ሃምሳ፡ የሚሆኑ፡ ተማሪዎች፡ አሉን።
ከትምህርት፡ ቤት፡ ያገኘኸው፡ ገንዘብ፡ አነሰህ?	የለም፤ አላነሰኝም።
የለማን፡ መኪና፡ ወስደህ፡ አስረከብኸው?	የለም፤ ገና፡ አላስረከብሁትም።
እንድትሰጣቸው፡ የሰጠሁህን፡ ገንዘብ፡ ለሁሉም፡ ሰጠሃቸው?	ለማማሾች፡ ብቻ፡ ሰጠሁዋቸው።
ለሆቴሉ፡ ክፍል፡ ቀብድ፡ ሰጠህ?	አዎ፤ አሥር፡ ብር፡ ሰጥቻለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ያሜሪካ፡ መንግሥት፡ ለኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ገንዘብ፡ መስጠቱን፡ ሰምተሃል?	አዎ፤ ሰምቻለሁ።
ገንዘቡን፡ ስትቀበል፡ ደረሰኝ፡ ሰጠኸው?	አዎ፤ ሰጥቼዋለሁ።
ምሳህን፡ በሳህን፡ ላስቀምጥልህ?	እሺ፤ አስቀምጥልኝ።
ወይዘሮ፡ አልማዝ፡ ሹካ፤ ቢላዎና፡ ማንኪያ፡ ገዛች?	የለም፤ ገና፡ እገዛለሁ፡ አለችና፡ ወደ፡ ቤትዋ፡ ሄደች።
አንድ፡ ብርጭቆ፡ ውሃ፡ ትፈልጋለህ?	አሁን፡ አልፈልግም።
የሚሰጥህን፡ አረቄ፡ በመለኪያ፡ መለካት፡ ይፈልጋል?	አዎ፤ ይመስለኛል።
ካዲስ፡ አበባ፡ የመጣውን፡ ዕቃ፡ መቼ፡ መረከብ፡ ትፈልጋለህ?	ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ መረከብ፡ እፈልጋለሁ።
ወጥ፡ ቤት፡ የተቀመጠችዋ፡ ሴት፡ ስም፡ ማን፡ ነው?	አልማዝ፡ ነው።
ከበደ፡ ስምህን፡ አስታወሰው?	የለም፤ አላስታወሰውም።
የዛሬ፡ ሳምንት፡ ወደ፡ አገራችሁ፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፤ እንፈልጋለን።
ወይዘሮ፡ አልማዝ፡ ወንዶቿን፡ ጠየቀቻቸው?	የለም፤ አልጠየቀቻቸውም።
ከሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ጥሩ፡ ምግብ፡ ቤት፡ አለ?	አዎ፤ በጣም፡ ጥሩ፡ ምግብ፡ ቤት፡ አለ።

ጥያቄ	መልስ
የሆነው፡ ሆኖ፡ ነገ፡ እኛ፡ ቤት፡ ትመጣላችሁ?	የለም፤ ነገ፡ መምጣት፡ አንችልም።
ወደ፡ ጎጃም፡ የሚሄደው፡ አውራ፡ ጎዳና፡ ተሠርቷል?	የለም፤ ገና፡ አልተሠራም።
ክቡር፡ ገዢው፡ በጣም፡ ቸር፡ ሰው፡ ይመስሉሃል?	እዎን፤ በጣም፡ ቸር፡ ሰው፡ ናቸው።
ጠላትህን፡ ትወዳለህ?	አልወድም።
የትንሣኤ፡ በዓል፡ መቼ፡ ነው?	የነገ፡ ሳምንት፡ ነው።
ልደት፡ መቼ፡ ነው?	በታህሳስ፡ ሀያ፡ ዘጠኝ፡ ቀን፡ ነው።
ዝናቡ፡ ዘንቦ፡ ማብቃቱ፡ ነው?	የለም፤ ገና፡ ይዘንባል።
ሰዎቹ፡ ሠርተው፡ አበቁ?	የለም፤ ገና፡ ይሠራሉ።
ስንት፡ አውራ፡ ዶሮዎች፡ አሉህ?	አሥር፡ የሚሆኑ፡ አሉኝ።
በጎዳናው፡ ላይ፡ ሰው፡ ይሄድበታል?	የለም፤ አይሄድበትም።
እስከ፡ መስከረም፡ የሚያሸጋግርህ፡ ምግብ፡ አለህ?	አዎ፤ አለኝ።
ባውራው፡ ጎዳና፡ ላይ፡ ብዙ፡ መኪናዎች፡ አይተሃል?	ሠላሳ፡ የሚሆኑ፡ ትላልቅ፡ መኪናዎች፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሲሄዱ፡ አይቻለሁ።
ወንድምህ፡ ቸር፡ ሰው፡ በመሆኑ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ይወደዋል?	ቸር፡ መሆኑን፡ የሚያውቁ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይወዱታል።
ለጠላትህ፡ ቸር፡ ብትሆን፡ ምን፡ ታገኛለህ?	ብዙ፡ ወዳጆች፡ አገኛለሁ።

ወንዙ፡ በክረምት፡ ያሸጋግራል? ዓሎም፣ አያሸጋግርም።

ድርሰት

አልጋው፡ ከተገዛ፡ በኋላ፣ ወዲያው፡ ወደ፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ ቤት፡ ለመውሰድ፡ አልተቻለም። ምክንያቱም፡ አቶ፡ አበበ፡ ባጠገቡ፡ የሚረዳው፡ ሰው፡ ስለሌለ፡ ነው። በማግስቱ፡ አቶ፡ አበበ፡ አልጋውን፡ በመኪና፡ አስጭኖ፡ ወደ፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ ቤት፡ ላከው።

በመጀመሪያ፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ ግማሹን፡ ዋጋ፡ እንደ፡ ቀብድ፡ ከፍለው፡ ስለነበር፣ የቀረበትን፡ ገንዘብ፡ አልጋውን፡ ሲቀበሉ፡ ከፈሉ።

ከዚያ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ አቶ፡ ዓለሙና፡ አቶ፡ አበበ፡ በጣም፡ ስለተዋወቁ፣ አቶ፡ ዓለሙ፡ የሚገዛውን፡ ዕቃዎች፡ ካቶ፡ አበበ፡ ሱቅ፡ ይገዛ፡ ነበር። ከዚያም፡ በላይ፡ ጓደኞቹን፡ ሁሉ፡ እየመጣ፡ ካቶ፡ አበበ፡ ጋር፡ ስላስተዋወቃቸው፣ አቶ፡ አበበ፡ ብዙ፡ ደንበኞች፡ አገኙ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዓለሙ፡ አልጋውን፡ ወዲያው፡ ለምን፡ አልተረከቡም?

አቶ፡ ዓለሙ፡ አልጋውን፡ መቼ፡ ለማግኘት፡ ቻሉ?

አቶ፡ አበበ፡ አልጋውን፡ በምን፡ ላከው?

መጀመሪያ፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ የከፈሉት፡ ገንዘብ፡ ምን፡ ይባላል?

አቶ፡ አበበና፡ አቶ፡ ዓለሙ፡ እንዴት፡ ተዋወቁ?

አቶ፡ ዓለሙ፡ ዕቃውን፡ ሁሉ፡ የሚገዛው፡ ከየት፡ ነበር?

አቶ፡ አበበ፡ እንዴት፡ ብዙ፡ ደንበኞች፡ ለማግኘት፡ ቻሉ?

የቤት፡ ዕቃህን፡ የምትገዛባቸው፡ ሱቆች፡ ስንት፡ ናቸው?

ሠላሳ፡ስድስተኛ፡ትምህርት

ንግግር

ከበደ

አቶ፡ዮሐንስ፡ ካሜሪካ፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡መቼ፡መጣህ?

ጆን

አዲስ፡አበባ፡ከገባሁ፡ሦስት፡ቀኖች፡ሆኖኛል።

ከበደ

ኢትዮጵያ፡ውስጥ፡ብዙ፡ጊዜ፡መቆየት፡ ታስባለህ?

ጆን

አዎን፣ ጠቅላይ፡ግዛቶቹን፡ሁሉ፡ እየተዘዋወርኩ፡ እስካይ፡ድረስ፡ እቆያለሁ።

ከመሆኑ፡ኢትዮጵያ፡ ስንት፡ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ አሉዋት?

ከበደ

ኢትዮጵያ፡ አሥራ፡ አራት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ አሉዋት። ስማቸውም፡ በጌምድር፣ ጐጃም፣ ትግሬ፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ አሩሲ፣ ሲዳሞ፣ ከፋ፣ ኢሊባቦር፣ ገሙጎፋ፣ ወለጋ፣ ሐረርጌ፣ ኤርትራና፡ ባሌ፡ ናቸው።

ጆን

ከጠቅላይ፡ግዛቶች፡ሁሉ፡በስፋት፡የትኛው፡ይበልጣል?

ከበደ

በስፋት፡ከሁሉ፡የሚበልጠው፡ጠቅላይ፡ግዛት፡ ሐረርጌ፡ ነው።

ከሁሉም፡የሚያንሰው፡ጠቅላይ፡ግዛት፡ደግሞ፡አሩሲ፡ነው።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ኢትዮጵያ፡ስንት፡ጠቅላይ፡ግዛቶች፡ አሉዋት?	ኢትዮጵያ፡ አሁን፡ አሥራ፡ አራት፡ ጠቅላይ፡ግዛቶች፡አሉዋት።

ጥያቄ	መልስ
ከአሥር፡ ዓመት፡ በፊት፡ ስንት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ነበሩዋት?	አሥራ፡ ሁለት፡ ብቻ፡ ነበሩ።
ኤርትራውያን፡ በሙሉ፡ አማርኛ፡ ያውቃሉ?	የለም፣ ሁሉም፡ አይደሉም።
ኤርትራ፡ የምትገኘው፡ በምሥራቅ፡ ኢትዮጵያ፡ ነው፡ ወይስ፡ በምዕራብ?	የምትገኘው፡ በሰሜን፡ ነው።
ከፍተኛ፡ ተራራዎች፡ የሚገኙት፡ የት፡ ነው?	በበጌምድር፡ ውስጥ፡ ይመስለኛል።
በመካከለኛው፡ ኢትዮጵያ፡ የሚገኙት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ እነማን፡ ናቸው?	ሐረርጌ፣ ወሎ፣ ሸዋና፡አሩሲ፡ ናቸው።
በምሥራቅ፡ እነማን፡ ይገኛሉ?	ሐረርጌና፡ ባሌ፡ ናቸው።
በምዕራብስ፡ በኩል፡ ያሉት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ማን፡ ማን፡ ይባላሉ?	ከፋ፣ ወለጋና፡ ኢሉባቦር፡ ናቸው።
ገሙጐፋና፡ ሲዳሞ፡ በየት፡ በኩል፡ ናቸው?	እነሱ፡ በስተ፡ ደቡብ፡ ናቸው።
የጣና፡ ሐይቅ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ ትልቅ፡ ሐይቅ፡ ነው።
የጣና፡ ሐይቅ፡ በየትኛው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ነው?	በጐጃምና፡ በበጌምድር፡ መካከል፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ፍራፍሬ፡ ይበቅላል?	አዎ፣ ይበቅላል። አብዛኛው፡ ግን፡ ሐረርጌ፡ ውስጥ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ከሁሉም፡ በስፋት፡ የሚበቅለው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ማን፡ ነው?	ሐረር፡ ነው።
ከሁሉም፡ በስፋት፡ የሚያንሰው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ማን፡ ነው?	አሩሲ፡ ነው።
አብዛኛው፡ ቡና፡ የሚመጣው፡ ከየት፡ ነው?	ከከፋ፣ ሲዳሞና፡ ሐረር፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ወንዞች፡ ይገኛሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ ወንዞች፡ ይገኛሉ።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ይሞቃል?	ካንዳንድ፡ ዝቅተኛ፡ ቦታዎች፡ በስተቀር፡ አብዛኛው፡ ቦታ፡ አይሞቅም።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ያብዛኛው፡ ሰው፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?	ያብዛኛው፡ ሰው፡ ሥራ፡ ግብርና፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የምትሸጣቸው፡ ምን፡ ዓይነት፡ ነገሮች፡ ናቸው?	ቆዳ፡ ቡናና፡ የዘይት፡ እህሎች፡ ናቸው።
ሥጋስ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ትሸጣለች?	አዎ፣ መሸጥ፡ ጀምራለች።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በሚገኙት፡ ወንዞች፡ ላይ፡ መርከቦችና፡ ጀልባዎች፡ ይሄዱባቸዋል?	በጥቂቶች፡ ወንዞች፡ ጀልባዎች፡ ይሄዱባቸዋል። መርከብ፡ የሚሄድባቸው፡ ወንዞች፡ ግን፡ የሉም።
የኢትዮጵያ፡ ክረምት፡ እንደ፡ አሜሪካ፡ ክረምት፡ ይበርዳል?	የለም፣ አይበርድም።

ጥያቄ	መልስ
በኢትዮጵያ፡ ወንዞችና፡ ሐይቆች፡ ብዙ፡ ዓሣ፡ ይገኝባቸዋል?	አዎ፣ አብዛኛዎቹ፡ ውስጥ፡ ይገኝባቸዋል።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚበቅሉትን፡ ፍራፍሬዎች፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ በምን፡ ትልካላችሁ?	በመርከብና፡ ኣይሮፕላን፡ ነው።
አዲሱ፡ አውራ፡ ጐዳና፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ ስንት፡ መኪናዎች፡ ያስኬዳል?	አራት፡ መኪናዎች፡ ያስኬዳል።
ያገሩ፡ ወንዝ፡ ጀልባ፡ ያስኬዳል?	አዎ፣ ያስኬዳል።
ኢትዮጵያ፡ ስንት፡ ወደቦች፡ አሉዋት?	ሁለት፡ ትልልቅ፡ ወደቦች፡ አሉዋት።
የወደቦቹ፡ ስም፡ ማን፡ ማን፡ ይባላል?	አሰብና፡ ምፅዋ፡ ይባላል።
የኢትዮጵያ፡ ወደቦች፡ ሁሉ፡ ጀልባ፡ ያስኬዳሉ?	ሁሉም፡ ትናንሽ፡ ጀልባዎች፡ ማስሄድ፡ ይችላሉ።
በአዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ አቅራቢያ፡ ፍራፍሬዎች፡ ይበቅላሉ?	ብዙ፡ ፍራፍሬዎች፡ ይበቅላሉ።
ያገሩ፡ ወንዝ፡ ከኢትዮጵያ፡ ወጥቶ፡ ወዴት፡ ይሄዳል?	ከኢትዮጵያ፡ ወጥቶ፡ ወደ፡ ሱዳን፡ ይሄዳል።
በኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ሁሉ፡ ግብርና፡ የተለመደ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ከውጭ፡ አገሮች፡ ብዙ፡ ቆዳ፡ ትሸጣለች?	አዎ፣ ብዙ፡ ቆዳ፡ ትሸጣለች።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚበቅለው፡ የእህል፡ ዓይነት፡ ብዙ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ከጐጃም፡ ወደ፡ በጌምድር፡ በጣና፡ ሐይቅ፡ ላይ፡ በመርከብ፡ መሄድ፡ ይቻላል?	በጣና፡ ሐይቅ፡ ላይ፡ መርከብ፡ የለም። ነገር፡ ግን፡ ትልልቅ፡ ጀልባዎች፡ ስላሉ፤ በነሱ፡ መሄድ፡ ይቻላል።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ጀልባ፡ መከራየትና፡ መንሸርሸር፡ ይቻላል?	አዎ፤ ይቻላል።
አባይ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ወንዝ፡ ነው?	አዎ፤ ከዓለም፡ ትልልቅ፡ ወንዞች፡ አንዱ፡ እሱ፡ ነው።
ከገበያው፡ የመጡትን፡ ሰዎች፡ የምታውቃቸው፡ ይመስልሃል?	የለም፤ የማውቃቸው፡ አይመስለኝም።
ትልቁን፡ መጽሐፍ፡ የምትገዛው፡ ይመስልሃል?	አዎ፤ እገዛው፡ ይሆናል።
የዛሬ፡ አሥር፡ ዓመት፡ ሰው፡ ወደ፡ ጨረቃ፡ የሚሄድ፡ ይመስልሃል?	አዎ፤ ምናልባት፡ ከአሥር፡ ዓመት፡ በፊት፡ ይሄድ፡ ይሆናል።
ላንተ፡ ስልክ፡ የሚደውል፡ ይመስልሃል?	አዎ፤ የሚደውል፡ ይመስለኛል።
ለማ፡ ፈተናውን፡ የሚወስድ፡ ይመስልሃል?	የለም፤ የሚወስድ፡ አይመስለኝም።
በሚመጣው፡ ዓመት፡ ወዳገራችን፡ የምንመለስ፡ ይመስልሃል?	የለም፤ አንመለስም።
ለዚህ፡ ጥያቄዎች፡ የሚጠይቁ፡ ይመስልሻል?	የለም፤ የሚጠይቁ፡ አይመስለኝም።
ወደፊት፡ አዲስ፡ ባንክ፡ የሚከፍቱ፡ ይመስላችኋል?	አዎ፤ ይከፍታሉ።

ጥያቄ	መልስ
ዝናብ፡ የሚዘንብ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይዘንብ፡ ይሆናል።
ጠጩን፡ የተነጠ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ተነጥቋል።
ከበደ፡ ሊጁሌ፡ የሚያጠጣ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ያጠጣል።
እናልማዝ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ሽርሽር፡ የሚሄዱ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይሄዳሉ።
[illegible]ንከማ፡ አስተማሪ፡ ለመሆን፡ የሚችሉ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይችላሉ።
ዕቃውን፡ የሚሸከምልህ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይሸከምልኛል።
መኪናውን፡ ለኛ፡ የሚሸጥልን፡ ይመስልሃል?	የለም፣ አይሸጥልንም።
ለጁ፡ እንግዶን፡ የሚጠብቅ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይጠብቅ፡ ይሆናል።
እቴ፡ ዮሐንስ፡ ገንዘብ፡ የሰጡልህ፡ መሰሉሃል?	አዎ፣ የሰጡልኝ፡ መሰሉኛል።
ለማ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ የሄደ፡ መሰለሃል?	አዎ፣ የሄደ፡ መሰለኛል።
ጀርመንኛ፡ የሚያውቅ፡ መሰለሃል?	አዎ፣ የምታውቅ፡ መሰለኝ፡ ነበር።
ለማ፡ ኅይሠሌ፡ የከበረ፡ መሰለህ፡ ነበር?	የለም፣ አልመሰለኝም።
ሳንሠሌ፡ ገንዘብ፡ የምታገኝ፡ መሰለሃል?	የለም፣ አልመሰለኝም።

ጥያቄ	መልስ
መኪናቸውን፡ የሚለውጡ፡ መሰለህ?	አዎ፣ መስሎኝ፡ ነበር።
ቡና፡ የምንጠጣ፡ መስሎህ፡ ነበር?	አዎ፣ የምትጠጡ፡ መስሎኝ፡ ነበር።
እነዮሐንስ፡ ምሳቸውን፡ የበሉ፡ መስሎሃል?	አዎ፣ የበሉ፡ መስሎኛል።
ለማ፡ የመኪናውን፡ ጎማ፡ የቀየረ፡ መስሎህ፡ ነበር?	አዎ፣ የቀየረው፡ መስሎኝ፡ ነበር።
አስተማሪዎ፡ ጥዋት፡ የሚመጣ፡ መስለዎት፡ ነበር?	አዎ፣ መስሎኝ፡ ነበር።
ትናንት፡ ዝናብ፡ የሚዘንብ፡ መስሎህ፡ ነበር?	አዎ፣ የሚዘንብ፡ መስሎኝ፡ ነበር።
ተማሪዎቹ፡ ሕግ፡ የጣሱ፡ መስሏችሁ፡ ነበር?	አዎ፣ መስሎን፡ ነበር።
ልጅሽ፡ ትምህርቱን፡ የቀጠለ፡ መስሎሽ፡ ነበር?	አዎ፣ የቀጠለ፡ መስሎኝ፡ ነበር።
ዛሬን፡ የቀረጽሁት፡ መስሎህ፡ ነበር?	አዎ፣ የቀረጽኸው፡ መስሎኝ፡ ነበር።

ድርሰት

ዮሐንስ፡ የተባለ፡ አሜሪካዊ፡ ኢትዮጵያን፡ ለመጐብኘት፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ መጣ። አዲስ፡ አበባ፡ ገብቶ፡ ጥቂት፡ ቀናት፡ ያህል፡ ከቆየ፡ በኋላ፣ ሌሎቹን፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ለመጐብኘት፡ ፈለገ።

ካዲስ፡ አበባ፡ ከመነሳቱ፡ በፊት፣ ስለ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶቹና፡ ስለ፡ አቀማመጣቸው፡ ለማወቅ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ጠየቀው። አቶ፡ ከበደም፡ በጠቅላላው፡ አስረዳው።

አሁን፡ ኢትዮጵያ፡ አሥራ፡ አራት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ አሉዋት። ስማቸውም፡ በጌምድር፣ ጐጃም፣ ትግሬ፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ አሩሲ፣ ሲዳሞ፣ ከፋ፣ ኢሉባቦር፣ ገሙጐፋ፣ ወለጋ፣ ሐረርጌ፣ ኤርትራና፡ ባሌ፡ ይባላል።

አዲስ፡ አበባ፡ የሚገኘው፡ በሸዋ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ነው። በሸዋ፡ ዙሪያ፡ ያሉት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ አሩሲ፣ ወሎ፣ ጐጃም፣ ወለጋና፡ ሐረርጌ፡ ናቸው። ሐረርጌ፡ ከሁሉም፡ ሰፊ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ነው። አሩሲ፡ ግን፡ ከሁሉ፡ ያነሰ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ነው።

ዮሐንስ፡ እንደዚህ፡ ያለውን፡ ወሬ፡ ጠይቆ፡ ከተረዳ፡ በኋላ፣ ዕቃውን፡ ይዞ፡ ጉዞውን፡ ጀመረ።

ጥያቄዎች

ዮሐንስ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነው?

ዮሐንስ፡ ከየት፡ መጣ?

ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ለምን፡ መጣ?

ዮሐንስ፡ አቶ፡ ከበደን፡ ምን፡ ጠየቀው?

የኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ስንት፡ ናቸው?

ስማቸው፡ ማን፡ ማን፡ ይባላል?

አዲስ፡ አበባ፡ በየትኛው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ይገኛል?

በሸዋ፡ ዙሪያ፡ የሚገኙት፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ እነማን፡ ናቸው?

ከጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ሁሉ፡ ሰፊ፡ የትኛው፡ ነው?

ከጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ሁሉ፡ የሚያንሰው፡ የትኛው፡ ነው?

አንተ፡ ኢትዮጵያን፡ ከመጐብኘት፡ ትፈልጋለህ?

ብዙ፡ አገሮች፡ ጐብኝተሃል?

ሠላሳ፡ሰባተኛ፡ትምህርት

ንግግር

ጆን

የዩንጓንጊ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ዓየር፡ እንዳዲስ፡ አበባ፡ መስካኅም፡ ነው?

ከበደ

የለም፤ የዩንጓንጊ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ዓየር፡ የተለየ፡ ነው።

ጆን

ከኢትዮጵያ፡ የትኛው፡ ክፍል፡ በጣም፡ ይሞቃል?

ከበደ

እብዛኛውን፡ ጊዜ፡ በቀይ፡ ባሕር፡ ዙሪያና፡ በዝቅተኛ፡ ቦታዎች፤ ማለት፡ በቆላው፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ይሞቃል።

በከፍተኛ፡ ቦታዎች፤ ማለት፡ በደጋው፡ ቀዝቃዛ፡ ነው።

በመካከለኛው፡ ቦታ፤ ማለት፡ በወይና ደጋው፡ የሚገኘው፡ ዓየር፡ ተስማሚ፡ ነው።

ጆን

ኢትዮጵያ፡ ስንት፡ የክረምት፡ ወራት፡ አሉዋት?

ከበደ

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ሁለት፡ የክረምት፡ ወራቶች፡ አሉ። ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ እናንተ፡ ክረምት፡ በረዶ፡ የለውም።

ጆን

በረዶ፡ አይተው፡ ያውቃሉ?

ከበደ

የለም፤ እስካሁን፡ ድረስ፡ በረዶ፡ አይቼ፡ አላውቅም።

ጆን

በጣም፡ በኃይል፡ ይዘንባል?

ከበደ

አዎ፤ እንዳንዴ፡ ኃይለኛ፡ ዝናብ፡ ይዘንባል። ከዝናቡም፡ ኃይለኛነት፡ የተነሳ፤ ወንዞች፡ በጣም፡ ይሞላሉና፡ ንብረት፡ ያጠፋሉ።

ጆን

አሁን፡ የዝናብ፡ ወራት፡ ቀርቦአል። ስለዚህ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶቹን፡ በመኪና፡ እየተጓዝሁ፡ ለማየት፡ እድገኛ፡ ይመስልዎታል?

ከበደ

በክረምት፡ ሆነ፡ በበጋውም፡ ኢትዮጵያ፡ ተራራማ፡ አገር፡ ከመሆንዋ፡ የተነሳ፡ ብዙ፡ መኪናዎች፡ መንገዶች፡ የአቀማመጥና፡ በአደርጎችን፡ በዛዱ፡ ይገኛል።

ጆን

ከመሆኑ፡ የኢትዮጵያ፡ ዋና፡ መንገድ፡ በየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ዋና፡ ከተሞች፡ ይርቃሉ?

ከበደ

አዎ፡ በየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ዋና፡ ከተሞች፡ ሁሉ፡ ይርቃሉ።

ጆን

እንግዲያስ፡ በክረምትን፡ እጓዛለሁ። ላደረጋልኝ፡ እርዳታ፡ አመሰግናለሁ። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ። መልካም፡ ጉዞ፡ እመኝልዎታለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ያሜሪካንን፡ አገር፡ ጎብኝተው፡ ያውቃሉ?	ወደፊት፡ መጎብኘት፡ እፈልጋለሁ። እነጂ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ጎብኝቼው፡ አላውቅም።
ያዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ አቀማመጥ፡ ያውቃሉ?	የምኖርበትን፡ የከተማዋን፡ አቀማመጥ፡ በደንብ፡ አላውቅም።

ጥያቄ	መልስ
ስለልጅዎ፡ ወሬ፡ ሰምተው፡ ያውቃሉ?	የለም፡ ሰምቼ፡ አላውቅም።
የምትሄዱበትን፡ ቦታ፡ አይታችሁት፡ ታውቃላችሁ?	የለም፡ አይተነው፡ አናውቅም።
እቆላ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ኖራችሁ፡ ታውቃላችሁ?	የለም፡ ኖረን፡ አናውቅም።
እከፍተኛ፡ ቦታ፡ ላይ፡ ለመኖር፡ ፈልገሽ፡ ታውቂያለሽ?	የለም፡ ፈልጌ፡ አላውቅም።
ቀዝቃዛ፡ ቡና፡ ጠጥተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፡ ጠጥቼ፡ አላውቅም።
ያዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ዓየር፡ እንደወይና፡ ደጋ፡ ነው?	እኔ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሄጄ፡ አላውቅም። ስለዚህ፡ ስላየሩ፡ ልነግርህ፡ አልችልም።
በክረምቱ፡ ወራት፡ ወዳዲስ፡ አበባ፡ ሄዳችሁ፡ ታውቃላችሁ?	የለም፡ ሄደን፡ አናውቅም።
ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ በረዶውን፡ ወደኸው፡ ታውቃለህ?	ወድጄው፡ አላውቅም።
ኃይለኛ፡ ዝናብ፡ ሲዘንብ፡ አይታችሁ፡ ታውቃላችሁ?	አዎ፡ አይተናል።
ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ የክረምቱን፡ ወራት፡ አይተውት፡ ያውቃሉ?	አዎ፡ ባለፈው፡ የክረምት፡ ወራት፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ነበርኩ።
እዋሽንግተን፡ ውስጥ፡ መንገድ፡ ጠፍቶህ፡ ያውቃል?	አንድ፡ ጊዜ፡ ጠፍቶብኝ፡ ነበር።
ንብረትህ፡ ጠፍቶብህ፡ ያውቃል?	አዎ፡ ጠፍቶብኝ፡ ያውቃል።

ጥያቄ	መልስ
በቀን፡ ከሃምሳ፡ ብር፡ በላይ፡ እንዳጠፋችሁ፡ ታውቃላችሁ?	አዎ፣ አንዳንዴ፡ እናጠፋለን።
የመኪና፡ አደጋ፡ ደርሶብህ፡ ያውቃል?	የለም፣ ደርሶብኝ፡ አያውቅም።
ከተራራ፡ ላይ፡ ሆነህ፡ ከተማውን፡ አይተኸው፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አንድ፡ ጊዜ፡ አይቼዋለሁ።
ባይሮፕላን፡ ሄደህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ሄጃለሁ።
የኢትዮጵያ፡ ያየር፡ መንገድ፡ ከኢትዮጵያ፡ ውጭ፡ ሄዶ፡ ያውቃል?	አዎ፣ ብዙ፡ ቦታዎች፡ ሄዷል።
በእኛ፡ ቤት፡ በኩል፡ ሲያልፉ፡ አይተሃቸው፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ባለፈው፡ ቅዳሜ፡ ሲያልፉ፡ አይቻቸዋለሁ።
መኪናህን፡ አረንጓዴ፡ ቀለም፡ ቀብተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ ቀብቼው፡ አላውቅም።
ራስህን፡ አሞህ፡ ያውቃል?	ከአንድ፡ ዓመት፡ በፊት፡ አሞኝ፡ ነበር።
ቤታችሁን፡ በዚህ፡ ዓመት፡ አሳድሳችሁት፡ ታውቃላችሁ?	አዎ፣ አሳድሰነው፡ ነበር።
እንግሊዝኛ፡ ቋንቋ፡ አስተምረህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አንድ፡ ዓመት፡ አስተምሬያለሁ።
ባማርኛ፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ድርሰት፡ አዘጋጅተህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አዘጋጅቻለሁ።
አሜሪካ፡ ከመጣህ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሄደህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሄጃለሁ።
አጋሌሽ፡ ውስኪ፡ ሠርተህ፡ ታውቃለህ?	አሁን፡ የምሠራው፡ አጋሌሽ፡ ውስኪ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ከኢትዮጵያ፡ ከመጣህ፡ ጀምሮ፡ ወደ፡ አገርህ፡ ደብዳቤ፡ ጽፈህ፡ ታውቃለህ?	ብዙ፡ ጊዜ፡ ጽፌ፡ አላውቅም።
በፈረስ፡ ተጓዝህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ተጓዤ ያለሁ።
ከዚህ፡ በፊት፡ እዚህ፡ መጥተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ መጥቼ፡ አላውቅም።
ገማርኛ፡ የተጻፈ፡ መጽሐፍ፡ አንብበህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ብዙ፡ ጊዜ፡ አንብቤያለሁ።
ለውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሥራ፡ ሠርተው፡ ያውቃሉ?	የዛሬ፡ ዓመት፡ ካሥር፡ ሳምንት፡ ያህል፡ ሠርቼያለሁ።
ከወዳጆቹ፡ ጋር፡ ኖሮ፡ ያውቃል?	ሥራ፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ ከወዳጆቹ፡ ጋር፡ ይኖር፡ ነበር።

ድርሰት

ኢትዮጵያ፡ የምትገኘው፡ በሰሜን፡ ምሥራቅ፡ አፍሪካ፡ ውስጥ፡ ነው። የሚያዋስኗትም፡ አገሮች፣ በሰሜንና፡ በምዕራብ፡ ሱዳን፣ በደቡብ፡ ኬንያ፣ በምሥራቅ፡ ቀይ፡ ባሕርና፡ የሶማሌ፡ ሬፑብሊክ፡ ናቸው።

የኢትዮጵያ፡ ስፋት፡ አራት፡ መቶ፡ ሰማንያ፡ ሺ፡ አስኴር፡ ማይሎች፡ ሲሆን፡ የሕዝብዋ፡ ቁጥር፡ በሀያና፡ በሀያ፡ ሁለት፡ ሚሊዮን፡ መካከል፡ ይገመታል።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ወንዞች፡ ይፈሳሉ።

የኢትዮጵያ፡ ያየር፡ ጠባይ፡ በሦስት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላል። የመጀመሪያው፡

ክፍል፡ ደጋ፡ ይባላል። ይህም፡ ክፍል፡ በጣም፡ ከፍተኛና፡ ቀዝቃዛ፡ ነው። ሁለተኛው፡ ክፍል፡ ወይናደጋ፡ ይባላል። የዚህ፡ ቦታ፡ ዓየር፡ በጣም፡ ጥሩና፡ ለጤና፡ ተስማሚ፡ ነው። ሦስተኛው፡ ክፍል፡ ቆላ፡ ይባላል። ይህ፡ ቦታ፡ ዝቅ፡ ያለና፡ ዓየሩ፡ ሙቀት፡ ነው።

ጥያቄዎች

ኢትዮጵያ፡ የምትገኘው፡ የት፡ ነው?

ኢትዮጵያን፡ የሚያዋስኑዋት፡ እነማን፡ ናቸው?

ሱዳን፡ የሚገኘው፡ ከኢትዮጵያ፡ ምሥራቅ፡ ነው?

የኢትዮጵያ፡ ስፋት፡ ስንት፡ ነው?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሕዝብ፡ ይገኛል?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ተራራዎች፡ ይገኛሉ?

ስንት፡ ያየር፡ ጠባዮች፡ ይገኛሉ?

ስማቸውን፡ ጥሩ።

ደጋው፡ ከወይናደጋው፡ በምን፡ ይለያያል?

የቆላውንና፡ የደጋውን፡ ልዩነት፡ አስረዳ?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በየትኛው፡ ክፍል፡ ለመኖር፡ ትወዳለህ?

ሠላሳ፡ ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

አብዛኛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ምን፡ ይሠራል?

ከበደ

አብዛኛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የሚኖረው፡ በግብርና፡ ነው።

ጆን

ዘመናዊው፡ የርሻ፡ ሥራ፡ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው?

ከበደ

ዘመናዊው፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ ገና፡ በጣም፡ የተለመደ፡ አይደለም። ነገር፡ ግን፡ አሁን፡ ባንዳንድ፡ ቦታዎች፡ ተጀምሮአል።

ጆን

አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ የሚያበቅሉት፡ ምን፡ ዓይነት፡ እህል፡ ነው?

ከበደ

ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ጥራጥሬዎችና፡ ፍራፍሬዎች፡ እንዲሁም፡ አትክልቶች፡ ይበቅላሉ። ከዚህም፡ በላይ፡ ጤፍ፡ የሚባል፡ አንድ፡ ዓይነት፡ እህል፡ አለን።

ጆን

ጥራ፡ ጥሬ፡ ስትል፡ ምን፡ ማለትህ፡ ነው?

ከበደ

ጥራጥሬ፡ የሚባሉት፡ እንደ ባቄላ፣ አተር፣ ስንዴ፣ አጃ፣ ገብስ፣ በቆሎ፡ ያሉት፡ ናቸው።

ደግሞ፡ ለዘይት፡ የሚሆኑ፡ እህሎች፡ እንደ ኑግ፣ ተልባ፣ ጉሎ፣ ሱፍ፡ ያሉት፡ ናቸው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
በሰሜን፡ ምሥራቅ፡ የኢትዮጵያ፡ ወሰን፡ እንዴት፡ ነው?	በሰሜን፡ ምሥራቅ፡ ወሰንዋ፡ ቀይ፡ ባሕር፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሐይቆዎች፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ አሉ።
ያገርዎ፡ ዓየር፡ ጠባይ፡ እንዴት፡ ነው?	በጣም፡ ጥሩ፡ አይደለም።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ደጋው፡ ብርድ፡ ነው?	በጣም፡ ብርድ፡ አይደለም።
የአዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ከፍተኛ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ ከፍተኛ፡ ነው።
እቆላው፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ እህል፡ ይበቅላል?	ባቄላ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ሩዝና፡ አተር፡ ይበቅላል።
ስለ፡ ግብርና፡ የሚማሩ፡ ኢትዮጵያውያን፡ እዚህ፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ተማሪዎች፡ አሉ።
አዲስ፡ የግብርና፡ ዘዴ፡ አገሪቷን፡ ይረዳ፡ ይመስለሃል?	አዎ፣ የሚረዳት፡ ይመስለኛል።
ከጤፍና፡ ከበቆሎ፡ እንጀራ፡ የትኛው፡ የተለመደ፡ ነው?	የጤፍ፡ እንጀራ፡ ነው።
አረቄ፡ የሚሠራው፡ ከምን፡ ዓይነት፡ ጥራጥሬ፡ ነው?	ከገብስ፣ ከበቆሎ፣ ከስንዴና፡ ካጃ፡ ነው።
ኑግ፡ ለምን፡ ይጠቀማል?	ለዘይት፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
ሌላስ፡ ለዘይት፡ የሚሆኑ፡ ምን፡ ዓይነት፡ እህሎች፡ አሉ?	ሱፍ፣ ተልባና፡ ጉሎ፡ ናቸው።

ጥያቄ	መልስ
እነዚህ፡ የዘይት፡ እህሎች፡ የት፡ ቦታ፡ ይበቅላሉ?	በብዙ፡ ቦታዎች፡ ይበቅላሉ።
ከመሆኑ፡ ገበሬዎች፡ እነዚህን፡ የዘይት፡ እህሎች፡ ወደፊት፡ በብዙ፡ ማብቀል፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፣ ማብቀል፡ የሚፈልጉ፡ ይመስለኛል።
ከጐጃም፡ ወደ፡ በጌምድር፡ እህል፡ በጀልባ፡ ልካችሁ፡ ታውቃላችሁ?	አንዳንዴ፡ እንልካለን።
የዘይት፡ እህሎችን፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ትሸጣላችሁ?	አዎ፣ እንሸጣለን።
ለዳቦ፡ የሚሆኑ፡ እህሎች፡ የትኞቹ፡ ናቸው?	ስንዴና፡ አጃ፡ ናቸው።
ጤፍ፡ ከኢትዮጵያ፡ ውጭ፡ የታወቀ፡ እህል፡ ነው?	ከኢትዮጵያ፡ ውጭ፡ የታወቀ፡ አይመስለኝም።
ነገሬችሁ፡ ባቄላ፣ አተር፣ ስንዴ፣ አጃና፡ ገብስ፡ ያበቅላል።	አዎ፣ ማናቸውንም፡ ዓይነት፡ እህል፡ ያበቅላል።
መሬትህ፡ ወሰን፡ ሸለቆው፡ ነው?	አዎ፣ ወሰኑ፡ ሸለቆው፡ ነው።
ኖራችሁበት፡ አገር፡ ዓየር፡ ጠባይ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነበር?	አዎ፣ በጣም፡ ጥሩ፡ ነበር።
ከደጋውና፡ ከቆላው፡ ዓየር፡ ጠባይ፡ የትኛውን፡ ወደድኸው?	የደጋው፡ ዓየር፡ በጣም፡ ቀዝቃዛ፡ ስለነበር፡ አልወደድሁትም። የቆላው፡ ግን፡ ስለሚሞቅ፡ ደህና፡ ነበር።
በዝቅተኛው፡ ቦታ፡ ውስጥ፡ ጥራጥሬ፡ ማብቀል፡ ይቻላል?	አዎ፣ ብዙ፡ ዓይነት፡ ጥራጥሬዎች፡ ማብቀል፡ ይቻላል።

ጥያቄ	መልስ
ግብርና፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ሥራ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ በጣም፡ ጥሩ፡ ይመስለኛል።
ጤፍ፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሸጣል?	የለም፣ አገር፡ ውስጥ፡ እንጂ፣ ወደ፡ ውጭ፡ አይሸጥም።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ኑግ፣ ተልባና፡ ጉሎ፡ ይበቅላሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ዓይነት፡ እህሎች፡ ይበቅላሉ።
የሜሪካ፡ ሕዝብ፡ ፍራፍሬ፡ መብላት፡ ይወዳል?	አዎ፣ በጣም፡ ይወዳል።
ያባይ፡ ወንዝ፡ ከየት፡ እንደሚመነጭ፡ ታውቃላችሁ?	የለም፣ አናውቅም።
ባባይ፡ ወንዝ፡ ላይ፡ ብዙ፡ መርከቦችና፡ ጀልባዎች፡ ይሄዳሉ?	የለም፣ አይሄዱም።
ኢትዮጵያ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ የምትሸጣቸው፡ ቆዳዎች፡ ምን፡ ዓይነት፡ ናቸው?	ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ናቸው።
ኢትዮጵያ፡ ጀልባና፡ መርከብ፡ ትሠራለች?	ትንንሽ፡ ጀልባዎች፡ መሥራት፡ ትችላለች። መርከብ፡ ግን፡ መሥራት፡ አትችልም።
ከወይናደጋና፡ ከቆላ፡ ዓየር፡ የትኛውን፡ ይወዳሉ?	ለኔ፡ የወይናደጋው፡ ዓየር፡ ይስማማኛል።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ንብረት፡ አለህ?	ብዙ፡ አይደለም፡ እንጂ፡ አለኝ።

ድርሰት

ኢትዮጵያ፡ በኢንዱስትሪ፡ የተራመደች፡ አገር፡ ስላልሆነች፣ አብዛኛው፡ ሕዝቧ፡ የሚኖረው፡ በግብርና፡ ነው። ከመቶ፡ ዘጠና፡ አምስት፡ የሚሆነው፡ ሕዝብ፡ በርሻ፡ ላይ፡ ይገኛል።

ያሁኑ፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ ከጥንቱ፡ በጣም፡ የተሻሻለ፡ ሆኖአል። ባንዳንዱም፡ ቦታዎች፡ ገበሬዎች፡ የጥንቱን፡ ዘዴዎች፡ ይጠቀሙባቸዋል። ባብዛኛዎቹ፡ ቦታዎች፡ ግን፡ ገበሬዎች፡ አዲሱን፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ በሰፊው፡ ይሠሩበታል። ሆኖም፣ አዲሱን፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ ለጠቅላይ፡ ግዛቶቹ፡ ሁሉ፡ ለማስፋፋት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ ሁሉን፡ ዓይነት፡ እህል፡ ለማብቀል፡ ይችላሉ። አብዛኞቹ፡ ግን፡ የሚያበቅሉት፡ እህል፡ ጤፍ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ስንዴ፣ አጃ፣ ገብስ፣ በቆሎና፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉ፡ ናቸው። ደግሞ፡ ከዘይት፡ የሚሆኑ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ እህሎች፡ ይበቅላሉ።

ጥያቄዎች

ኢትዮጵያ፡ በኢንዱስትሪ፡ የተራመደች፡ አገር፡ ናት?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ዋና፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ያሁኑ፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ እንዴት፡ ነው?

ገበሬዎች፡ የጥንቱን፡ ዘዴ፡ ይጠቀሙበታል?

አዲሱ፡ የርሻ፡ ዘዴ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ይሠራበታል?

የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ ምን፡ ያበቅላሉ?

ስድስት፡ የእህል፡ አይነቶች፡ ጻፍ?

ምን፡ ዓይነት፡ የዘይት፡ እህል፡ ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ይበቅላል?

ሠላሳ፡ ዘጠነኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

አቶ፡ ከበደ፣ የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ ምን፡ ዓይነት፡ ፍራፍሬ፡ እንደሚያበቅሉ፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?

ከበደ

አዎ፣ እንደሎሚ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ትርንጎ፣ መንደሪን፣ ፓፓያ፣ ሮማን፣ ወይን፡ ያሉትን፡ ፍራፍሬዎች፡ ያበቅላሉ።

ከዚሁም፡ በላይ፡ በጫካ፡ ውስጥ፡ እንደ፡ እንጆሪ፣ ቀጋ፡ ያሉ፡ ፍሬዎች፡ ይበቅላሉ።

እንጆሪ፡ በብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ይከፈላል።

ጆን

ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ አትክልት፡ ያበቅላሉ?

ከበደ

በጣም፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ አይደለም። የሆነው፡ ሆኖ፡ ጐመን፣ ድንች፣ ካሮት፣ ሰላጣ፣ ቲማቲምና፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ዱባዎች፡ ይበቅላሉ።

ጆን

ገበሬዎች፡ እነዚህን፡ ነገሮች፡ ለመሸጥ፡ ነው፡ ወይስ፡ ለራሳቸው፡ ምግብ፡ ነው?

ከበደ

ስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ለራሳቸው፡ ብቻ፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ ለመሸጥ፡ ማብቀል፡ ጀምረዋል።

ጆን

ለመሆኑ፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉ?

ከበደ

ኢትዮጵያ፡ በኢንዱስትሪ፡ የሰለጠነች፡ አገር፡ ስላልሆነች፣ ብዙ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉን፡ ብዬ፡ ለመናገር፡ አያስደፍረኝም። ሆኖም፡ አንዳንድ፡ ትንንሽ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አልፎ፡ አልፎ፡ ይገኛሉ።

ጆን	ከበደ
ለምሳሌ፡ ምን፡ምን፡ ዓይነት፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉዋችሁ?	የጥጥ፣ የጫማ፣ የሱካር፣ የምስማር፣ የሳሙና፣ የመጠጥና፡ የብስኩት፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉን።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ አቅራቢያ፡ ብስኩት፡ የሚሠሩበት፡ ኢንዱስትሪ፡ አለ?	አዎ፣ አለ።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ በነበርክበት፡ ጊዜ፡ ብዙ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ ጐበኘህ?	አዎ፣ ብዙ፡ ትላልቅ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ ጐብኝቻለሁ።
ከጐበኘሃቸው፡ አገሮች፡ መካከል፡ በኢንዱስትሪ፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለ፡ ማን፡ ነው?	እኔ፡ ከጐበኘሁዋቸው፡ አገሮች፡ በኢንዱስትሪ፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለው፡ አሜሪካ፡ ነው።
አገርህ፡ ከጥንቱ፡ አሁን፡ ብዙ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉዋት?	አዎን፣ ብዙ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ አሉዋት።
የግብርና፡ ሥራ፡ አገርህ፡ውስጥ፡ እየተስፋፋ፡ ሄዷል?	አዎ፣ ከጥንቱ፡ አሁን፡ እየተስፋፋ፡ ሄዷል።
ከሎሚና፡ ከብርቱካን፡ ጭማቂ፡ የሚሠሩ፡ መጠጦች፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ መጠጦች፡ ይሠራሉ።
ሎሚና፡ ትርንጐ፡ ይመሳሰላሉ?	የለም፣ በጣም፡ የተለያዩ፡ ፍሬዎች፡ ናቸው።

ጥያቄ	መልስ
ብዙ፡ ብርቱካን፡ የሚያበቅል፡ ገበሬ፡ ደህና፡ ገንዘብ፡ ማግኘት፡ ይችላል፡ ይመስልሃል?	አዎን፤ ብርቱካን፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ሊያመጣ፡ ይችላል።
ትርንጐ፤ መንደሪን፤ ብርቱካን፤ ፓፓያና፡ ሮማን፡ በየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ይገኛሉ?	ሁሉም፡ አንድ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ አይበቅሉም። ሆኖም፡ በየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ቢያንስ፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ፍሬ፡ ይገኝበታል።
ገበሬዎች፡ እንጆሪና፡ ቀጋ፡ ለብዙ፡ ይተክላሉ?	አንዳንድ፡ ገበሬዎች፡ ጥቂት፡ እንጆሪና፡ ቀጋ፡ ይተክላሉ።
ገበሬዎች፡ ጐመን፤ ድንች፤ ካሮት፤ ሰላጣ፤ ቲማቲምና፡ ዱባ፡ ያበቅላሉ፡	አዎን፤ ብዙ፡ ገበሬዎች፡ እነዚህን፡ አትክልቶች፡ ያበቅላሉ።
ጥጥ፡ ከውጭ፡ አገር፡ ትገዛላችሁ፤ ወይስ፡ ለውጭ፡ አገር፡ ትሸጣላችሁ?	እኛ፡ ከውጭ፡ አገር፡ እንገዛለን።
የሎሚ፡ ጭማቂ፡ መጠጣት፡ ትፈልጋለህ?	የለም፤ የሎሚ፡ ጭማቂ፡ አልወድም።
ጥቂት፡ ሙዝ፡ መብላት፡ ትወዳለህ?	የለም፤ አልወድም።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ትርንጐ፡ አይተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፤ አይቼ፡ አላውቅም።
ከሱቅ፡ የብርቱካን፡ ጭማቂ፡ ገዛህ?	የለም፤ አልገዛሁም። አሁን፡ መሄድና፡ መግዛት፡ እፈልጋለሁ።
የሮማንና፡ የወይን፡ ፍሬ፡ ይመሳሰላሉ?	የለም፤ የተለያዩ፡ ናቸው።
ስንት፡ ዓይነት፡ ጐመንና፡ ድንች፡ እንድገዛ፡ ትፈልጋለህ?	ሁለት፡ ዓይነት፡ ጐመንና፡ ሁለት፡ ዓይነት፡ ድንች፡ ግዛ።

ጥያቄ	መልስ
በሳምንት፡ ስንት፡ ዓይነት፡ ፍሬፍሬዎች፡ ትበላለህ?	ሦስት፡ ዓይነት፡ ፍሬፍሬዎች፡ አበላለሁ።
ሁልጊዜ፡ ከራት፡ በፊት፡ ሰላጣና፡ ቲማቲም፡ ትበላላችሁ?	ሁልጊዜ፡ አይደለም። ነገር፡ ግን፡ አንዳንዴ፡ እንበላለን።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ድንች፡ በየቦታው፡ ይበቅላል?	ምንም፡ እንኳን፡ በጥቂት፡ ቦታዎች፡ ባይበቅል፡ ባብዛኛው፡ ቦታዎች፡ ይበቅላል።
ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ዓይነት፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዱባዎች፡ ይገኛሉ?	በውነቱ፡ አላውቅም።
ሠላጣ፡ ከቲማቲም፡ ጋር፡ ይወዳሉ?	አዎን፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
ዱባ፡ ምን፡ ዓይነት፡ መልክ፡ አለው?	ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ መልክ፡ አለው።
የሎሚ፡ ጭማቂ፡ ከስኳር፡ ጋር፡ ይጣፍጣል?	አዎን፡ በጣም፡ ይጣፍጣል።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ቀጋ፡ ይበቅላል?	የለም፡ እኔ፡ አላየሁም።
ወይን፡ ገዝታችሁ፡ መብላት፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፡ እንገዛና፡ እንበላለን።
ለራት፡ የምትፈልጉት፡ እንጀራ፡ ነው፡ ወይስ፡ ዳቦ?	ለራት፡ የምንፈልገው፡ እንጀራ፡ ነው፡ እንጂ፡ ዳቦ፡ አይደለም።
አቶ ከበደ፡ የጐመን፡ ወጥ፡ በጣም፡ ይወዳሉ?	የለም፡ አይወዱም።
ካፈሉ፡ ዓመት፡ ወዳገርሽ፡ ሄደሽ፡ የለም?	አዎ፡ ሄጃለሁ።
ለሚመጣው፡ ዓመት፡ አውሮፓ፡ ትሄዱ፡ የለም?	አዎ፡ እንሄዳለን።

ጥያቄ	መልስ
ትናንት፡ እናታችሁን፡ አይታችሁ፡ የለም?	አዎ፡ አይተናል።
ዛሬ፡ ስለውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ትናገር፡ የለም?	አዎ፡ እናገራለሁ።
ከልጆቹ፡ ጋር፡ ሽርሽር፡ መሄድ፡ አስበው፡ የለም?	አዎ፡ አስቤያለሁ።
በሚመጣው፡ ሳምንት፡ ትዋኙ፡ የለም?	አዎ፡ እንዋኛለን።
አቶ፡ ለማን፡ አይተሽው፡ የለም?	አዎ፡ አይቼዋለሁ።
በሸለቆው፡ መካከል፡ ቡና፡ ተክላችሁ፡ የለም?	የለም፡ አልተከልንም።
ሸሚዝ፡ ገዝተሽልኝ፡ የለም?	የለም፡ አልገዛሁልህም።
ለማና፡ ተሰማ፡ ወዳዲስ፡ አበባ፡ ሄደው፡ የለም?	አዎ፡ ሄደዋል።
በአሥር፡ ሰዓት፡ ቡና፡ መጠጣት፡ አስበው፡ የለም?	የለም፡ አላሰቡም።
ተማሪዎች፡ መጥተው፡ የለም?	የለም፡ አልመጡም።
ገንዘብ፡ ያገኙ፡ የለም?	አዎን፡ አገኛለሁ።
ገንዘብ፡ አግኝተው፡ የለም?	አዎን፡ አግኝቻለሁ።
ሽማግሌዎቹን፡ ወደቤትህ፡ ጠርተሃቸው፡ የለም?	አዎ፡ ጠርቻቸዋለሁ።
ነገ፡ አዲስ፡ ሸሚዝ፡ ትገዢልኝ፡ የለም?	አዎ፡ እገዛልሃለሁ።

ድርሰት

የኢትዮጵያ፡ መሬት፡ በጣም፡ ሃብታም፡ ስለሆነ፣ ብዙ፡ ዓይነት፡ አትክልቶችና፡ ፍራፍሬዎች፡ ይበቅላሉ። ካትክልት፡ እንደ፡ ድንች፣ ካሮት፣ ሰላጣ፣ ቲማቲም፡ ዱባና፡ ጐመን፡ ያሉት፡ ይበቅላሉ። ገበሬዎች፡ ጥቂቶችን፡ አትክልቶች፡ ለራሳቸው፡ ምግብ፡ እያደረጉ፣ ብዙዎቹን፡ ይሸጣሉ።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚበቅሉት፡ ፍራፍሬዎች፡ ብዙ፡ ዓይነቶች፡ ናቸው። ለምሳሌ፡ እንደ፡ ሎሚ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ትርንጎ፣ መንደሪን፣ ፓፓያ፣ ሮማንና፡ ወይን፡ የሚመሳሰሉት፡ ይበቅላሉ። አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ፍራፍሬዎች፡ እየተሸጡ፡ ለገበሬዎች፡ የገንዘብ፡ ምንጭ፡ ሆነዋል።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚገኙት፡ ኢንዱስትሪዎች፡ በጣም፡ ትልልቅ፡ አይደሉም። የጥጥ፣ የጫማ፣ የስኳር፣ የምስማር፣ የሳሙና፣ የብስኩት፣ የመጠጥና፡ የቤት፡ ዕቃ፡ ኢንዱስትሪዎች፡ በብዙ፡ ይገኛሉ። ወደፊትም፡ በጣም፡ እየተስፋፉ፡ ይሄዳሉ።

ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ፡ መሬት፡ እንዴት፡ ነው?
ምን፡ ዓይነት፡ አትክልቶች፡ ይበቅላሉ?
አትክልቶቹ፡ ለምን፡ ይጠቅማሉ?
ኢትዮጵያ፡ የፍራፍሬዎች፡ አገር፡ ናት?
ምን፡ ዓይነት፡ ፍራፍሬዎች፡ ይበቅላሉ?
ገበሬዎች፡ ፍሬዎቹን፡ ይሸጣሉ?
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚገኙትን፡ የኢንዱስትሪዎች፡ ስም፡ ዘርዝር፡ ጻፍ።
አንድ፡ አገር፡ ኢንዱስትሪዎችን፡ ለማስፋፋት፡ ምን፡ ማድረግ፡ ይገባዋል?

አርባኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

እስቲ፡ እባክዎ፡ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ከብቶችና፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ዓይነት፡ በጥቂቱ፡ ይንገሩኝ።

ከበደ

የኢትዮጵያ፡ ከብቶች፡ ላም፣ በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ግመልና፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉ፡ ናቸው።

የዱር፡ አውሬዎች፡ ደግሞ፡ አንበሳ፣ ዝሆን፣ ቀጭኔ፣ ነብር፣ ጅብ፣ ተኩላ፣ ቀበሮና፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉ፡ ናቸው።

ከዚህም፡ በላይ፡ እንደ፡ ውሻና፡ ድመት፡ ያሉ፡ የቤት፡ እንስሳዎች፡ ይገኛሉ።

ጆን

አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ ከውጭ፡ አገር፡ የምትሸጣቸው፡ ምን፡ ዓይነት፡ ነገሮች፡ ናቸው?

ከበደ

አሁን፡ ወደ፡ ሥራ፡ ከመሄዴ፡ ስለቸኮለሁ፣ ሁሉንም፡ ልዘረዝርልዎ፡ ጊዜ፡ የለኝም። ግን፡ ዋናዎቹ፡ ቡና፣ ቆዳና፡ የዘይት፡ እህሎች፡ ናቸው።

ጆን

እሺ፣ አሁን፡ ሥራ፡ ካስፈታዎ፡ እስፈለጋምና፡ ይበሉ፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

አሜን፣ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ብዙ፡ ዓይነት፡ እንስሳዎች፡ ከቤትህ፡ ውስጥ፡ አሉ?	አዎን፣ ሁለት፡ የሚሆኑ፡ ለቤት፡ እንስሳዎች፡ አሉኝ።

ጥያቄ	መልስ
ከዱር፡ ውስጥ፡ አውሬ፡ አይተህ፡ ታውቃለህ?	አዎን፣ በቀደምለት፡ አንድ፡ አንበሳ፡ አየሁ።
የቤት፡ እንስሳዎች፡ ከዱር፡ ውስጥ፡ ያድራሉ?	የለም፣ አያድሩም። ቢያድሩ፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ይበሉዋቸዋል።
አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ የቤት፡ እንስሳዎች፡ ምን፡ ዓይነት፡ ምግብ፡ ይመገባሉ?	እሱ፡ እንደ፡ እንስሳው፡ ዓይነት፡ ነው። ለምሳሌ፡ ውሻና፡ ድመት፡ አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ ሥጋና፡ ወተት፡ ይመገባሉ።
ብዙ፡ ዓይነት፡ ከብቶች፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ትሸጣላችሁ?	የለም፣ አንሸጥም።
ገበሬዎች፡ ከብቶችን፡ ለመሸጥ፡ ያረባሉ?	አዎ፣ ያረባሉ።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከብት፡ ማርባት፡ ትልቅ፡ ሥራ፡ ነው?	አዎን፣ አብዛኛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የሚኖረው፡ በርሻና፡ ከብት፡ በማርባት፡ ነው።
መሸጥ፡ የምትፈልጓቸውን፡ እንስሳዎች፡ የት፡ ትሸጡዋቸዋላችሁ?	ከገበያ፡ እንወስድና፡ እንሸጣቸዋለን።
ገበሬዎች፡ ብዙ፡ ከብቶች፡ አሉዋቸው?	አዎ፣ ብዙ፡ ከብቶች፡ አሉዋቸው።
ወባ፡ ባለበት፡ ሥፍራ፡ እንስሳዎች፡ ይኖራሉ?	አዎን፣ ይኖሩ፡ ይመስለኛል።
ከብት፡ ማርባት፡ ትልቅ፡ ጥቅም፡ አለው?	አዎን፣ በጣም፡ ብዙ፡ ጥቅም፡ አለው።

ጥያቄ	መልስ
እንዴ፡ ሰው፡ ሲያድን፡ በጣም፡ መጠንቀቅ፡ ያስፈልገዋል?	አዎን፣ በጣም፡ መጠንቀቅ፡ ያስፈልገዋል።
ጓደኛህ፡ እንዳንተ፡ አደን፡ ማደን፡ ይወዳል?	አዎን፣ በጣም፡ ይወዳል።
ይህኛው፡ ፈረስ፡ ከዚያኛው፡ ይበልጣል?	በጣም፡ አይደለም።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ወጣቶች፡ አደን፡ ያድናሉ?	አዎ፣ ትንንሽ፡ አውሬዎችን፡ ያድናሉ።
ለወተት፡ የሚሆኑት፡ እንስሳዎች፡ በጣም፡ ብዙ፡ ናቸው?	በጣም፡ የታወቀችው፡ ላም፡ ናት። ነገር፡ ግን፡ ግመልና፡ ፍየል፡ ደግሞ፡ ወተት፡ ይሰጣሉ።
እርስዎ፡ የግመልና፡ የፍየል፡ ወተት፡ ጠጥተው፡ ያውቃሉ?	የለም፣ ጠጥቼ፡ አላውቅም።
ብዙ፡ አውሬዎች፡ የሚገኙበትን፡ ዱር፡ ልታሳየኝ፡ ትችላለህ?	የለም፣ ላሳይዎ፡ አልችልም። ምክንያቱም፡ ስለማላውቀው፡ ነው።
ከዝሆንና፡ ካንበሳ፡ የቱ፡ ትልቅ፡ ነው?	ካንበሳ፡ ዝሆን፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው።
ቀጭኔ፡ የቤት፡ እንስሳ፡ ናት?	የለም፣ የዱር፡ አውሬ፡ ናት።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የነብር፡ ቆዳ፡ ይሸጣል?	አዎ፣ ከፍ፡ ያለ፡ ገንዘብ፡ ያወጣል።
ተኩላና፡ ቀበሮ፡ ይመሳሰላሉ?	የለም፣ በጣም፡ አይመሳሰሉም።
እዚህ፡ አገር፡ ጅብ፡ አይተው፡ ያውቃሉ?	የለም፣ ከመጣሁ፡ ጀምሮ፡ እስካሁን፡ ጅብ፡ አላየሁም።

ጥያቄ	መልስ
አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ የወተት፡ ላም፡ ስንት፡ ብር፡ ታወጣለች?	አንድ፡ መቶ፡ ብር፡ ያህል፡ ታወጣለች።
የርሻ፡ በሬ፡ ምን፡ ያህል፡ ያወጣል?	እሱ፡ በጣም፡ ውድ፡ ነው።
የቤት፡ እንስሳ፡ አርብተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላረባሁም።
ግመልን፡ ከቀጭኔ፡ መለየት፡ ይቻላል?	አዎ፣ ሁለቱ፡ የተለያዩ፡ እንስሶች፡ ስለሆኑ፡ መለየት፡ አስቸጋሪ፡ አይደለም።
ከበቅሎና፡ ከፈረስ፡ የትኛው፡ ቅን፡ እንስሳ፡ ነው?	ፈረስ፡ ሁለጊዜ፡ ቅን፡ እንስሳ፡ ይባላል።
ከበቅሎና፡ ካህያ፡ የትኛው፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ያወጣል?	በቅሎ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ገንዘብ፡ ያወጣል።
ካሜሪካ፡ ውስጥ፡ አህያ፡ አይተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አይቼ፡ አላውቅም።
ያገርህ፡ ሥራ፡ ከብት፡ ማርባት፡ ነው?	አዎን፣ ከብት፡ ማርባት፡ ነው።
እቤትህ፡ ውስጥ፡ ድመት፡ አለህ?	አዎ፣ ሁለት፡ ድመቶች፡ አሉኝ።
ውሻዎ፡ ጥሩ፡ ነው?	አዎን፣ በጣም፡ ጥሩና፡ ቅን፡ ነው።

ድርሰት

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ከብቶች፡ የቤት፡ እንስሶችና፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ይገኛሉ። አንዳንድ፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ በሌሎች፡ አገሮች፡ ውስጥ፡ ስለማይገኙ፡ እየተሸጡ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሄዳሉ።

በጠቅላላው፣ በብዙ፡ የሚገኙት፡ ከብቶች፡ እንደ፡ ላም፣ በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ አህያ፣ በቅሎ፣ ፈረስና፡ ግመል፡ የመሳሰሉ፡ ናቸው። እነዚህም፡ ከብቶች፡ ለብዙ፡ ነገሮች፡ ስለሚያገለግሉ፣ ገበሬዎች፡ ሁሉ፡ እንደነዚህ፡ ያሉ፡ ከብቶች፡ አሉዋቸው።

እንዳንድ፡ ሰዎች፡ በቤታቸው፡ ውስጥ፡ ውሻና፡ ድመት፡ እንደ፡ ለማዳ፡ እንስሳ፡ ያስቀምጣሉ።

ከዱር፡ አውሬዎች፡ ዋና፡ ዋናዎች፡ አንበሳ፣ ዝሆን፣ ነብር፣ ቀጭኔ፣ ጅብ፣ ተኩላ ቀበሮና፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉ፡ ናቸው። የዱር፡ አውሬዎች፡ ለማደን፡ በሕግ፡ የተከለከለ፡ በመሆኑ፣ ማንም፡ ሰው፡ ያለፈቃድ፡ ሊያድን፡ አይችልም።

ጥያቄዎች

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከብቶች፡ ይገኛሉ?

የከብቶቹን፡ ስም፡ ጥሩ።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ይገኛሉ?

ለምን፡ እንዳንድ፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይላካሉ?

ከብቶች፡ ለምን፡ ያገለግላሉ?

ድመቶች፡ የት፡ ይኖራሉ?

ውሻ፡ ለምን፡ ይጠቅማል?

ማንም፡ ሰው፡ ለማደን፡ ይችላል?

ቀበሮና፡ ጅብ፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ?

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ የሚገኙትን፡ የዱር፡ አውሬዎች፡ ስም፡ ጥሩ?

አርባ፡ አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ጆን

ሀሎ፡ ማዞሪያ፣ እባክሽ፡ ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡ አገናኚኝ።

ኦፐሬተር

ከማ፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ ይፈልጋሉ፣ ጌታዬ?

ጆን

ከስማት፡ ክፍል፡ ዋና፡ ዲሬክተር፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ ለመነጋገር፡ እፈልጋለሁ።

ኦፐሬተር

ጥቂት፡ ይቆዩ፣ አገናኝዎታለሁ።

ከበደ

ከበደ፡ ነኝ። ማን፡ ልበል፡ ጌታዬ?

ጆን

እኔ፡ ዮሐንስ፡ ነኝ። በውሉ፡ መሠረት፡ ያዋሽን፡ ወንዝ፡ ግድብ፡ ሥራ፡ ለመጀመር፡ የመጣሁ፡ ዋና፡ መሐንዲስ፡ ነኝ።

ከበደ

እዎ፣ አስታውሳለሁ። እንደምን፡ እሉ፡ አቶ፡ ዮሐንስ? መምጣትዎን፡ በተስፋ፡ እንጠባበቅ፡ ነበር። ካገርዎ፡ መቼ፡ መጡ?

ጆን

አዲስ፡ አበባ፡ ከገባሁ፡ ሁለት፡ ቀን፡ ሆኖኛል።

ዳሩ፡ ግን፡ ጉዞዬ፡ በጣም፡ ረጅም፡ ስለ ነበርና፡ ስላደከመኝ፣ ከዚህ፡ ቀደም፡ ብዬ፡ እርስዎ፡ ዘንድ፡ ለመጣ፡ አልቻልሁም።

ከበደ

ምንም፡ አይደል። አሁን፡ በቂ፡ ዕረፍት፡ አገኙ?

ጆን

አዎ፣ በቂ፡ ዕረፍት፡ አግኝቻለሁ። አሁን፡ ግን፡ እዚሁ፡ ያዋሽ፡ ግድብ፡ የሚሠራበትን፡ ቦታ፡ ለማየት፡ እፈልጋለሁና፡ ዕርዳታዎን፡ ያደርጉልኝ፡ ዘንድ፡ እለምናለሁ።

ከበደ

በደስታ። ለመሆኑ፡ መቼ፡ ለመሄድ፡ አስበዋል።

ጆን

በሚመጣው፡ ሳምንት፡ መጀመሪያ፡ ካዲስ፡ አበባ፡ ለመነሳት፡ ቆርጫለሁ።

ከበደ

በጣም፡ ጥሩ፡ ነው። ጉዞዎ፡ እንዲቃናልዎ፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ።

ዳሩ ግን፡ ከመሄድዎ፡ በፊት፡ በዚህ፡ ሳምንት፡ ውስጥ፡ ተገናኝተን፡ ራት፡ አብረን፡ ብንበላና፡ ብንጨዋወት፡ መልካም፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።

ጆን

ደስታዬ፡ ነው።

እንግዲያስ፡ የሚመችዎን፡ ሰዓት፡ ያስታውቁኝና፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ ድረስ፡ እንገናኝ።

ከበደ

መልካም፡ ነው። ቅዳሜ፡ ከምሽቱ፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ ብናደርገውስ?

ጆን

ተስማሚ፡ ነው።

ከበደ

እስከዚያ፡ ድረስ፡ አቢሮዬ፡ መጥተው፡ ጥያቄዎች፡ እንዳሉዎት፡ ቢጠይቁኝ፡ ለመመለስ፡ ፈቃደኛ፡ ነኝ።

ጆን

እንግዲያስ፡ ነገ፡ ገምስት፡ ሰዓት፡ አቢሮዎ፡ ድረስ፡ መጥቼ፡ ጥያቄዎቼን፡ ለማቅረብ፡ እወዳለሁ።

ከበደ

እሺ፣ በዚህ፡ ሰዓት፡ እጠብቅዎታለሁ። እስከምንገናኝ፡ ድረስ፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጆን

አሜን። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ አስማ፡ ዘንድ፡ ትሄዳለህ?	ዛሬ፡ መሄድ፡ አልችልም።

ጥያቄ	መልስ
ከጥሩነሽ፡ ጋ፡ ያለውን፡ ሰውዬ፡ ስም፡ ታውቀዋለህ?	አዎን፣ አውቀዋለሁ።
አጎትህ፡ ዘንድ፡ ደርሰህ፡ መጣህ?	የለም፣ ገና፡ አሁን፡ ስሄድ፡ ነው።
ጥሩነሽ፡ ካዲስ፡ አበባ፡ ስትመጣ፡ የምታርፈው፡ ከማን፡ ዘንድ፡ ነው?	አጎትዋ፡ ዘንድ፡ ይመስለኛል።
ለረፍት፡ መሄድ፡ የምትፈልጉት፡ አጎታችሁ፡ ዘንድ፡ ነው?	አዎ፣ አጎታችን፡ ዘንድ፡ ነው።
እግድቡ፡ ጋ፡ የቆሙት፡ ሰዎች፡ መሐንዲሶች፡ ናቸው?	የለም፣ ዋናው፡ ዲሬክተርና፡ ጸሐፊው፡ ናቸው።
ከመሐንዲሱ፡ ዘንድ፡ ሄዳችሁ፡ ስለምን፡ ተጠየቃችሁ?	ስለ፡ ግድቡ፡ ነው።
እዩና፡ ከማ፡ ዘንድ፡ ያለው፡ ጋዜጣ፡ የማን፡ እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ?	የለም፣ አናውቅም።
ከመሐንዲሱ፡ ጋ፡ ያለውን፡ ጀልባ፡ ትወስዱት፡ ዘንድ፡ ማን፡ ነገራችሁ?	አንድ፡ ሾፌር፡ ነገረኝ።
እዚህ፡ ሆቴል፡ ውስጥ፡ እናርፍ፡ ዘንድ፡ ይፈቀድልናል?	አዎ፣ ይፈቀድላችኋል።
ጥሩ፡ ሲኒማ፡ ታዩ፡ ዘንድ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ መምጣት፡ ትፈልጋላችሁ?	አዎ፣ መምጣት፡ እንፈልጋለን።
ከዚህ፡ ጋ፡ የወሰዳችሁትን፡ እንቁላሉ፡ የት፡ አደረጋችሁት?	ከቤት፡ ውስጥ፡ አደረግነው።
እዚህ፡ ከመጣችሁ፡ ዘንድ፡ ለምን፡ ሲኒማ፡ አይታችሁ፡ አትሄዱም?	ጥሩ፡ ሲኒማ፡ ካለ፡ እናያለን።

ጥያቄ	መልስ
እንደ፡ አገር፡ ሃብታም፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋታል?	ብዙ፡ ሠራተኞች፡ ያስፈልጋታል።
በቀደምለት፡ ከሐኪሙ፡ ጋ፡ የነበረው፡ ሰውዬ፡ አሁን፡ አንተ፡ ዘንድ፡ ነው?	አዎ፣ ከኔ፡ ዘንድ፡ ነው።
እኔ፡ ዘንድ፡ የነበረውን፡ ሰውዬ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
ጐማውን፡ ይሸጥልኝ፡ ዘንድ፡ የነገርሁት፡ ሰውዬ፡ አንተ፡ ዘንድ፡ መጥቶ፡ ነበር?	የለም፣ ዛሬ፡ አላየሁትም።
ፎርሙን፡ ይሞሉት፡ ዘንድ፡ ሰጠሃቸው?	አዎን፣ ሰጠሁዋቸው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ ፈቃድ፡ ያስፈልገናል?	አዎን፣ ፈቃድ፡ ያስፈልጋችኋል።
ያለፈውን፡ ደሞዛችንን፡ እናገኝ፡ ዘንድ፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልገናል?	ለዲሬክተሩ፡ መንገር፡ ያስፈልጋችኋል።
እናቱነሽ፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ ገንዘብ፡ ወሰድኸው?	የለም፣ አልወሰድሁትም።
ከመሐንዲሱ፡ ዘንድ፡ እንድትወስደው፡ የነገርሁህን፡ መኪና፡ ገና፡ አልወሰድኸውም?	የለም፣ ገና፡ አልወሰድሁትም። ብቻዬ፡ ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ እወስደዋለሁ።
የገበሬ፡ ባለቤት፡ አንተ፡ ዘንድ፡ መጥታ፡ ስንት፡ ቀን፡ ሰነበተች?	አንድ፡ ቀን፡ ብቻ፡ ውላ፡ ወዲያውኑ፡ ተመለሰች።
ለማ፡ ከመሥሪያ፡ ቤቱ፡ ተሰናብቶ፡ ከማን፡ ዘንድ፡ ሄዷል?	እናቱና፡ አጎቱ፡ ዘንድ፡ ሄዷል።

ጥያቄ	መልስ
ጥሩነሽ፡ ከሁን፡ ለማን፡ ዘንድ፡ ናት?	እኅቷና፡ አበበች፡ ዘንድ፡ ነች።
ዛሬ፡ ምሳችሁን፡ ትበሉ፡ ዘንድ፡ አለሙ፡ ዘንድ፡ አትሄዱም?	ዛሬ፡ መሄድ፡ አንችልም፤ነገ፡ግን፡ እኔ፡ ብቻ፡ እሄድ፡ ይሆናል።
ዛሬ፡ እኔ፡ ጋ፡ ትመጡ፡ ዘንድ፡ ማን፡ ነገራችሁ?	ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ነገሩኝ።
ብዙ፡ ገንዘብ፡ አለህ?	ከጊዜው፡ የለኝም። ወደፊት፡ ግን፡ ይኖረኝ፡ ይሆናል።
እንደ፡ የልጅ፡ ልጅ፡ ብትኖርህ፡ አሜሪካ፡ ትመጣ፡ ነበር?	አዎን፤ በዚህ፡ ፋንታ፡ እመጣ፡ ነበር።
ብዙ፡ የጌጥ፡ ዕቃ፡ ቢኖርሽ፡ ለማን፡ ትሰጪያለሽ?	ለዮሐንስ፡ ሚስት፡ እሰጣታለሁ።
ርቲውን፡ ከመውሰድ፡ መቼ፡ ትመጣለህ?	ነገ፡ ጊዜ፡ ስለሚኖረኝ፡ እመጣለሁ።
ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ጊዜ፡ ቢኖርህ፡ አቶ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ አትሄድም?	ሐኪሙ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አይገኝም።

ድርሰት

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የሚያውቁት፡ አሜሪካዊ፡ መሐንዲስ፡ ለጥናት፡ ወንዝ፡ ገደብ፡ ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ጋር፡ ያደረገውን፡ ውል፡ መሠረት፡ ሥራቸው፡ ለቀነ፡ ለሁለተኛው፡ ቀኑ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ነው።

ከሪቻርድም፡ ጋር፡ የተገናኙ፡ ለማየ፡ ሊጠብቁ፡ ነበርና፤ ሁለት፡ ቀናት፡ ያህሉ፡ በሆቴሉ፡ ውስጥ፡ ግሪኩ፡ በኋላ፤ አቶ፡ ዮሐንስ፡ ለሰለሱ፡ ተገናኝተው፡ ለስለመሟቸው።

ከነገሩዋቸው፡ በኋላ፥ መቼ፡ መገናኘት፡ እንደሚችሉ፡ ቀጠሮ፡ ጠየቁ።

አቶ፡ ከበደ፡ በደስተኛ፡ ድምፅ፡ እንኳን፡ ደህና፡ ገቡ፡ ካሉዋቸው፡ በኋላ፡ ስለአሜሪካ፡ ወሬ፡ ጠየቋቸው። ከዚያም፡ ጥቂት፡ ካወሩ፡ በኋላ፡ ከሚመጣው፡ ቅዳሜ፡ በሁለት፡ ሰዓት፡ ጊዮን፡ ሆቴል፡ እንገናኝ፡ ተባብለው፡ ተለያዩ።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ለምን፡ መጡ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ስልክ፡ ለምን፡ ደወሉ?

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ በስልክ፡ ስለምን፡ ተነጋገሩ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የየት፡ አገር፡ ሰው፡ ናቸው?

ግድቡ፡ የሚሠራው፡ የት፡ ነው?

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ መቼ፡ ለመገናኘት፡ ተስማሙ?

በስልክ፡ ስንት፡ ሰዓት፡ አወሩ?

ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስላሉት፡ ትልልቅ፡ ግድቦች፡ ንገሩኝ።

አርባ፡ ሁለተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ከበደ

እንደምን፡ ደህና፡ ዋሉ። እንግዲህ፡ ተላወጹቶ?

ዮሐንስ

ምንም፡ አልሉ። ገና፡ ለመነጋገድ፡ ላይ፡ ነኝ።

ከበደ

በወምበሩ፡ ላይ፡ ይቀመጡ።

ዮሐንስ

እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ። እንደሰማሁት፡ ያዲስ፡ አበባ፡ ዓየር፡ በጋም፡ መከረም፡ ነው።

ከበደ

በዚህ፡ ብቻ፡ የለንም፡ እንጂ፡ ዓየሩ፡ በጋም፡ አስደሳች፡ ነው።

ለመሆኑ፡ ሻይ፡ ወይስ፡ ቡና፡ ይምጣልዎት።

ዮሐንስ

ቡና፡ እመርጣለሁ። አመሰግናለሁ።

ከበደ

ቡናው፡ እስከሚመጣ፡ ድረስ፡ ስለዓባይ፡ ወንዝ፡ ግድብ፡ ያሉዎትን፡ ጥያቄዎች፡ ሊጠይቁኝ፡ ይችላሉ።

ዮሐንስ

ለግድቡ፡ የታቀደው፡ ቦታ፡ በጣም፡ ተስማሚ፡ መሆኑንና፡ አለመሆኑን፡ አላውቅም። ምን፡ ይመስልዎታል?

ከበደ

ያዋሽ፡ ወንዝ፡ ሸለቆ፡ በዝናብ፡ ውሃ፡ ካገኘ፡ በጣም፡ ለም፡ ይሆናል፡ ተብሎ፡ የሚገመት፡ ቦታ፡ ነው።

ዳሩ፡ ግን፡ ውሃ፡ ስለማያገኝ፡ ሸለቆው፡ ገጠር፡ ሆኖ፡ ቀርቷል።

በተወን፡ ሂደው፡ ግድብ፡ ጊዜ፡ የሸለቆውን፡ ሣብታዎችን፡ ሊረዱት፡ ይችላሉ።

ዮሐንስ

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ግድቡን፡ ለመሥራት፡ ያሰበው፡ ለመስኖ፡ ብቻ፡ ነው፡ ወይስ፡ ለኢንዱስትሪ፡ ኃይል፡ ጭምር፡ ነው።

ከበደ

ከግዜው፡ የመንግሥቱ፡ ዋና፡ ዓላማ፡ ለወሰዩ፡ ብቻ፡ ነው።

ነገር፡ ግን፡ ከሌሎቹ፡ ቦታዎን፡ ከምንተው፡ በሚመጡበት፡ ጊዜ፡ አስተያየትዎን፡ በሬፖርቱ፡ ላይ፡ እንደገለጹልን፡ እንፈልጋለን።

ከዚያ፡ በኋላ፡ ሊታከሉ፡ የሚገባውን፡ ነገር፡ እናስገባለን።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ችግርህን፡ ለማን፡ ልትነግረው፡ ትፈልጋለህ?	ምናልባት፡ ለባለቤቴ፡ ልነግራት፡ ይሆናል።
ልጆችሽን፡ ከመገብሽ፡ በኋላ፡ ከወሬሽኝ፡ ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ መሄድ፡ ትፈልጊያለሽ?	አዎ፡ ካንቺ፡ ጋር፡ መሄድና፡ ሲኒማ፡ ማየት፡ በጣም፡ ደስ፡ ይለኛል።
የሰጠሃት፡ ቡና፡ በጣም፡ ጣፋጭ፡ ነበር?	አዎ፡ በጣም፡ ጣፋጭ፡ ነበር።
ጥሬ፡ ሙዝ፡ በጣም፡ መራራ፡ ነው?	በጣም፡ መራራ፡ አይደለም።
የኢትዮጵያ፡ ድምፅ፡ የሚባለው፡ ጋዜጣ፡ የሚታተመው፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ነው?	አዎ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ነው።
ሳክሊርንሷይ፡ ከገር፡ እንደታወለዳችሁ፡ ሴትዮዋን፡ መረመራችኋት?	አዎ፡ መርምረናታል። ምናልባት፡ ነገ፡ ጠዋት፡ ትወልዳለች፡ ይሆናል።
እዚህ፡ መንደር፡ የሚኖሩትን፡ ሰዎች፡ ሰም፡ በሙሉ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።

ጥያቄ	መልስ
በሥልጣኔ፡ ከፍ፡ ያሉትን፡ አገሮች፡ ሄደህ፡ ማየት፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ በጣም፡ ደስ፡ ይለኛል።
በግምት፡ ከበደ፡ አሁን፡ የት፡ የደረሰ፡ ይመስልሃል?	ምናልባት፡ አዲስ፡ ከተማ፡ ይደርስ፡ ይሆናል።
ትምህርት፡ ቤት፡ ሄደህ፡ ልጆቹን፡ ቆጥረህ፡ መምጣት፡ ትችላለህ?	አዎ፣ ልሄድና፡ ልቆጥራቸው፡ እችላለሁ።
ሚኒስትሩን፡ በደንብ፡ አያችሁዋቸው?	አዎ፣ አየናቸው።
ከበደ፡ በጣም፡ አዋቂ፡ ሰው፡ ነው፡ የሚሉት፡ እውነት፡ ነው?	እኔ፡ አቶ፡ ከበደን፡ አላውቃቸውም።
ከጊዜ፡ ጊዜ፡ ችግር፡ ደርሶብህ፡ ያውቃል?	አዎ፣ ብዙ፡ ጊዜ፡ በአንዳንድ፡ ነገሮች፡ ምክንያት፡ ችግር፡ ደርሶብኛል።
ያቶ፡ ከበደ፡ ካሣች፡ ዘር፡ ምን፡ ዓይነት፡ እንደሆነ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ከእንግዶች፡ ጋር፡ ተላመድክ?	አዎን፣ ተላምጃለሁ።
ልጅህ፡ ሥራውን፡ ወደደው?	ምንም፡ አይል።
አገራችሁ፡ ውስጥ፡ ሻይ፡ ይበቅላል?	አዎ፣ ይበቅላል።
ከቡናና፡ ከሻይ፡ የቱን፡ ትመርጣለህ?	ከሻይ፡ ቡናን፡ እመርጣለሁ።
ለሎሚ፡ በታቀደው፡ እርሻ፡ ምን፡ ተተከለበት?	ቡናና፡ መንደሪን፡ ተከሉበት።
አገራችሁ፡ ለእርሻ፡ በጣም፡ ለም፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ ለም፡ ነው።
የምትኖረው፡ ገጠር፡ ነው፣ ወይስ፡ ከተማ፡ ውስጥ?	ከተማ፡ ውስጥ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ያቶ፡ ለማን፡ ሃብታምነት፡ የሰማህ፡ ከየት፡ ነው?	ከጓደኞቼ፡ ሰማሁ።
ግድቡ፡ የሚያስፈልገው፡ ለመስኖ፡ ነው፣ ወይስ፡ ለሌትሪክ?	ለሁለቱም፡ ሊሆን፡ ይችላል።
ወደ፡ አሜሪካ፡ የምትሄድ፡ ብቻህን፡ ነው?	የለም፣ አባቴና፡ እናቴ፡ ጭምር፡ ከኔ፡ ጋር፡ ይሄዳሉ።
ትምህርታችሁን፡ ከጨረሳችሁ፡ በኋላ፡ ዓላማችሁ፡ ምንድን፡ ነው?	ወዳገራችን፡ ተመልሰን፡ ለመንግሥታችን፡ ለመሥራት፡ ነው።
ስለትናንቱ፡ ነገር፡ አስተያየትህ፡ ምንድን፡ ነው?	እኔ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነገር፡ ይመስለኛል።
አንተ፡ ለአለቃ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ሪፖር፡ ትሰጣለህ?	እኔ፡ ደህና፡ ሪፖር፡ እሰጣለሁ።
እቤትህ፡ አጠገብ፡ ምንጭ፡ አለ?	አዎን፣ አንድ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ምንጭ፡ አለ።
ያዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ እየተስፋፋ፡ ሄደ?	አዎ፣ ተስፋፍቷል።
ዋጋው፡ ከአሥር፡ ብር፡ ቢያንስ፡ ትገዛዋለህ?	አዎ፣ እገዛዋለሁ።
ቢያንስ፡ አሥር፡ ብር፡ ያወጣ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ አሥር፡ ብር፡ ልትሸጠው፡ ትችላለህ።
የሰውዬው፡ መኪና፡ እንዴት፡ ያለ፡ ነው?	በጣም፡ ቀይ፡ ነው።
ለምን፡ ለማ፡ እንዲመጣ፡ አትፈልገውም?	ሥራ፡ ስለሚያስፈታኝ፡ ነው።
የለማ፡ ቤት፡ ትልቅ፡ ነው?	ምንም፡ አይል።
ትናንት፡ የበላችሁት፡ ራት፡ ጥሩ፡ ነበር?	ምንም፡ አይል።

ጥያቄ	መልስ
ሰዓትህን፡ ወደድሃት?	ምንም፡ አትል።
የአዲስ፡ አበባ፡ ሕዝብ፡ ግምት፡ ብዙ፡ ነው?	ምንም፡ አይል።
ልጆችዎ፡ ተሻላቸው?	ምንም፡ አይሉ።
ራስዎን፡ ተሻለዎት?	ምንም፡ አልል።
ቀኑ፡ ብርድ፡ ነው?	ምንም፡ አይል።
ዋሽንግተን፡ ሙቀት፡ ነው?	ምንም፡ አይል።
ከተማዋ፡ እየተስፋፋች፡ ሄደች?	ምንም፡ አትል።
ዳቦው፡ ጣፋጭ፡ ነው?	ምንም፡ አይል።
ለጤናችሁ፡ ደህና፡ ናችሁ?	ምንም፡ አንል።
ደህና፡ ናችሁ?	ምንም፡ አንል።
ዓይንህን፡ ተሻለህ?	ምንም፡ አልል።
ጥሩ፡ ተማሪዎች፡ ናቸው?	ምንም፡ አይሉ።

ድርሰት

ዮሐንስ፡— የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ በጣም፡ ብርቱ፡ መሆናቸውን፡ አውቃለሁ። አሁን፡ አብዛኞቹ፡ ገበሬዎች፡ የት፡ እንደሚኖሩ፡ ልትነግረኝ፡ ትችላለህ?

ለማ፡— ብዙዎቹ፡ ገበሬዎች፡ በርሻቸው፡ አጠገብ፡ በሚገኙት፡ በትንንሽ፡ መንደሮች፡ ውስጥ፡ ይኖራሉ።

ዮሐንስ፡— ከብት፡ እርባ፡ በሰፊው፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ይገኛል?

ለማ፡— አዎን፡ ግማሾቹ፡ ገበሬዎች፡ የሚገኙት፡ ለእርሻ፡ ሊሆን፡ ግማሾቹ፡ ደግሞ፡ ከብት፡ በማርባት፡ ነው። ለመሆኑ፡ ወደዚህ፡ አገር፡ ከመጣህ፡ ጀምሮ፡ ከብቶች፡ አይተህ፡ አታውቅም?

ዮሐንስ፡- ብዙ፡ ከብቶች፡ በየመንገዱና፡ በየጋራው፡ ሲመገቡ፡ አይቻለሁ። ከመሆኑ፡ ገበሬዎች፡ ከብቶቻቸውን፡ እንዴት፡ አድርገው፡ ይጠብቃሉ?

ከማ፡- አዲሱ፡ የከብት፡ እርባ፡ ዘዴ፡ በሰፊው፡ ስላልተካሄደ፤ አብዛኛዎቹ፡ ገበሬዎች፡ ከብቶቻቸውን፡ በረኛ፡ ያስጠብቃሉ። ይህ፡ የቀድሞ፡ ልማድ፡ ስለሆነ፡ ገበሬዎች፡ በቀላሉ፡ ሊተውት፡ አይችሉም።

ዮሐንስ፡- የኢትዮጵያ፡ ኢኮኖሚ፡ የተመሠረተው፡ በርሻ፡ ላይ፡ ስለሆነ፤ ስለኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ ማወቅ፡ በጣም፡ ይጠቅማል። በሰፊው፡ ስላስረዳኸኝ፡ አመሰግናለሁ። ደህና፡ ዋል።

ከማ፡- አሜን፡ ደህና፡ ዋል።

ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ፡ ገበሬዎች፡ እንዴት፡ ናቸው?

አብዛኛዎቹ፡ ገበሬዎች፡ የት፡ ይኖራሉ?

ከብት፡ እርባ፡ በኢትዮጵያ፡ ተስፋፍቷል?

ከብቶች፡ የሚገኙበት፡ ቦታ፡ ወዴት፡ ነው?

የከብቶች፡ አጠባበቅ፡ እንዴት፡ ነው?

የአዲሱ፡ ከብት፡ እርባ፡ ዘዴ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ተስፋፍቷል?

ብዙ፡ አረኞች፡ በኢትዮጵያ፡ ይገኛሉ?

የአረኞች፡ ዋና፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ገበሬዎች፡ የሚከተሉት፡ የቀድሞ፡ ልማድ፡ ምንድን፡ ነው?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ የቀድሞ፡ ልማዶች፡ አሉ?

ለኢትዮጵያ፡ ኢኮኖሚ፡ መሠረት፡ የሆነው፡ ምንድን፡ ነው?

በአንድ፡ አገር፡ ውስጥ፡ የርሻን፡ ሥራ፡ ለማስፋፋት፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋል?

አርባ፡ሦስተኛ፡ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ለግድቡ፡መሥሪያ፡የሚያስፈልጉትን፡ መሣሪያዎች፡ከየት፡እናስመጣለን?

ከበደ

የሚያስፈልጉ፡መሣሪያዎች፡ሁሉ፡ከጀርመን፡አገር፡እንዲገዙ፡ተዋውለናል።

ጥቂቶቹ፡ደርሰውን፡በመጋዘናችን፡ውስጥ፡ይገኛሉ።

ከጉዞዎ፡በሚመለሱበት፡ጊዜ፡መሣሪያዎቹን፡ልናሳይዎ፡እንችላለን።

ዮሐንስ

ሊሠራ፡የታቀደው፡ግድብ፡ያዋሽን፡ወንዝ፡ሸለቆ፡በመላ፡ውሃ፡ለማጠጣት፡የሚችል፡ይመስልዎታል?

ከበደ

አሁን፡የሚሠራው፡ግድብ፡የሸለቆውን፡ሦስት፡አራተኛ፡የሚሆነውን፡መሬት፡ውሃ፡እንዲያጠጣ፡ተስፋ፡እናደርጋለን።

ወደፊት፡ደግሞ፡ከዚህ፡የበለጠ፡ግድብ፡እንዲሠራ፡ታስቦአል።

ዮሐንስ

ከመሄዴ፡በፊት፡የግድቡን፡ሥራ፡የሚያመለክተውን፡ካርታ፡ለማየት፡እፈልጋለሁ።

የሚቻል፡ከሆነ፡አንድ፡ኮፒ፡ቢሰጡኝ፡በጣም፡እወድ፡ነበር።

ከበደ

አንድ፡ኮፒ፡ልንሰጥዎት፡እንችላለን።

ከዚህ፡ሲወጡ፡ወደ፡መሐንዲሱ፡ክፍል፡ይሂዱና፡አቶ፡ተሰማን፡አንድ፡ኮፒ፡ይጠይቁት።

እኔም፡እጠራውና፡አንድ፡ኮፒ፡እንዲያዘጋጅልዎ፡አስታውሰዋለሁ።

ዮሐንስ

ስለ፡እርዳታዎና፡ስለ፡አቀረቡልኝ፡መልካም፡አሳብ፡በጣም፡አመሰግንዎታለሁ

ካዋሽ፡እንደተመለሱ፡እጠራዎታለሁ።

ከበደ

ደግ፡ ነው። ሥራዎ፡ እንዲከናወንልዎ፡ ሙሉ፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ።

ለሊት፡ የተቃጠርነውን፡ ቀጠሮ፡ እንዳይዘነጉት።

ዮሐንስ

አልዘነጋም። በዚያው፡ ሰዓት፡ እጊዮን፡ ሆቴል፡ እጠብቅዎታለሁ

ከበደ

መልካም፡ ነው። ይበሉ፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ዮሐንስ

አሜን፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ልጅህ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ የሄደው፡ ስለ፡ ከብት፡ እርባ፡ ለመማር፡ ነው?	የለም፤ መሐንዲስነት፡ ለመማር፡ ነው።
ከኔ፡ ጋር፡ ወደ፡ ጋራው፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	ከሰዓት፡ በኋላ፡ ብትሄድ፡ አብረንህ፡ እንሄዳለን።
የከብቶችህ፡ እረኛ፡ ብርቱ፡ ሰው፡ ይመስላል?	አዎ፤ በጣም፡ ብርቱ፡ ሰው፡ ነው።
ቀድሞ፡ የተመሠረተውን፡ ካምፕ፡ ሄዳችሁ፡ ታዩታላችሁ?	አዎ፤ እንሄድና፡ እናየዋለን።
የሕዝብ፡ ጤና፡ አጠባበቅ፡ ሥራ፡ እየተስፋፋ፡ ሄደ?	አዎን፤ ከቀድሞው፡ አሁን፡ ተስፋፍቷል።
የጽሕፈት፡ መሣሪያ፡ የሚሸጥበት፡ ሱቅ፡ ታውቃለህ?	አዎን፤ ከባንኩ፡ ፊት፡ ለፊት፡ አንድ፡ ሱቅ፡ አለ።

ጥያቄ	መልስ
ከአሜሪካ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ መሣሪያዎች፡ መግዛት፡ ይፈልጋሉ?	ፈቃድ፡ ካገኘሁ፡ መግዛት፡ እፈልጋለሁ።
ብዙ፡ መሣሪያዎች፡ ለማስመጣት፡ ከማን፡ ጋር፡ መዋዋል፡ ያስፈልጋል?	ከዋናው፡ ዲሬክተር፡ ጋር፡ መዋዋል፡ ያስፈልግዎታል።
እዚህ፡ መጋዘን፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ልዩ፡ መሣሪያዎች፡ አስቀምጠሃል?	አሁን፡ ልነግራችሁ፡ አልፈልግም።
ያመጣሽውን፡ የወጥ፡ ቤት፡ ዕቃ፡ በሙሉ፡ መለሽው?	አዎ፣ በሙሉ፡ መልሼዋለሁ።
አትክልቱን፡ ውሃ፡ ለማጠጣት፡ የምትፈልገው፡ መቼ፡ ነው?	ምናልባት፡ ዛሬ፡ ማታ፡ ሳላጠጣው፡ አልቀርም።
ያዋሽ፡ መሬት፡ ምን፡ ዓይነት፡ አትክልት፡ ያበቅል፡ ይመስልሃል?	በውነቱ፡ ምን፡ ዓይነት፡ አትክልት፡ እንደሚያበቅል፡ ልነግርህ፡ አልችልም።
ማናቸውንም፡ ነገር፡ በደብዳቤ፡ አመልክተሃል?	አዎ፣ አመልክቻለሁ።
ያዋሽን፡ ወንዝ፡ ግድብ፡ እካርታው፡ ላይ፡ አመልክተሃል?	አዎን፣ አመልክቻለሁ።
እርብ፡ ማታ፡ ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ እንሂድም?	መሄድ፡ ከፈለጋችሁ፡ ደግ፡ እንሂድ።
የጠየቃችሁትን፡ መሣሪያ፡ አገኛችሁ?	አዎ፣ አገኘን።
ሥራው፡ በሙሉ፡ ተከናወነላችሁ?	የለም፣ አልተከናወነልንም።
ካምባሳደሩ፡ ጋር፡ ቀጠሮ፡ አደረግህ?	የለም፣ ገና፡ ለመቀጠር፡ መጣሁ።
ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ መቀጠራችሁን፡ ዘነጋችሁት?	አዎ፣ ዘነጋነው።

ጥያቄ	መልስ
ዛሬ፡ በውጭ፡ አገር፡ መንግሥት፡ መገዛት፡ የሚፈልግ፡ ሕዝብ፡ ይኖር፡ ይመስልሃል?	አይመስለኝም።
ከግቢው፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ትልቁ፡ ቢሚ፡ ቤት፡ ምን፡ እንዲሆን፡ ታስቦ?	ዋጋሽ፡ ሊደግ፡ ቤት፡ ዋጋሽ፡ ዲፕሎማ፡ ግብ፡ ቤት፡ እንዲሆን፡ ታስቦ።
ይህ፡ ደግ፡ ሐሳብ፡ ይመስላችኋል?	አዎ፣ ደህና፡ ነው።
እነአሜን፡ ቡና፡ ለመጋበዝ፡ ወዲ፡ ሆቴል፡ እሄዳለሁ፡ አለክ?	አዎ፣ አሁን፡ መሄዴ፡ ነው።
የሸጥኸው፡ ወንበርና፡ ጠረጴዛ፡ በወካ፡ ስንት፡ ነው?	ቁጥሩ፡ ስንት፡ እንደሆነ፡ አላውቅም።
ከብት፡ ከሚያረባው፡ ሰውዬ፡ ጋር፡ የሚኖሩ፡ ብዙ፡ እረኞች፡ አሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ብዙ፡ እረኞች፡ አሉ።

ድርሰት

ባሁኑ፡ ዘመን፡ ብዙ፡ አገሮች፡ በኢኮኖሚ፡ ለማደግና፡ የሕዝባቸውን፡ የኑሮ፡ ደረጃ፡ ለማሻሻል፡ በየጊዜው፡ ብዙ፡ ጥረት፡ ያደርጋሉ።

ከነዚህም፡ ጥረቶች፡ አንዱ፡ በትልልቅ፡ ወንዞች፡ ላይ፡ ግድብ፡ እየሠሩ፡ በዙሪያው፡ የሚገኘውን፡ መሬት፡ በመስኖ፡ ውሃ፡ እንዲጠጣ፡ ማድረግ፡ ነው። ውሃ፡ በማጣት፡ ምክንያት፡ ገጠር፡ ሆኖ፡ ያለአንዳች፡ ሃብት፡ ይኖር፡ የነበረው፡ መሬት፣ ባጭር፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ በልጽጎ፡ ማናቸውንም፡ ዓይነት፡ እህል፣ ፍሬና፡ አትክልት፡ ሊሰጥ፡ ይችላል።

ከዚህም፡ በላይ፡ ግድብ፡ ሌላ፡ ጥቅም፡ አለው። ከውሃ፡ የሚገኘው፡ ኤሌክትሪክ፡ ኃይል፡ ኢንዱስትሪ፡ ለማደራጀትና፡ ለማስፋፋት፡ በጣም፡ አስፈላጊ፡ ነው።

ይህን፡ በማሰብ፡ አሁን፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ግዛቱ፡ ውስጥ፡ በሚገኙት፡ በትልልቅ፡ ወንዞች፡ ላይ፡ ግድብ፡ ለመሥራትና፡ በወንዙ፡ ውሃ፡ በዙሪያው፡ የሚገኙትን፡ ቦታዎች፡ ለማጠጣት፡ አስቧል።

ለምሳሌ፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ የተፈጸመው፡ የቆቃ፡ ግድብ፡ የኤሌክትሪክ፡ ኃይል፡ በመስጠቱ፡ ጥቅሙ፡ ታውቋል።

ወደፊትም፡ ይህን፡ የመሳሰሉ፡ ግድቦች፡ ለማደራጀት፡ ስለታሰበ፤ የአገሩ፡ ኢኮኖሚ፡ ባጭር፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ አድጎ፡ የሕዝቡን፡ የኑሮ፡ ደረጃ፡ እንደሚያሻሽል፡ ይታመናል።

ጥያቄዎች

ባንዳንድ፡ ቦታዎች፡ ውስጥ፡ የግድብ፡ ሥራ፡ ለምን፡ በጣም፡ አስፈላጊ፡ ሆነ?

ግድብ፡ ለአንድ፡ አገር፡ ሕዝብ፡ ከሚሰጠው፡ ጥቅሞች፡ ጥቂቶቹን፡ ተናገር?

አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ለም፡ ቦታ፡ አለ?

ኢትዮጵያ፡ ወደፊት፡ ስንት፡ ግድብ፡ ለመሥራት፡ ትወዳለች?

በዓለም፡ ውስጥ፡ በትልቅነቱ፡ የታወቀው፡ ግድብ፡ የት፡ አገር፡ ነው?

ስሙስ፡ ማን፡ ይባላል?

እርስዎ፡ ግድብ፡ አይተው፡ ያውቃሉ?

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የታወቀው፡ ግድብ፡ ማን፡ ይባላል?

አሜሪካ፡ አሁን፡ እንዳሰለው፡ ጊዜ፡ ገጠሯ፡ ውስጥ፡ ግድቦች፡ ተሠሩላት?

አርባ፡ አራተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

እንደምን፡ አሉ፡ አቶ፡ ከበደ?

ከበደ

እግዚአብሔር፡ ይመስገን። አርስዎስ፡ እንደምን፡ አሉ? ከተገናኘን፡ ሰነበትን።

ዮሐንስ

እርግጥ፡ ነው። ሥራ፡ ስለሚበዛብኝ፡ ከመገናኘት፡ ጊዜ፡ አላገኘንም። በዚህ፡ ሰሞን፡ ከመሥሪያ፡ ቤቴ፡ ፈቃድ፡ ስለምወስድ፣ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ስለሚገኙት፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የረፍት፡ ጊዜን፡ ማሳለፊያዎች፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?

ከበደ

ከማወቅ፡ የሚፈልጉት፡ ዘመናዊውን፡ ዓይነት፡ ነው፣ ወይስ፡ የጥንቱን?

ዮሐንስ

ሁለቱንም፡ ዓይነት፡ ቢነግሩኝ፡ አይከፋም።

ከበደ

እንግዲያማ፡ የጥንቱ፡ ዓይነት፡ የጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ እንደ፡ ቀና፣ አደን፣ ጉግስና፡ ገና፡ ናቸው።

ዮሐንስ

አብዛኛዎቹ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እነዚህን፡ የረፍት፡ ጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ ጨዋታዎች፡ ያውቋቸዋል?

ከበደ

እንዴታ፣ በደንብ፡ ነዋ! በተለይ፡ አደንና፡ ገና፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ አብሯቸው፡ ያደገ፡ ነገር፡ ነው።

ዮሐንስ

ቀናና፡ ጉግስ፡ የቱን፡ ያህል፡ የተለመዱ፡ ናቸው?

ከበደ

ቀናና፡ ጉግስ፡ በገጠሮች፡ መካከል፡ በጣም፡ የተወደዱ፡ ናቸው።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ካሜሪካ፡ ከያመጣችሁ፡ የተከላችሁት፡ ዛፍ፡ አደገላችሁ?	አዎ፤ አደገልን።
ከሄዱበት፡ አገር፡ ከተመለሱ፡ በኋላ፡ ምን፡ ሠሩ?	እስካሁንም፡ ሥራ፡ አልሰሩም።
ሣጥንህ፡ በሙሉ፡ ያለው፡ ጉምሩክ፡ ውስጥ፡ እንደሆነ፤ ከዚያ፡ ማውጣት፡ አስቸጋሪ፡ አይመስለህም?	የለም፤ አስቸጋሪ፡ አይመስለኝም።
ወዳገርህ፡ ተመልሰህ፡ ስትሄድ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ሥራ፡ መሥራት፡ ትፈልጋለህ?	መንግሥት፡ የሚሰጠኝ፡ ሥራ፡ ሊሠራ፡ ይሆናል።
በሰው፡ ከመተማመን፡ በራስ፡ መተማመን፡ የሚሻል፡ አይመስለህም?	እንዴታ፤ በራስ፡ መተማመን፡ ከሁሉ፡ ይበልጣል።
ዛሬ፡ ከዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ መቆየት፡ ትችላላችሁ?	ዛሬ፡ ሥራ፡ ስላለብን፡ መቆየት፡ አንችልም።
ላባትና፡ ለእናትህ፡ ለም፡ መሬት፡ ለመግዛት፡ እርግጠኛ፡ ነህ?	አዎ፤ እርግጠኛ፡ ነኝ።
በዚህ፡ ሰሞን፡ ውስጥ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ከተኛከሁ፡ ያለ፡ ማን፡ ነው?	የትምህርት፡ ቤታችን፡ ዲሬክተር፡ ናቸው።
ባለፈው፡ ዓመት፡ ልጆችህን፡ እየሄድክ፡ ትጎበኛቸው፡ ነበር?	አዎን፤ በየጊዜው፡ እየሄድኩ፡ እጎበኛቸው፡ ነበር።
ወንድምህ፡ ወዳገሩ፡ እንደሚሄድ፡ እርግጠኛ፡ ነው?	ምናልባት፡ በሚመጣው፡ ዓመት፡ ይሄድ፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
ጥሩ፡ የጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ ቦታ፡ ለኖር፡ ከብሊህ፡ ወደምንሄድበት፡ ቦታ፡ ትዝዴ፡ ነበር?	አዎን፣ ለዲስታ፡ አዲሱ፡ ነበር።
የጥንት፡ ሰዓትና፡ የዛሬ፡ ሰዓት፡ ጉሮ፡ ይመሳሰላል?	የለም፣ በብዙ፡ ነገሮች፡ አይመሳሰሉም።
የጥንት፡ ሰዎች፡ ጊዜን፡ ይለኩ፡ ነበር፡ የሚባለው፡ እውነት፡ ነው?	አዎ፣ እውነት፡ ነው።
የጥንቱ፡ መኖሪያህ፡ የት፡ ነበር?	አዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ነበር።
አገራችሁ፡ ውስጥ፡ ትግል፡ የተለመደ፡ የጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ ጨዋታ፡ ነው?	አንድ፡ ጊዜ፡ በጣም፡ የተለመደ፡ ጨዋታ፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ አይታይም።
ትልቅማ፡ ከሆንክ፡ በኋላ፡ ምን፡ ጨዋታ፡ ትወድ፡ ነበር?	ገና፣ ትግል፣ እሩጫና፡ ዋና፡ በጣም፡ እወድ፡ ነበር።
የትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ዳሬክተርና፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ዳሬክተር፡ ምን፡ ተባባሉ?	ወደፊት፡ አንድ፡ አዲስ፡ መጽሐፍ፡ ቤት፡ እንሠራለን፡ ተባባሉ።
በልጅነትህ፡ ገጠር፡ ውስጥ፡ ኖረሃል?	አዎ፣ የልጅነቴን፡ ጊዜ፡ በሙሉ፡ የኖርኩት፡ ገጠር፡ ነው።
ሁልጊዜ፡ ከምሳ፡ ስትሄድ፡ ታስታውቃህ፡ ነው?	አዎን፣ ቀድሞ፡ ማስታወቅ፡ አለብኝ።
አባትህ፡ አጭር፡ ናቸው፣ አንተ፡ እንዴት፡ ረጅም፡ ሆንክ?	አያቴ፡ ረጅም፡ ነበሩ።
ያዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ የተመሠረተው፡ በማን፡ ነው?	በንጉሥ፡ ምኒልክ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ከመሐንዲሱና፡ ከሐኪሙ፡ ጋር፡ ቀጠሮ፡ ማድረግህን፡ አረሳኸው?	የለም፣ አረሳሁትም።
የናንተ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ስንት፡ ቅርንጫፎች፡ አሉት?	አሥር፡ የሚሆኑ፡ ቅርንጫፎች፡ አሉት።
እሱ፡ በቀጠሮው፡ ሰዓት፡ ባይመጣ፡ ሳታየው፡ ትሄዳለህ?	በቀጠሮው፡ ሰዓት፡ ካልተገኘ፡ ሳላየው፡ እሄዳለሁ።

ድርሰት

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በብዙ፡ የሚቆጠሩ፡ የቤት፡ ውስጥና፡ የውጭ፡ ጨዋታዎች፡ አሉ። ከነዚህም፡ በጣም፡ የታወቁት፡ የውጭ፡ ጨዋታዎች፡ እንደ፡ ዋና፣ ጉግስ፣ እሩጫና፡ ገና፡ ናቸው።

እነዚህ፡ ጨዋታዎች፡ ከቦታ፡ ቦታ፡ በመለያየታቸው፡ ምክንያት፣ አንዳንድ፡ ቦታዎች፡ ሴቶች፡ ከጨዋታው፡ ተካፋይ፡ ሲሆኑ፣ አንዳንድ፡ ቦታዎች፡ ደግሞ፡ ሴቶች፡ በጭራሽ፡ ከጨዋታው፡ ተካፋይ፡ ከመሆን፡ አይችሉም። ባብዛኛው፡ የኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ውስጥ፡ ወላጆች፡ ወንዶች፡ ልጆቻቸውን፡ ቀደም፡ ብለው፡ ጨዋታዎቹን፡ ያስተምሩዋቸዋል።

ጉግስ፡ ጨዋታ፡ በጣም፡ አስቸጋሪ፡ ከመሆኑ፡ በላይ፡ በጣም፡ አደገኛ፡ ነው። ባሁኑ፡ ዘመን፡ ይህ፡ ጨዋታ፡ ወደ፡ መረሳቱ፡ ደርሷል። የገና፡ ጨዋታም፡ እንዲሁ፡ ወደፊት፡ ሳይረሳ፡ አይቀርም። እሩጫና፡ ዋና፡ ግን፡ በጣም፡ እየተስፋፉ፡ ሄደዋል። ሴቶችም፡ ከጨዋታው፡ ተካፋይ፡ መሆን፡ ጀምረዋል።

ጥያቄዎች

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ የተለመዱት፡ የውጭ፡ ጨዋታዎች፡
እነማን፡ ናቸው?

በሁሉም፡ ጨዋታዎች፡ ሴቶች፡ ተካፋይ፡ ናቸው?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ገጠራማ፡ ቦታዎች፡ ሴቶች፡ ከምን፡ የውጭ፡
ጨዋታዎች፡ አይጫወቱም?

ልጆችን፡ ጨዋታ፡ ማን፡ ያስተምራል?

ጉግስ፡ የሚባለው፡ ጨዋታ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ነው?

ጉግስ፡ በጣም፡ ቀላል፡ ጨዋታ፡ ነው?

ወደቤት፡ የሚረጋው፡ ጨዋታ፡ የትኛው፡ ነው?

ዋና፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው?

ከገናና፡ ከዋና፡ የቱን፡ ትወዳለህ?

አሜሪካ፡ ውስጥ፡ የተለመዱትን፡ የውጭ፡ ጨዋታዎች፡ ንገረኝ።

አርባ፡ አምስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ጉግስ፡ ጨዋታ፡ ምንድን፡ ነው?

ከበደ

ጉግስ፡ የሚባለው፡ ጨዋታ፡ በፈረስ፡ ተቀምጦ፡ በዘንግ፡ መዋጋትና፡ በጋሻ፡ መመከት፡ ነው።

ዮሐንስ

በጣም፡ አደገኛ፡ ጨዋታ፡ ነው?

ከበደ

አዎ፤ አደገኛ፡ ነው።

ዮሐንስ

አደገኛ፡ የሆነበት፡ ምክንያት፡ እንዴት፡ ነው?

ከበደ

ምክንያቱ፤ ጨዋታው፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ በዘንግ፡ መዋጋት፡ ስላለበት፡ ነው።

ዮሐንስ

ይህም፡ ጦርነት፡ ይመስላል። ለመሆኑ፡ ተጫዋቾቹ፡ ሊጐዱ፡ ይችላሉ?

ከበደ

መጐዳት፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ መሞትም፡ ይችላሉ።

ዮሐንስ

አንድ፡ ሰው፡ በጨዋታው፡ ውስጥ፡ ሕይወቱ፡ ቢያልፍ፤ ነፍስ፡ ገዳዩ፡ በፍርድ፡ ቤት፡ ይከሰሳል?

ከበደ

አውቆ፡ ካልገደለው፡ በቀር፡ በፍርድ፡ ቤት፡ አይከሰስም።

ዮሐንስ

አንዳንድ፡ ጨዋታዎች፡ ለምሳሌ፡ እንደ፡ ቦክስ፡ ያሉ፡ በጣም፡ አደገኛ፡ በመሆኑ፤ በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ በሕግ፡ እንዲከለከሉ፡ ታስቦአል።

ጉግስም፡ እንደዚሁ፡ ምናልባት፡ ወደፊት፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚከለከል፡ ይመስልዎታል?

ከበደ

ባሁኑ፡ ጊዜ፡ የጉግስ፡ ተወዳጅነት፡ እየተቀነሰ፡ ሄዷል።

እንዲያውም፡ በጊዜ፡ ብዛት፡ ፈጽሞ፡ ይቀር፡ ይሆናል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
በሚመጣው፡ በጋ፡ ለሚደረገው፡ ጨዋታ፡ ተካፋይ፡ ለመሆን፡ ወደ፡ እስዊዘር፡ ላንድ፡ ትሄዳለህ?	ለጨዋታው፡ ተካፋይ፡ ለመሆን፡ ብቻ፡ ሳይሆን፣ ለማየትም፡ እሄዳለሁ።
ጉግስ፡ መጫወት፡ ትፈልግ፡ እንደሆን፡ የኔን፡ ዘንግና፡ ጋሻ፡ ልስጥህ?	ጉግስ፡ የምትሉትን፡ ጨዋታ፡ እንዴት፡ እንደምትጫወቱት፡ በጭራሽ፡ አይቼ፡ አላውቅም።
ዘንግ፡ መወርወርና፡ ጋሻ፡ መመከት፡ ትችላለህ?	አዎ፣ እችላለሁ።
በዘንግ፡ መዋጋት፡ በጣም፡ አደገኛ፡ ጨዋታ፡ አይመስልህም?	አዎ፣ በጣም፡ አደገኛ፡ ጨዋታ፡ ነው።
በጊዜ፡ ብዛት፡ የጉግስ፡ ጨዋታ፡ ከሚሌካ፡ ውስጥ፡ ይቀር፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ምናልባት፡ እንደጉግስ፡ ጨዋታ፡ ይረሳ፡ ይሆናል።
ፈረስ፡ ግልቢያ፡ ከማየታቸው፡ በፊት፡ መኛታው፡ ምክር፡ ጠይቀውህ፡ ነበር?	እኔ፡ ቤት፡ በጭራሽ፡ አልመጡም።
የጉግስ፡ ጨዋታ፡ በጭራሽ፡ የሚረሳ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ አሁንም፡ ተረስቷል።
ነፍስ፡ ገዳይ፡ መቼ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ይሄዳል?	በቅርብ፡ ቀን፡ ይሄዳል።
ነፍስ፡ ገዳይ፡ እፍርድ፡ ቤት፡ ቀርቦ፣ ምን፡ ፍርድ፡ ተቀበለ?	በነፃ፡ ተለቀቀ።
ጆን፡ የእንግሊዝ፡ ተወካጅ፡ መሆኑን፡ ሰምተህ፡ ነበር?	የለም፣ ገና፡ መስማቴ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ወንድምህ፡ ስለምን፡ መጫወት፡ ይፈልጋል?	በጭራሽ፡ ጨዋታ፡ መጫወት፡ አይፈልግም።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ አንበሳ፡ ለመግደል፡ ብትፈልግ፡ ወደ፡ የትኛው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ትሄዳለህ?	በማንኛውም፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ አንበሳ፡ ሞልቷል።
አንበሳ፡ መግደል፡ ክልክል፡ ነው?	አዎን፣ ልዩ፡ ፈቃድ፡ ማውጣት፡ ያስፈልጋል።
ከነብርና፡ ካንበሳ፡ ወይም፡ ከዝሆን፡ የቱን፡ ማደን፡ ትፈልጋለህ?	ዝሆን፡ ማደን፡ እፈልጋለሁ።
ከወላጆችህ፡ ያገኘኸው፡ ምክር፡ ጠቃሚ፡ ሆኖ፡ አገኘኸው?	አዎን፣ በጣም፡ ጠቃሚ፡ ሆኖ፡ አገኘሁት።
ጉግስ፡ ለሕይወት፡ አደገኛ፡ ጨዋታ፡ አይመስላችሁም?	አዎን፣ በጣም፡ አደገኛ፡ ነው።
አንተ፡ በሕይወትህ፡ ጦርነት፡ ሜዳ፡ ላይ፡ ተዋግተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ ተዋግቼ፡ አላውቅም።
አገርህ፡ ጦርነት፡ አድርጋ፡ ታውቃለች?	አገሬ፡ ከማንም፡ ጋር፡ ተዋግታ፡ አታውቅም።
በጦርነቱ፡ ጊዜ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ ገድለሃል?	እኔ፡ አንድም፡ ሰው፡ አልገደልሁም።
የኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ የሚገኘው፡ የት፡ ነው?	አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ነው።
ሌሎች፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶችስ፡ የራሳቸው፡ ፍርድ፡ ቤቶች፡ አሏቸው?	አዎን፣ እያንዳንዱ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ የራሱ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ አለው።
አሁንም፡ ሕዝቡ፡ ጉግስ፡ ይጫወታል?	አሁን፡ በሕግ፡ ተከልክሏል።
ከመሆኑ፡ በጉግስ፡ ጨዋታ፡ ጊዜ፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይሞት፡ ነበር?	የለም፣ ብዙ፡ ሰው፡ አይሞትም፡ ነበር።

ጥያቄ	መልስ
ለፍርድ፡ ቤት፡ ተከሰህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ ተከስሼ፡ አላውቅም።
ባገራችሁ፡ የቦክስ፡ ጨዋታ፡ እንደ፡ ጉግስ፡ ጨዋታ፡ የተለመደ፡ ነው?	የለም፣ በጣም፡ የተለመደ፡ አይደለም።
ከቤቱ፡ ዋጋ፡ ስንት፡ ብር፡ ተቀነሰልህ?	አምስት፡ መቶ፡ ብር፡ ተቀነሰልኝ።
የእናንተ፡ አገር፡ ባሕል፡ ከአሜሪካ፡ አገር፡ ባሕል፡ ጋር፡ በጣም፡ ይመሳሰላል?	አዎ፣ በጣም፡ ይመሳሰላል።
አቶ፡ ለማ፡ በተወዳጅነቱ፡ ትልቅ፡ ሥራ፡ ለማግኘት፡ ቻለ?	በተወዳጅነቱ፡ ብቻ፡ ሳይሆን፣ በደግነቱም፡ ጭምር፡ ነው።
የሃብት፡ ብዛት፡ ብቻ፡ ተወዳጅ፡ ያደርግ፡ ይመስልሃል?	የሃብት፡ ብዛት፡ ተወዳጅ፡ አያደርግም፤ ግን፡ በጣም፡ ይረዳል።
ባለቤትህ፡ የወዴት፡ አገር፡ ተወላጅ፡ ናት?	ባለቤቴ፡ አሜሪካዊት፡ ናት።
ልጆችህ፡ የተወለዱት፡ እዚህ፡ ነው?	አዎ፣ እዚህ፡ ነው።
ዛሬ፡ ቦክስ፡ ጨዋታ፡ ለማየት፡ ወደ፡ ጨዋታው፡ ቦታ፡ ትሄዳለህ?	የለም፣ ሌላ፡ ብዙ፡ ሥራ፡ አለኝ።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ የፈረስ፡ ግልቢያ፡ ጨዋታ፡ የሚታየው፡ የት፡ ነው?	የት፡ እንደሆነ፡ ቦታውን፡ አላውቅም።
ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መሄድና፡ ጉግስ፡ መጫወት፡ ትፈልጋለህ?	ጥንት፡ ነበር፡ እንጂ፡ አሁንስ፡ አልፈልግም።
ኢትዮጵያዊያን፡ ከምን፡ የተሠራ፡ ጋሻ፡ አላቸው?	ከጉማሬ፡ ቆዳ፡ የተሠራ፡ ነው።

ድርሰት

ምንም፡ እንኳን፡ አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የቅርብ፡ ጓደኞች፡ ቢሆኑ፣ በሥራ፡ መብዛት፡ የተነሣ፡ ሁልጊዜ፡ ለመገናኘት፡ አልቻሉም። አቶ፡ ዮሐንስ፡ ያመት፡ እረፍታቸውን፡ ከመሥሪያ፡ ቤታቸው፡ ወስደው፡ ስለነበር፣ የእረፍት፡ ጊዜያቸውን፡ በደስታ፡ ለማሳለፍ፡ የሚችሉበት፡ ቦታ፡ ለማግኘት፡ ፈለጉ። አቶ፡ ዮሐንስ፡ ላገሩ፡ እንግዳ፡ በመሆናቸውና፡ ያገሩን፡ ባሕል፡ በጣም፡ ስለማያውቁት፣ ላገሩ፡ ተወላጅ፡ ከሆኑት፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ምክር፡ ጠየቁ። አቶ፡ ከበደም፡ ያቶ፡ ዮሐንስን፡ ፍላጎት፡ ካወረዱ፡ በኋላ፣ ልዩ፡ ልዩ፡ ዓይነት፡ ጨዋታዎች፡ ወዴት፡ እንደሚገኙ፡ አስረዱዋቸው።

በአሁኑ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የጥንትና፡ ዘመናዊ፡ የሆኑ፡ የጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ ጨዋታዎች፡ አሉ። የጥንቶቹ፡ ጨዋታዎች፡ እንደ፡ ዋና፣ ገና፣ ትግልና፡ እነዚን፡ ያሉ፡ ናቸው። ዘመናዊ፡ ጨዋታዎች፡ ደግሞ፡ እንደ፡ ዳንስ፣ ቮሌቦል፣ አደንና፡ ፈረስ፡ ግልቢያ፡ ያሉ፡ ናቸው። ባንዳንድ፡ ቦታዎች፡ አዲሱንና፡ የጥንቱን፡ ዓይነት፡ ጨዋታዎች፡ በሰፊው፡ ይጫወቱዋቸዋል። በከተማዎች፡ ውስጥ፡ ግን፡ አብዛኛው፡ ሕዝብ፡ የሚጫወተው፡ ዘመናዊ፡ ጨዋታዎችን፡ ብቻ፡ ነው። በጥንት፡ ጊዜ፡ ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ ከልጅነት፡ ጀምረው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ጨዋታዎችን፡ ያስተምሩ፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ እንደዚህ፡ ያለው፡ ልምድ፡ እየተቀነሰ፡ ስለሄደ፣ ወደፊት፡ የጥንት፡ ጨዋታዎች፡ እየተረሱ፡ መሄዳቸው፡ አይቀርም።

ጥያቄዎች

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ምናቸው፡ ነው?

ለምን፡ ሁልጊዜ፡ አልተገናኙም?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ ወሰዱ?

ረፍታቸውን፡ ከየት፡ ወሰዱ?

አፄ፡ ዮሐንስ፡ ምን፡ ፈለጉ?

አፄ፡ ዮሐንስ፡ አፄ፡ ከበደን፡ ምን፡ ጠየቁት?

ለምን፡ ጠየቁት?

አፄ፡ ከበደ፡ ምን፡ መለሱ?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ የጊዜ፡ ማሳለፊያ፡ ጨዋታዎች፡ አሉ?

የጥንት፡ ጨዋታዎች፡ ስም፡ ማን፡ ማን፡ ይባላል?

የዘመናዊ፡ ጨዋታዎችን፡ ስም፡ ጥሩ?

የትኛው፡ ዓይነት፡ ጨዋታ፡ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው?

አርባ፡ ስድስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ጤና፡ ይስጥልኝ። አገኩዎ፡ ለኪራይ፡ የሚሆን፡ ቤት፡ አለዎ?

ተሰማ

አዎ፣ ብዙ፡ ቤቶች፡ አሉኝ። ለመሆኑ፡ ጌታዬ፡ የሚፈልጉት፡ ምን፡ ዓይነት፡ ቤት፡ ነው?

ዮሐንስ

የምፈልገው፡ አንድ፡ ራሱን፡ የቻለ፡ ቢያንስ፡ ሁለት፡ መኝታ፡ ቤቶች፣ አንድ፡ ወጥ፡ ቤት፣ መታጠቢያ፡ ቤት፣ ማረፊያ፡ ቤትና፡ ምግብ፡ ቤት፡ ያለው፡ ቤት፡ ነው።

ተሰማ

ለመሆኑ፡ የት፡ ቦታ፡ ይመርጣሉ?

ዮሐንስ

ቢቻል፡ ወዳሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ገደማ፡ ቢሆን፡ ደስ፡ ይለኛል።
ባይቻል፡ ደግሞ፡ ሰፈሩ፡ ካማረ፡ የትም፡ ቢሆን፡ ግድ፡ የለኝም።

ተሰማ

አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ቤት፡ በመሥፍን፡ ሐረር፡ መንገድ፡ ላይ፡ ራስ፡ ደስታ፡ ሆስፒታል፡ ጀርባ፡ አለኝ።

ዮሐንስ

እሱን፡ ሰፈር፡ በጣም፡ እወደዋለሁ። ወደ፡ ውስጥ፡ የሚያስገባ፡ ደህና፡ መንገድ፡ አለው?

ተሰማ

አዎ፣ በጣም፡ ጥሩ፡ መንገድ፡ አለው። ከዚያም፡ በላይ፡ ለመኪናዎ፡ ማቆሚያ፡ የሚሆን፡ ቤት፡ አለው።

ዮሐንስ

እንዳነጋገርዎ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ይመስላል። ለመሆኑ፡ ሄደን፡ ለማየት፡ ይቻላል?

ተሰማ

በደስታ፡ ነዎ፣ እንሂድ።

ዮሐንስ

ቤቱን፡ ወድጄዋለሁና፡ ስለ፡ ኪራይ፡ ይንገሩኝ።

ተሰማ

ቤቱ፡ ከመብራትና፡ ከውሃ፡ ሌላ፣ በወር፡ ሁለት፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ ብር፡ ነው።

ዮሐንስ

መልካም። እከራየዋለሁ።

ተሰማ

ደህና። ቤቱ፡ ተጠርጎ፡ በሰም፡ እንዲወለወልልዎት፡ መቼ፡ መግባት፡ ይፈልጋሉ?

ዮሐንስ

እበር፡ ብገባ፡ ደስ፡ ይለኛል።

ተሰማ

አርብ፡ እንዲዘጋጅልዎት፡ እንሞክራለን።

ዮሐንስ

እሺ። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ተሰማ

አሜን። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የምትፈልጉትን፡ የኪራይ፡ ቤት፡ ዓይነት፡ አገኛችሁ?	የለም፣ ገና፡ በመፈለግ፡ ላይ፡ ነን።
ለማ፡ ያገኛችሁን፡ ቤት፡ አልወደዳችሁትም?	የግድግዳው፡ ቀለም፡ አረንጓዴ፡ ስለሆነ፡ አልወደድነውም።
ለመሆኑ፡ የት፡ ሰፈር፡ ብታገኙ፡ ትፈቅዳላችሁ?	አንተ፡ ወደምትሮርበት፡ ሰፈር፡ ቢገኝልን፡ ደስ፡ ይለናል።
ለመሆኑ፡ ከእናንተ፡ ቤት፡ ጀርባ፡ ያለው፡ ቤት፡ የሚከራይ፡ ነው?	አዎ፣ የሚከራይ፡ ነው።
ውስጡን፡ ገብተህ፡ አይተኸዋል?	የለም፣ ገብቼ፡ አላየሁትም።
ነገ፡ ከባለቤቱ፡ ቁልፍ፡ ተቀብለህ፡ ልትጠራኝ፡ ትችላለህ?	እሺ፡ ዛሬ፡ ማታ፡ ስልክ፡ እደውልላቸውና፡ ቁልፍ፡ እንዲሰጡ፡ አደርጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
ስንት፡ ክፍሎች፡ ይኖረው፡ ይመስልሃል?	ቤቱ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ስለሆነ፣ ቢያንስ፡ አሥር፡ ክፍሎች፡ ይኖሩት፡ ይሆናል።
መንገዱስ፡ መብራት፡ አለው?	አዎ፣ መብራት፡ አለው።
ሰፈሩ፡ ሌሊቱን፡ በሙሉ፡ ብርሃን፡ ነው፡ ማለት፡ ነዋ!	አዎ፣ ብርሃን፡ ነው።
ታዲያ፡ የቤቱን፡ ኪራይ፡ ጠይቀው፡ መልሱን፡ አገኙልኝ?	የለም፣ አረሳሁት።
ታዲያ፡ መቼ፡ ልትጠይቅልኝ፡ ነው?	ነገ፡ ጠይቄ፡ እነግርሃለሁ።
ስንት፡ መኝታ፡ ቤትና፡ መታጠቢያ፡ ቤት፡ አለው?	ከፎቅ፡ ላይ፡ ሦስት፡ መኝታ፡ ቤትና፡ ሁለት፡ መታጠቢያ፡ ቤት፡ አሉት።
ምድር፡ ቤቱስ፡ ስንት፡ ክፍሎች፡ አሉት?	ምድር፡ ቤቱ፡ አንድ፡ ማረፊያ፡ ቤት፣ ምግብ፡ ቤትና፡ አንድ፡ ሽንት፡ ቤት፡ አሉት።
ከመኝታ፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ ቁም፡ ሳጥኖች፡ አሉ?	አዎ፣ በሦስቱም፡ ክፍሎች፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ጥሩ፡ ቁም፡ ሳጥኖች፡ አሉ።
ለሺ፣ እኔ፡ እዚህ፡ ለመግባት፡ ብፈልግ፡ ለውሃና፡ ለመብራት፡ ማንኛኙን፡ ይከፍላል?	እርስዎ፡ ነዎ።
ከዚህ፡ እኔ፡ የከፈልሁ፡ እንደሆን፡ የቤቱ፡ ኪራይ፡ ስንት፡ ይሆናል?	ሦስት፡ መቶ፡ ብር፡ ይሆናል።
ለውሃና፡ ለመብራት፡ በወር፡ የሚፈጀው፡ ሃያ፡ አምስት፡ ብር፡ ብቻ፡ ነው?	አዎ፣ ከዚያ፡ በላይ፡ አይወስድም።

ጥያቄ	መልስ
እርስዎ፡ በስንት፡ መከራየት፡ ይፈልጋሉ?	በሁለት፡ መቶ፡ ሰባ፡ አምስት፡ ብር፡ ቢያከራዩኝ፡ እገባበታለሁ።
እርስዎ፡ ባሉት፡ ዋጋ፡ ባከራይዎ፡ የመብራቱን፡ ዋጋ፡ ይችላሉ?	የለም፣ ሁሉንም፡ እርስዎ፡ ይቻሉ።
መስኮቶች፡ በሙሉ፡ መጋረጃ፡ አሉዋቸው?	አዎ፣ ሁሉም፡ ባለመጋረጃ፡ ናቸው።
ማረፊያ፡ ቤቱስ፡ ምንጣፍ፡ አለው?	ማረፊያ፡ ቤቱ፡ ምንጣፍ፡ የለውም።
የመዝጊያዎቹ፡ ቁልፎች፡ በሙሉ፡ ደህና፡ ይሠራሉ?	አዎ፣ ሁሉም፡ አዲስ፡ ነው።
ታዲያ፡ ወለሉን፡ መቼ፡ በሰም፡ ያስጠርጉታል?	ነገ፡ ቀኑን፡ በሙሉ፡ ሰዉን፡ በማስጠረግና፡ በማስወልወል፡ እውላለሁ።
አጥሩ፡ ላይ፡ መብራት፡ ስለሌለ፡ እንዳስገባልዎ፡ ይፈልጋሉ?	አዎ፣ በጣም፡ ደስ፡ ይለኛል።
ታዲያ፡ ቤቱን፡ አስጠርገው፡ ሲጨርሱ፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?	አዎ፣ ነገ፡ ማታ፡ አስታውቅዎታለሁ።
የቤቱን፡ ኪራይ፡ የምከፍልዎት፡ በየወሩ፡ መጀመሪያ፡ ነው፡ ወይስ፡ መጨረሻ?	በየወሩ፡ መጀመሪያ፡ ላይ፡ ነው።
በወሩ፡ መጀመሪያ፡ ግማሹን፡ መጨረሻ፡ ደግሞ፡ የቀረውን፡ ልከፍልዎ፡ እችላለሁ?	ለርስዎ፡ ምቹ፡ ከሆነ፡ እኔ፡ ግድ፡ የለኝም።
እንግዲያስ፡ ውሉን፡ መቼ፡ እንፈራረም?	እኔ፡ አሁንም፡ ቢሆን፡ ግድ፡ የለኝም።

ድርሰት

የቤት፡ ኪራይ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ውድ፡ አይደለም። በትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ውስጥ፡ እንደ፡ አዲስ፡ አበባ፥ አስመራና፡ ድሬዳዋ፡ የቤት፡ ኪራይ፡ ጥቂት፡ ወደድ፡ ያለ፡ ነው። ምክንያቱም፡ እነዚህ፡ ከተማዎች፡ የንግድ፡ ቦታዎች፡ ከመሆናቸው፡ በላይ፡ ብዙ፡ የውጭ፡ አገር፡ ሰዎች፡ ስለሚኖሩባቸው፥ የቤት፡ ኪራይ፡ በየጊዜው፡ እያደገ፡ ሄዷል።

አንድ፡ ሰው፡ ቤት፡ ለመከራየት፡ ሲፈልግ፥ ወደ፡ ቤቱ፡ ጌታ፡ ዘንድ፡ ሄዶ፡ ስለዋጋው፡ መነጋገር፡ አለበት። የቤቱ፡ ኪራይ፡ የሚወሰነው፡ በተከራዩና፡ ባከራዩ፡ መካከል፡ በሚደረገው፡ ስምምነት፡ ነው። ተከራዩ፡ አሽከርና፡ ገረድ፡ እንዲሁም፡ ቤተ፡ ሰብ፡ ያለው፡ እንደሆነ፡ ትልቅ፡ ቤት፡ ያስፈልገዋል። ከከተማ፡ ወጣ፡ ብሎ፡ ለመኖር፡ ከፈለገ፥ ራሱን፡ የቻለ፡ አጥር፡ ግቢ፡ ያለው፡ ቤት፡ በቀላል፡ ዋጋ፡ ያገኛል።

ብዙ፡ ቤተ፡ ሰብ፡ ያላቸው፡ ሰዎች፡ የልጆቻቸውን፡ ጤንነት፡ ለመጠብ፡ ሲሉ፡ ከከተማ፡ ወጣ፡ ብለው፡ ይከራያሉ። ብዙ፡ ዓመት፡ በኪራይ፡ ቤት፡ ከመቀመጥ፡ ይልቅ፡ ቤት፡ መሥራት፡ ስለሚረክስ፥ የከተማው፡ ነዋሪዎች፡ የራሳቸውን፡ ቤት፡ ለመሥራት፡ ይወዳሉ።

ከቅርብ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ መንግሥት፡ ቤቶች፡ እየሠራ፡ ለሕዝብ፡ ያከራያል። የመሥሪያ፡ ዋጋና፡ ሠራተኛ፡ እርካሽ፡ በመሆኑ፥ መንግሥት፡ የሚያከራያቸው፡ ቤቶች፡ ኪራያቸው፡ በጣም፡ ቀላል፡ ነው። በዚህ፡ አያያዝ፡ የቀጠለ፡ እንደሆነ፡ ወደፊት፡ የቤት፡ ኪራይ፡ ችግር፡ እየተቀነሰ፡ ይሄዳል።

ጥያቄዎች

የቤት፡ ኪራይ፡ ለማግኘት፡ የት፡ መሄድ፡ ያስፈልጋል?

የቤት፡ ኪራይ፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ እንዴት፡ ነው?

አንድ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ቤት፡ በወር፡ ስንት፡ ይከራያል?

ኢትዮጵያና፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ቤት፡ የመፈለግ፡ ዘዴ፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ነው?

በኢትዮጵያና፡ በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ የቤት፡ መፈለግ፡ ዘዴን፡ ልዩነት፡ አስረዳ።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ቤት፡ የት፡ አገኘ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የተከራየውን፡ ቤት፡ ዓይነት፡ ባጭሩ፡ ግለጽ።

የቤት፡ ኪራይን፡ ችግር፡ ለማሻሻል፡ መንግሥት፡ ምን፡ ያደርጋል?

አርባ፡ ሰባተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

አቶ፡ ከበደ፣ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሃይማኖት፡ ብዙ፡ ስላልነገሩኝ፡ አሁን፡ እንዲነግሩኝ፡ እፈልጋለሁ።

ከበደ

ማወቅ፡ የሚፈልጉት፡ ምን፡ እንደሆነ፡ ካወቅሁትና፡ ማስረዳት፡ ከቻልሁ፡ ይጠይቁኝና፡ ልንገርዎት።

ዮሐንስ

መጀመሪያ፡ ማወቅ፡ የምፈልገው፡ አብዛኛው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የሚያምንበትን፡ ሃይማኖት፡ ነው።

ከበደ

ምንም፡ እንኳን፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በብዙ፡ የሚቆጠሩ፡ ሃይማኖቶች፡ ቢኖሩ፣ አብዛኛው፡ ሕዝብ፡ ኦርቶዶክስ፡ ነው።

ዮሐንስ

ሌሎችስ፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚገኙት፡ ሃይማኖቶች፡ ምን፡ ምን፡ ዓይነት፡ ናቸው?

ከበደ

ምንም፡ እንኳን፡ ሁሉንም፡ ባለማወቄ፡ ልነግርዎ፡ ባልችል፣ ከብዙው፡ ጥቂቶቹ፡ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንትና፡ እስላም፡ ናቸው።

ዮሐንስ

የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ሃይማኖት፡ የተወረሰው፡ ከየት፡ ነው?

ከበደ

የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ሃይማኖት፡ ከመጣው፡ ከግሪክ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።

ዮሐንስ

ኢትዮጵያ፡ የክርስቲያንን፡ ሃይማኖት፡ የተቀበለችው፡ በስንተኛው፡ መቶ፡ ዓመት፡ ነው?

ከበደ

ኢትዮጵያ፡ ክርስቲያን፡ የሆነችው፡ በራተኛው፡ መቶ፡ ዓመት፡ ነው።

ዮሐንስ

የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ቄሶች፡ ሚስት፡ ማግባት፡ ይፈቀድላቸዋል?

ከበደ

እዎ፣ በኢትዮጵያ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ከመነኩሴዎቹ፡ በቀር፡ ቄስ፡ ለመሆን፡ ሚስት፡ ማግባት፡ አለባቸው።

ዮሐንስ

ለመሆኑ፡ አንድ፡ ቄስ፡ ሚስቱ፡ ብትሞትበት፡ ሌላ፡ ማግባት፡ ይችላል?

ከበደ

የለም፣ አይችልም።

ዮሐንስ

እሺ፣ ለሁሉም፡ አመሰግናለሁ። አምላክ፡ ይስጥልኝ።

ከበደ

ምንም፡ አይደለ። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
በዚህ፡ ሰፈር፡ ውስጥ፡ የሚገኙት፡ ቤቶች፡ በጣም፡ መወደዳቸውን፡ ከማን፡ ሰማህ?	አንድ፡ ሰው፡ ነገረኝ።
ረጅሙን፡ ሰማያዊ፡ ፎቅ፡ ቤት፡ ለመግዛት፡ ካቶ፡ ለማ፡ አባት፡ ጋር፡ ተስማማህ?	የለም፣ ገና፡ በመነጋገር፡ ላይ፡ ነን።
ያስተማሪው፡ ገረድ፡ ጥሩ፡ ፓስታ፡ ትሠራለች?	እዎ፣ ጥሩ፡ ትሠራለች።
አተከራየኸው፡ ቤት፡ አጥር፡ ግቢ፡ ውስጥ፡ የመኪና፡ ማቆሚያ፡ አለ?	አዎ፣ አንድ፡ ሰፊ፡ የመኪና፡ ማቆሚያ፡ አለ።
በሚመጣው፡ ዓመት፡ መኪና፡ ቢረክስ፡ ምን፡ ዓይነት፡ መኪና፡ ትገዛለህ?	ካዲላክ፡ ነዋ! ሌላ፡ ምን፡ እገዛ፡ ይመስልሃል።

ጥያቄ	መልስ
የገረድህና፡ ያሽከርህ፡ የቤት፡ አያያዝ፡ አስደሰተህ?	አዎ፣ በጣም፡ አስደስቶኛል።
የንግድ፡ ሚኒስትሩ፡ ሃይማኖት፡ ምንድን፡ ነው?	ኦርቶዶክስ፡ ይመስለኛል።
አከተማው፡ ውስጥ፡ የሚኖሩት፡ እስላሞች፡ መስጊድ፡ አላቸው?	አዎ፣ በጣም፡ ጥሩ፡ መስጊድ፡ አላቸው።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ቢሞት፡ ንብረቱን፡ የሚወርሰው፡ ልጅ፡ አለው?	አዎ፣ አንዲት፡ ሴት፡ ልጅ፡ አላቸው።
ያቶ፡ ከበደ፡ ሃብት፡ ከምን፡ ተወረሰበት?	አንድ፡ የሠራው፡ መኖጃ፡ ሥራ፡ ይኖር፡ ይሆናል።
ሃይማኖትህ፡ ከግሪክ፡ ኦርቶዶክስ፡ ሃይማኖት፡ ጋር፡ ይመሳሰላል?	አዎ፣ በጣም፡ የተቀራረበ፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ቄስ፡ ሚስት፡ ማግባት፡ ይፈቀድለታል?	አዎ፣ ይፈቀድለታል።
መነኩሴዎችስ፡ ማግባት፡ ይፈቀድላቸዋል?	የለም፣ አይፈቀድላቸውም።
አሜሪካ፡ ከመጣህ፡ ጀምሮ፡ እሁድ፡ እሁድ፡ የትኛው፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ትሄዳለህ?	ግሪክ፡ ኦርቶዶክስ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እሄዳለሁ።
አውሮፓ፡ ውስጥ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መርከቡን፡ ማን፡ ነገረህ?	ወንድሜ፡ እዚያ፡ ይማር፡ ነበርና፡ ከእርሱ፡ ሰማሁ።
አዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ የሱፍ፡ ልብስ፡ መሸጡን፡ በስልክ፡ ጠየቅህ?	አዎ፣ ጠየቅሁ።

ጥያቄ	መልስ
የቤተ፡ክርስቲያኑ፡ ደሐሌ፡ ቄስ፡ ነው?	አዎ፣ ቄስ፡ ነው።
ነገ፡ ቤተ፡ክርስቲያኑ፡ በስንት፡ ሰዓት፡ ይዘጋል?	በስምንት፡ ሰዓት፡ ከሃያ፡ ደቂቃ፡ ይዘጋል።
የስላሞች፡ መስጊድ፡ ቅዳሜ፡ ጥዋት፡ ክፍት፡ ነው?	አዎ፣ ሁልጊዜ፡ ክፍት፡ ነው።
መስጊዱ፡ ውስጥ፡ አንድ፡ ሰው፡ ከመግባቱ፡ በፊት፡ ጫማውን፡ የግዴታ፡ ማውለቅ፡ አለበት?	አዎ፣ ማውለቅ፡ አለበት።
ኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ ስትገባ፡ ማውለቅ፡ ግዴታ፡ ነው?	አዎን፣ አብዛኛው፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ ከመግባትህ፡ በፊት፡ ማውለቅ፡ ያስፈልጋል።
የኢትዮጵያ፡ የቤተ፡ክርስቲያን፡ መጽሐፎች፡ ወደ፡ አማርኛ፡ ተተርጉመዋል?	የለም፣ አልተተረጎሙም።
የቤተ፡ክርስቲያኖች፡ ሁኔታ፡ አሁን፡ ተሻሽሏል?	አዎ፣ ትንሽ፡ ተሻሽሏል።
የቅኔ፡ አመጣጥ፡ ከምን፡ እንደሆነ፡ ይገባሃል?	የለም፣ አይገባኝም።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በየትኛው፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ቤተ፡ክርስቲያኖች፡ አሉ?	በጐጃምና፡ በትግሬ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ነው።

ድርሰት

ኢትዮጵያ፡ የክርስቲያንን፡ ሃይማኖት፡ የተቀበለችው፡ በአራተኛው፡ መቶ፡ ዓመተ፡(ምሀረት)፡ነው። የሆነው፡ ሆኖ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሃይማኖቷን፡ ለመደምሰስ፡ የተነሱ፡ ሰዎች፡ ነበሩ። ምንም፡ እንኳን፡ እነዚህ፡ ሰዎች፡ በየጊዜው፡ አዲስ፡ አሳብ፡ እየፈጠሩ፡ ሃይማኖቷን፡ ለመደምሰስ፡ ቢሞክሩም፣ ኢትዮጵያ፡ እነሱን፡ በመቃወም፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ሃይማኖቷን፡ ጠብቃ፡ ትገኛለች።

አንድ፡ ጊዜ፡ አንድ፡ ግራኝ፡ መሐመድ፡ የሚባል፡ ሰው፡ ከምሥራቅ፡ ኢትዮጵያ፡ ተነስቶ፣ በክርስቲያኖች፡ ላይ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ጉዳት፡ አድርጎ፡ ነበር። ብዙ፡ የጥንት፡ ታሪክ፡ ያላቸውን፡ አሮጌ፡ ቤተ፡ ክርስቲያኖች፡ አቃጠለ። ቀሳውስቶችንም፡ ጨፈጨፋቸው። ከሱም፡ ሌላ፡ አንዲት፡ ዮዲት፡ የምትባል፡ ኃይለኛ፡ ሴት፡ በኋላም፡ ተነስታ፡ የክርስቲያንን፡ ሃይማኖት፡ በመቃወም፣ በቤተ፡ ክርስቲያንና፡ በክርስቲያኖች፡ ላይ፡ ጉዳት፡ ማድረጓን፡ በታሪክ፡ ላይ፡ ተጽፎ፡ እናገኛለን።

ጥያቄዎች

የክርስቲያን፡ ሃይማኖት፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የገባው፡ መቼ፡ ነው?

የኢትዮጵያ፡ ሃይማኖት፡ ከየትኛው፡ ሃይማኖት፡ ጋር፡ ይመሳሰላል?

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የክርስቲያንን፡ ሃይማኖት፡ የተቃወሙትን፡ ሰዎች፡ ስም፡ ጥራ።

እነዚህ፡ ሰዎች፡ ሃይማኖትን፡ የተቃወሙት፡ ለምን፡ ይመስልሃል?

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከሚገኙት፡ ብዙ፡ ሃይማኖቶች፡ ጥቂቶቹን፡ ንገረኝ።

የኢትዮጵያ፡ ቄሶች፡ ሚስት፡ ማግባት፡ ይፈቀድላቸዋል?

አርባ፡ ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ኢትዮጵያ፡ ላደን፡ ምቹ፡ አገር፡ መሆንዋን፡ ከመምጣቴ፡ በፊት፡ ሰማ፡ አድርጌ፡ ነበር።

አሁን፡ ስላደን፡ በሰፊው፡ ሊያስረዱኝ፡ ይችላሉ?

ከበደ

ለመሆኑ፡ የፈቃድ፡ ወረቀት፡ አለዎት?

ዮሐንስ

የፈቃድ፡ ወረቀት፡ ያስፈልጋል፡ እንዴ?

ከበደ

አዎ፣ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ያለፈቃድ፡ ወረቀት፡ ማደን፡ አይቻልም።

ዮሐንስ

ታዲያ፡ ፈቃድ፡ ከየት፡ ማግኘት፡ እችላለሁ።

ከበደ

ማመልከቻ፡ ጻፍ፡ አድርገው፣ ወደ፡ አገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡ ቢሄዱ፣ ለጸሐፊው፡ ቢነግሩዋቸው፣ ወዲያውኑ፡ ቀረጡን፡ አስከፍለው፡ የፈቃድ፡ ወረቀቱን፡ ይሰጡዎታል።

ዮሐንስ

ይህን፡ ነገር፡ ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ አፈጽማለሁ።

ከበደ

አዳኝ፡ ከመሆንዎ፡ በፊት፡ ማሰብ፡ የሚያስፈልግዎ፡ በጣም፡ ጨካኝና፡ ሰውን፡ ስብርብር፡ የሚያደርጉ፡ አውሬዎች፡ መኖራቸውን፡ ማወቅ፡ ነው።

ዮሐንስ

እንደፈለጉት፡ ስብር፡ ያድርጉኛል፡ እንጂ፡ ማደኔን፡ አላቆምም።

ከበደ

ከሁሉም፡ ቢያስቡበት፡ አይከፋም። ለምሳሌ፡ ትልልቅ፡ አውሬዎችን፡ ከማደን፡ ትናንሽ፡ አውሬዎችን፡ ማደን፡ ይሻላል።

ዮሐንስ

እነዚህ፡ ትናንሽ፡ አውሬዎች፡ የት፡ ይገኛሉ?

ከበደ	ዮሐንስ
እነሱ፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ በየሜዳውና፡ በየኮረብታው፡ ጎራቸውን፡ ሲያቋቁሙ፡ ይገኛሉ።	ይሁን። ብቻ፥ የፍቃድ፡ ወረቀቱን፡ አውጥቼ፡ አዲሱን፡ እጀምራለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ከወንበሩ፡ ላይ፡ እንዲቀመጥ፡ ብሎ፡ የተነሳ፡ ማን፡ ነው?	ያስተማሪዋ፡ ልጅ፡ ነው።
አንድ፡ ነገር፡ ቢመጣ፡ አገርህን፡ ለመከላከል፡ ፈቃደኛ፡ ነህ?	አዎን፤ ፈቃደኛ፡ ነኝ።
ከሽርሽር፡ ስትሄዱ፡ ቤታችሁን፡ የሚጠብቅላችሁ፡ ሰው፡ አገኛችሁ?	አዎ፤ አንድ፡ ተማሪ፡ ሊጠብቅልን፡ ነው።
ስኒውን፡ የት፡ አስቀመጠው?	ለማ፡ ዘንድ፡ አስቀመጥሁት።
የቡናውን፡ ዛፍ፡ ጭፍጭፍ፡ ያደረገው፡ ማን፡ ነው?	መንገድ፡ ሠራተኞች፡ ናቸው።
ስለ፡ ከብት፡ ማርባት፡ ከመጽሐፉ፡ ውስጥ፡ ተጠቀሰ?	የለም፤ ገና፡ አልተጠቀሰም።
ከጋዜጣው፡ ውስጥ፡ የሰዎቹን፡ ስም፡ መጥቀስ፡ ያስፈልጋል?	አዎን፤ መጥቀስ፡ ያስፈልጋል።
ለምን፡ የሚኒስትሩን፡ ንግግር፡ ለማ፡ እደርጋችሁ፡ አትሄዱም?	አሁን፡ ለመስማት፡ ጊዜ፡ የለንም።

ጥያቄ	መልስ
ያለ፡ መኪና፡ ወደ፡ ጐጃም፡ መሄድ፡ ይቻላል?	የለም፣ አይቻልም።
ከናንተ፡ መካከል፡ ያለ፡ ጥሪ፡ የመጣ፡ ሰው፡ አለ?	አዎ፣ ሁለታችን፡ አልተጠራንም።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ያለ፡ ፈቃድ፡ ማደን፡ ይቻላል?	የለም፣ ያለ፡ ፈቃድ፡ ማደን፡ አይቻልም።
አገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ የሚሠራ፡ ወንድም፡ አለህ?	አዎ፣ እዚያ፡ የሚሠራ፡ ወንድም፡ አለኝ።
ከደሞዝህ፡ ቀረጥ፡ ስንት፡ ትከፍላለህ?	አሥር፡ ብር፡ እከፍላለሁ።
ሠራተኞች፡ ከፍ፡ ያለ፡ ቀረጥ፡ ይከፍላሉ?	አዎን፣ ቀረጡ፡ በጣም፡ ከፍተኛ፡ ነው።
ከኔ፡ ጋር፡ የሚሄድ፡ ጥሩ፡ አዳኝ፡ ታውቃለህ?	አዝናለሁ፣ የማውቀው፡ ጥሩ፡ አዳኝ፡ የለም።
አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከመንገዱ፡ ዳር፡ ቆመው፡ ምን፡ ይሠራሉ?	ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ ስለተቃጠሩ፡ እሱን፡ ይጠብቃሉ።
እኮረብታው፡ ላይ፡ ሣር፡ የሚከታተሙት፡ ፍየሎች፡ ያንተ፡ ናቸው?	የለም፣ የኔ፡ አይደሉም።
ከብቶችህን፡ የት፡ ሣር፡ ታበላቸዋለህ?	እወንዙ፡ ዳር፡ ነው።
የሴትዮዋ፡ የሥራ፡ እያያዝ፡ በጣም፡ አስደሳች፡ ነው?	አዎ፣ ምንም፡ አይል።
በሚመጣው፡ ዓመት፡ የመሬት፡ ዋጋ፡ በቀነሰ፡ መሬት፡ ገዝተህ፡ ቤት፡ መሥራት፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ በጣም፡ እፈልጋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ የቤት፡ ዋጋ፡ መርከሱንና፡ መወደዱን፡ እንዴት፡ ላውቅ፡ እችላለሁ?	እከተማው፡ ውስጥ፡ የምታውቀው፡ ሰው፡ እንዳለ፡ እሱን፡ በደብዳቤ፡ ጠይቀው።
አጥር፡ ግቢያችሁ፡ ውስጥ፡ የነበረችውን፡ አሮጌ፡ መኪና፡ ማን፡ ወሰዳት?	ባለቤቷ፡ ወስዳ፡ ጋራዥ፡ ተወቻት።
ላሽከርህ፡ ደሞዙን፡ ከፈልከው?	የለም፣ አልከፈልኩትም።
ወደፊት፡ የቤት፡ ኪራይ፡ መወደዱንና፡ አለመወደዱን፡ ታውቃለህ?	የለም፣ እንዴት፡ ላውቅ፡ እችላለሁ።
የቤቱን፡ ወለል፡ በሰም፡ አስወለወልከው?	የለም፣ ገና፡ አላስወለወልኩትም።
የቤቱን፡ ምንጣፍ፡ ሊለውጡልኝ፡ ይችላሉ?	አዎ፣ አዲስ፡ ምንጣፍ፡ አስገባልዎታለሁ።
ቁም፡ ሳጥኑ፡ የተሠራ፡ ከእንጨት፡ ነው?	ከንጨት፡ የተሠራ፡ ነው።
የቤቱ፡ ግድግዳ፡ የተሠራ፡ ከእንጨት፡ ነው፡ ወይስ፡ ከድንጋይ?	የለም፣ ከጡብ፡ ነው።
እንግሊዝኛ፡ ቋንቋ፡ ለመማር፡ የት፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ ጥሩ፡ ነው?	እንግሊዝ፡ አገር፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው።
ቤቱ፡ ከጥንቱ፡ አሁን፡ አሳማረም?	አዎ፣ በጣም፡ አምሯል።
አግቢያችሁ፡ ውስጥ፡ መኪና፡ ማቆም፡ ክልክል፡ ነው?	አዎ፣ ክልክል፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
እርግጠውን፡ ቤት፡ ከቀየሩ፡ አዲሱ፡ ቤት፡ መቼ፡ ይገባሉ?	ከአንድ፡ ሳምንት፡ በኋላ፡ አዲሱ፡ ቤት፡ ይገባሉ።
ቤቱ፡ መለቀቁን፡ ከሰማችሁ፡ ቆይታችኋል?	አዎን፤ ከሰማን፡ ቆይተናል።
እዚህ፡ የመጣህ፡ አገሩን፡ ለማየት፡ ነው?	አገሩን፡ ለማየት፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ ትምህርትም፡ ለመማር፡ ነው።
በሩን፡ የሰበርከው፡ ልትከፍት፡ ስትል፡ ነው?	አዎ፤ ልከፍት፡ ስል፡ ነው።
የንጠቆን፡ አልጋ፡ ያገኘኸው፡ የብረት፡ አልጋ፡ ልትፈልግ፡ ስትል፡ ነው?	አዎ፤ የብረት፡ አልጋ፡ ልፈልግ፡ ስል፡ ነው።
ለማ፡ የሄደው፡ ምሳ፡ ሊሰጡት፡ ሲሉ፡ ነው?	አዎ፤ ሊሰጡት፡ ሲሉ፡ ነው።
ጠላ፡ የሰጣችሁት፡ ራቱን፡ ሊበላ፡ ሲል፡ ነው?	የለም፤ ከዚያ፡ በኋላ፡ ነው።
ለማ፡ የሚወስድህ፡ ራት፡ ልትበላ፡ ስትል፡ ነው?	አዎ፤ ራት፡ ልበላ፡ ስል፡ ነው።
እግሯን፡ የቆረጠችው፡ ዛፍ፡ ልትቆርጥ፡ ስትል፡ ነው?	አዎ፤ እንጨት፡ ልትቆርጥ፡ ስትል፡ ነው።
መኪናቸውን፡ እጥቃ፡ ውስጥ፡ የሌነቃሩት፡ ሊነዱ፡ ሲሉ፡ ነው?	አዎ፤ ሊነዱ፡ ሲሉ፡ ነው።
ወገባቸውን፡ የትሌት፡ ድንጋዩን፡ ሊያነሱ፡ ሲሉ፡ ነው?	አዎ፤ ድንጋዩን፡ ሊያነሱ፡ ሲሉ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የመኪናቸው፡ ጎማ፡ የፈነዳው፡ ጡብ፡ ከያመጡ፡ ሊኩ፡ ነው?	አዎ፣ ጡብ፡ ከያመጡ፡ ሊኩ፡ ነው።

ድርሰት

አንድ፡ ሰው፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ለማደን፡ ቢፈልግ፣ ማደን፡ የሚፈልጋቸውን፡ አውሬዎች፡ ስምና፡ ዓይነት፡ እንዲሁም፡ ቁጥር፡ በመተንተን፡ አንድ፡ ማመልከቻ፡ ጽፎ፡ ወደ፡ አገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡ ይዞ፡ መሄድ፡ አለበት። ከዚያም፡ ጉዳዩን፡ ከሚመለከተው፡ ባለሥልጣን፡ ዘንድ፡ የፍቃድ፡ ወረቀት፡ ማስወጣት፡ አለበት።

ይህ፡ ሰው፡ በጥያቄው፡ መሠረት፡ የፈቃዱ፡ ወረቀት፡ ሲዘጋጅለት፡ የተወሰነውን፡ ቀረጥ፡ ከፍሎ፡ መውሰድ፡ ይችላል። ከዚያ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የትም፡ እየተዘዋወረ፡ የተመኛቸውን፡ አውሬዎች፡ ማደን፡ ይችላል።

ነገር፡ ግን፡ ከተወሰነው፡ ቁጥር፡ በላይ፡ ወይም፡ ያልተፈቀደለትን፡ አውሬ፡ ገድሎ፡ ቢገኝ፣ በሕግ፡ ተላላፊነት፡ ተከሶ፣ ፍርድ፡ ቤት፡ ቀርቦ፡ የፈቃድ፡ ወረቀቱን፡ ከማጣቱም፡ በላይ፡ መቀጫ፡ ይከፍላል። ስለዚህ፡ አንድ፡ ሰው፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ለማደን፡ ቢፈልግ፣ ፍቃድ፡ ማስወጣት፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ ከተወሰነው፡ እንዳያልፍ፡ መጠንቀቅ፡ ግዴታ፡ ይሆንበታል።

ጥያቄዎች

አንድ፡ሰው፡ የፈቃድ፡ ወረቀት፡ ለማግኘት፡ የት፡ መሄድ፡ አለበት?

በደብዳቤው፡ ውስጥ፡ ምን፡ ነገር፡ መግለጥ፡ አለበት?

ያዳኙን፡ ፈቃድ፡ ወረቀት፡ ሲያወጣ፡ ምን፡ መክፈል፡ አለበት?

እርስዎ፡ ኢትዮጵያ፡ቢሄዱ፣ ምን፡ ዓይነት፡ አውሬዎች፡ ማደን፡ ይፈልጋሉ?

አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ላደን፡ የሚሆኑ፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ አውሬዎች፡ አሉ?

ለመሆኑ፡ ለሥጋ፡ የሚሆኑትን፡ አውሬዎች፡ ብቻ፡ ማደን፡ ይፈልጋሉ፡ ወይስ፡ ሌሎችንም፡ ያድናሉ?

አንድ፡ አዳኝ፡ ፈቃድ፡ ካወጣ፡ በኋላ፡ ለማደን፡ የት፡ ይሄዳል?

አዳኝ፡ ያልተፈቀደለትን፡ አውሬ፡ ገድሎ፡ ቢገኝ፡ ምን፡ ይደርስበታል?

ብዙ፡ አዳኞች፡ ባሜሪካ፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ?

እርስዎ፡ አዳኝ፡ ነዎት?

አርባ፡ ዘጠነኛ፡ ትምህርት

ንግግር

(የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴርን፡ መጐብኘት)

ዮሐንስ

ጤና፡ ይስጥልኝ፡ ጌታዬ፣ ስሜ፡ ዮሐንስ፡ ይባላል።

ከበደ

ጤና፡ ይስጥልኝ፣ ከበደ፡ እባላለሁ። ምን፡ ላድርግልዎ፡ ጌታዬ?

ዮሐንስ

አንድ፡ ጉዳይ፡ ስላለኝ፡ የክቡርነትዎን፡ እርዳታ፡ ለመጠየቅ፡ መጣሁ።

ከበደ

በተቻለኝ፡ መጠን፡ ጉዳይዎን፡ ለመፈጸም፡ እጥራለሁ።

ዮሐንስ

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ የሚባሉ፡ ያሜሪካ፡ መንግሥት፡ ልዩ፡ መልክተኛ፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ይገባሉ። ስለዚህ፡ ከክቡር፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ የሚገባው፡ ዝግጅት፡ እንዲደረግላቸው፡ በማሰብ፣ ለዚሁ፡ ጉዳይ፡ እርዳታዎን፡ ለመጠየቅ፡ መጣሁ።

ከበደ

ከክቡር፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ አስፈላጊውን፡ ዝግጅት፡ ለማድረግ፡ በኤምባሲያችሁ፡ በኩል፡ የሚገባውን፡ ጥያቄ፡ በደንቡ፡ መሠረት፡ እንዲቀርብልኝ፡ ያስፈልጋል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የንጨቱ፡ አርዝመት፡ ስንት፡ ሜትር፡ ነው?	ስምንት፡ ሜትር፡ ያህል፡ ነው።
ትምህርት፡ ቤታችሁ፡ ከእንጨት፡ የተሠራ፡ ነው?	የለም፣ ከድንጋይ፡ የተሠራ፡ ነው።
ከጡብ፡ ከተሠራና፡ ከድንጋይ፡ ከተሠራ፡ ቤት፡ የቱ፡ የበለጠ፡ ውድ፡ ነው?	ከድንጋይ፡ የተሠራው፡ ቤት፡ የበለጠ፡ ይወደዳል።
የንጨቶን፡ ቤት፡ ትቶ፡ ለጡብ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ገባ?	የለም፣ የእንጨቶን፡ ቤት፡ አልተወውም።
የከብቶቹ፡ በሽታ፡ ተላላፊ፡ ነው?	የለም፣ ተላላፊ፡ አይደለም።
ይህ፡ ሰውዬ፡ የበሽታውን፡ ተላላፊነት፡ እንዴት፡ አወቀ?	እንዴት፡ እንዳወቀ፡ አላውቅም።
ዛሬ፡ ጥዋት፡ በሰዓቱ፡ ሥራው፡ ስላልገባ፡ ተቆጣ?	የለም፣ አልተቆጣም።
ቢቆጣ፡ ኖሮ፡ መቆጣው፡ ስንት፡ ይሆን፡ ነበር?	ምናልባት፡ የግማሽ፡ ቀን፡ ደሞዙን፡ ያጣ፡ ነበር።
በተቻላቸው፡ መጠን፡ ለመምጣት፡ ሞክረው፡ ነበር?	የለም፣ ለመምጣት፡ በጭራሽ፡ አልሞከሩም።
በተቻለህ፡ መጠን፡ ልትረዳው፡ ፈቃደኛ፡ ነህ?	የለም፣ ጊዜ፡ ስለሌለኝ፡ ልረዳው፡ አልችልም።
ዓለም፡ ታሪክ፡ መጽሐፎች፡ ብዙ፡ አንብበሃል?	በተቻለኝ፡ መጠን፡ ስለአውሮፓ፡ ታሪክ፡ አንብቤአለሁ።

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ መጽሐፍ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስለ ገሌቾን፡ የተጻፉ፡ ብዙ፡ የታሪክ፡ መጽሐፎች፡ ይገኛሉ?	የለም፣ ብዙ፡ የታሪክ፡ መጽሐፎች፡ አይገኙም።
ታሪካችንን፡ ለመደምሰስ፡ የተነሳውን፡ ሰው፡ ስም፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
አንድ፡ ሰው፡ ያገርህንና፡ የሕዝብህን፡ ታሪክ፡ ለመደምሰስ፡ ቢነሳ፡ ምን፡ ታደርጋለህ?	በተቻለኝ፡ መጠን፡ እከላከላለሁ።
ከጠቀስኸው፡ በኋላ፡ እጎካሌው፡ መጥቶ፡ ነበር?	የለም፣ አልመጣም።
እርጊውን፡ ልብስህን፡ አውልቀህ፡ እዴሉን፡ ሞከርኸው?	የለም፣ አልሞከርሁትም።
እዚህ፡ ለመምጣት፡ ብዙ፡ ጥረሃል?	የለም፣ በቀላሉ፡ ለመምጣት፡ አልጣርሁም።
ባለፈው፡ ጊዜ፡ ከያገሩ፡ ብዙ፡ መልክተኞች፡ መጥተው፡ ነበር?	የለም፣ በጣም፡ ብዙ፡ አልነበሩም።
ወደ፡ አሜሪካ፡ የሚሄዱት፡ መልክተኞች፡ ተመለሱ?	የለም፣ ገና፡ አልተመለሱም።
እናንተ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ባለ፡ ሥልጣኖች፡ አሉ?	አንድ፡ አምስት፡ ይሆናሉ።
ለሕዝቡ፡ የተሰጠው፡ ደንብ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ይመስልሃል?	በጣም፡ ጥሩ፡ አይመስለኝም።
ለመሆኑ፡ ገንዘቡን፡ ለማስጠጣት፡ የሚጥር፡ ይመስልሃል?	የለም፣ አይመስለኝም።

ጥያቄ	መልስ
ሰዓቶን፡ አውልቀው፡ የት፡ አስቀመጡ?	እመሳቢያው፡ ላይ፡ ይመስለኛል።
መስከተኛው፡ እንዴት፡ ያለ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ነው፡ የሚኖር?	እደንጋይ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ነው።
ከየንዳንዳቸው፡ ከመቶ፡ ብር፡ በላይ፡ ያገባቸው፡ ይመስልሃል?	የለም፣ አይገባቸውም።
እኛ፡ መጽሐፍ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስንት፡ የታሪክ፡ መጻሕፍት፡ ያስፈልጉ፡ ይመስልሃል?	ቢያንስ፡ ሃምሳ፡ የታሪክ፡ መጻሕፍት፡ ያስፈልጋሉ።
ስለ፡ ቤቱ፡ ኪራይ፡ ዘርዝረው፡ ነገርሃቸው?	አዎ፣ ማንኛውንም፡ ነገር፡ ነገርሁዋቸው።
ከአሽከርህና፡ ገረድህ፡ በሕግ፡ ተካካሪንት፡ መቀጫቸው፡ ስንት፡ ነው?	አዎ፣ አሥር፡ ብር፡ ተቀጡ።
ከዚህ፡ አገር፡ ከመቅረትህ፡ ተማክረህ፡ ነበር?	የለም፣ አልተማከርሁም።
ካገርዎ፡ ዘንድ፡ የመጣውን፡ መንገደኛ፡ ተገናኙት?	የለም፣ አልተገናኘሁትም።

ድርሰት

ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ለሥራው፡ መሄድ፡ ለዲፕሎማቶች፡ መግባት፡ የተለመደ፡ ነገር፡ ነው። ዲፕሎማቶች፡ ከውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ብዙ፡ ውለታ፡ ሲደርስ፣ የሚገባው፡ እየተቀበሉና፡ ለሳምንት፡ ይስማማቸውና፡ ለመንገዳቸው፡ ከሚፈ

ሰዎች፡ ሰው፡ ጋር፡ እንዲገናኙ፡ ወደ፡ ቢሮው፡ ይገባሉ።

አንድ፡ ቀን፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የሚባሉ፡ አሜሪካዊ፡ ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ ለመነጋገር፡ ሄዱ። አቶ፡ ዮሐንስ፡ በአዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ በሚገኘው፡ በአሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ውስጥ፡ የሚኖሩ፡ ሠራተኛ፡ ናቸው። አቶ፡ ዮሐንስ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ቢሮ፡ እንደገቡ፡ ጉዳያቸውን፡ ካቶ፡ ከበደ፡ አቀረቡ። አቶ፡ ከበደም፡ በደስታ፡ ከተቀበሉዋቸው፡ በኋላ፡ ጉዳያቸውን፡ በትዕግሥት፡ አዳመጡዋቸው።

የአቶ፡ ዮሐንስ፡ ጉዳይ፡ እንደሚከተለው፡ ነው። ሚስተር፡ ስሚዝ፡ የተባሉ፡ ያሜሪካን፡ መንግሥት፡ ልዩ፡ መልክተኛ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ስለሚመጡ፡ የሚያስፈልገው፡ አቀባበል፡ እንዲደረግላቸው፡ ነው። ሚስተር፡ ስሚዝ፡ ከክቡር፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ጋር፡ በሰፊው፡ ከተነጋገሩ፡ በኋላ፡ ግርማዊ፡ ጃንሆይን፡ እጅ፡ እንዲነሱ፡ ነው። አቶ፡ ከበደ፡ ያቶ፡ ዮሐንስን፡ አሳብ፡ ካዳመጡ፡ በኋላ፡ ማናቸውንም፡ ነገር፡ በደንቡ፡ መሠረት፡ እንዲፈጸም፡ እናደርጋለን፡ ብለው፡ አሰናበቷቸው።

ጥያቄዎች

ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ በየጊዜው፡ የሚሄዱ፡ እነማን፡ ናቸው?

ዲፕሎማቶች፡ እውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሲደርሱ፡ እንዴት፡ ይቀበሉዋቸዋል?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ናቸው?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የት፡ ይሠራሉ?

ከማን፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ ወደ፡ ውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሄዱ?

የቶ፡ ከበደ፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

አቶ፡ ከበደና፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ በፊት፡ ይተዋወቃሉ?

በቢሮ፡ ውስጥ፡ ምን፡ አደረጉ?

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ለምን፡ መጡ?

ከማን፡ ጋር፡ ለመነጋገር፡ ፈለጉ?

ሃምሳኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ግርማዊ፡ ጃንሆይን፡ ከመገናኘትና፡ እጅ፡ ከመንሳት፡ በእናንተው፡ በኩል፡ ሊዘጋጅ፡ ይቻላል?

ከበደ

ከዚህ፡ ቶሎ፡ ለ ገልዎት፡ አልችልም። መጀመሪያ፡ የፕሮቶኮል፡ ክፍል፡ ከግቢ፡ ሚኒስቴር፡ ጋር፡ እንዲነጋገርና፡ በነገሩ፡ እንዲስማሙበት፡ ያስፈልጋል።

ከዚያ፡ በኋላ፡ አስፈላጊ፡ ሆኖ፡ ቢገኝ፥ ቀጠሮ፡ ይደረግልዎታል።

ዮሐንስ

ይህን፡ ከመነጋገር፡ ወደ፡ ግቢ፡ ሚኒስቴር፡ መሄድ፡ ያስፈልገኛል?

ከበደ

የለም፥ እርስዎ፡ ወደ፡ ግቢ፡ ሚኒስቴር፡ መሄድ፡ አያስፈልግዎትም። ነገሩ፡ የመሥሪያ፡ ቤት፡ ጉዳይ፡ ስለሆነ፥ አሁን፡ የፕሮቶኮል፡ ሹሙን፡ ጠርቼ፡ እንነጋገርበታለን።

ዮሐንስ

ክቡርነትዎ፡ በጉዳዩ፡ አሁን፡ ተነጋግሮበት፡ መልሱን፡ ወዲያው፡ ሊያስታውቁኝ፡ ይችላል?

ከበደ

ይህ፡ በችኮላ፡ የሚሆን፡ ነገር፡ አይደለም።

መጀመሪያ፡ ከፕሮቶኮሉ፡ ሹም፡ ጋር፡ ተነጋግረን፥ የቃል፡ ስምምነት፡ ካደረግን፡ በኋላ፥ ማመልከቻ፡ ጽፈን፡ ጉዳዩን፡ በዝርዝር፡ ለግቢ፡ ሚኒስትር፡ ማስረዳት፡ አለብን።

ዮሐንስ

ብዙ፡ ጊዜ፡ የሚፈጅ፡ ከሆነ፡ ነገሩን፡ ለማፋጠን፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋል?

ከበደ

ብዙ፡ ጊዜ፡ አይፈጅም። ዳሩ፡ ግን፡ ደንበኛውን፡ የቢሮ፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ መከተል፡ ስለሚያስፈልግ፥ የግቢ፡ ሚኒስትሩ፡ ራሳቸው፡ ጉዳዩን፡ ለግ

ርማዊነታቸው፡ አቅርበው፣ መልስ፡ መጠበቅ፡ ያስፈልጋቸዋል።

ዮሐንስ

በስንት፡ ቀኖች፡ ውስጥ፡ እርሳቸው፡ መልስ፡ ማግኘት፡ ይችላሉ?

ከበደ

ምናልባት፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሦስት፡ ቀን፡ ይፈጅ፡ ይሆናል።

ግን፡ ትዛዙ፡ ከግቢ፡ እንዲመጣልን፡ ወዲያው፡ እናስታውቃችኋለን።

ዮሐንስ

በዚህ፡ ሳምንት፡ ውስጥ፡ ከርስዎ፡ ዘንድ፡ መልስ፡ ልጠባበቅ።

ከበደ

አዎ፣ እናሰማዎታለን። ይበሉ፡ ጤና፡ ይስጥልኝ።

ዮሐንስ

እግዚአብሔር፡ ይስጥልኝ። ጤና፡ ይስጥልኝ።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
ከጃንሆይ፡ ጋራ፡ አቀባበሉ፡ ተደረገላቸው?	አዎን፣ በጣም፡ ጥሩ፡ አቀባበል፡ ተደረገላቸው።
የሚሉትን፡ መተርጐም፡ ትችላለህ?	የለም፣ መተርጐም፡ አልችልም።
ለምን፡ ተከትላችሁት፡ ሄዳችሁ?	ቤቱን፡ እዩልኝ፡ ስላለን፡ ነው።
ፖሊሱ፡ እንደሚከተለው፡ ያውቅ፡ ነበር?	የለም፣ በጭራሽ፡ አያውቅም፡ ነበር።
ግርማዊነታቸው፡ መኝታው፡ በነበሩ፡ ጊዜ፡ ጠየቅሃቸው?	የለም፣ መምጣታቸውን፡ አልሰማሁም።

ጥያቄ	መልስ
ጃንሆይ፡ ብዙ፡ ሴት፡ ልጆች፡ አሉዋቸው?	አዎን፣ ሴት፡ ልጆች፡ አሉዋቸው።
ዛሬ፡ በአምስት፡ ሰዓት፡ ጃንሆይን፡ እጅ፡ ለመንሳት፡ ትሄዳለህ?	የለም፣ በአምስት፡ ሰዓት፡ መሄድ፡ አልችልም።
በሚመጣው፡ ማክሰኞ፡ ለታየቸው፡ ቃል፡ ገብተሃል?	የለም፣ ቃል፡ አልገባሁም።
የግቢውን፡ አቅጣጫ፡ ታውቁታላችሁ?	የለም፣ አናውቅም።
እግቢው፡ አጠገብ፡ የነበረው፡ ሆቴል፡ አሁንም፡ አለ?	የለም፣ አሁን፡ የለም።
ነገሩን፡ በዝርዝር፡ ለማስረዳት፡ አመነታ?	የለም፣ በጭራሽ፡ አላመነታም።
ጃንሆይ፡ ከፕሬዚዳንቱ፡ ጋር፡ ያመሻሉ?	የለም፣ አያመሹም።
ጃንሆይ፡ አውሮጳን፡ የጐበኙ፡ በየትኛው፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ነው?	በአሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ አምስት፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ነው።
የሠራውን፡ ሥራ፡ በዝርዝር፡ አመነ?	የለም፣ እንዱንም፡ አላመነም።
ሰሌ፡ እንቦለክ፡ አለህ?	የለም፣ በጣም፡ ሰሌ፡ አይደለም።
ደንበኛ፡ ቤት፡ ሠራህ?	የለም፣ ገና፡ አልሠራሁም።
ቤቱን፡ ሲሠሩ፡ በጣም፡ ያፋጥናሉ?	የለም፣ በጣም፡ አያፋጥኑም።
እግቢው፡ ውስጥ፡ ያስቀመጣችሁትን፡ ዕቃ፡ ወሰዳችሁት?	የለም፣ አልወሰድነውም።
ነገሩን፡ ለሰዎች፡ ማሰማት፡ ያስፈልጋል?	የለም፣ አያስፈልግም።

ጥያቄ	መልስ
የመጡትን፡ ደብዳቤዎች፡ በዝርዝር፡ ማጥናት፡ ያስፈልጋል?	አዎ፣ ያስፈልጋል።
አቶ፡ ለማ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ በመርከብ፡ እንዲሄዱ፡ አዘዝኸው?	የለም፣ አላዘዝሁትም።
ልብስህ፡ እንዲታጠብልህ፡ ትዕዛዝ፡ ሰጠህ?	የለም፣ ገና፡ አልሰጠሁም።
የቤተ፡ መንግሥቱን፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ ታውቀዋለህ?	የለም፣ ገና፡ ልጠይቅ፡ ነው።
አዲስ፡ ቦርሳ፡ ገዝተህ፡ ሰጠኸው?	የለም፣ አልሰጠሁትም።
መቀሚውን፡ አስከፈሉህ?	የለም፣ አላስከፈሉኝም።
ባንኩ፡ የተሠራ፡ ከጡብና፡ ከእንጨት፡ ነው?	የለም፣ ከድንጋይ፡ ብቻ፡ ነው።
መልክተኛው፡ እግሩ፡ መጠራትህን፡ ነገረህ?	የለም፣ አልነገረኝም።
በምን፡ ምክንያት፡ የተቀጣ፡ ይመስልሃል?	በእውነቱ፡ አላወቅሁም።

ድርሰት

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ የተባሉ፡ የአሜሪካ፡ መንግሥት፡ ልዩ፡ መልክተኛ፡ ኢትዮጵያን፡ ለመጐብኘት፡ በአይሮፕላን፡ ከኒው፡ ዮርክ፡ ከተማ፡ ተነሥተው፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ተጓዙ።

አዲስ፡ አበባ፡ ከመግባታቸው፡ በፊት፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ የተባሉ፡ የአሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ሠራተኛ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ሄደው፣ ካቶ፡ ከበደ፡ ጋር፡ በስልክ፡ ተነጋገሩ።

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ ከፍ፡ ያሉ፡ የመንግሥት፡ ባለሥልጣን፡ በመሆናቸው፣ ኢትዮጵያ፡ በሚገቡበት፡ ጊዜ፡ ደንበኛው፡ የፕሮቶኮል፡ አቀባበል፡ እንዲደረግላቸውና፡ ግርማዊነታቸውን፡ እጅ፡ እንዲነሱ፡ የሚያስፈልገው፡ ነገር፡ እንዲዘጋጅላቸው፡ ሆነ።

ይህንን፡ ሥራ፡ ለማከናወን፡ ሥልጣኑ፡ ያቶ፡ ከበደ፡ በመሆኑ፣ ከፕሮቶኮል፡ ክፍል፡ ሹም፡ ጋር፡ ተነጋግረው፡ አንድ፡ ማመልከቻ፡ ለግቢ፡ ሚኒስቴር፡ እንዲላክ፡ ተደረገ። የግቢው፡ ሚኒስትር፡ ጉዳዩን፡ መርምረው፡ ለግርማዊ፡ ጃንሆይ፡ አቀረቡ።

ግርማዊ፡ ጃንሆይ፡ መልካም፡ ፈቃዳቸው፡ መሆኑን፡ በማስታወቃቸው፣ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴሩ፡ ሠራተኛ፡ አቶ፡ ከበደ፡ ከአሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ባለሥልጣን፡ ካቶ፡ ዮሐንስ፡ ጋር፡ ነገሩን፡ አዘጋጁ።

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ አዲስ፡ አበባ፡ በሚገቡበት፡ ሰዓት፡ የፕሮቶኮል፡ ሹምና፡ ያሜሪካን፡ አምባሳደር፡ ከነተከታዮቻቸው፡ አይሮፕላን፡ ማረፊያ፡ ድረስ፡ ሄደው፡ እንግዳውን፡ ተቀበሉ። በማግሥቱ፡ እንግዳው፡ ግርማዊነታቸውን፡ እጅ፡ ለመንሳት፡ ወደ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ ሄዱ።

ጥያቄዎች

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ ሥራቸው፡ ምንድን፡ ነው?

ከየት፡ አገር፡ መጡ?

ሚስተር፡ ስሚዝ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሲገቡ፡ ምን፡ ዓይነት፡ አቀባበል፡ እንዲደረግላቸው፡ ያስፈልጋል?

ለምን፡ ግርማዊነታቸውን፡ እጅ፡ ለመንሳት፡ ፈለጉ?

ያቶ፡ ካቢኔ፡ ሥልጣን፡ ምንድን፡ ነው?

ለምን፡ እንደ፡ ማመልከቻ፡ ለግቢ፡ ሚኒስቴር፡ እንዲጻፍ፡ አደረገ?

ጉዳዩን፡ ማን፡ መረመረው?

ጉዳዩ፡ ከተመረመረ፡ በኋላ፡ ለማን፡ ቀረበ?

እንግዳውን፡ የተቀበሉ፡ ሰዎች፡ እነማን፡ ናቸው?

ከውጭ፡ አገር፡ እንግዳ፡ ሲመጣ፡ ተቀብለህ፡ ታውቃለህ?

ሃምሳ፡ አንደኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ስለ፡ ትምህርት

ዮሐንስ

በኢትዮጵያና፡ በአሜሪካ፡ ትምህርት፡ መካከል፡ ብዙ፡ ልዩነት፡ አለ?

ከበደ

በጠቅላላው፡ ሲታሰብ፡ የኢትዮጵያ፡ ትምህርትና፡ የአሜሪካ፡ ትምህርት፡ በብዙ፡ ነገር፡ ይመሳሰላሉ። ሆኖም፡ በአንዳንድ፡ ነገር፡ ይለያያሉ።

ለምሳሌ፡ በኮሌጅ፡ ደረጃ፡ የሚሰጠው፡ ትምህርት፡ ካሜሪካ፡ ትምህርት፡ ጋር፡ በጣም፡ ይመሳሰላል

በአንደኛ፡ ደረጃና፡ በሁለተኛ፡ ደረጃ፡ የሚሰጠው፡ ትምህርት፡ ግን፡ ካሜሪካ፡ ትምህርት፡ ጋር፡ አይመሳሰልም።

ዮሐንስ

አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ስንት፡ ክፍሎች፡ አሉዋቸው?

ከበደ

አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በስምንት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላሉ።

በያንዳንዱ፡ ክፍል፡ የአንድ፡ ዓመት፡ ትምህርት፡ ስለሚሰጥ፡ አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤትን፡ ለመጨረስ፡ ስምንት፡ ዓመት፡ ያስፈልጋል።

ዮሐንስ

ሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶችስ፡ አከፋፈላቸው፡ እንዴት፡ ነው?

ከበደ

ሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በአራት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላሉ። እንደዚህ፡ ባሉት፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ሁሉ፡ የአራት፡ ዓመት፡ ትምህርት፡ ይሰጣል።

በኮሌጅና፡ በዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ የሚሰጠው፡ ትምህርት፡ ከአሜሪካ፡ ትምህርት፡ ጋር፡ በብዙ፡ ነገር፡ ስለሚመሳሰል፡ ለርስዎ፡ አዲስ፡ ነገር፡ አይደለም።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ወደዚህ፡ አገር፡ የመጣህ፡ ለምንድን፡ ነው?	ለትምህርት፡ ነው።
ያንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ ነው፡ ወይስ፡ የሁለተኛ፡ ደረጃ?	የለም፣ የኮሌጅ፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ ነው።
ያንደኛና፡ የሁለተኛ፡ደረጃ፡ ትምህርትህን፡ የት፡ ተማርክ?	አገሬ፡ ውስጥ፡ ተምሬ፡ ጨረስኩ።
የአሜሪካ፡ ትምህርትና፡ የኢትዮጵያ፡ ትምህርት፡ ይመሳሰላል?	አዎን፣ የተቀራረበ፡ ነው።
ለምን፡ የኮሌጅ፡ ትምህርትህን፡ አገርህ፡ ውስጥ፡ አልቀጠልህም?	እስኮላርሺፕ፡ ስላገኘሁ፡ መጣሁ፡ እንጂ፡ እዚያው፡ ልቆይና፡ ልቀጥል፡ እችል፡ ነበር።
ለመሆኑ፡ በጣም፡ ብዙ፡ ኮሌጆች፡ አሉዋችሁ?	የለም፣ በጣም፡ ብዙ፡ አይደሉም።
አሁን፡ እዚህ፡ አገር፡ የት፡ ትምህርት፡ ቤት፡ እንደምትሄድና፡ ምን፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ እንደምትማር፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ትምህርትህን፡ ከጨረስክ፡ በኋላ፡ በቀጥታ፡ ወደ፡ አገርህ፡ ትመለሳለህ?	የለም፣ ለጥቂት፡ ጊዜ፡ እውሮጳን፡ ለመጎብኘት፡ እመኛለሁ።
ከተመለስክ፡ በኋላ፡ ማስተማር፡ ትፈልጋለህ?	አዎን፣ የማስተማር፡ ሥራ፡ በጣም፡ ደስ፡ ይለኛል።

ጥያቄ	መልስ
እኮሌጅ፡ ውስጥ፡ የሚያስተምሩ፡ ብዙ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ አስተማሪዎች፡ አሉ?	በጣም፡ ብዙ፡ አይደሉም። ሆኖም፡ መኖሩን፡ አሉ።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ የሕክምና፡ ኮሌጅ፡ የት፡ ከተማ፡ ነው?	በጎንደር፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ነው።
አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ኮሌጆች፡ አሉ?	የለም፣ ጥቂት፡ ናቸው።
አንተ፡ የተማርከበት፡ ትምህርት፡ ቤት፡ በሺ፡ የሚቆጠሩ፡ ተማሪዎች፡ አሉት?	አዎ፣ ብዙ፡ ሺ፡ ተማሪዎች፡ አሉት።
የትምህርት፡ ቤቱ፡ ዲሬክተር፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነበር?	አዎ፣ ኢትዮጵያዊ፡ ነበር።
በኢትዮጵያ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ ወንድና፡ ሴት፡ ተማሪዎች፡ አብረው፡ ይማራሉ?	አዎ፣ አብረው፡ ይማራሉ።
ትምህርት፡ ቤቶች፡ በሙሉ፡ የመንግሥት፡ ናቸው?	የለም፣ አንዳንድ፡ የግል፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ።
የቤተ፡ ክርስቲያን፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ከመንፈሳዊ፡ ትምህርት፡ ሌላ፡ ምን፡ ያስተምራሉ?	ሌላ፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ ያስተምራሉ።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ተማሪዎች፡ ለትምህርታቸው፡ ገንዘብ፡ ይከፍላሉ?	አዎ፣ ጥቂት፡ ገንዘብ፡ ይከፍላሉ።

ጥያቄ	መልስ
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ የግል፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ?	በጣም፡ ብዙ፡ አይደሉም። ያሉትም፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ የሚገኙት፡ አትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ውስጥ፡ ነው።
በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በያመቱ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በምን፡ ወር፡ ይጀመራሉ?	እንደዚህ፡ አገር፡ በመስከረም፡ ወር፡ ውስጥ፡ ነው።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ የሚሲዮን፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ብዙ፡ የርሻ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ናቸው።
የአስተማሪ፡ ደሞዝ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነው?	የለም፣ በጣም፡ ጥሩ፡ አይደለም።
የቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ የግል፡ ነው፡ ወይስ፡ የመንግሥት?	የመንግሥት፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ነው።
የሚገኘውስ፡ የት፡ ከተማ፡ ነው?	አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ነው።
ብዙ፡ ተማሪዎች፡ ይገኙበታል?	መጠነኛ፡ ናቸው።

ድርሰት

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በየቦታው፡ ተከፍተው፡ በብዙ፡ ሺ፡ የሚቆጠሩ፡ የኢትዮጵያ፡ ወጣቶች፡ ይማሩባቸዋል። እነዚህም፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በሦስት፡ ዋና፡ ክፍሎች፡ ይከፈላሉ። የመጀመሪያው፡ ክፍል፡ አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ይባላሉ። በነዚህ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ የስምንት፡

ዓመት፡ ኮርስ፡ ይሰጣል። በሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ግን፡ የአራት፡ ዓመት፡ ትምህርት፡ ይሰጣል።

ማናቸውም፡ ዓይነት፡ ከፍተኛ፡ ትምህርት፡ የሚሰጠው፡ በኮሌጅና፡ በዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ ስለሆነ፣ ለከፍተኛ፡ ትምህርት፡ የተዘጋጁት፡ ተማሪዎች፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ይሄዳሉ። በኮሌጅ፡ ውስጥ፡ የሚሰጠው፡ ትምህርት፡ ለአራት፡ ዓመት፡ ነው። በዚህ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ተማሪዎች፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ትምህርት፡ ይማራሉ። የኮሌጅ፡ ትምህርታቸውን፡ ሲያከናውኑ፡ ግማሾቹ፡ ሥራ፡ ይይዛሉ። ግማሾቹ፡ ግን፡ ለከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ወደ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ይሄዳሉ። በአዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ የተከፈተው፡ አዲሱ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ እየተስፋፋ፡ ሲሄድ፡ የተማሪዎቹ፡ ቁጥር፡ እየበዛ፡ እንደሚሄድ፡ የማይካድ፡ ነው።

ጥያቄዎች

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ተማሪዎች፡ ይገኛሉ?

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ አሉ?

የኢትዮጵያ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በስንት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላሉ?

የመጀመሪያው፡ ክፍል፡ ምን፡ ይባላል?

በአንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ የስንት፡ ዓመት፡ ኮርስ፡ ይሰጣል?

ከፍተኛ፡ ትምህርት፡ የት፡ ይገኛል?

በኮሌጅ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ ይሰጣል?

ዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ ለመግባት፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋል?

ዩኒቨርሲቲ፡ ውስጥ፡ ለመግባት፡ ሃብታም፡ መሆን፡ ያስፈልጋል?

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ዩኒቨርሲቲዎች፡ ይገኛሉ?

ሃምሳ፡ሁለተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

በአንደኛና፡ በሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ ይሰጣል?

ከበደ

በጠቅላላው፡ እርስዎ፡ አገር፡ የሚሰጠው፡ ትምህርት፡ እዚህም፡ ይሰጣል።

ከምሳሌ፡ ጆግራፊ፣ ቁጥር፣ ታሪክ፣ ሥነ፡ ጥበብ፣ ቋንቋና፡ ሃይማኖት፡ በአንደኛና፡ በሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ ይሰጣሉ።

በኮሌጅ፡ ደግሞ፡ እንደ፡ ፍልስፍና፣ ሕግ፣ ፖለቲካ፣ አስተዳደር፣ መሐንዲስነት፣ ሳይንስና፡ ሕክምና፡ የመሳሰሉት፡ ትምህርቶች፡ ይሰጣሉ።

ዮሐንስ

ተማሪዎች፡ እነዚህን፡ ትምህርቶች፡ የሚማሩት፡ በእንግሊዝኛ፡ ነው?

ከበደ

በአንደኛና፡ በሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ውስጥ፡ አማርኛንና፡ እንግሊዝኛን፡ ይጠቀሙባቸዋል። በኮሌጅ፡ ውስጥ፡ ግን፡ እንግሊዝኛንና፡ ፈረንሳይኛን፡ ይጠቀሙባቸዋል።

ዮሐንስ

ተማሪዎችን፡ መንግሥት፡ እየከፈለ፡ ነው፡ የሚያስተምራቸው፣ ወይስ፡ ራሳቸው፡ እየከፈሉ፡ ነው?

ከበደ

ቀደም፡ ከአንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ኮሌጅ፡ ድረስ፡ መንግሥት፡ ማናቸውንም፡ ወጪ፡ እየከፈለ፡ ተማሪዎችን፡ ያስተምር፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ ግማሹን፡ መንግሥት፣ ግማሹን፡ ተማሪዎች፡ እንዲከፍሉ፡ ተደርጓል።

ሐንስ	ከበደ
ትምህርት፡ በጣም፡ እየተወደደ፡ በመሄዱ፡ ተማሪዎቹን፡ መንግሥት፡ ካላገዛቸው፡ በስተቀር፡ በራሳቸው፡ እየከፈሉ፡ ከመማር፡ በጣም፡ ያስቸግራቸዋል።	ይህ፡ የማይጠረጠር፡ ነው። ስለዚህ፡ መንግሥት፡ ላንዳንድ፡ ተማሪዎች፡ እስኮላርሺፕ፡ ይሰጣል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
እዚህ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ስለሕክምና፡ የሚያውቁ፡ ሰዎች፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ባለቤትህ፡ የግል፡ ሃብት፡ አላት?	እንዴታ፣ በተለይ፡ አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ሞልቷታል።
የመንፈሳዊ፡ ትምህርት፡ ከመማር፡ የሚፈልጉ፡ ሰዎች፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
እሚስዮን፡ ትምህርት፡ ማስተማር፡ የሚፈልጉ፡ አስተማሪዎች፡ እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ?	አዎን፣ ሞልተዋል።
የትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ብዙ፡ እስኮላርሺፕ፡ አለው?	አዎ፣ ሞልቶታል።
አሁን፡ ቤቱ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ሰው፡ አለ?	አዎ፣ ሞልቶታል።

ጥያቄ	መልስ
የጆግራፊና፡ የታሪክ፡ ትምህርት፡ የተማሩ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ከሥነ፡ ጥበብ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ ፖሊቲካና፡ ፍልስፍና፡ የሚማሩ፡ ተማሪዎች፡ ሞልተዋል?	የለም፣ እነዚህን፡ ትምህርቶች፡ እዚህ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አያስተምሩም።
ከኢትዮጵያ፡ የመጡ፡ ሰዎች፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ዋሽንግተን፡ ውስጥ፡ ሞልተዋል።
በሚመጣው፡ ሳምንት፡ ብዙ፡ ወጪ፡ ታደርጋለህ?	ወጪ፡ የማደርግበት፡ ብዙ፡ ምክንያት፡ ሞልቶኛል።
ቤትህን፡ ስትሠራ፡ የሚያገዙህ፡ ጓደኞች፡ አሉህ?	አዎ፣ ሞልተውኛል።
በዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ የሚኖሩት፡ ሰዎች፡ መካከል፡ በፖሊቲካ፡ የሚጠረጠሩ፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ዛሬ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ምን፡ ታደርጋለህ?	ቀጠሮ፡ ሞልቶኛል።
እናንተ፡ መንደር፡ ቀበሮ፡ ሞልቷል?	ጥንት፡ ነበር፡ እንጂ፡ አሁን፡ አንድም፡ አይገኝም።
የሚሸጥ፡ ፍየል፡ አለህ?	አዎ፣ ሞልቶኛል።
አገርህ፡ ብዙ፡ ከብት፡ አላቸው?	አዎ፣ ሞልቷቸዋል።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ዓይነት፡ ከብት፡ አለ?	አዎ፣ ሞልቷል።

ጥያቄ	መልስ
በከተማው፡ አጠገብ፡ የሚታደን፡ አውሬ፡ አለ?	አዎ፣ ለሥጋ፡ የሚሆኑ፡ አውሬዎች፡ ሞልተዋል።
እናንተ፡ ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ ውስጥ፡ ትልልቅ፡ ተራራዎች፡ ይገኛሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ሲኒማ፡ ቤት፡ ማቋቋም፡ የሚፈልጉ፡ ሰዎች፡ ታውቃለህ?	ሲኒማ፡ ቤት፡ ለማቋቋም፡ የሚፈልጉ፡ ሰዎች፡ ሞልተዋል።
አስተማሪ፡ መሆን፡ የሚፈልጉ፡ ሰዎች፡ አሉ?	አዎ፣ ብዙ፡ ጎልማሶች፡ ሞልተዋል።
በዚህ፡ ወር፡ ውስጥ፡ ወደ፡ አዲስ፡ አበባ፡ የሚሄዱ፡ ሰዎች፡ አሉ?	አዎ፣ እኛ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ሞልተዋል።
ከልጆችህ፡ መካከል፡ ሕክምና፡ መማር፡ የሚፈልግ፡ ማን፡ ነው?	ትልቁ፡ ልጄ፡ ነው።
የትኛው፡ የሚሲዮን፡ ሆስፒታል፡ ሐኪሞች፡ አሉት?	አዲሱ፡ የሚሲዮን፡ ሆስፒታል፡ ሐኪሞች፡ ሞልቶታል።
ፖሊቴክ፡ የሚማሩ፡ ብዙ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ አሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
ኢትዮጵያን፡ ሄደው፡ ያዩ፡ ብዙ፡ አሜሪካዊያን፡ አሉ?	አዎ፣ በየከተማው፡ ሞልተዋል።

ድርሰት

ከኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ የሥራ፡ ፕሮግራሞች፡ ሁሉ፡ ቀዳምትነትን፡ የያዘ፡ ትምህርት፡ ነው። ሃገር፡ መሻሻል፡ አስፈላጊ፡ ከሆኑት፡ ነገሮች፡ አንዱ፡ ትምህርት፡ መሆኑን፡ በመገንዘብ፣ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ሲሶ፡ በጀቱን፡ የሚያጠፋው፡ ለትምህርት፡ ላይ፡ ነው።

ከአሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ አርባ፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ጀምሮ፡ የትምህርትና፡ ሥነ፡ ጥበብ፡ ሚኒስቴር፡ በኢትዮጵያ፡ በመላ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በየከተማው በመሥራት፣ የትምህርት፡ መሣሪያ፡ በመግዛትና፡ አስተማሪዎች፡ በመቅጠር፡ ብዙ፡ ጥረት፡ አድርጓል። ቀድሞ፡ አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ ብቻ፡ በትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ብቻ፡ ይገኙ፡ ነበር። አሁን፡ ግን፡ በትንንሽ፡ ከተማዎች፣ በመንደሮችና፡ በቀበሌዎች፡ በብዙ፡ ተስፋፍተው፡ ይገኛሉ።

በከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ረገድ፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አስደናቂ፡ እርምጃ፡ አድርጐአል። ቀድሞ፡ የነበሩት፡ ኮሌጆች፡ ከመስፋፋታቸውም፡ በላይ፡ ብዙ፡ አዳዲስ፡ ኮሌጆች፡ በየቦታው፡ ተከፍተዋል። ከልዩ፡ ልዩ፡ ኮሌጆች፡ ትምህርታቸውን፡ ጨርሰው፡ የወጡ፡ ተማሪዎች፡ በቁጥር፡ እየበዙ፡ ሄደዋል። ከዚህም፡ በላይ፡ በትምህርታቸው፡ በጣም፡ ልቀው፡ ለሚገኙት፡ ተማሪዎች፡ እስኮላርሽፕ፡ እየተሰጠ፡ ለከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ በብዛት፡ ይሄዳሉ። የኢትዮጵያ፡ ዕድገትና፡ ብልጽግና፡ የተመሠረተው፡ በተማሩት፡ ልጆችዋ፡ ላይ፡ ስለሆነ፣ ትምህርት፡ ወደፊት፡ በጣም፡ እየተስፋፋ፡ እንደሚሄድ፡ ብዙ፡ ተስፋ፡ ይደረጋል።

ጥያቄዎች

ትምህርት፡ ለምን፡ ይጠቅማል?

የኢትዮጵያ፡ ሊቦ፡ ገጃት፡ ለምን፡ ካይ፡ ይጠፋል?

ብዙ፡ ትምህርት፡ ቤቶች፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ?

ትምህርት፡ ቤቶች፡ የት፡ ይገኛሉ?

በከፍተኛ፡ ትምህርት፡ ረገድ፡ የተፈጸመውን፡ ነገር፡ አስረዳ።

ተማሪዎች፡ ትምህርታቸውን፡ ሲጨርሱ፡ ምን፡ ያደርጋሉ?

ተማሪዎች፡ ለምን፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ይሄዳሉ?

ትምህርት፡ ወደፊት፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ለምን፡ እየተስፋፋ፡ ይሄዳል?

እስኮላርሽፕ፡ የሚሰጣቸው፡ ተማሪዎች፡ ብዙ፡ ናቸው?

እስኮላርሽፕ፡ ለማግኘት፡ ምን፡ ማድረግ፡ ያስፈልጋል?

ሃምሳ፡ ሦስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ስለ፡ ኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ከብዙ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ ለማወቅ፡ እፈልግ፡ ነበር።

ፍቃድዎ፡ ቢሆን፡ ቢነግሩኝ፡ ይወዳሉ?

ከበደ

ከድሮ፡ ጀምሮ፡ ኢትዮጵያ፡ የምትገዛው፡ በንጉሥ፡ ስለሆነ፣ የመንግሥትዎ፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ የተመሠረተው፡ በንጉሥ፡ ላይ፡ ነው።

ዮሐንስ

ለምን፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሦች፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ተብለው፡ ይጠራሉ?

ከበደ

በቀድሞ፡ ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ተከፋፍላ፡ ነበር።

እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ በንጉሥ፡ ይተዳደር፡ ነበር።

ኃይለኛ፡ ንጉሦች፡ እንደ፡ አጼ፡ ቴዎድሮስና፡ እንደ፡ አጼ፡ ምኒልክ፡ ያሉ፡ ተነስተው፣ ኢትዮጵያን፡ አንድ፡ ለማድረግ፡ በጣሩበት፡ ጊዜ፡ ደካማ፡ ንጉሦችን፡ አሸንፈው፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ተብለው፡ ገዝተዋል።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
በጠባይ፡ ረገድ፡ ጥሩነሽ፡ እንዴት፡ ናት?	በጣም፡ ጥሩ፡ ናት።
ሥራው፡ በፕሮግራሙ፡ መሠረት፡ የሚሠራ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ የሚሠራ፡ ይመስለኛል።
ሥራውን፡ ያገኘው፡ በቀደምትነት፡ ነው?	የለም፣ በትምህርቱ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የቄሱን፡ ንግግር፡ በሙሉ፡ ተገነዘብኸው?	አዎ፣ ተገነዘብሁት።
የመሥሪያ፡ ቤታችሁ፡ ባጀት፡ በዓመት፡ ስንት፡ ነው?	አንድ፡ መቶ፡ ሺ፡ ብር፡ ነው።
በሚመጣው፡ ዓመት፡ ብዙ፡ ሠራተኞች፡ ትቀጥራላችሁ?	አዎ፣ ሁለት፡ መቶ፡ ሠራተኞች፡ እንቀጥራለን።
በእናንተ፡ ቀበሌ፡ ባቡር፡ ጣቢያ፡ አለ?	ያውቶቡስ፡ ጣቢያ፡ እንጂ፡ የባቡር፡ ጣቢያ፡ የለም።
አሜሪካ፡ መኪና፡ በመሥራት፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለ፡ እርምጃ፡ አድርጎአል?	አዎ፣ ከፍ፡ ያለ፡ እርምጃ፡ አድርጓል።
ያፄ፡ ቴዎድሮስ፡ ብልፅግና፡ ከአፄ፡ ምኒልክ፡ ብልፅግና፡ ይበልጥ፡ ነበር?	ማን፡ ያውቃል።
ያገርህ፡ የትምህርት፡ ዕድገት፡ አሁን፡ ከፍ፡ እያለ፡ ሄዷል?	አሁን፡ በጣም፡ ከፍ፡ ብሏል።
በትምህርት፡ እረገድ፡ ኢትዮጵያ፡ ያደረገችው፡ እርምጃ፡ በጣም፡ አስደናቂ፡ መስሎ፡ ይታይሃል?	አዎ፣ በጣም፡ አስደናቂ፡ ነው።
የእናንተ፡ ቀበሌ፡ አስተዳዳሪ፡ ስም፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ዮሐንስ፡ ይባላል።
የሳይንስ፡ ትምህርት፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለበት፡ አገር፡ ማን፡ ነው?	አሜሪካ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ልጅህ፡ ሳይንስ፡ ከመማር፡ ይፈልጋል?	የለም፣ የሳይንስ፡ ትምህርት፡ በጭራሽ፡ አያስደስተውም።
ከመሆኑ፡ ወደ፡ ሌላ፡ አገር ሄደህ፡ ያደረጋቷን፡ እርምጃ፡ ተመልክተሃል?	አዎ፣ ተመልክቻለሁ።
በምን፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ ደካማ፡ ትመስለሃለች?	በሳይንስ፡ ደካማ፡ ትመስለኛለች።
አጼ፡ ምኒልክ፡ ደካማ፡ ንጉሥ፡ ነበሩ?	የለም፣ በጣም፡ ኃይለኛ፡ ንጉሥ፡ ነበሩ።
በየወሩ፡ የደመወዝህን፡ ሩብ፡ ለማን፡ ትሰጣለህ?	ለእናቴ፡ እልክላታለሁ።
የወር፡ በጀትህን፡ በወሩ፡ መጀመሪያ፡ ማወቅ፡ ትችላለህ?	ብዙ፡ ጊዜ፡ አውቀዋለሁ።
አሽከርህን፡ በስንት፡ ቀጠርኸው?	በአሥር፡ ብር፡ ቀጠርሁት።
የተናገርከው፡ ነገር፡ መጥፎ፡ መሆኑን፡ አሁን፡ ተገነዘብኸው?	አዎ፣ ተገንዝቤዋለሁ።
ለትምህርትህ፡ የሚሆንህ፡ ገንዘብ፡ ለማግኘት፡ ቸግሮህ፡ ነበር?	አዎ፣ በጣም፡ ቸግሮ፡ ነበር።
የዚህ፡ አገር፡ የሳይንስ፡ እርምጃ፡ በጣም፡ አስደናቂ፡ አይደለም?	አዎ፣ በጣም፡ አስደናቂ፡ ነው።
በሳይንስ፡ ረገድ፡ ከዚህ፡ አገር፡ የላቀ፡ አገር፡ ያለ፡ ይመስልሃል?	እኔ፡ የማውቀው፡ ሌላ፡ አገር፡ የለም።
የአሜሪካና፡ የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አስተዳደር፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ይመስልሃል?	የለም፣ የተለያየ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ሌት፡ በሥራዎና፡ በመገደዎ፡ የምትወሬድ፡ ይመስለሃል?	ማን፡ ያውቃል።
ካንተና፡ ከጥሩነሽ፡ ማን፡ አሸነፈ?	ጥሩነሽ፡ አሸነፈች።
ዱሮ፡ ከዚህ፡ አገር፡ ኖረሃል?	የለም፡ አሁን፡ የመጀመሪያ፡ ጊዜዬ፡ ነው።
ዱሮ፡ ያየኸውን፡ አገር፡ ደግመህ፡ ማየት፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፡ ማየት፡ እፈልጋለሁ።
ዱሮ፡ አማርኛ፡ ትናገር፡ ነበር?	አዎ፡ ዱሮ፡ እናገር፡ ነበር።
ዱሮ፡ የተማርኸውን፡ ዛሬ፡ ታስታውሰዋለህ?	የለም፡ አላስታውሰውም።
የዱሮውን፡ የኢትዮጵያን፡ ከተማ፡ ታውቃለህ?	አዎ፡ አውቃለሁ።
የዱሮው፡ ስምህ፡ ማን፡ ነበር?	ከማ፡ ነበር።
ዱሮ፡ ከከተማው፡ ውስጥ፡ ሲኒማ፡ ቤቶች፡ ነበሩ?	አዎ፡ ብዙ፡ ሲኒማ፡ ቤቶች፡ ነበሩ።
ዱሮ፡ በየጊዜው፡ ሲኒማ፡ ታይ፡ ነበር?	አዎ፡ በየሳምንቱ፡ አይ፡ ነበር።
ከዚህ፡ አገር፡ ዱሮ፡ መጥተህ፡ ነበር?	አዎ፡ በልጅነቴ፡ መጥቼ፡ ነበር።
የዱሮውን፡ ገንዘብ፡ ለወጡት?	አዎ፡ አዲስ፡ ገንዘብ፡ ወጥቷል።
የዱሮው፡ ዓይነት፡ መኪና፡ አሁን፡ ይገኛል?	አዎ፡ ይገኛል።
የዱሮው፡ ቤትህ፡ የተሠራ፡ ከእንጨት፡ ነበር?	አዎ፡ ከእንጨት፡ ነበር።

ድርሰት

በአሁኑ፡ ዘመን፡ ኢትዮጵያ፡ የምትገዛው፡ በንጉሠ፡ ነገሥት፡ ሥልጣን፡ ሥር፡ ነው። አንድ፡ ሰው፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ማለት፡ ምን፡ ማለት፡ ነው፡ ብሎ፡ ቢጠይቅ፡ የሚመለስለት፡ መልስ፡ እንደሚከተለው፡ ነው።

ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ማለት፡ የንጉሦች፡ ንጉሥ፡ ማለት፡ ነው። በቀድሞ፡ ዘመን፡ ኢትዮጵያ፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ተከፋፍላ፡ ነበር። እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ ራሱን፡ የቻለ፡ አገር፡ ነበር። እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ ራሱን፡ የቻለ፡ አገር፡ ነበር። ከሌላው፡ ክፍል፡ ጋር፡ የሚያገናኘው፡ ብዙ፡ ነገር፡ አልነበረም። መንገድና፡ መገናኛ፡ ስላልነበረ፤ ከአንዱ፡ ክፍል፡ ወደ፡ ሌላው፡ ክፍል፡ መሄድ፡ በጣም፡ አስቸጋሪ፡ ነበር። በዚህ፡ ምክንያት፡ እያንዳንዱ፡ አገር፡ በራሱ፡ ንጉሥ፡ ይተዳደር፡ ነበር።

ኢትዮጵያን፡ አንድ፡ ለማድረግ፡ ብዙ፡ ስመጥሩ፡ ንጉሦች፡ ተነስተው፡ ተለያይታ፡ የነበረውን፡ አገር፡ አንድ፡ ካደረጉት፡ በኋላ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ተብለው፡ ነግሠዋል። እንደዚህ፡ ያሉት፡ ታላላቅ፡ ንጉሦች፡ ስማቸው፡ በኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ ላይ፡ ተጽፎ፡ ይገኛል።

ጥያቄዎች

በአሁኑ፡ ዘመን፡ ኢትዮጵያ፡ የምትገዛው፡ እንዴት፡ ነው?

ኢትዮጵያን፡ የሚገዛ፡ ማን፡ ነው?

ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ምን፡ ማለት፡ ነው?

በቀድሞ፡ ዘመን፡ ኢትዮጵያ፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ተከፋፍላ፡ ነበር?

እያንዳንዱን፡ ክፍል፡ ማን፡ ይገዛው፡ ነበር?

ከአንዱ፡ ክፍሉ፡ ወደ፡ ሌላው፡ ክፍሉ፡ በቀላሉ፡ መሄድ፡
ይቻል፡ ነበር?

የመንገድና፡ የመገናኛ፡ ጥቅም፡ ምንድን፡ ነው?

ኢትዮጵያን፡ አንድ፡ ያደረገ፡ ማን፡ ነው?

አገርን፡ አንድ፡ ማድረግ፡ አስቸጋሪ፡ ነው?

አሜሪካን፡ አንድ፡ ያደረገ፡ ማን፡ ነው?

ሃምሳ፡ አራተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ኢትዮጵያ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አላት?

ከበደ

እንደ፡ አውሮፓ፡ አቆጣጠር፡ በአሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ አንድ፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ኢትዮጵያ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አውጥታለች።

ይህ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ በአሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ሃምሳ፡ አምስት፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ እንደገና፡ ተስፋፍቶ፡ ወጥቷል።

ዮሐንስ

ፓርላማው፡ በስንት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላል?

ከበደ

የኢትዮጵያ፡ ፓርላማ፡ በሁለት፡ ክፍሎች፡ ይከፈላል።

የመጀመሪያው፡ ክፍል፡ የሕግ፡ መምሪያ፡ ይባላል።

የሁለተኛው፡ ክፍል፡ ደግሞ፡ የሕግ፡ መወሰኛ፡ ይባላል።

ዮሐንስ

የፓርላማ፡ ምርጫ፡ እንዴት፡ ነው?

ከበደ

ለሕግ፡ መምሪያ፡ የሚሆኑትን፡ አባሎች፡ ሕዝቡ፡ ከየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ከየአውራጃውና፡ ከየወረዳው፡ ይመርጣል።

ለሕግ፡ መወሰኛ፡ የሚሆኑትን፡ አባሎች፡ ደግሞ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በሥራቸው፡ ከታወቁት፡ መኳንንቶችና፡ ባላባቶች፡ መካከል፡ መርጠው፡ ይሾማሉ።

ዮሐንስ

አባሎቹ፡ ለስንት፡ ዓመት፡ ይመረጣሉ?

ከበደ

የሕግ፡ መምሪያ፡ አባሎች፡ ለአራት፡ ዓመት፡ ብቻ፡ ሲመረጡ፣ የሕግ፡ መወሰኛ፡ አባሎች፡ ለስድስት፡ ዓመት፡ ይሾማሉ።

ጥያቄና·መልስ

ጥያቄ	መልስ
የመገናኛ·ሚኒስትሩ·ማን·ናቸው?	አቶ·ዮሐንስ·ናቸው።
የጥሩነሽ·አጎት·ሰው·ጥሩ·ነበሩ?	አዎ፣ ሰው·ጥሩ·ነበሩ።
በኢትዮጵያ·ላይ·መንገሥ·የሚችሉ·ሰው·እንዴት·ያለ·መሆን·አለበት?	አብዛኛውን·ጊዜ·የንጉሥ·ልጅ·መሆን·አለበት።
ኢትዮጵያ·ውስጥ·ንጉሥ·ስንት·ዓመት·መንገሥ·ይችላል?	የተወሰነ·አይደለም።
ታላቁ·ወንድምህ·የሚማረው·የት·አገር·ነው?	አሜሪካ·ውስጥ·ነው።
ከመጽሐፉ·ሥር·የነበረውን·ጋዜጣ·ማን·ወሰደው?	እኔ·ወስጄ·ለአልማዝ·ሰጠሁዋት።
አቶ·ለማ·የሚሠራው·ከማን·ሥር·ነው?	ከንግድ·ሚኒስትሩ·ሥር·ነው።
የኢትዮጵያ·ፓርላማ·የሚገኘው·በየትኛው·ከተማ·ውስጥ·ነው?	በአዲስ·አበባ·ከተማ·ውስጥ·ነው።
ስለ·አገርህ·ሕገ·መንግሥት·የት·ተማርክ?	ትምህርት·ቤት·ውስጥ·ነው።
በሕግ·መወሰኛ·ክፍሉ·ውስጥ·ሠርተህ·ታውቃለህ?	የለም፣ ሠርቼ·አላውቅም።
የፓርላማው·አባሎች·አሁን·ይመጣሉ?	የለም፣ አይመጡም።

ጥያቄ	መልስ
ወንድምህ፡ የሕግ፡ መወሰኛ፡ አባል፡ ናቸው?	አዎ፡ ናቸው።
የትኛው፡ ወረዳ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ የሚያስፈልገው፡ ይመስልሃል?	ወረዳዎቹ፡ ሁሉ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ያስፈልጋቸዋል።
ካገሩ፡ ባላገሮች፡ አንዱ፡ አገረ፡ ገዢ፡ እንዲሆን፡ ተሾመ?	አዎ፡ አንዱን፡ ሾሙት።
የክለብ፡ ቤት፡ ያስተማሪዎች፡ መገናኛ፡ ነው?	አዎ፡ ያስተማሪዎች፡ ሁሉ፡ መገናኛ፡ ነው።
እናንተ፡ አውራጃ፡ ውስጥ፡ ያለው፡ ትልቁ፡ ወንዝ፡ ማን፡ ይባላል?	ዓባይ፡ ይባላል።
ከሁላችሁ፡ ትልቁ፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ከበደ፡ ነው።
የወረዳውን፡ ባላገር፡ አየኸው?	የለም፡ አላየሁትም።
ተማሪዎች፡ መምሪያና፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ መሄድ፡ እንችላለን?	አዎ፡ አንድ፡ አሥር፡ ተማሪዎች፡ መምሪያና፡ መሄድ፡ ትችላላችሁ።
ከማ፡ ለአንተ፡ ሥራ፡ መሥራት፡ ይፈልጋል?	የለም፡ አይፈልግም።
አሜሪካዊያን፡ የፓርላሜንት፡ ምርጫ፡ የሚያደርጉት፡ መቼ፡ ነው?	ከአንድ፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ነው።
የወረዳው፡ ገዢ፡ የተማረው፡ የት፡ አገር፡ ነው?	እንግሊዝ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ነው።
የፓርላማው፡ አባሎች፡ በዓመት፡ ውስጥ፡ የዕረፍት፡ ጊዜ፡ አላቸው?	በበጋ፡ ወር፡ ውስጥ፡ ያርፋሉ።

ድርሰት

አዲስዋ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደ፡ አውሮፓ፡ አቆጣጠር፡ በአሥራ፡ ዘጠኝ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ አንድ፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ የመጀመሪያውን፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አወጣች። ይህ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ እንደገና፡ ተሻሽሎ፡ ከሃያ፡ አራት፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ወጣ። አዲሱ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ የመንግሥቱን፡ ጠቅላላ፡ ሥራና፡ የፓርላማውን፡ ሥልጣን፡ አስፋፍቶ፡ ይገልጻል።

እንደ፡ ሌሎቹ፡ አገሮች፡ ሁሉ፡ የኢትዮጵያ፡ ፓርላማ፡ ወይም፡ ምክር፡ ቤት፡ ሁለት፡ ክፍሎች፡ አሉት። የመጀመሪያው፡ ክፍል፡ የሕግ፡ መምሪያ፡ ሊሆን፤ ሁለተኛው፡ ደግሞ፡ የሕግ፡ መወሰኛ፡ ነው። የሕግ፡ መምሪያ፡ አባሎች፡ የሚመረጡት፡ በሕዝብ፡ ድምፅ፡ ብቻ፡ ነው። ከየወረዳው፡ ከየአውራጃውና፡ ከየጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ሕዝብ፡ የመረጣቸው፡ ሰዎች፡ ለሕግ፡ መምሪያ፡ ክፍል፡ አባሎች፡ ይሆናሉ። ለሕግ፡ መወሰኛው፡ ክፍል፡ የሚመረጡት፡ አባሎች፡ በሕዝቡ፡ አይደሉም። ብዙ፡ ጊዜ፡ በመንግሥት፡ ሥራ፡ ላይ፡ ሆነው፡ አገራቸውን፡ በማገልገል፡ በሥራቸው፡ ከታወቁት፡ ሰዎች፡ መካከል፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ መርጠው፡ አባል፡ እንዲሆኑ፡ ይሾማቸዋል።

ለፓርላማው፡ የሚመረጡት፡ አባሎች፡ ሕግ፡ በማውጣትና፡ የሕዝቡን፡ ጥቅም፡ በመደገፍ፡ ሥራቸውን፡ ያከናውናሉ። አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ ሕግ፡ የሚመነጨው፡ ከፓርላማው፡ ሳይሆን፡ ከሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ነው። ሆኖም፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ከሕግ፡ መምሪያው፡ ክፍል፡ ሕግ፡ ሊመነጭ፡ ይችላል። የሕግ፡ መምሪያው፡ አባሎች፡ የሚመረጡት፡ ለአራት፡ ዓመት፡ ሊሆን፤ የሕግ፡ መወሰኛው፡ አባሎች፡ ግን፡ ለስድስት፡ ዓመት፡ ነው።

ጥያቄዎች

የመጀመሪያው፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ በስንት፡ ዓመተ፡ ምህረት፡ ወጣ?

አዲሱ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ መቼ፡ ወጣ?

አዲሱ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ ዋና፡ ዓላማው፡ ምንድን፡ ነው?

የኢትዮጵያ፡ ፓርላማ፡ ስንት፡ ክፍሎች፡ አሉት?

በማቸው፡ ማን፡ ማን፡ ይገኛሉ?

የሕግ፡ መምሪያ፡ አባሎች፡ የሚመረጡት፡ እንዴት፡ ነው?

የሕግ፡ መወሰኛ፡ አባሎች፡ እንዴት፡ ይመረጣሉ?

የሕግ፡ መምሪያ፡ አባሎች፡ ለስንት፡ ዓመት፡ ይመረጣሉ?

የፓርላማው፡ አባሎች፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ ሕግ፡ ከየት፡ ይመነጫል?

ሃምሳ፡ አምስተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

የኢትዮጵያ፡ ሕግ፡ አወጣጥ፡ እንዴት፡ ነው?

ከበደ

መጀመሪያ፡ ሕግ፡ የሚመነጨው፡ ከሕግ፡ መምሪያው፡ ክፍል፡ ነው። የሕግ፡ መምሪያው፡ ክፍል፡ የወሰነው፡ ሕግ፡ ወደ፡ ሕግ፡ መወሰኛው፡ ክፍል፡ ይሄድና፡ እንደገና፡ እንዲነጋገሩበትና፡ ውሳኔ፡ እንዲሰጡ፡ ይደረጋል። የመጨረሻው፡ ውሳኔ፡ ከንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በቀረበ፡ ጊዜ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ውሳኔውን፡ ያጸናዋል፡ወይም፡ ይሽረዋል።

ዮሐንስ

ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ሥልጣን፡ ስላላቸው፣ ማናቸውንም፡ መኳንንትና፡ መሳፍንት፡ የሚመርጡ፡ ራሱ፡ ነው?

ከበደ

የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ሚኒስትሮችንና፡ ታላላቅ፡ ባለሥልጣኖችን፡ ሁሉ፡ ለመምረጥ፡ ሥልጣን፡ አላቸው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ምክር፡ ስትፈልግ፡ የት፡ ትሄዳለህ?	ወደ፡ ሽማግሌ፡ እሄዳለሁ።
ጠቅላይ፡ ግዛቶች፡ መላክተኞቻቸውን፡ በየስንት፡ ዓመቱ፡ ይመርጣሉ?	በየአራት፡ ዓመት፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
በድምፅ፡ ብልጫ፡ የተመረጡት፡ ሰዎች፡ ለስንት፡ ዓመት፡ ያገለግላሉ?	አራት፡ ዓመት፡ ነው።
በተቻለህ፡ መጠን፡ አባትና፡ እናትህን፡ መደገፍ፡ ትወዳለህ?	አዎ፣ በጣም፡ ደስ፡ ይለኛል።
በሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ሠርተህ፡ ታውቃለህ?	የለም፣ ሠርቼ፡ አላውቅም።
ጃንሆይ፡ ካሜሪካ፡ ሲመለሱ፡ መኳንንቱና፡ መሳፍንቱ፡ ተቀበሏቸው?	አዎ፣ በሙሉ፡ መጥተው፡ ተቀበሉዋቸው።
የፍርዱን፡ ውሳኔ፡ ለመስማት፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ትሄዳለህ?	አዎ፣ እሄዳለሁ።
የቤቱን፡ ዋጋ፡ አንቺ፡ መወሰን፡ ትችያለሽ?	የለም፣ አልችልም።
እመዝጊያው፡ ላይ፡ የተንጠለጠለው፡ ኮት፡ የማን፡ ነው?	የወንድሜ፡ ነው።
የዓባይ፡ ወንዝ፡ ድልድይ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው?	አዎ፣ ትልቅ፡ ነው።
ከድልድዩ፡ ላይ፡ የወደቀው፡ ሰው፡ የት፡ ይኖር፡ ነበር?	አዲስ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ነበር።
በጫካው፡ መካከል፡ ወንዝ፡ አለ?	አዎ፣ ሁለት፡ ትላልቅ፡ ወንዞች፡ አሉ።
ወታደሮች፡ ኳስ፡ መቼ፡ ይጫወታሉ?	ቅዳሜ፡ ከሰዓት፡ በኋላ፡ ይጫወታሉ።
ጫካ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ይቃጠላል?	አዎ፣ ብዙ፡ ጊዜ፡ ይቃጠላል።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ሥራሽ፡ ስትሄጂ፡ ሕፃኑን፡ ማን፡ ይጠብቀዋል?	አያቴ፡ ትጠብቀዋለች።
በቤታችሁ፡ ዙሪያ፡ አጥር፡ አለ?	አጥር፡ የለም።
ካንተ፡ አጠገብ፡ ተቀምጦ፡ የነበረው፡ ሰው፡ ማን፡ ነበር?	በውነቱ፡ አላውቀውም።
ከፎቁ፡ ላይ፡ መታጠቢያ፡ ቤት፡ አለ?	አዎ፡ ሁለት፡ መታጠቢያ፡ ቤቶች፡ አሉ።
ከወንዙ፡ በላይ፡ ያለው፡ እርሻ፡ የማን፡ ነው?	ያጐቴ፡ ነው።
እሳጥኑ፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ ልብስ፡ ወሰደኸው?	የለም፡ አልወሰድሁትም።
ከቤተ፡ መንግሥቱ፡ ግርጌ፡ ኳስ፡ ሜዳ፡ አለ?	አዎ፡ አለ።
ካልጋው፡ በታች፡ ምን፡ አለ?	ምንም፡ የለም።
ከመኪናው፡ ውስጥ፡ ወጥቶ፡ የት፡ ሄደ?	ምግብ፡ ቤት፡ ገባ።
ከቤቱ፡ ውጭ፡ ሄደው፡ ሊጫወቱ፡ ይችላሉ?	አዎ፡ ይችላሉ።
እስክትመጡ፡ ድረስ፡ ልጠብቃችሁ?	አዎ፡ ጠብቀን።
ቤቱን፡ ከቦታው፡ ጋር፡ ገዛኸው?	አዎ፡ ገዛሁት።
እናትህ፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ መኪና፡ ልውሰደው?	አዎ፡ ውሰደው።
ጥዋት፡ እኛ፡ ጋ፡ ትመጣላችሁ?	አዎ፡ በጥዋት፡ እመጣለሁ።
ካልጋው፡ ግርጌና፡ ራስጌ፡ ምን፡ አለ?	ምንም፡ የለም።

ጥያቄ	መልስ
እበሩ፡ ፊት፡ ለፊት፡ ያሉትን፡ ወንበሮች፡ አነሳሃቸው?	እዎ፣ አነሳሁዋቸው።
ካንተ፡ ፊት፡ ተቀምጣ፡ መጽሐፍ፡ ያነበበች፡ ማን፡ ናት?	ወይዘሮ፡ አስማዝ፡ ናት።
ከሰዓት፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሲኒማ፡ ቤት፡ መሄድ፡ ትፈልጋላችሁ?	የለም፣ አንፈልግም።
ከለማ፡ በፊት፡ ማን፡ መጥቶ፡ ነበር?	ማንም፡ አልመጣም።
በአንተና፡ በለማ፡ መካከል፡ ምን፡ ነገር፡ አለ?	ምንም፡ ነገር፡ የለም።
ከባንኩ፡ ጐን፡ ያለውን፡ ቤት፡ ማን፡ ገዛው?	ወይዘሮ፡ ጥሩነሽ፡ ገዛቸው።
በቤተ፡ ክርስቲያኑ፡ ዙሪያ፡ ያሉት፡ ቤቶች፡ ሁሉ፡ የመንግሥት፡ ናቸው?	የለም፣ ያቶ፡ ተሰማ፡ ናቸው።
በስምምነታችን፡ መሠረት፡ ገንዘቡን፡ ትሰጠኛለህ?	እዎ፣ እሰጥሃለሁ።
ወንድምህን፡ ባየኸው፡ ጊዜ፡ ምን፡ ነገርኸው?	ምንም፡ አልነገርሁትም።
በወንዙ፡ ዳር፡ ዛፎች፡ ተከላችሁ?	እዎ፣ ተከልን።

ድርሰት

የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ የጥንቱንና፡ የአሁኑን፡ የአስተዳደር፡ ሁናቴ፡ ይዞ፡ ይገኛል። ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ታላቅ፡ ሥልጣን፡ ስላላቸው፡ ማናቸውንም፡ የአስተዳደር፡ ክፍል፡ ሊያዝ፡ ይችላሉ። የውጭ፡ አገር፡ ጉዳይ፡ አመራርን፡ የሚከታተሉና፡ የሚወስኑ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ነው። ያገሪቱን፡ የመከላከያ፡ ኃይል፡ በጠቅላላ፡ የሚያዝና፡ እንደዚሁም፡ ታላላቅ፡ የመንግሥት፡ ባለሥልጣኖችን፡ የሚሾምና፡ የሚሽር፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ነው።

ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩና፡ ሌሎች፡ ሚኒስትሮች፡ በአንድነት፡ የሚኒስትሮች፡ የምክር፡ ቤት፡ አባሎች፡ ናቸው። ማናቸውም፡ ያገር፡ አስተዳደር፡ ሕግጋት፡ የሚወጣው፡ የሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ አባሎች፡ ተማክረው፡ በወሰኑት፡ ውሳኔ፡ ነው። የሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ሊቀ፡ መንበር፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ነው። በአሁኑ፡ ጊዜ፡ የመንግሥቱ፡ ሥልጣን፡ ከፓርላማው፡ ይልቅ፡ ወደ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱና፡ ወደ፡ ሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ያዘነብላል።

ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አስተዳደር፡ እንዴት፡ ነው?

የንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ሥልጣን፡ እስከምን፡ ድረስ፡ ነው?

የአገሪቱን፡ የመከላከያ፡ ኃይል፡ የሚያዝ፡ ማን፡ ነው?

ስለ፡ ውጭ፡ ጉዳይና፡ ስለ፡ አገር፡ ውስጥ፡ ጉዳይ፡ የሚወስን፡ ማን፡ ነው?

ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ሊቀመጡ፡ ይችላሉ?

በሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ ውስጥ፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱ፡
ሥልጣን፡ ምንድን፡ ነው?

በንጉሠ፡ ነገሥቱና፡ በሚኒስትሮች፡ መካከል፡ ያለውን፡
ግንኙነት፡ አስረዳ።

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሚኒስትሮች፡ አሉ?

ከሁሉም፡ ሚኒስትሮች፡ በሥልጣን፡ የሚበልጥ፡ የትኛው፡
ነው?

ስለ፡ አሜሪካ፡ መንግሥት፡ በሰፊው፡ ግለጽ።

ሃምሳ፡ስድስተኛ፡ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

የሚኒስትሮች፡ ሥልጣን፡ ከጀሬት፡ እንደሆነ፡ ሊያስረዱኝ፡ ይችላሉ?

ገብሬ

እያንዳንዱ፡ ሚኒስትር፡ በተሰጠው፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ የሚሠራውን፡ ሥራ፡ በሙሉ፡ ይመራል።

ከዚህም፡ በላይ፡ ለሚኒስትሮች፡ ምክር፡ቤት፡ አባል፡ ስለሆነ፣ ከተ ሊንገገው፡ ሐዳና፡ ከተሰጠው፡ ውጭ፡ ሁሉ፡ ኃላፊ፡ ነው።

ከበታቹ፡ ያሉትን፡ ሠራተኞች፡ ለመሾምና፡ ለመሻር፣ እንደዚሁም፡ ሥልጣናቸውን፡ ለመወሰንና፡ ለማስፋት፡ ችሎታ፡ አለው።

ዮሐንስ

ዋና፡ ዋና፡ ሚኒስቴሮችን፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?

ገብሬ

ዋና፡ ዋና፡ ሚኒስቴሮች፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፤ ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፤ የፍርድ፡ ሚኒስቴር፤ የገንዘብ፡ ሚኒስቴር፤ የጽሕፈት፡ ሚኒስቴር፤ የመከላከያ፡ ሚኒስቴር፤ የሥራ፡ ሚኒስቴር፤ የንግድና፡ የኢንዱስትሪ፡ ሚኒስቴር፤ የጦሬታ፡ ሚኒስቴር፤ የማዕድንና፡ የመገናኛ፡ ሚኒስቴር፤ የፖስታ፡ የቴሌግራፍና፡ የቴሌፎን፡ ሚኒስቴር፤ የእርሻ፡ ሚኒስቴር፤ የሕዝብ፡ ጤና፡ ጥበቃ፡ ሚኒስቴርና፡ የትምህርትና፡ ሥነ፡ ጥበብ፡ ሚኒስቴር፡ ናቸው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
አዲስ፡ አበባ፡ በነበሩበት፡ ጊዜ፡ ያገሩን፡ ሁኔታ፡ ወደዱት?	አዎ፣ ወድጄው፡ ነበር።
የእንግሊዝና፡ የኢትዮጵያ፡ የመንግሥት፡ አመራር፡ ይመሳሰላል?	በጣም፡ አይመሳሰሉም።
የመከላከያ፡ ሚኒስትሩን፡ ታውቃቸዋለህ?	የለም፣ አላውቃቸውም።
ባገርህ፡ ውስጥ፡ ሚኒስትሮቹን፡ የሚሾምና፡ የሚሽር፡ ማን፡ ነው?	ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነው።
ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ እዚህ፡ አገር፡ መጥተው፡ ነበር?	የለም፣ አላየሁዋቸውም።
የአሜሪካን፡ ሕዝብ፡ የመንግሥቱን፡ አስተዳደር፡ ወዶታል?	አዎ፣ በጣም፡ ወዶታል።
ምን፡ ዓይነት፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ መጣህ?	መሐንዲስነት፡ ለመማር፡ መጣሁ።
ትምህርትህን፡ የምትፈጽመው፡ መቼ፡ ነው?	ከአምስት፡ ዓመት፡ በኋላ፡ ነው።
ሊቀ፡ መንበሩ፡ ስንት፡ ዓመታቸው፡ ነው?	አንድ፡ ሃምሳ፡ ዓመት፡ ይኖራቸዋል።
ተማሪው፡ ከመሐንዲስነት፡ ይልቅ፡ የፖሊቲካ፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ ያዘነበለ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ ይመስለኛል።

ጥያቄ	መልስ
የትምህርት፡ ቤቶች፡ ሕግ፡ የኢንገገው፡ ማን፡ ነው?	የትምህርት፡ ሚኒስቴር፡ ነው።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፡ ኃላፊ፡ ማን፡ ናቸው?	የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትሩ፡ ናቸው።
የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ ደህና፡ ሰው፡ ናቸው?	አዎ፣ በጣም፡ ደግ፡ ናቸው።
የሚኒስትሩ፡ የትምህርት፡ ችሎታ፡ ምንድን፡ ነው?	እኔ፡ አላውቅም።
የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ ከፍተኛ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ አለው?	አዎ፣ አለው።
የገንዘብ፡ ሚኒስትሩ፡ እንደወጡ፡ ወደ፡ ቤትህ፡ ትሄዳለህ?	የለም፣ እዚሁ፡ እመጣለሁ።
የመከላከያ፡ ሚኒስቴር፡ ያለበትን፡ ቦታ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ አውቃለሁ።
እጦሬታ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ ሠርተህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ሠርቼአለሁ።
የሕዝብ፡ ጤና፡ ጥበቃ፡ ሚኒስቴር፡ ብዙ፡ ተማሪዎች፡ ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ልኳል?	አዎ፣ ልኳል።
የገንዘብ፡ ሚኒስቴር፡ ሠራተኞች፡ ከፍ፡ ያለ፡ ገንዘብ፡ ያገኛሉ?	አዎ፣ ያገኛሉ።

ጥያቄ	መልስ
እዚሁ፡ የትምህርትና፡ የሥነ፡ ጥበብ፡ ሚኒስቴር፡ የት፡ ነው?	ከዩኒቨርሲቲው፡ በስተጀርባ፡ ነው።
የፖስታ፡ የቴሌግራፍና፡ የቴሌፎን፡ ሚኒስቴር፡ እዚሁ፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ተሠርቶለታል?	የለም፤ አልተሠራለትም።

ድርሰት

በአሁኑ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከአሥራ፡ አራት፡ በላይ፡ የሚሆኑ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ሚኒስቴሮች፡ ይገኛሉ። ከነዚህ፡ ሚኒስቴሮች፡ ዋና፡ ዋናዎቹ፡ የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስቴር፤ የገንዘብ፡ ሚኒስቴር፤ ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፤ የርሻ፡ ሚኒስቴር፤ የሥራ፡ ሚኒስቴር፤ የንግድ፡ ሚኒስቴር፤ የትምህርትና፡ የሥነ፡ ጥበብ፡ ሚኒስቴርና፡ ሌሎችም፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉት፡ ናቸው።

እያንዳንዱ፡ ሚኒስቴር፡ በሚኒስትር፡ ይመራል። ሚኒስትሩ፡ ለተሾመው፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ ከሚሠራው፡ ከማንኛቸውም፡ ነገር፡ ኀላፊ፡ ነው። በሕግ፡ በተሰጠው፡ ሥልጣን፡ መሠረት፡ ከበታቹ፡ ያሉትን፡ ሹማምንቶች፣ የሚሾምና፡ የሚሽር፡ እሱ፡ ነው። ከዚህም፡ በላይ፡ ሠራተኞቻቸውን፡ ከማሰናበትና፡ ከመሾም፡ ሙሉ፡ ችሎታ፡ አለው።

ሚኒስትሩ፡ ከሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ አባል፡ በመሆኑ፤ በሱ፡ ሥልጣን፡ ሥር፡ ከሚተዳደረው፡ ሚኒስቴር፡ ለጠቅላላ፡ ተጠያቂ፡ ነው። በየጊዜው፡ ከሚፈጸመው፡ ሥራ፡ ዋና፡ ዲሬክተሩ፡ ኀላፊ፡ ነው።

ጥያቄዎች

በአሁኑ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ሚኒስቴሮች፡ ይገኛሉ?

ከሦስቱ፡ ዋና፡ ዋና፡ ሚኒስቴሮች፡ እነማን፡ ናቸው?

የንግድ፡ ሚኒስቴር፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ከያንዳንዱ፡ ሚኒስቴር፡ የሚወሉ፡ ማን፡ ነው?

የሚኒስትሩ፡ ሥልጣን፡ ምንድን፡ ነው?

የሚኒስትሩን፡ ሥራ፡ ዘርዝር.

ለሚኒስትሩ፡ የመሾምና፡ የመሻር፡ ሥልጣን፡ ማን፡ ሰጠው?

ሚኒስትሮች፡ ሁሉ፡ ከሚኒስትሮች፡ ምክር፡ ቤት፡ አባል፡ መሆን፡
አለባቸው?

የዋና፡ ዲሬክተሩ፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

እርስዎ፡ አሁን፡ በየትኛው፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ ይሠራሉ?

ሃምሳ፡ ሰባተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

በተባበረው፡ አሜሪካ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ እንደሚወቀው፡ እያንዳንዱ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ይከፈላል?

ይህ፡ ሁናቴ፡ በኢትዮጵያ፡ ሚኒስቴሮች፡ ውስጥ፡ ይገኛል?

ከበደ

አዎ፤ ሚኒስቴሮች፡ ሁሉ፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ተከፍለዋል።

እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ በዲሬክተር፡ ስለሚካሄድ፤ በክፍሉ፡ ለሚሠራው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ኃላፊው፡ ዲሬክተሩ፡ ነው።

ሆኖም፡ ማናቸውም፡ ዲሬክተር፡ ለሚኒስትሩ፡ ወይም፡ ለምክትል፡ ሚኒስትሩ፡ ታዛዥ፡ ነው።

ሚኒስትሮቹና፡ ምክትል፡ ሚኒስትሮች፡ ደግሞ፡ በተራቸው፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ታዛዦች፡ ናቸው።

ዮሐንስ

ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ የኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ገዢ፡ በመሆኑ፤ ዳኞችን፡ የሚመርጥና፡ የሚሾም፡ እሱ፡ ይመስለኛል።

ከበደ

እርግጥ፡ ነው። ከፍተኛ፡ የፍርድ፡ ቤት፡ ዳኞችን፡ የሚሾም፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ነው።

ዳሩ፡ ግን፡ ዳኞችን፡ መርጦ፡ ለሹመት፡ የሚያቀርበው፡ የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ ነው።

የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ ዳኞችን፡ መርጦ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ካቀረበ፡ በኋላ፡ በዚያው፡ መሠረት፡ ሹመት፡ ለዳኞች፡ ይሰጣል።

ጥያቄና፡መልስ

ጥያቄ	መልስ
የሥራ፡ሚኒስቴር፡ብዙ፡ሠራተኞች፡አለው?	አዎ፤ ከአንድ፡ሺ፡በላይ፡ጎይሆኑ፡አይቀሩም።
ኢትዮጵያ፡ውስጥ፡የንግድ፡ሥራ፡ጥሩ፡ይመስልሃል?	አዎ፤ ጥሩ፡ነው።
የንግድና፡የኢንዱስትሪ፡ሚኒስትሩ፡ማን፡ናቸው?	አላውቃቸውም።
የአናንተ፡መሥሪያ፡ቤት፡አላፊ፡ማን፡ነው?	አቶ፡ተሰማ፡ነው።
የትምህርት፡ሚኒስቴር፡ሹሞች፡በጣም፡ደግ፡ሰዎች፡ናቸው?	አዎ፤ በጣም፡ደግ፡ሰዎች፡ናቸው።
ባምስት፡መቶ፡ብር፡ስንት፡ጊዜ፡መተዳደር፡ትችላላችሁ?	ሁለት፡ወር፡ያህል፡መተዳደር፡እንችላለን።
በዓለም፡ውስጥ፡በውጭ፡አገር፡∧መንግሥት፡የሚተዳደሩ፡ብዙ፡አገሮች፡አሉ?	አዎ፤ ብዙ፡ናቸው።
የኢትዮጵያ፡መልክተኞች፡ሆነው፡የሚሄዱት፡እነማን፡ናቸው?	ስማቸውን፡አላውቅም።
የትምህርትና፡ሥነ፡ጥበብ፡ሚኒስቴር፡የሚከያሄደው፡በምክትል፡ሚኒስቴር፡ነው?	አዎን፡በምክትል፡ሚኒስትር፡ነው።
ከማ፡ኃገትና፡ለአናቶ፡ታዛዥ፡ነው?	አዎ፤ ታዛዥ፡ነው።
ከዚህ፡አገር፡የሚሄዱትን፡ሹሞች፡ሁሉ፡ትገናኛቸዋለህ?	አዎ፤ አገናኛቸዋለሁ።

ጥያቄ	መልስ
በአገሩ፡ውስጥ፡ የንግድ፡ ሥራ፡ እየተስፋፋ፡ የሚሄድ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ እየተስፋፋ፡ ሄዶአል።
ተማሪዎቹን፡ ከመጐብኘት፡ የሚመጡት፡ ምክትል፡ ሚኒስትር፡ ማን፡ ናቸው?	አቶ፡ ዮሐንስ፡ ናቸው።
አቶ፡ ለማ፡ ተራ፡ ሠራተኛ፡ ነው?	የለም፣ የመሥሪያ፡ ቤቱ፡ ሹም፡ ነው።
የሚመጡት፡ ዳኞች፡ ስንት፡ ናቸው?	አሥር፡ ይሆናሉ።
ሹመት፡ የሚፈልጉት፡ ሰዎች፡ ብዙ፡ ናቸው?	በጣም፡ ብዙ፡ አይደሉም።
ስንት፡ ተራ፡ ወታደሮች፡ አይተሃል?	አምስት፡ ተራ፡ ወታደሮች፡ አይቻለሁ።
ዳኞቹ፡ ከፍርድ፡ቤቱ፡ ውስጥ፡ ናቸው?	አይደሉም።
ስለ፡ ሕግ፡ ተምረህ፡ ዳኛ፡ መሆን፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ እፈልጋለሁ።
ምክትሉ፡ የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ አባትህ፡ ናቸው?	አዎ፣ አባቴ፡ ናቸው።
ተራ፡ ሠራተኞች፡ ለሹሞች፡ ታዛዥ፡ ናቸው?	አዎ፣ ቅን፡ ታዛዦች፡ ናቸው።
ሕዝቡ፡ በሕጉ፡ መሠረት፡ መተዳደር፡ ይፈልጋል?	አዎ፣ ከሕግ፡ ውጭ፡ የሚሠሩትን፡ ሰዎች፡ አይወዱም።
ሹመት፡ የሚፈልግ፡ ሰው፡ የት፡ መሥራት፡ ያስፈልገዋል?	ከመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ መሥራት፡ ያለበት፡ ይመስለኛል።

ጥያቄ	መልስ
አንተ፡ የመንግሥት፡ ሹም፡ ነህ?	አይደለሁም።
ዳኞች፡ ከነገሩ፡ ውሳኔ፡ ሰጡት?	የለም፤ ገና፡ ናቸው።
በሥራ፡ ሚኒስቴር፡ ውስጥ፡ ከሚሠሩት፡ ሰዎች፡ መካከል፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ የሚሄዱት፡ ስንት፡ ናቸው?	አምስት፡ ሰዎች፡ ይሄዳሉ።
የወሎ፡ መኳንንት፡ ለምን፡ መጡ?	ጃንሆይን፡ ለማየት፡ ነው።
ሠራተኞቹ፡ አሁን፡ ተገብረዋል?	የለም፤ አልተገበሩም።
ለሕዝቡ፡ መካከተኛ፡ የሚሆኑት፡ ሰዎች፡ የሚመረጡት፡ ከተራው፡ ሕዝብ፡ ነው?	አዎ፤ ከሁሉም፡ ነው።

ድርሰት

እንደ፡ ማናቸውም፡ አገሮች፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤቶች፡ ሁሉ፡ በልዩ፡ ልዩ፡ ክፍሎች፡ ይከፈላሉ። ከያንዳንዱ፡ ክፍል፡ ኃላፊ፡ ሆኖ፡ ተገቢው፡ ሥራ፡ እንዲፈጸም፡ የሚያደርገው፡ የክፍል፡ ሹሙ፡ ነው። በጠቅላላው፡ የመሥሪያ፡ ቤቱን፡ የሥራ፡ አፈጻጸም፡ የሚቆጣጠርና፡ የሚወስን፡ ሚኒስትሩ፡ በመሆኑ፤ የክፍል፡ ሹሙ፡ መጀመሪያ፡ ከበላይ፡ ላሉት፡ ሹማምንቶች፤ በመጨረሻውም፡ ለሚኒስትሩ፡ ታዛዥ፡ ነው።

አነስተኛ፡ የሆኑትን፡ ዳኞች፡ ለመሾምና፡ ለመሻር፡ ሥልጣን፡ የተሰጠው፡ የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ ነው። ከፍተኛ፡ ዳኞችን፡ ግን፡ ለመሾምና፡ ለመሻርም፡ ሥልጣን፡ ያለው፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ብቻ፡ ነው።

በመጀመሪያ፡ የፍርድ፡ ሚኒስትሩ፡ ተገቢዎቹን፡ ሰዎች፡ ከመረጠ፡ በኋላ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ያቀርባል። በፍርድ፡ ሚኒስትር፡ ሥልጣን፡ የተመረጡትን፡ ሰዎች፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ይሾማል።

የዳኝነት፡ ሥራ፡ በጣም፡ አስቸጋሪ፡ በመሆኑ፣ ምርጫው፡ በጥንቃቄ፡ መሠራት፡ አለበት።

ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ፡ መሥሪያ፡ ቤቶች፡ በብዙ፡ ክፍሎች፡ ተከፋለዋል?

እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ ኃላፊ፡ አለው?

የክፍሉ፡ ኃላፊ፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

የክፍሉ፡ ሹም፡ ከማን፡ ታዛዥ፡ ነው?

የመሥሪያ፡ ቤቱን፡ ጠቅላላ፡ የሥራ፡ አፈጻጸም፡
የሚቆጣጠር፡ ማን፡ ነው?

አነስተኛ፡ ዳኞችን፡ የሚሾመው፡ ማን፡ ነው?

ከፍተኛ፡ ዳኞችን፡ ለመሾምና፡ ለመሻርም፡
የሚችል፡ ማን፡ ነው?

የዳኞች፡ አመራረጥ፡ እንዴት፡ ነው?

የዳኝነት፡ ሥራ፡ አስቸጋሪ፡ ነው?

በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ ከፍተኛ፡ ዳኞች፡ እንዴት፡
እንደሚመረጡ፡ አስረዳ።

ሃምሳ፡ ስምንተኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ፍርድ፡ ቤት፡ አለ?

ከበደ

ከሁሉም፡ ከፍተኛ፡ የሆነው፡ ፍርድ፡ ቤት፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ጠቅላይ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ይባላል።

ከበታቹ፡ ብዙ፡ ከፍተኛ፡ ፍርድ፡ ቤቶች፡ አሉ።

በየአውራጃው፣ በየወረዳውና፡ በየቀበሌው፣ የአውራጃ፡ ፍርድ፡ ቤቶች፣ የወረዳ፡ ፍርድ፡ ቤቶችና፡ የቀበሌ፡ ፍርድ፡ ቤቶች፡ የሚባሉ፡ ይገኛሉ።

ከፍተኛው፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ከበታቹ፡ ያሉትን፡ የፍርድ፡ ቤቶች፡ ፍርድ፡ ሊሽርና፡ ሊዳመሰስ፡ ይችላል።

ዮሐንስ

የኢትዮጵያ፡ ሕግ፡ የተመሠረተው፡ በምን፡ ላይ፡ ነው?

ከበደ

አዲሱ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕግ፡ የተመሠረተው፡ በፈረንሳይና፡ በጀርመን፡ የሕግ፡ መሰመር፡ ላይ፡ ነው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
የይለፍ፡ ወረቀትዎን፡ ለማግኘት፡ ተገዘውን፡ ነገር፡ ፈጽመዋል?	አዎ፣ ከአንድ፡ ወር፡ በፊት፡ ፈጽሜ፡ ነበር።
የሠራውን፡ አፈጻጸም፡ አየኸው?	ብዙ፡ ሥራ፡ ስለነበረኝ፡ አላየሁትም።

ጥያቄ	መልስ
በጥንቃቄ፡ እንዲነግሩ፡ ነገርኸው?	አዎ፣ ነገርሁት።
እስረኞችን፡ የሚቆጣጠር፡ ማን፡ ነው?	ከፖሊስ፡ ሠራዊት፡ የመጣ፡ ሰው፡ ነው።
የወህኒ፡ ቤቱን፡ አለቃ፡ የሚሾመው፡ ማን፡ ነው?	ያገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡ ነው።
የፍርድ፡ ሚኒስቴር፡ ሠራተኞች፡ ደሞዝ፡ ከሌሎች፡ ሠራተኞች፡ አነስተኛ፡ ይመስልሃል?	የለም፣ አነስተኛ፡ አይመስለኝም።
የከፍተኛውን፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ዳኛ፡ የሚሾምና፡ የሚሽር፡ ማን፡ ነው?	ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነው።
ዳኝነቱ፡ ትክክለኛ፡ ነበር?	አዎ፣ ትክክለኛ፡ ዳኝነት፡ ነበር።
የዳኝነት፡ ሥራ፡ ሠርተሃል?	የለም፣ አልሠራሁም።
አንድ፡ ሰው፡ ለሕግ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ገብቶ፡ ሕግ፡ ሳይማር፡ ጠበቃ፡ ለመሆን፡ ይችላል?	አዎ፣ በልምድ፡ ባገኘው፡ ዕውቀቱ፡ ጠበቃ፡ መሆን፡ ይችላል።
ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ዳኞች፡ ሁሉ፡ በሕግ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ውስጥ፡ የተማሩ፡ ናቸው?	የለም፣ አብዛኛዎቹ፡ በልማድ፡ ብቻ፡ ያገኙት፡ ዕውቀት፡ ነው።
አዲስ፡ አበባ፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ እስር፡ ቤቶች፡ አሉ?	በውነቱ፡ ስንት፡ እስር፡ ቤቶች፡ እንዳሉ፡ አላውቅም።

ጥያቄ	መልስ
ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ሄዶ፡ ማመልከት፡ ተገቢ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ በጣም፡ ተገቢ፡ ነው።
የመሥሪያ፡ ቤቱ፡ ኃላፊ፡ ሠራተኞቹን፡ በደንብ፡ ይቆጣጠራቸዋል?	አዎ፣ ይቆጣጠራቸዋል።
የሰጠህ፡ ዳኛው፡ አነስተኛ፡ ነበር?	አዎ፣ አነስተኛ፡ ነበር።
የዳኝነት፡ ሥራ፡ በጣም፡ ያስደስትሃል?	አዎ፣ ያስደስተኛል።
የተደሰትኸው፡ ለምንድን፡ ነው?	ጠበቃውን፡ ስለማውቀው፡ ነው።
የንግዱን፡ ሥራ፡ የሚቆጣጠርልህ፡ ሰው፡ አለ?	አዎን፣ ወንድሜ፡ ይቆጣጠርልኛል።
ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ሄደህ፡ የጃንሆይን፡ ፍርድ፡ ሰምተህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሰምቻለሁ።
የጠበቆችን፡ ክርክር፡ ሰምተህ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ሰምቻለሁ።
ብዙ፡ የጦር፡ ሠራዊት፡ አገርህ፡ ውስጥ፡ አለ?	አዎ፣ ብዙ፡ የጦር፡ ሠራዊት፡ አገሬ፡ ውስጥ፡ ይገኛል።

ድርሰት

ምንም፡ እንኳን፡ ኢትዮጵያ፡ የምትገዛው፡ በንጉሥ፡ ቢሆን፤ መንግሥቷ፡ በሦስት፡ ዋና፡ ክፍሎች፡ ተከፍሏል። እያንዳንዱ፡ ክፍል፡ የተወሰነ፡ ሥራ፡ አለው። ፓርላማው፡ ሕግ፡ ያወጣል። ያስተዳደር፡ ክፍል፡ የወጣውን፡ ሕግ፡ እንዲከበር፡ ያደርጋል። በፍርድ፡ ረገድ፡ ያለውን፡ ማናቸውንም፡ ሥራ፡ የፍርድ፡ ሚኒስቴርና፡ ፍርድ፡ ቤቶች፡ ይሠራሉ።

ኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስቴር፡ አላት። ዳሩ፡ ግን፡ የጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ሥራ፡ በጣም፡ የተወሰነ፡ ነው። የጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ዋና፡ ሥራ፡ በየአንዳንዱ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ መፋለስ፡ እንዳይኖርና፡ የአስተዳደሩም፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ በደንብ፡ እንዲካሄድ፡ የሚያደርግ፡ ነው። ከዚህም፡ በላይ፡ በፓርላማውና፡ በንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ መካከል፡ የሚደረገውን፡ ግንኙነት፡ የሚያስማማ፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ነው። በሁለት፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ፡ ቤቶች፡ መካከል፡ መፋለስ፡ የተፈጠረ፡ እንደሆን፤ ሁለቱን፡ መሥሪያ፡ ቤቶች፡ የሚዳኝ፤ የሚቀጣና፡ የሚያስማማ፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ነው። ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በቀጥታ፡ ታዛዥ፡ ነው።

ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ ስንት፡ ክፍሎች፡ አሉት?

የያንዳንዱ፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ፓርላማው፡ ምን፡ ዓይነት፡ ሥራ፡ አለው?

የፍርድ፡ ሚኒስትር፡ ዋና፡ ሥራ፡ ምንድን፡ ነው?

ኢትዮጵያ፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስትር፡ አላት?

የጠቅላይ፡ ሚኒስትሩ፡ ሥልጣን፡ ምንድን፡ ነው?

የአስተዳደር፡ ደንብ፡ የሚያወጣ፡ ማን፡ ነው?

ጠቅላይ፡ ሚኒስትሩን፡ የሚሾም፡ ማን፡ ነው?

ጠቅላይ፡ ሚኒስትር፡ በአሜሪካ፡ መንግሥት፡ ውስጥ፡ አለ?

ከፕሬዚዳንትና፡ ከጠቅላይ፡ ሚኒስትር፡ ማን፡ ይበልጣል?

ሃምሳ፡ ዘጠነኛ፡ ትምህርት

ንግግር

ዮሐንስ

በአሁኑ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚደረገው፡ የጋብቻ፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ ከጥንቱ፡ ጋር፡ ይመሳሰላል?

ከበደ

እንደ፡ ቦታው፡ ነው። በትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ውስጥ፡ የሚደረገው፡ የጋብቻ፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ ከጥንቱ፡ ልማድ፡ ራቅ፡ ይላል።

በባላገር፡ ውስጥ፡ ግን፡ የሚደረገው፡ የጋብቻ፡ አፈጻጸም፡ ወደ፡ ጥንቱ፡ ልማድ፡ ይጠጋል።

ዮሐንስ

ስለ፡ ጋብቻ፡ በሰፊው፡ ሊያስረዱኝ፡ ይችላሉ?

ከበደ

የኢትዮጵያ፡ የጋብቻ፡ ልማድ፡ ብዙ፡ ሐተታ፡ አለበት።

ነገር፡ ግን፡ ዋና፡ ዋናውን፡ ነገር፡ ልገልጽልዎት፡ እችላለሁ።

መጀመሪያ፡ የጋብቻው፡ ቀን፡ በተጫጩት፡ ልጆችና፡ በወላጆቻቸው፡ መካከል፡ ከተወሰነ፡ በኋላ፣ ለሠርጉ፡ የሚያስፈልገውን፡ ድግስ፡ ያዘጋጃሉ።

ዮሐንስ

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሠርግ፡ ድግስ፡ ብዙ፡ ሥራ፡ ይጠይቃል?

ከበደ

በጣም፡ እንጂ፣ ሠርግ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ አድካሚ፡ ሥራ፡ ነው።

ሦስት፡ ወይም፡ አራት፡ ወር፡ ቀደም፡ ብሎ፡ የልጆቹ፡ ወላጆች፡ ድግስ፡ መደገስ፡ ይጀምራሉ።

አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ የሠርግ፡ ድግስ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ስለሆነ፣ የዘመድንና፡ የወዳጅን፡ እርዳታ፡ ይጠይቃል።

ዮሐንስ

በሠርግ፡ ቀን፡ ብዙ፡ ሰው፡ ይመጣል?

ከበደ

በኢትዮጵያ፡ ለሚደረግ፡ ሠርግ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ክብር፡ ስለአለው፣ የሩቅና፡ የቅርብ፡ ዘመዶች፣ ያገር፡ ሽማግሌዎችና፡ አሮጊቶች፡ እንዲሁም፡ እንዳንድ፡ የከተማ፡ ነዋሪዎች፡ ይጠራሉ።

እንዲያውም፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ያልተያዩ፡ ዘመዶች፡ የሚገናኙት፡ በሠርግ፡ ቀን፡ ነው።

ዮሐንስ

ከሠርጉ፡ የመጡት፡ እንግዶች፡ የት፡ ይጋበዛሉ?

ከበደ

በትልቅ፡ አዳራሽ፡ ውስጥ፡ ሆነው፡ ይጋበዛሉ።

ዮሐንስ

በዚያ፡ ቀን፡ ብዙ፡ ዘፈንና፡ ጭፈራ፡ አለ?

ከበደ

ሴቶችና፡ ወንዶች፡ ጥሩ፡ ጥሩ፡ ልብሳቸውን፡ ለብሰው፣ ከበሮአቸውን፡ እየመቱ፡ ሲዘፍኑና፡ ሲጨፍሩ፡ ይውላሉ።

ዮሐንስ

ለሙሽሪዎቹ፡ ስጦታ፡ መስጠት፡ የተለመደ፡ ነው?

ከበደ

አዎን፣ በጣም፡ የተለመደ፡ ነው።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ሚስት፡ ማግባት፡ የምትፈልግ፡ ከከተማ፡ ነው፡ ወይስ፡ ከባላገር?	ከባላገር፡ ማግባት፡ እፈልጋለሁ።
ጋብቻ፡ ጥሩ፡ ነገር፡ አይመስልህም?	አዎን፣ ጋብቻ፡ በጣም፡ ጥሩ፡ ነገር፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የወንድምህ፡ ሠርግ፡ መቼ፡ ነው?	አሁን፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ ይሆናል።
ድግሱን፡ የሚደግሰው፡ ማን፡ ነው?	አባትና፡ እናቱ፡ ናቸው።
ያገራችሁን፡ ክብር፡ ከፍ፡ ለማድረግ፡ ምን፡ ሠራችሁ?	የተቻለንን፡ ሁሉ፡ ሞከርን።
የቅርብ፡ ዘመድ፡ አለህ?	አዎን፣ የቅርብ፡ ዘመዶች፡ አሉኝ።
የጋብቻው፡ ሁናቴ፡ እንዴት፡ ነበር?	በጣም፡ አስደሳች፡ ነበር።
ከማና፡ ጥሩነሽ፡ በተጫጩ፡ በስንተኛው፡ ወር፡ ተጋቡ?	ባመታቸው፡ ተጋቡ።
ሠርጉን፡ ለማየት፡ ትሄዳለህ?	አዎ፣ ጊዜ፡ ባገኝ፡ እሄዳለሁ።
አገካገር፡ ውስጥ፡ ስንት፡ ዓመት፡ ኖረሃል?	ሦስት፡ ዓመት፡ ብቻ፡ ነው።
ስንት፡ የሚሆኑ፡ ዘመዶች፡ አሉህ?	ሁለት፡ ብቻ፡ ናቸው።
አዳራሹ፡ ውስጥ፡ ያሉት፡ ሰዎች፡ እነማን፡ ናቸው?	እናቱ፡ ዮሐንስ፡ ናቸው።
ያማርኛ፡ ዘፈን፡ መዝፈን፡ ትችላለህ?	አዎ፣ እችላለሁ።
ከበሮውን፡ የሚመታው፡ ማን፡ ነው?	የኔ፡ ገለበት፡ ናት።
ከበሮ፡ መምታት፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ከእናንተ፡ መካከል፡ መዝፈን፡ የሚፈልግ፡ ማን፡ ነው?	እማ፡ ነው።
ለሙሽራውና፡ ለሙሽራዋ፡ ምን፡ ሰጠሃቸው?	ገና፡ ምንም፡ አልሰጠሁዋቸውም።
አማርኛ፡ መማር፡ አድካሚ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ አድካሚ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የወንድምህ፡ ጋብቻ፡ እንዴት፡ ነበር?	በጣም፡ ጥሩ፡ ነበር።
ነገሩ፡ የተፋለሰ፡ ይመስልሃል?	አዎ፣ በጣም፡ የተፋለሰ፡ ይመስለኛል።
ድግስ፡ መደገስ፡ አድካሚ፡ ነው?	አዎ፣ በጣም፡ አድካሚ፡ ነው።
መፈጠርክን፡ ትወደዋለህ?	አዎ፣ እወደዋለሁ።
ነገ፡ ወደ፡ ገጠር፡ መሄድ፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ እፈልጋለሁ።
አቶ፡ ዮሐንስን፡ ስንት፡ ብር፡ መቅጣት፡ ያስፈልጋል?	ሃምሳ፡ ብር፡ መቅጣት፡ ያስፈልጋል።
የይለፍ፡ ወረቀትህን፡ ለማን፡ ሰጠኸው?	ለፖሊሱ፡ ሰጠሁት።
እስረኞችን፡ አየሃቸው?	አዎ፣ አየሁዋቸው።
ብዙ፡ ሰዎች፡ እስር፡ ቤት፡ ገቡ?	የለም፣ አልገቡም።
አዲስ፡ ወህኒ፡ ቤት፡ ተሠራ?	አዎ፣ ተሠራ።
አቶ፡ ከበደንና፡ አቶ፡ ለማን፡ አስማማሃቸው?	አዎ፣ አስማማሁዋቸው።
እናቶ፡ ለማን፡ ማን፡ ዳኛቸው?	ፖሊሱ፡ ዳኛቸው።
ከሁለታችሁ፡ ማን፡ ተቀጣ?	አቶ፡ ተሰማ፡ ተቀጣ።
የጠየቃችሁትን፡ የይለፍ፡ ወረቀት፡ አገኛችሁ?	አዎ፣ አገኘን።
እስረኞቹ፡ ተለቀቁ?	አዎ፣ ተለቀቁ።
ስንት፡ ጠበቃዎች፡ ገዛህ?	ሁለት፡ ጠበቆች፡ ገዛሁ።
የጥያቄውን፡ መልስ፡ ታውቀዋለህ?	የለም፣ አላውቀውም።

ጥያቄ	መልስ
ጠበቃው፡ ስለነገሩ፡ በጣም፡ ያውቃል?	አዎ፤ ያውቃል።
አንድ፡ ሰው፡ በልምድ፡ ባገኘው፡ እውቀቱ፡ ጠበቃ፡ ለመሆን፡ ይችላል?	አዎ፤ ይችላል።
አዲሱ፡ እስር፡ ቤት፡ የተሠራ፡ የት፡ ነው?	ከከተማው፡ በጣም፡ ራቅ፡ ብሎ፡ ነው።
እስረኞቹን፡ ለመጠየቅ፡ ወደ፡ እስር፡ ቤት፡ እንሄድም?	እሺ፤ እንሄድ።
እፍርድ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ የነበረው፡ ክርክር፡ ምን፡ ነበር?	ምን፡ እንደነበር፡ አላውቅም።
ከፍርድ፡ ቤቱ፡ የተገኘው፡ መልስ፡ ትክክለኛ፡ ነው?	አዎ፤ ትክክለኛ፡ ነው።

ድርሰት

ሠርግ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ ከፍ፡ ያለ፡ በዓል፡ በመሆኑ፤ ትልቅ፡ ድርጅት፡ ይጠይቃል። የሠርጉ፡ ድግስ፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ የሠርጉ፡ ቀን፡ ይወሰናል። ሠርጉ፡ የሚደገሰው፡ አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ በልጅትዋና፡ በልጁ፡ ወላጆች፡ ቤት፡ ነው። በሆቴል፡ ውስጥ፡ ሠርግ፡ መደገስ፡ በኢትዮጵያ፡ የተለመደ፡ ነገር፡ አይደለም።

ከሠርጉ፡ ቀን፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሦስት፡ ወር፡ ቀደም፡ ብሎ፡ የቅርብና፡

የሩቅ፡ ዘመዶች፡ ሁሉ፡ ስለ፡ ጋብቻውና፡ ስለ፡ ሠርጉ፡ ስለሚነገሩቸው፣ የሚችሉትን፡ እርዳታ፡ ለማድረግ፡ ይሞክራሉ። ሠርግ፡ ሁልጊዜ፡ አድካሚና፡ ብዙ፡ ዝግጅትን፡ የሚጠይቅ፡ በመሆኑ፣ የዘመድ፡ እርዳታ፡ በጣም፡ ተፈላጊ፡ ነው።

በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ የሚደረገው፡ ሠርግ፡ ከቦታ፡ ቦታ፡ ይለያያል። በትልልቅ፡ ከተማዎች፡ ውስጥ፡ የሚደረገው፡ ሠርግ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ አይደለም። ምክንያቱም፡ የከተማ፡ ኑሮ፡ በጣም፡ ውድ፡ ስለሆነና፡ ብዙ፡ ወጪ፡ ስለሚጠይቅ፡ ትልቅ፡ ድግስ፡ ለመደገስ፡ አስቸጋሪ፡ ነው። በገጠር፡ ውስጥ፡ የሚደረገው፡ ድግስ፡ ግን፡ አብዛኛውን፡ ጊዜ፡ በጣም፡ ትልቅ፡ ነው። በተለይ፡ ሃብታም፡ የሆኑ፡ ወላጆች፡ ለልጆቻቸው፡ የሚያደርጉት፡ ድግስ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ነው።

በገጠር፡ ውስጥ፡ የሚፈጸመው፡ ጋብቻ፡ ከጥንቱ፡ ልማድ፡ ጋር፡ የተመሳሰለ፡ ስለሆነ፣ የጋብቻው፡ ሥነ፡ ሥርዓትና፡ ድግስ፡ ለተመልካች፡ በጣም፡ አስደሳች፡ ነው።

ጥያቄዎች

ሠርግ፡ ማለት፡ ምን፡ ማለት፡ ነው?

ሠርግ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ድግስ፡ ነው?

ሠርግ፡ የሚደገሰው፡ የት፡ ነው?

በሆቴል፡ ውስጥ፡ ሠርግ፡ መደገስ፡ የተለመደ፡ ነው?

ከሠርጉ፡ ቀን፡ በፊት፡ የሚሆነውን፡ ነገር፡ አስረዳ።

ሠርግ፡ ለምን፡ ብዙ፡ ዝግጅት፡ ይጠይቃል?

ሠርግ፡ ለመደገስ፡ የዘመድ፡ እርዳታ፡ ያስፈልጋል?

በገጠር፡ ሠርግና፡ በከተማ፡ ሠርግ፡ መካከል፡ ያለውን፡
ልዩነት፡ አስረዳ።

ሃብታም፡ ወንዶች፡ ከልጆቻቸው፡ የሚያደርጉት፡ የሠርግ፡
ድግስ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ነው?

በኢትዮጵያና፡ በአሜሪካ፡ ውስጥ፡ የሚደረገውን፡
የጋብቻ፡ ልዩነት፡ ግለጽ።

ስልሳኛ፡ ትምህርት

ንግግር

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የአሜሪካን፡ ቆንሲል፡ ሆኖ፡ አስመራ፡ ውስጥ፡ እንደደረሰ፡ አገረ፡ ገዢውን፡ ለመገናኘት፡ ወደ፡ አገር፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ሄደ።

ዮሐንስ

ይህ፡ ያገር፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ነው?

ጉዳይ፡ አስፈጻሚ

አዎ፣ ይህ፡ ያገር፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ነው።

ምን፡ ላድርግልዎ፡ ጌታዬ?

ዮሐንስ

ስሜ፡ ዮሐንስ፡ ይባላል። በአስመራ፡ ውስጥ፡ በቆንሲልነት፡ ሥራ፡ እንዳገለግል፡ ከአሜሪካን፡ መንግሥት፡ የተላክሁ፡ ነኝ።

ከአገረ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ ስለምፈልግ፣ ምን፡ ማድረግ፡ እንደሚገባኝ፡ ሊነግሩኝ፡ ይችላሉ?

ጉዳይ፡ አስፈጻሚ

ክቡርነታቸውን፡ ጠይቄ፡ እስካስታውቅዎ፡ ድረስ፡ ፈቃድዎ፡ ቢሆን፡ እዚህ፡ ገብተው፡ ሊቆዩ፡ ይችላሉ?

ዮሐንስ

አመሰግናለሁ።

ጉዳይ፡ አስፈጻሚ

አገረ፡ ገዢው፡ መምጣትዎን፡ በመስማት፡ በጣም፡ ተደስተዋል። ነገ፡ በአራት፡ ሰዓት፡ መጥተው፡ እንዲያነጋግሩዋቸው፡ ቀጠሮ፡ ሰጥተዎታል።

ክፍል፡ ፷

በማግስቱ

አገረ፡ ገዢ

እንደምን፡ ዋሉ፡ አቶ፡ ዮሐንስ፣ ትናንት፡ መምጣትዎን፡ ስሰማ፡ በጣም፡ ተደሰትሁ። አገሩ፡ ተስማማዎት?

ዮሐንስ

እንደምን፡ አሉ። ክቡርነትዎን፡ በመገናኘቴ፡ በጣም፡ ደስ፡ ብሎኛል።

አገረ፡ ገዢ

እባክዎ፡ ይቀመጡ። ኢትዮጵያ፡ ከደረሱ፡ ስንት፡ ቀን፡ ሆነዎ?

ዮሐንስ

ኢትዮጵያ፡ ከደረስሁ፡ ሁለት፡ ሳምንት፡ ያህል፡ ሆኖኛል።
ዳሩ፡ ግን፡ በአሜሪካን፡ ኤምባሲ፡ ውስጥ፡ ጥቂት፡ የማከናውናቸው፡ ጉዳዮች፡ ስለነበሩኝ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ከረምሁ።

አገረ፡ ገዢ

አስመራ፡ ከተማ፡ መቼ፡ ደረሱ?

ዮሐንስ

አስመራ፡ ትናንት፡ በመኪና፡ ደረስሁ።

አገረ፡ ገዢ

በመንገድዎ፡ ላይ፡ የሚገኙትን፡ ከተማዎች፡ ለመጎብኘት፡ ጊዜ፡ አገኙ?

ዮሐንስ

አመጣጤ፡ በችኮላ፡ ስለነበር፣ ለመጎብኘት፡ የፈለግሁዋቸውን፡ ከተማዎች፡ ለማየት፡ ጊዜ፡ አላገኘሁም።

አገረ፡ ገዢ

ምናልባት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ይቆዩ፡ እንደሆነ፣ ወደፊት፡ ጊዜ፡ ሲያገኙ፡ ለመ[illegible]ብኘት፡ ይችላሉ።

ዮሐንስ

ታሪካዊ፡ የሆኑ፡ አያሌ፡ ከተማዎች፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ መገኘታቸውን፡ በመጽሐፍ፡ ውስጥ፡ አንብቤያለሁ።

አሁን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ ከመምጣት፡ ዕድል፡ በማግኘቴ፡ አንዳንዶቹን፡ ከተማዎች፡ ለመጎብኘት፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ።

አገረ፡ ገዢ

ከጊዜው፡ የሚያስፈልግዎትን፡ ቤትና፡ የቤት፡ ዕቃዎች፡ ለማግኘት፡ ቻሉ?

ዮሐንስ

ስላሳሰቡልኝ፡ በጣም፡ አመሰግናለሁ። የሚያስፈልጉኝን፡ ነገሮች፡ ሁሉ፡ ለማግኘት፡ ችያለሁ።

አገረ፡ ገዢ

ምናልባት፡ ወደፊት፡ ልንረዳዎ፡ የምንችለው፡ ነገር፡ እንዳለ፣ እንዲያስታውቁን፡ እንወዳለን።

ዮሐንስ

ስለ፡ ደግነትዎ፡ በጣም፡ አመሰግንዎታለሁ። የሚገጥመኝን፡ ችግር፡ ሁሉ፡ አስታውቅዎታለሁ።

ጥያቄና፡ መልስ

ጥያቄ	መልስ
ከአሜሪካ፡ ወደ፡ አስመራ፡ የተላከውን፡ ቆንሲል፡ ስም፡ ታውቃለህ?	የለም፣ አላውቅም።
ቆንሲሉ፡ ከመጣ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ ወደ፡ አገራቸው፡ ተመልሰው፡ ያውቃሉ?	የለም፣ ተመልሰው፡ አያውቁም።
አገረ፡ ገዢውን፡ ለግብዣ፡ [illegible] ጠርተዋቸው፡ ነበር?	የለም፣ አልጠሩዋቸውም።

ጥያቄ	መልስ
ክረምቱን፡ የምትከርመው፡ የት፡ ነው?	አዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ሳይሆን፡ አይቀርም።
እዚህ፡ ከመምጣታችሁ፡ በፊት፡ የት፡ ከረማችሁ?	እፈረንሳይ፡ አገር፡ ከርመን፡ መጣን።
እዚህ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ አያሌ፡ ሰዎች፡ ታውቂያለሽ?	ጥቂት፡ ሰዎች፡ ብቻ፡ አውቃለሁ።
ጃንሆይ፡ አገረ፡ መንገዳቸውን፡ ትምህርት፡ ቤታችሁን፡ ጐበኙላችሁ?	አዎ፡ ጐብኝተውልናል።
ዛሬ፡ አገረ፡ መንገዳችሁን፡ ወደ፡ ጥሩነሽ፡ ቤት፡ ሄዳችሁ፡ ልትጠይቋት፡ ትችላላችሁ?	አዎ፡ እንችላለን።
የዲፕሎማቲክ፡ ሥራ፡ የሚሠራ፡ ዘመድ፡ አለህ?	አዎ፡ አለኝ።
ወደ፡ አሜሪካ፡ ከመሄድ፡ ዕድል፡ ገጥሞህ፡ ያውቃል?	አዎ፡ ለሁለት፡ ወር፡ ሄጄ፡ ነበር።
የሚመጡት፡ አገረ፡ ገዢ፡ ከዚህ፡ በፊት፡ የትኛውን፡ አገር፡ ይገዙ፡ ነበር?	የአሩሲ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ ገዢ፡ ነበሩ።
የተማሪዎች፡ ጠባይ፡ አስተማሪውን፡ ስላሳስደሰተው፡ ሕጉን፡ የሚያጠነክረው፡ ይመስለሃል?	ምናልባት፡ ያጠነክረው፡ ይሆናል።

ጥያቄ	መልስ
አስተማሪ፡ ከመሆን፡ የጋለ፡ መንፈስ፡ አለው?	የለውም።
አሜሪካ፡ ውስጥ፡ ታሪካዊ፡ ሥራ፡ የሠሩ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይገኛሉ?	አዎ፣ ሞልተዋል።
የመጽሐፍ፡ ቤቱ፡ ኃላፊ፡ በደግነታቸው፡ የታወቁ፡ እንደነበሩ፡ ታውቃለህ?	አዎ፣ ደግነታቸውን፡ አውቃለሁ።
ወታደሮች፡ ጦርነት፡ መግጠማቸውን፡ የት፡ ሰማህ?	ከባልንጀራዬ፡ ደብዳቤ፡ ደረሰኝ።
ጉዳዩን፡ እንድንነግራቸው፡ ትፈልጋለህ?	አዎ፣ በግልጽ፡ ንገሩዋቸው።
ወደ፡ ውጭ፡ አገር፡ ከመሄድ፡ ዕድል፡ ቢገኝልህ፡ የት፡ መሄድ፡ ትፈልጋለህ?	ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ መሄድ፡ እፈልጋለሁ።
አቶ፡ ከማ፡ ካንተ፡ ዘመድህ፡ ነው?	አዎ፣ ዘመዴ፡ ነው።
የዲፕሎማቲክ፡ ሥራ፡ ያስደስተሃል?	በጣም፡ እያደሌከም።
እጃንሆይ፡ ግቢ፡ ጉዳይ፡ አስፈጻሚውን፡ ታውቀዋለህ?	የለም፣ አላውቀውም።
የጠቅላይ፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ጉዳይ፡ አስፈጻሚ፡ አለው?	አዎ፣ አቶ፡ ከማ፡ ጉዳይ፡ አስፈጻሚ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
ተማሪዎች፡ ክረምቱን፡ የትኛው፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከረሙ?	ምኒልክ፡ ትምህርት፡ ቤት፡ ከረሙ።
መዝጊያውን፡ የገጠመው፡ ማን፡ ነው?	ሠራተኛው፡ ነው።
ከገሊ፡ መንገድህን፡ ትጠይቃናለህ?	አዎ፡ ምናልባት፡ አጠይቃችሁ፡ ይሆናል።
ወደቤታቸው፡ ሲሄዱ፡ ከገሊ፡ መንገዳቸውን፡ አንተ፡ ዘንድ፡ መጥተው፡ ነበር?	አዎ፡ መጥተው፡ ጠየቁኝ።
ቪዛዬን፡ ከአሜሪካን፡ ቆንስል፡ አመጣህልኝ?	የለም፡ ገና፡ አልሄድኩም።
በግልጽ፡ መኪና፡ ሆኖ፡ ከተማውን፡ ይዞር፡ የነበረው፡ ማን፡ ነበር?	ማን፡ እንደነበር፡ አላውቅም።
አቶ፡ ተሰማ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ግልጽ፡ ይመስልሃል?	የለም፡ በጣም፡ ግልጽ፡ አይመስለኝም።
የተባበሩት፡ መንግሥታት፡ ድርጅት፡ ዋና፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ የት፡ ነው?	ኒው፡ ዮርክ፡ ውስጥ፡ ነው።
የሠራውን፡ ድርጅት፡ በጣም፡ ወደኸዋል?	አዎ፡ በጣም፡ ወድጄዋለሁ።
ከሥራው፡ ተመልካች፡ ሆነው፡ ነበር?	አዎ፡ ነበርሁ፡ አሁንም፡ ነኝ።
ከዚህ፡ ጉዳይ፡ ተመልካች፡ ማን፡ ነው?	አቶ፡ ተሰማ፡ ነው።

ጥያቄ	መልስ
የእናንተ፡ ድርጅት፡ ዓላማው፡ ምንድን፡ ነው?	ለድሆች፡ ልጆች፡ ትምህርት፡ ቤት፡ መሥራት፡ ነው።
መኪናህን፡ አሠራህ?	አዎ፣ ትናንት፡ አሠራሁዋት።
ጃንሆይ፡ አዲስ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ አሠሩ?	ሁለት፡ አዳዲስ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ አሠሩ።
ትምህርቱን፡ በጨረሰ፡ በሳምንቱ፡ ሥራ፡ አገኘ?	አዎን፡ ጥሩ፡ ሥራ፡ አገኘ።
ለማና፡ ከበደ፡ ዋሽንግተን፡ በመጡ፡ በሦስት፡ ወራቸው፡ ተማሪዎች፡ ሆኑ?	የለም፣ አልሆኑም።
የጥሩነሽ፡ ልጅ፡ ባገባች፡ በሁለት፡ ዓመትዋ፡ ወደ፡ ፈረንሳይ፡ አገር፡ ሄደች?	አዎ፣ ለትምህርት፡ ሄደች።
አሜሪካ፡ በገባህ፡ በወርህ፡ ምን፡ አደረግህ?	ትልቅ፡ የታሪክ፡ መጽሐፍ፡ አነበብሁ።
አልማዝና፡ ከበደ፡ በተጋቡ፡ በሳምንታቸው፡ የት፡ ሄዱ?	ወደ፡ አውሮፓ፡ ሄዱ።
ትምህርት፡ ቤት፡ በገባችሁ፡ በሁለት፡ ሳምንታችሁ፡ ስለ፡ ትምህርት፡ ቤቱ፡ ማወቅ፡ ትችላላችሁ?	የለም፣ አንችልም።

ጥያቄ	መልስ
ገንዘቡ፡ በመጣ፡ በወሩ፡ ደሞዝ፡ ተሰጠ?	የለም፣ አልተሰጠም።
ብርቱካንን፡ በተከልህ፡ በወርህ፡ የት፡ ሄደህ፡ ነበር?	ወደ፡ ከተማ፡ ሄጄ፡ ነበር።
የውጭ፡ ጉዳይ፡ ሚኒስትር፡ በሆነ፡ በሦስት፡ ዓመቱ፡ የት፡ ሄዶ፡ ነበር?	ወደ፡ ፈረንሳይ፡ አገር፡ ሄዶ፡ ነበር።
በሄዳችሁ፡ ባመታችሁ፡ ካሜሪካ፡ ተመለሳችሁ?	አዎ፣ ባመታችን፡ ተመለስን።
በመጣችሁ፡ በማግሥቱ፡ የት፡ ሄዳችሁ?	ሲኒማ፡ ቤት፡ ሄደን፡ ነበር።
በተጋቡ፡ በወራቸው፡ ምን፡ አደረጉ?	ምንም፡ አላደረጉም።
ባየኸው፡ በወሩ፡ ሞተ?	አዎን፣ ባየሁት፡ በወሩ፡ ሞተ።
ጥሩነሽ፡ በታጨች፡ በአምስተኛው፡ ዓመት፡ ባል፡ አገባች?	አዎ፣ አገባች።
አባትሽ፡ በመጡ፡ ባመታቸው፡ አስተማሪ፡ ሆኑ?	አዎ፣ አስተማሪ፡ ሆኑ።
በተያያችሁ፡ በሦስተኛው፡ ወር፡ መኪና፡ ገዛችሁ?	አዎ፣ ገዛን።
ባገባህ፡ ባመትህ፡ ቤት፡ ሠራህ?	አዎ፣ ሠራሁ።
ስለ፡ አውሮፓ፡ በተናገርሁ፡ ባመቱ፡ ወደ፡ አውሮፓ፡ ሄድህ?	የለም፣ አልሄድሁም።

ድርሰት

በአሜሪካና፡ በኢትዮጵያ፡ መካከል፡ የንግድና፡ የኢኮኖሚ፡ ግንኙነት፡ ስለአለ፣ የአሜሪካን፡ መንግሥት፡ በአስመራ፡ ውስጥ፡ አንድ፡ ቆንሲል፡ አቋሞአል።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ የተባሉ፡ አሜሪካዊ፡ በአስመራ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ቆንሲል፡ ሆነው፡ እንዲሠሩ፡ ከመንግሥታቸው፡ ተልከው፣ አስመራ፡ ከተማ፡ ደረሱ።

አስመራ፡ ከመድረሳቸው፡ በፊት፡ አግረ፡ መንገዳቸውን፡ አዲስ፡ አበባ፡ ሰንብተው፡ ስለነበር፣ በአዲስ፡ አበባ፡ ዓየር፡ ሁናቴ፡ እጅግ፡ ተደሰቱ።

በአስመራና፡ በአዲስ፡ አበባ፡ የዓየር፡ ሁናቴ፡ መካከል፡ በጣም፡ ልዩነት፡ ስለሌለ፣ የአስመራ፡ የዓየር፡ ሁናቴ፡ ለጤናቸው፡ እንደሚስማማ፡ በግልጽ፡ ተረዱ።

አቶ፡ ዮሐንስ፡ በኢትዮጵያና፡ በአሜሪካ፡ መካከል፡ ያለውን፡ የንግድ፡ ግንኙነት፡ ለማጠንከርና፡ ለማስፋፋት፡ የጋለ፡ መንፈስ፡ ስለነበራቸው፣ ወዲያው፡ እንደደረሱ፡ ካገሩ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ለመገናኘት፡ ፈለጉ።

በመጀመሪያው፡ ቀን፡ ያገር፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤትን፡ ጠይቀው፡ ካገኙ፡ በኋላ፡ ከጉዳይ፡ አስፈጻሚው፡ ጋር፡ ተነጋግረው፣ ከሱም፡ አገሩ፡ ገዢውን፡ ለመገናኘት፡ እንደሚችሉ፡ ቀጠሮ፡ ተቀብለው፡ ተመለሱ።

በሁለተኛው፡ ቀን፡ በቀጠሮው፡ መሠረት፡ ወደ፡ አገር፡ ግዛት፡ መሥሪያ፡ ቤት፡ ሄደው፡ ካገሩ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ተገናኙ።

ካገሩ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ስለንግዱና፡ ስለችግሮቻቸው፡ ከተማዎቹ፡ በሰፊው፡ ተጨዋወቱ። ከዚያም፡ በኋላ፡ ምናልባት፡ አቶ፡ ዮሐንስ፡ ነገሩ፡ እንግዳ፡ በመሆናቸው፡ እርዳታ፡ ሳያስፈልጋቸው፡ አይቀርም፡ በማለት፣ ሙሉ፡ እርዳታ፡ እንዲደረግላቸው፡ ጠየቋቸው። አቶ፡ ዮሐንስም፡

በቀረበላቸው፡ እርዳታ፡ በጣም፡ ስለተደሰቱ፣ አገሬ፡ ገዢውን፡ አመስግነው፣ ወደ፡ ቤታቸው፡ ተመለሱ።

ጥያቄዎች

በአስመራ፡ ከተማ፡ ውስጥ፡ ምን፡ አለ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ ከምን፡ ወደ፡ አስመራ፡ መጡ?

አስመራ፡ ከመግባታቸው፡ በፊት፡ የት፡ ደርሰው፡ ነበር?

አዲስ፡ አበባ፡ የዓየር፡ ሁናቴ፡ እንዴት፡ ነው?

በኢትዮጵያና፡ በአሜሪካ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ልዩነት፡ አለ?

አቶ፡ ዮሐንስ፡ አስመራ፡ ሲገቡ፡ ምን፡ አደረጉ?

ካገሬ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ከመገናኘታቸው፡ በፊት፡ ምን፡ አደረጉ?

ካገሬ፡ ገዢው፡ ጋር፡ ምን፡ ተጨዋወቱ?

አገሬ፡ ገዢው፡ ምን፡ ዓይነት፡ እርዳታ፡ አቀረቡላቸው?

በሁለቱ፡ አገሮች፡ መካከል፡ ያለውን፡ የዲፕሎማቲክ፡ ግንኙነት፡ አስረዳ።

GLOSSARY

a

abal	አባል	member
abarra - mabarat	አባራ - ማባራት	to stop raining
abbabba	አባባ	daddy, papa
abbat	አባት	father
abbay	አባይ	Blue Nile
abbede - mabed	አበደ - ማበድ	to be insane, to get crazy
abbelašše - mabbelašet	አበላሸ - ማበላሸት	to waste, to spoil, to destroy
abbere - mabber	አበረ - ማበር	to unite
abbeTe - mabeT	አበጠ - ማበጥ	to swell
abet	አቤት	yes sir, sir?
abetuta	አቤቱታ	complaint
abeba	አበባ	flower
abeddere - mabedder	አበደረ - ማበደር	to lend (money)
abejje - mabejjet	አበጀ - ማበጀት	to make, to construct
abeKKa - mabKat	አበቃ - ማብቃት	to cease, to stop, to end; to live up to
abeKKele - mabKel	አበቀለ - ማብቀል	to cultivate, to grow (trans.)
abeleSSege - mabelSeg	አበለጸገ - ማበልጸግ	to enrich, to make prosperous
abella - mablat	አበላ - ማብላት	to feed, to bribe
aberekkete - maberket	አበረከተ - ማበርከት	to extend, to offer, to make abundant
aberra - mabrat	አበራ - ማብራት	to light up, to turn on the light, to shine
aberrere - mabrer	አበረረ - ማብረር	to chase, to expel
abessele - mabsel	አበሰለ - ማብሰል	to cook
abezza - mabzat	አበዛ - ማብዛት	to multiply
abro	አብሮ	together
abro yisTen	አብሮ፡ይስጠን	you're welcome!
abwara	አቧራ	dust
abzaNNa	አብዛኛ	most, majority
aCese - maCes	አጨሰ - ማጨስ	to smoke

aCCawwete - maCCawet	አጫወተ - ማጫወት	to keep company
aCCir	አጭር	short
adane - madan	አዳነ - ማዳን	to cure, to save
addammeTe - maddameT	አዳመጠ - ማዳመጥ	to listen
addañ	አዳኝ	hunter
addaraš	አዳራሽ	hall
addebabay	አደባባይ	city square, court of justice
addeballeKe - maddebaleK	አደባለቀ - ማደባለቅ	to mix
addefe - madef	አደፈ - ማደፍ	to be dirty
addege - madeg	አደገ - ማደግ	to grow
addele - maddel	አደለ - ማደል	to distribute
addene - madden	አደነ - ማደን	to hunt
addere - mader	አደረ - ማደር	to spend the night
addese - maddes	አደሰ - ማደስ	to repair, to renew
addis	አዲስ	new
addis abeba	አዲስ፡አበባ	Addis Abeba
addis ketema	አዲስ፡ከተማ	downtown section of Addis Abeba
adega	አደጋ	danger, accident, damage
adegeñña	አደገኛ	dangerous
adekkeme - madkem	አደከመ - ማድከም	to tire
aden	አደን	hunting
aderrege - madreg	አደረገ - ማድረግ	to do, to perform, to make
aderrese - madres	አደረሰ - ማድረስ	to cause to arrive
adkami	አድካሚ	tiring, tiresome, boring
adrašša	አድራሻ	address
af	አፍ	mouth, language
afegeffege - mafegfeg	አፈገፈገ - ማፈግፈግ	to retreat, to withdraw (intr.)
afeKKere - mafKer	አፈቀረ - ማፍቀር	to love
afer	አፈር	soil, dirt
aferrese - mafres	አፈረሰ - ማፍረስ	to destroy, to demolish, to cancel
afessese - mafses	አፈሰሰ - ማፍሰስ	to spill

affaTTenə - maffaTən	አፋጠነ - ማፋጠን	to expedite
affəlaləg	አፈላለግ	search, investigation
affərə - mafər	አፈረ - ማፈር	to be shy, to be ashamed
affeSaSəm	አፈጻጸም	performance, completion
affətatəš	አፈታተሽ	testing, searching
afınCa	አፍንጫ	nose
afwaCCə - mafwaCət	አፏጨ - ማፏጨት	to whistle
ageTə - mageT	አጌጠ - ማጌጥ	to be decorated, to be adorned
agəbba - magbat	አገባ - ማግባት	to marry, to bring in
agəC	አገጭ	chin
agələggələ - magəlgəl	አገለገለ - ማገልገል	to serve
agəlgılot	አገልግሎት	service
agəññə - magñet	አገኘ - ማግኘት	to find, to get
agər	አገር	country
yagər gızat minister	ያገር፡ግዛት፡ሚኒስቴር	Ministry ~~of Interior~~
agərə gəži	አገረ፡ገዢ	governor
aggaTTəmə - maggaTəm	አጋጠመ - ማጋጠም	to join, to attach, to occur, to encounter
aggaTami	አጋጣሚ	chance
ındaggaTami	እንዳጋጣሚ	by chance, accidentally, luckily
aggəbab	አገባብ	method; the way of entering
aggənaññə - maggənañət	አገናኘ - ማገናኘት	to connect, to cause to meet
aggəzə - maggəz	አገዘ - ማገዝ	to assist, to help
aggiyageT	አጊያጌጠ	decoration
aggot	አጎት	uncle
agwazə - magwaz	አጓዘ - ማጓዝ	to transport
ahıyya	አህያ	donkey
ahun	አሁን	now
ajja	አጃ	oat
ajjəbə - majjəb	አጀበ - ማጀብ	to accompany
akalat	አካላት	body

akebbere - makber	አከበረ - ማክበር	to honor, to celebrate, to accept (invitation)
akıst	አክስት	aunt
akkababî	አካባቢ	outskirts, surroundings, vicinity
akkefafel	አከፋፈል	dividing, paying back
akkefaffele - makkefafel	አከፋፈለ - ማከፋፈል	to distribute
akkeke - makek	አከከ - ማከክ	to scratch
akkele - makkel	አከለ - ማከል	to be equal, to be worthy, to entrust
akkeme - makkem	አከመ - ማከም	to treat (a patient)
akkenawwene - makkenawen	አከናወነ - ማከናወን	to accomplish, to complete
akkerayye - makkerayet	አከራየ - ማከራየት	to let for rent
akkiyahed	አኪያሄድ	walking; progressing
akkwahwan	አኳኋን	state, condition
aKd	አቅድ	plan
aKebet	አቀበት	uphill
aKelleme - maKlem	አቀለመ - ማቅለም	to dye
aKerrebe - maKreb	አቀረበ - ማቅረብ	to bring, to present, to offer
aKeTTele - maKeTTel	አቀጠለ - ማቀጠል	to sprout
aKKaTTele - maKKaTel	አቃጠለ - ማቃጠል	to burn, to light
aKKebabel	አቀባበል	reception
aKKede - maKKed	አቀደ - ማቀድ	to plan, to design
aKKefe - maKef	አቀፈ - ማቀፍ	to embrace
aKKemameT	አቀማመጥ	situation, location, position
aKKoTater	አቆጣጠር	counting, computing
yegize aKKoTaTer	የጊዜ፡አቆጣጠር	time reckoning; calendar
aKKwaKwam	አቋቋም	establishment, position, posture
aKKwaKwame - maKKwaKwa	አቋቋመ - ማቋቋም	to establish, to found
aKKwarreTe - maKKwareT	አቋረጠ - ማቋረጥ	to interrupt, to cease, to cross
aKm / aKım	አቅም	ability, force
aKome / maKom	አቆመ - ማቆም	to erect, to stop
aKossele / maKusel	አቆሰለ - ማቁሰል	to wound

aKoyyə - maKoyyət	አቆየ — ማቆየት	to keep, to delay
aKrabbiya	አቅራቢያ	near by, around
aKTaCCa	አቅጣጫ	direction
aKwam	አቋም	policy, condition
alafi	አላፊ	one responsible for
alama	አላማ	aim, goal, purpose
albəKKam	አልበቃም	insufficient
alə - malət	አለ - ማለት	to say
aləbbəsə - malbəs	አለበሰ - ማልበስ	to dress (trans.)
aləKa	አለቃ	chief
aləKKəsə - malKəs	አለቀሰ - ማልቀስ	to weep
aləm	ዓለም	world
alənga	አለንጋ	whip
alət	አለት	rock
alfo alfo	አልፎ ፡ አልፎ	here and there, everywhere
alga	አልጋ	bed
allalak	አላላክ	sending, dispatching
allammədə - mallaməd	አላመደ - ማላመድ	to accustom, to make familiar
allə	አለ	there is
alləbabəs	አለባበስ	the way of dressing, fashion
alləfə - maləf	አለፈ - ማለፍ	to pass
alləKə - maləK	አለቀ - ማለቅ	to end, to be finished
alləyayət	አለያየት	separating
allıCCa	አልጫ	stew, sauce
almaz	አልማዝ	diamond
amac	አማች	brother-in-law; sister-in-law
amarə - mamar	አማረ - ማማር	to look better; to desire
amat	አማት	mother-in-law; father-in-law
amarıñña	አማርኛ	Amharic
ambasadər	አምባሳደር	ambassador
aməl	አመል	character, behavior
aməlləTə - mamləT	አመለጠ - ማምለጥ	to escape
amen	አሜን	amen

amerika	አሜሪካ	America
amerikan	አሜሪካን	American (adj.)
amerikawi	አሜሪካዊ	an American
aməlekkətə - maməlkət	አመለከተ-ማመልከት	to show, to indicate, to point out, to report
amənətta - mamentat	አመነታ- ማመንታት	to hesitate, to doubt
amənezzərə - mamənzər	አመነዘረ- ማመንዘር	to commit adultery
aməsəggənə - maməsgən	አመሰገነ- ማመስገን	to thank
aməššə - mamšət	አመሸ- ማምሸት	to spend the evening
amət	ዓመት	year
amətə mihrət	ዓመተ፡ምህረት	A.D.
aməTəñña / aməSəñña	አመጠኛ/አመጸኛ	rebel
ammakkərə - mammakər	አማከረ- ማማከር	to consult
ammassələ - mammasəl	አማሰለ- ማማሰል	to stir
aməTTa - mamTat	አመጣ- ማምጣት	to bring
amməmə - maməm	አመመ- ማመም	to cause physical pain
ammənə - mamən	አመነ- ማመን	to believe, to admit
ammənəzazər	አመነዛዘር	money changing
ammərar	አመራር	leading, conducting
ammərarəT	አመራረጥ	selecting, choosing, voting
amməsəgagən	አመሰጋገን	thanking
amməšaš / amməšašət	አመሻሽ/አመሻሸት	spending the evening
amməTaT	አመጣጥ	coming
ammist	አምስት	five
amlak	አምላክ	God
amsa / hamsa	አምሳ/ሃምሳ	fifty
ammwamwat	አሟሟት	dying
amna	አምና	last year
amoKə - mamoK	አሞቀ - ማሞቅ	to heat
anaTi	አናጢ	carpenter
anbəssa	አንበሳ	lion
anbəTTa	አንበጣ	locust

anbolık	አንቦልክ	envelope
anci	አንቺ	you (f.)
and	አንድ	one
and aynet	አንድ፡ ዓይነት	same
and gize	አንድ፡ ጊዜ	once
and madreg	አንድ፡ ማድረግ	to unify
andacc	አንዳች	nothing, something, anything
andand gize	አንዳንድ፡ ጊዜ	sometimes
andande	አንዳንዴ	sometimes
andeñña	አንደኛ	first
andınnet	አንድነት	unity
bandınnet	ባንድነት	together
anebbebe - manbeb	አነበበ — ማንበብ	to read
anessa - mansat	አነሣ — ማንሣት	to lift, to raise, to mention
anesteñña	አነስተኛ	inferior, insignificant
aneTTefe - manTef	አነጠፈ — ማንጠፍ	to spread out
aneTTese - manTes	አነጠሰ — ማንጠስ	to sneeze
anget	አንገት	neck
angol	አንጎል	brain
ankwakwa - mankwakwat	አንኳኳ — ማንኳኳት	to knock
annegager	አነጋገር	talk
anneKanneKe - manneKaneK	አነቃነቀ — ማነቃነቅ	to shake, to move (trans.)
annese - manes	አነሰ — ማነስ	to be small, to diminish
annwanwar	አኗኗር	living, subsistence
ante	አንተ	you (m.)
anTeleTTele - manTelTel	አንጠለጠለ — ማንጠልጠል	to suspend, to hang
bejj manTelTel	በእጅ፡ አንጠለጠለ	to carry by hand
araš	አራሽ	farmer
aratt	አራት	four
arawit	አራዊት	wild animal
arb	አርብ	Friday
arba	አርባ	forty

arəbba - marbat	አረባ — ማርባት	to raise, to breed
arəffədə - marfəd	አረፈደ — ማርፈድ	to be late in the morning
arəftənəgər	ዐረፍተ· ነገር	sentence
arəggəzəc - margəz	አረገዘች — ማርገዝ	to be pregnant
arəjjə - marjət	አረጀ — ማርጀት	to be old
arəKe	አረቄ	rakee
arəməne	አረመኔ	pagan
arəngwade	አረንጓዴ	green
ari'ist	አርእስት	title, topic
aroge	አሮጌ	old
arogit	አሮጊት	old woman
arrədə - marəd	አረደ — ማረድ	to slaughter, to deceive
arrəfə - marəf	አረፈ — ማረፍ	to rest
arrəgaggəTə - marrəgagəT	አረጋገጠ — ማረጋገጥ	to assure, to confirm
arrəmə - marrəm	አረመ — ማረም	to correct, to weed
arrəsə - marəs	አረሰ — ማረስ	to cultivate, to till, to plow
arusi	አሩሲ	Arusi (province)
asa	አሳ	fish
asaddəsə - masaddəs	አሳደሰ — ማሳደስ	to have repaired
asama	አሳማ	pig
asammənə - masammən	አሳመነ — ማሳመን	to persuade, to convince
asallafi	አሳላፊ	waiter
asalləfə - masalləf	አሳለፈ — ማሳለፍ	to let pass, to spend, to wait on, to serve
asannəsə - masannəs	አሳነሰ — ማሳነስ	to decrease
asassəbə - masassəb	አሳሰበ — ማሳሰብ	to remind
asawwəKe - masawwəK	አሳወቀ — ማሳወቅ	to let know
asayyə - masayyət	አሳየ — ማሳየት	to show
asbəjjə - masbəjjət	አስበጀ — ማስበጀት	to have made
ascəggari	አስቸጋሪ	difficult
ascəggərə - mascəggər	አስቸገረ — ማስቸገር	to cause difficulty
asCanə - masCan	አስጫነ — ማስጫን	to have something loaded

asCese - masCes	አስጨሰ- ማስጨስ	to cause to smoke
asdeffere - masdeffer	አስደፈረ- ማስደፈር	to cause to dare, to discredit
asdeneggeTe - masdengeT	አስደነገጠ- ማስደንገጥ	to frighten
asdennaKi	አስደናቂ	surprising, amazing, outstanding
asdenneKe - masdenneK	አስደነቀ - ማስደነቅ	to surprise, to astonish
asderrese - masderres	አስደረሰ- ማስደረስ	to cause to narrate; to make someone to write a composition
asdessac	አስደሳች	pleasant, enjoyable
asdessete - masdesset	አስደሰተ - ማስደሰት	to please
aseb	አሰብ	Assab (port in Ethiopia)
asekkere - masker	አሰከረ- ማስከር	to intoxicate
asfaffa - masfafat	አስፋፋ- ማስፋፋት	to develop, to expand, to enlarge
asfeKKede - masfeKKed	አስፈቀደ- ማስፈቀድ	to get permission, to acquire consent
asfellege - masfelleg	አስፈለገ- ማስፈለግ	to need
asferarra - masferarat	አስፈራራ- ማስፈራራት	to threaten
asferra - masferrat	አስፈራ- ማስፈራት	to frighten, to menace
asfeSSami	አስፈጻሚ	one responsible for, in charge of
asfetta - masfettat	አስፈታ -ማስፈታት	to have released
sira masfettat	ሥራ፡ ማስፈታት	to take someone's time, to disturb
asgabbeze -masgabez	አስጋበዘ- ማስጋበዝ	to ask somebody to invite s.o.
asgeTe - masgeT	አስጌጠ- ማስጌጥ	to decorate, to have decorated
asgebba - masgebbat	አስገባ- ማስገባት	to cause to be brought
asgeddede - masgedded	አስገደደ - ማስገደድ	to force
asgenezzebe - masgenzeb	አስገነዘበ- ማስገንዘብ	to make realize, to make aware of something
asgerrami	አስገራሚ	wonderful
ashede - mashed	አስሄደ- ማስሄድ	to cause to go
askeffele - maskeffel	አስከፈለ- ማስከፈል	to charge, to cause to pay

asKəddəmə - masKəddəm	አስቀደመ - ማስቀደም	to cause to precede
asKəddımo	አስቀድሞ	before
asKəmmeTə - masKəmmeT	አስቀመጠ - ማስቀመጥ	to put down, to let aside, to deposit
asKərrə - masKərrət	አስቀረ - ማስቀረት	to cancel
asKeTTələ - masKeTTəl	አስቀጠለ - ማስቀጠል	to have connected, to cause to add
asKəyyami	አስቀያሚ	ugly, unpleasant
asKomə - masKom	አስቆመ - ማስቆም	to cause to erect
asləbbəsə - masləbbəs	አስለበሰ - ማስለበስ	to have somebody dress s.o.
asləyyə - masləyyət	አስለየ - ማስለየት	to cause to separate
asmamma - masmamat	አስማማ - ማስማማት	to reconcile
asmat	አስማት	sorcery
asmatteñña	አስማተኛ	magician
asmeCCınna laki	አስመጪና፡ ላኪ	Export-Import Co.
asmənezzərə - masmənzər	አስመነዘረ - ማስመንዘር	to cause to change money
asməra	አስመራ	Asmara
asməseggənə - masməsgən	አስመሰገነ - ማስመስገን	to cause to thank
asməssələ - masməssəl	አስመሰለ - ማስመሰል	to pretend
asmeššə - masmeššət	አስመሸ - ማስመሸት	to cause to spend the evening
asmeTTa - masmeTTat	አስመጣ - ማስመጣት	to import
asnəffa - masnəffat	አስነፋ - ማስነፋት	to cause to inflate
asnəssa - masnəssat	አስነሳ - ማስነሳት	to start, to wake up
asrammıst	አሥራ፡ አምስት	fifteen
asrand	አሥራ፡ አንድ	eleven
asraratt	አሥራ፡ አራት	fourteen
asra hulətt	አሥራ፡ ሁለት	twelve
asra səbatt	አሥራ፡ ሰባት	seventeen
asra sıddıst	አሥራ፡ ስድስት	sixteen
asra sımmınt	አሥራ፡ ስምንት	eighteen
asra sost	አሥራ፡ ሦስት	thirteen
asrazəTəñ	አሥራ፡ ዘጠኝ	nineteen
asrədda - masrəddat	አስረዳ - ማስረዳት	to explain

asrəkkəbə - masrəkkəb	አስረከበ - ማስረከብ	to delıver
assab / hassab	አሳብ / ሃሳብ	thought, plan, ıntentıon, ıdea
assabinnət	አሳቢነት	ınıtıatıng, brıngıng forth
assasatə - massasat	አሳሳተ - ማሳሳት	to mıslead
assəbə - massəb	አሰበ - ማሰብ	to thınk, to ıntend
assəffa - massəffat	አሰፋ - ማሰፋት	to have a suıt made
assəmma - massəmmat	አሰማ - ማሰማት	to ınform, to let know, to broadcast
assənabbətə - massənab	አሰናበተ - ማሰናበት	to dısmıss, to fıre
assənadda - massənadat	አሰናዳ - ማሰናዳት	to arrange, to prepare
assənəbabət	አሰነባበት	sojourn
assərə - masər	አሰረ - ማሰር	to tıe, to bınd
assərra - massərrat	አሠራ - ማሠራት	to have buılt, to cause to work
assəTaT	አሰጣጥ	way of gıvıng
assır	አሥር	ten
astamami	አስታማሚ	nurse
astarrəKə - mastarəK	አስታረቀ - ማስታረቅ	to reconcıle
astawwəKə - mastawəK	አስታወቀ - ማስታወቅ	to ınform
astawwəsə - mastawəs	አስታወሰ - ማስታወስ	to remınd, to remember
astədadari	አስተዳዳሪ	admınıstrator
astədadəg	አስተዳደግ	rearıng, raısıng
astədaddərə - mastədadər	አስተዳደረ - ማስተዳደር	to admınıster
astədadər	አስተዳደር	admınıstratıon
astəlaləK	አስተላለቅ	massacrıng, exhaustıng
astəlalləfə - mastəlale	አስተላለፈ - ማስተላለፍ	to communıcate
astəmarə - mastəmar	አስተማረ - ማስተማር	to teach
astəmari	አስተማሪ	teacher
astəwalə - mastəwal	አስተዋለ - ማስተዋል	to understand, to observe
astəwawwəKə - mastəwawəK	አስተዋወቀ - ማስተዋወቅ	to ıntroduce (a person)
astəway	አስተዋይ	ıntellıgent, wıse
astəyayət	አስተያየት	opınıon, standpoınt
astəzazəz	አስተዛዘዝ	orderıng, commandıng

asTəbbəKə - masTəbbəK	አስጠበቀ - ማስጠበቅ	to keep waiting
asTərra - masTərrat	አስጠራ - ማስጠራት	to send for
asTərrəgə - masTərrəg	አስጠረገ - ማስጠረግ	to have cleaned
asTəTTa - masTəTTat	አስጠጣ - ማስጠጣት	to cause to drink
aswalə - maswal	አስዋለ - ማስዋል	to cause to spend the day
aswəggədə - maswəggəd	አስወገደ - ማስወገድ	to check, to drive away, to avoid
aswələwwələ - maswəlwəl	አስወለወለ - ማስወልወል	to have polished
asyazə - masyaz	አስያዘ - ማስያዝ	to cause to hold, to have s.o. arrested, to pawn
aSSaSaf	አጻጻፍ	writing
aSe	አጼ	emperor
aSənna - maSnat	አጸና - ማጽናት	to confirm, to approve, to ratify
ašangullit	አሻንጉሊት	toy, doll
ašəttətə - maštət	አሸተተ - ማሽተት	to smell (tr.)
ašəwa	አሸዋ	sand
aškər	አሽከር	servant
aššašalə - maššašal	አሻሻለ - ማሻሻል	to improve
aššašaT	አሻሻጥ	transaction
aššə - mašət	አሸ - ማሸት	to rub, to massage
aššəgaggərə - maššəgag	አሸጋገረ - ማሸጋገር	to let pass, to help to pass or to cross
aššənnəfə - maššənnəf	አሸነፈ - ማሸነፍ	to conquer, to win, to defeat
atər	አተር	peas
atərrəfə - matrəf	አተረፈ - ማትረፍ	to gain, to get profit, to save
atkilt	አትክልት	vegetables
ato	አቶ	Mr.
attallələ - mattaləl	አታለለ - ማታለል	to cheat, to deceive
attəmə - mattəm	አተመ - ማተም	to print
aTəffa - maTfat	አጠፋ - ማጥፋት	to destroy, to lose, to put out, to waste, to squander
aTəgəb	አጠገብ	near
aTəlla - maTlat	አጠላ - ማጥላት	to shade

aTenekkere - maTenker	አጠነከረ - ማጠንከር	to strengthen
aTenna - maTnat	አጠና - ማጥናት	to study
aTeTTa - maTeTTat	አጠጣ - ማጠጣት	to water, to irrigate, to offer a drink
aTint	አጥንት	bone
aTir	አጥር	fence
aTir gibbi	አጥር፡ ግቢ	backyard, compound
aTTa - maTat	አጣ - ማጣት	to fail to get, to miss, to lack
aTTarra - maTTarat	አጣራ - ማጣራት	to filter, to distill, to screen
aTTebabeK	አጠባበቅ	keeping, waiting, watching, care
aTTebe - maTeb	አጠበ - ማጠብ	to wash
aTTefe - maTef	አጠፈ - ማጠፍ	to fold
aTTere - maTer	አጠረ - ማጠር	to make a fence, to be short
awaj	አዋጅ	decree, proclamation
awaKi	አዋቂ	expert, learned
awale - mawal	አዋለ - ማዋል	to postpone, to cause to spend the day
awaš	አዋሽ	Awash (river)
awelleKe - mawleK	አወለቀ - ማውለቅ	to take off, to remove
awerra - mawrat	አወራ - ማውራት	to talk, to tell, to describe
awerrede - mewred	አወረደ - ማውረድ	to put down, to unload, to carry down
aweTTa - mawTat	አወጣ - ማውጣት	to pull out, to withdraw, to place on, to cost
awilo nefas	አውሎ፡ ነፋስ	hurricane, tornado, strong wind
awo / awon	አዎ / አዎን	yes
awra	አውራ	main, principal
awra doro	አውራ፡ ዶሮ	cock, rooster
awra godana	አውራ፡ ጎዳና	highway
awrajja	አውራጃ	county
awre	አውሬ	wild animal, beast; mean, wild, ferocious

awroPa	አውሮፓ	Europe
awroPawi	አውሮፓዊ	European
awroPlan/awroplan ayroPlan/ayroplan	አውሮፕላን/አይሮፕላን	airplane
awroPlan marəfiya	አውሮፕላን፡ ማረፊያ	airport
awtobus	አውቶቡስ	bus
awwalaj	አዋላጅ	midwife
awwassənə - mawwasən	አዋሰነ– ማዋሰን	to border
awwaTTa - mawwaTat	አዋጣ– ማዋጣት	to contribute
awwawal	አዋዋል	the way of spending the day; doing favor
awwəjə-mawwəj	አወጀ – ማወጅ	to proclaim, to declare
awwəkə - mawwək	አወከ – ማወክ	to disturb
awwəKə - mawəK	አወቀ – ማወቅ	to know
awwəTaT	አወጣጥ	emerging
hıgg awwəTaT	ሕግ፡ አወጣጥ	law making
ayat	አያት	grandparent
aydəlləm	አይደለም	is not
ayıb	አይብ	cottage cheese
ayımıro /a'ımro	አይምሮ/አእምሮ	mind, intelligence
ayn	ዓይን	eye
ayn affar	ዓይነ· አፋር	shy
aynət	ዓይነት	sort, kind
ayT	አይጥ	rat, mouse
ayyale	አያሌ	several
ayyayaz	አያያዝ	way of handling something, manner
ayyayazə - mayyayaz	አያያዘ– ማያያዝ	to fasten, to attach
ayyə - mayət	አየ – ማየት	to see
ayyər	አየር	air
yayyər Təbay	ያየር· ጠባይ	climate
ayyər məngəd	ያየር፡ መንገድ	air line
azən	አዘን	grief, sorrow
azənəbbələ - mazənbəl	አዘነበለ – ማዘንበል	to incline, to tend toward

azzawwərə - mazzawər	አዛወረ–ማዛወር	to remove, to transfer
azzəgaȷȷə - mazzəgaȷət	አዘጋጀ–ማዘጋጀት	to prepare
azzənə - mazən	አዘነ–ማዘን	to be sorry
azzezə - mazzez	አዘዘ–ማዘዝ	to order, to command
azzo	አዞ	crocodıle

b

babur	ባቡር	traın
babur Tabiya	ባቡር፡ጣቢያ	raılroad statıon
bada / ba'ıda	ባዳ/ባዕዳ	stranger, alıen, person not connected wıth another by blood
bado	ባዶ	empty
bahıl	ባሕል	custom, tradıtıon
bahır	ባሕር	sea
bahırdar	ባሕር፡ዳር	seashore, beach
bahri	ባሕሪ	character, nature
baȷət	ባጀት	budget
baKela	ባቄላ	beans
bal	ባል	husband
balabbat	ባላባት	nobleman
balagər	ባላገር	rural area, countrysıde; peasant, countryman
bale	ባሌ	Bale (provınce of)
balə	ባለ	owner
baləbet	ባለቤት	husband, wıfe, chıef
balege	ባለጌ	ımpolıte, rude
baləmulu sılTan	ባለሙሉ፡ሥልጣን	plenıpotentıary
baləsılTan	ባለሥልጣን	authorıtıes
baləSəgga	ባለጸጋ	wealthy, well-off
balınȷəra	ባልንጀራ	frıend
baltet	ባልቴት	old woman
bank	ባንክ	bank
bariya	ባሪያ	slave

barneTa	ባርኔጣ	hat
basə - məbas	ባሰ — መባስ	to get worse
benzın	ቤንዚን	gasolıne
bet	ቤት	house
betə krıstiyan	ቤተ፡ክርስቲያን	church
betə məngıst	ቤተ፡መንግሥት	palace
betə məSahıft	ቤተ፡መጻሕፍት	lıbrary
betəsəb	ቤተ፡ሰብ	famıly
bə'al / bal	በዓል/ባል	holıday
bə-...bəkkul	በ... በኩል	ın the dırectıon of...
bəbəkkulu	በበኩሉ	on hıs part
bəCırraš	በጭራሽ	utterly, completely, at all
bəddələ - məbəddəl	በደለ — መበደል	to offend
bəddənə - məbəddən	በደነ — መበደን	to be paralızed
bədəl	በደል	offense
bədın	በድን	corpse; numb
bədıngət	በድንገት	suddenly
bəfıSum	በፍጹም	absolutely, never, by no means
bəg	በግ	sheep
bəga	በጋ	summer
bəgəmıdır	በጌምድር	Bagemder (provınce)
bəggo	በጎ	welfare
bəɟɟə - məbəɟɟət	በጀ — መበጀት	to be useful
bəKəddəmlət	በቀደምለት	prevıously, last tıme
bəKəl	በቀል	revenge
bəKər	በቀር	except
bəKəssıta	በቀስታ	slowly
bəKəTTıta	በቀጥታ	straıght ahead
bəKi	በቂ	enough
bəKKa - məbKat	በቃ — መብቃት	to be suffıcıent
bəKKələ - məbKəl	በቀለ — መብቀል	to grow, to germınate
bəKlo	በቅሎ	mule

beKollo	በቆሎ	corn
belg	በልግ	autumn, fall
bella - meblat	በላ - መብላት	to eat
belleTe - mebleT	በለጠ - መብለጥ	to exceed, to be more, to be large
bemalet	በማለት	thinking that...
berberre	በርበሬ	pepper
bere	በሬ	ox, bull
berebbere - meberber	በረበረ - መበርበር	to search
beredo	በረዶ	hail, snow
bereha	በረሃ	desert
berekkete - meberket	በረከተ - መበርከት	to increase (intr.), to multiply
berenda	በረንዳ	porch, veranda, patio
beretta - mebertat	በረታ - መበርታት	to be strong
berkett malet	በርክት፡ማለት	to be numerous
berr	በር	doorway, passage
berra - mebrat	በራ - መብራት	to shine
berraf	በራፍ	doorway
berrede - mebred	በረደ - መብረድ	to get chilly, to be cold
berrere - mebrer	በረረ - መብረር	to fly
besebbese - mebesbes	በሰበሰ - መበስበስ	to be rotten
bessa - mebsat	በሳ - መብሳት	to pierce
bessele - mebsel	በሰለ - መብሰል	to be ripe, cooked
bestegra	በስተግራ	to the left
besteKeññ	በስተቀኝ	to the right
besteKer	በስተቀር	except that
bešita	በሽታ	illness
bešiteñña	በሽተኛ	ill
beteleyy	በተለይ	especially, in particular
bettene - mebetten	በተነ - መበተን	to disperse, to scatter
beTam	በጣም	very
beTTese - mebeTTes	በጠሰ - መበጠስ	to break

bəzza - məbzat	በዛ - መብዛት	to ıncrease, to be too much
biCa	ቢጫ	yellow
bihonım	ቢሆንም	even though
billawa	ቢላዋ	knıfe
bira	ቢራ	beer
biro	ቢሮ	offıce
biskılit	ቢስክሌት	bıcycle
biyans	ቢያንስ	at least
bı'ır	ብዕር	pen
bıcca	ብቻ	alone, only
bıddır	ብድር	loan
bıKK malət	ብቅ፡ ማለት	to emerge, to appəar
bılCa	ብልጫ	superıorıty, majorıty, preponderance
bılıClıC malət	ብልጭልጭ፡ ማለት	to shıne, to glıtter
bılıh	ብልህ	clever, ıntellıgent
bılSıgınna	ብልጽግና	wealth
bılT	ብልጥ	cunnıng, clever
bınnañ	ብናኝ	dust
bırCıKo	ብርጭቆ	glass
bırd	ብርድ	cold
bırd lıbs	ብርድ· ልብስ	blanket
bırət	ብረት	metal, ıron, steel
bırhan	ብርሃን	lıght, brıght
bırındo	ብርንዶ	lean meat
bırK	ብርቅ	rare, unusual
bırr	ብር	dollar, sılver
bırtat	ብርታት	vıgor
bırtu	ብርቱ	strong, heavy, ımportant
bırtukan	ብርቱካን	orange
bıruh	ብሩህ	clear
bısıl	ብስል	rıpe
bıskut	ብስኩት	bıscuıt

bızat	ብዛት	quantity
begize bızat	በጊዜ፡ብዛት	in the course of time
bızu	ብዙ	much, many
boks	ቦክስ	boxing
borsa	ቦርሳ	wallet, purse, briefcase
bota	ቦታ	place
bozzene - mebozzen	ቦዘነ - መቦዘን	to be idle
buda	ቡዳ	evil eye
bulla	ቡላ	light brown
bunna / bun	ቡና/ቡን	coffee
bunnabet	ቡና፡ቤት	café, bar
bunnamma	ቡናማ	brown
buš	ቡሽ	cork
butıtto	ቡትቶ	rag
buTi	ቡጢ	fist
bwalt	ቧልት	joke, fun
bwambwa	ቧንቧ	pipe
c		
cale - mecal	ቻለ - መቻል	to be able
cek	ቼክ	check
cel malet	ቸል፡ማለት	to neglect
cellıteñña	ቸልተኛ	neglectful
cekkole - mecekkol	ቸኮለ - መቸኮል	to hurry
cer	ቸር	generous, kind
cerınnet	ቸርነት	generosity, kindness
cıggar	ችጋር	famine, starvation
cıggır	ችግር	problem, difficulty
cıkko	ችኮ	stubborn
cıkkola	ችኮላ	haste, hurry
cıkkul	ችኩል	hasty
cılota	ችሎታ	ability
cok	ቾክ	chalk

C

Caf	ጫፍ	summit, top, end
Cakka	ጫካ	forest
Camma	ጫማ	shoes
Canə - məCan	ጫነ- መጫን	to load
CəbbəTə - məCəbbəT	ጨበጠ- መጨበጥ	to grasp, to seize, to clasp
ijj məCəbbəT	እጅ፡ መጨበጥ	to shake hands
CəfəCCəfə - məCəfCəf	ጨፈጨፈ- መጨፍጨፍ	to slash, to massacre
Cəffərə - məCəffər	ጨፈረ- መጨፈር	to dance
Cəkkañ	ጨካኝ	cruel, ruthless
Cəkkənə - məCəkkən	ጨከነ- መጨከን	to be determined, to be cruel
CəKKonə - məCəKKon	ጨቆነ- መጨቆን	to oppress, to suppress
Cəllema	ጨለማ	darkness
Cəlləmə - məCəlləm	ጨለመ- መጨለም	to get dark
Cəlləfə - məCəlləT	ጨለጠ- መጨለጥ	to empty
CəmməKə - məCməK	ጨመቀ- መጭመቅ	to squeeze
Cəmmərə - məCəmmər	ጨመረ- መጨመር	to pour in, to fill up, to add, to increase
CərəKa	ጨረቃ	moon
CərK	ጨርቅ	cloth, rag
Cərrəsə - məCərrəs	ጨረሰ- መጨረስ	to finish
Cəsə - məCəs	ጨሰ- መጨስ	to smoke (intr.)
Cəw	ጨው	salt
Cəwa	ጨዋ	gentle, polite, noble
Cəwata	ጨዋታ	game, play, sport; matter, topic
Ciffera	ጭፈራ	a popular dance
Cigag	ጭጋግ	mist
CiKa	ጭቃ	mud
CimCimta	ጭምጭምታ	rumor
CimmaKi	ጭማቂ	juice
Cimmari	ጭማሪ	additional

Cımmır	ጭምር	ıncludıng
Cın	ጭን	thıgh
Cınət	ጭነት	load
Cıs	ጭስ	smoke
yəCıs bınañ	የጭስ፡ ብናኝ	fall out
Cohə - məCoh	ጮኸ - መጮህ	to shout, to yell, to scream
Colle	ጮሌ	smart, clever
Coma	ጮማ	fat (n.)
Cuhət	ጩኸት	scream, cry, noıse
d		
dabbəsə - mədabəs	ዳበሰ - መዳበስ	to touch, to examıne, to search, to feel
dabbo	ዳቦ	bread
damməna	ዳመና	cloud
danə - mədan	ዳነ - መዳን	to be saved, to recover, to redeem, to heal
dañña	ዳኛ	ȷudge
daññə - mədañət	ዳኘ - መዳኘት	to ȷudge
daññınnət	ዳኝነት	legal; ȷudgement
dar	ዳር	shore, bank, edge
darugın	ዳሩግን	however, but
dəbbəKə - mədəbbəK	ደበቀ - መደበቅ	to hıde, to conceal
dəbdabbe	ደብዳቤ	letter
dəbəddəbə - mədəbdəb	ደበደበ - መደብደብ	to strıke, to hıt
dəbtər	ደብተር	notebook
dəbub	ደቡብ	south
dəffar	ደፋር	bold
dəffərə - mədfər	ደፈረ - መድፈር	to dare, to rısk, to venture
dəga	ደጋ	hıghland
dəgg	ደግ	kınd, fıne, nıce
dəggəfə - mədəggəf	ደገፈ - መደገፍ	to support
dəggəmə - mədgəm	ደገመ - መድገም	to repeat
dəggənə - mədəggən	ደገነ - መደገን	to aım

dəggəsə - mədəggəs	ደገሰ - መደገስ	to arrange a banquet
dəggınnət	ደግነት	kındness, generosıty
dəgmo	ደግሞ	agaın, also, moreover, too
dəha	ደኃ	poor
dəhınnət	ድኅነት	poverty
dəhna	ደህና	good, well, fıne
dəhnınnət	ድኅንነት	well beıng, goodness, good health
dəȷȷaf	ደጃፍ	doorway, threshold
dəkkama	ደካማ	weak
dəkkamannət	ደካማነት	weakness, feebleness
dəkkəmə - mədkəm	ደከመ - መድከም	to be tıred; to strıve, to work hard
dəKıKa	ደቂቃ	mınute
dəm	ደም	blood
dəm gıbat	ደም፡ግባት	charm, beauty
dəmam	ደማም	charmıng
dəmma - mədmat	ደማ - መድማት	to bleed
dəmmərə - mədəmmər	ደመረ - መደመር	to sum up, to add
dəməssəsə - mədəmsəs	ደመሰሰ - መደምሰስ	to destroy, to delete, to demolısh
dəmoz	ደሞዝ	salary, wages
dənb	ደንብ	rule, regulatıon
bədənb	በደንብ	properly
bədənb nəwa	በደንብ· ነዋ	certaınly, of course, very much so
dənbəñña	ደንበኛ	proper, regular; customer
dənəz	ደነዝ	dull (edge)
dənKoro	ደንቆሮ	deaf, ıgnorant, stupıd
dənnəsə - mədənnəs	ደነሰ - መደነስ	to dance
dərəȷa	ደረጃ	level, rank, step, stage, staır
dərəȷȷə - mədərȷət	ደረጀ - መደርጀት	to develop, to strıve
dərət	ደረት	chest
dərrəKə - mədrəK	ደረቀ - መድረቅ	to dry

dərrəsə - mədrəs	ደረሰ — መድረስ	to reach, to arrive
dərrəsəñ	ደረሰኝ	receipt
dəss malət	ደረስ፡ ማለት	to be pleased, to be happy
dəsset	ደሴት	island
dəssıta	ደስታ	pleasure
dəssıtəñña	ደስተኛ	pleasant, happy, gay
dəwəl	ደወል	bell
dəwwələ - mədəwwəl	ደወለ — መደወል	to dial, to ring
dıplomatik	ዲፕሎማቲክ	diplomate, diplomatic
dirəktər	ዲሬክተር	director
dıbulbul	ድቡልቡል	round
dıda	ድዳ	dumb, stutterer
dıfrət	ድፍረት	courage, insolence
dıggıs	ድግስ	banquet
dıhoc	ድሆች	the poor (pl. of /dəha/)
dıkam	ድካም	tiredness, fatigue
dıl madrəg	ድል፡ ማድረግ	to win, to be victorious
dıl məhon	ድል፡ መሆን	to be defeated
dıl mənsat	ድል፡ መንሳት	to defeat, to conquer
dıldıyy	ድልድይ	bridge
dımmət	ድመት	cat
dımmır	ድምር	sum, total
dımS	ድምፅ	voice, sound
dınbər	ድንበር	border, frontier
dıngay	ድንጋይ	stone, rock
dıngıl	ድንግል	vergin
dınguT	ድንጉጥ	nervous
dınK	ድንቅ	splendid, wonderful
dınıggaTe	ድንጋጤ	fright, shock, fear
dınkwan	ድንኳን	tent
dınnıc	ድንች	potato
dıres	ድረስ	up to, until

dırša	ድርሻ	share
dırıȷȷıt	ድርጅት	organization
yətəbabbərut məngıstat dırıȷȷıt	የተባበሩት፡መንግሥታት፡ ድርጅት	U.N.O.
dıro/duro	ድሮ/ዱሮ	ancient, former
dırsət	ድርሰት	narrative, story
dıst	ድስት	saucepan
doro	ዶሮ	chicken
dubba	ዱባ	pumpkin
duldum	ዱልዱም	dull (point)
duKet	ዱቄት	flour
dulla	ዱላ	stick, club
dur	ዱር	forest
yədur awre	የዱር፡ አውሬ	wild animal
duro/dıro	ዱሮ/ድሮ	ancient, former

e

ekonomi / ikonomi	ኤኮኖሚ/ኢኮኖሚ	economy
elektrik / lektrik	ኤሌክትሪክ/ሌትሪክ	electric
eli	ኤሊ	turtle
embassi	ኤምባሲ	embassy
ertra	ኤርትራ	Eritrea

ə

ərə	ኧረ!	oh!

f

fanos	ፋኖስ	lantern
fanta / fənta	ፋንታ/ፈንታ	instead of; turn, portion
fasika	ፋሲካ	Easter
fəCCə - məfCət	ፈጨ - መፍጨት	to grind
fəgəgg malət	ፈገግ፡ ማለት	to smile
fəgəgta	ፈገግታ	smile
fəȷȷə - məfȷət	ፈጀ - መፍጀት	to consume, to destroy, to burn, to use up (time, etc.)
fəKad / fıKad	ፈቃድ/ፍቃድ	permission; desire

feKadeñña	ፈቃደኛ	wıllıng
feKKede - mefKed	ፈቀደ– መፍቀድ	to be wıllıng, to allow
felallege - mefelaleg	ፈለገ መፈለግ	to look for (here and there)
feleg	ፈለግ	trace
felessefe - mefelsef	ፈለሰፈ– መፈልሰፍ	to ınvent
fella - meflat	ፈላ – መፍላት	to boıl, to ferment
fellege - mefelleg	ፈለገ– መፈለግ	to want, to look for
fenedda - mefendat	ፈነዳ – መፈንዳት	to burst, to blow up
ferensawi	ፈረንሳዊ	Frenchman
ferensay	ፈረንሳይ	French
yeferensay ager	የፈረንሳይ፡ አገር	France
ferensayıñña	ፈረንሳይኛ	French (language)
feres	ፈረስ	horse
fereseñña	ፈረሰኛ	horseman, cavalery
feres gılbiya	ፈረስ፡ ግልቢያ	horseback rıdıng
feri	ፈሪ	coward
ferra - mefrat	ፈራ – መፍራት	to be afraıd
ferrede - mefred	ፈረደ– መፍረድ	to judge
ferreme - meferrem	ፈረመ– መፈረም	to sıgn
ferrese - mefres	ፈረሰ – መፍረስ	to be demolıshed
fessese - mefses	ፈሰሰ– መፍሰስ	to flow, to spıll
feSSeme - mefeSSem	ፈጸመ– መፈጸም	to accomplısh, to complete
fetena	ፈተና	test, examınatıon
fetta - meftat	ፈታ – መፍታት	to untıe, to release, to dıvorce
fettene - mefetten	ፈተነ– መፈተን	to test, to try, to examıne
fetteše - mefetteš	ፈተሸ– መፈተሽ	to search
feTenn malet	ፈጠን፡ ማለት	to hurry, to be quıck
feTenn bılo	ፈጠን፡ ብሎ	fast, quıckly
feTTanınnet	ፈጣንነት	haste, hurry
feTTene - mefTen	ፈጠነ– መፍጠን	to hurry, to be quıck
feTTere - mefTer	ፈጠረ– መፍጠር	to create
fewwese - mefewwes	ፈወሰ– መፈወስ	to cure, to heal

fidel	ፊደል	letter, alphabet
fılsıfınna	ፍልስፍና	phılosophy
firma	ፊርማ	sıgnature
fit	ፊት	face, front, ahead, earlıer
befit	በፊት	before
wedefit	ወደ፡ፊት	ın the future
fitlefit	ፊትለፊት	ın front of
fıcc	ፍቺ	meanıng, ınterpretatıon
fıKad / feKad	ፍቃድ/ፈቃድ	permıssıon, desıre
fıKır	ፍቅር	love, affectıon
fıllagot	ፍላጎት	desıre
fırd	ፍርድ	justıce, judgement, trıal
yefırd minister	የፍርድ፡ሚኒስቴር	Mınıstry of Justıce
fırdbet	ፍርድ፡ቤት	Court of Justıce
fıre / fre	ፍሬ	fruıt
fırhat	ፍርሃት	fear, terror
fırraš	ፍራሽ	ruın
fıSSame	ፍጻሜ	completıon, end
fıTret	ፍጥረት	creatıon, nature
fıyyel	ፍየል	goat
foK	ፎቅ	storey, floor
form	ፎርም	form
foté	ፎቴ	easy chaır
foTa	ፎጣ	towel
frafre	ፍሬ	varıous sorts of fruıt
fraš	ፍራሽ	matress
fwafwate	ፏፏቴ	waterfall
g		
ga	ጋ	to, from, wıth, at
gabaž	ጋባዥ	host
gabbeze - megabez	ጋበዘ – መጋበዝ	to ınvite
gabıcca	ጋብቻ	marrıage

gallebe - megaleb	ጋለበ - መጋለብ	to gallop, to ride a horse
gar / gara	ጋር/ጋራ	with
gara	ጋራ	mountain
garaž	ጋራዥ	auto repair shop
gari	ጋሪ	cart
gašša	ጋሻ	shield
gazeTa	ጋዜጣ	newspaper
gazeTeñña	ጋዜጠኛ	reporter
geta	ጌታ	master, owner, sir; rich
geT	ጌጥ	decoration, ornament
gebba - megbat	ገባ - መግባት	to enter, to arrive
gebere	ገበሬ	farmer
gebeta	ገበታ	table
gebeya	ገበያ	market
gebs	ገብስ	barley
gedam	ገዳም	monastery
geday	ገዳይ	killer
nefse geday	ነፍሰ ገዳይ	murderer
geddam	ገዳም	lucky
geddele - megdel	ገደለ - መግደል	to kill
gedel	ገደል	cliff
gedema	ገደማ	approximately, about, vicinity
geffa - megfat	ገፋ - መግፋት	to push
geffefe - megfef	ገፈፈ - መግፈፍ	to skin (an animal); to strip (by force)
gehannem	ገሃነም	hell

gela	ገላ	body
geleba	ገለባ	straw; light (adj.)
gelebbeTe - megelbeT	ገለበጠ – መገልበጥ	to copy; to upset, to pour in
gelleSe - megleS (or, gelleTe - megleT)	ገለጸ – መግለጽ	to explain, to disclose
gemed	ገመድ	rope, string
gemma - megmat	ገማ – መግማት	to stink
gemmete - megemmet	ገመተ – መገመት	to estimate, to guess
gemugofa	ገሙጐፋ	Gomo Gofa (province)
gena	ገና	yet, still
genbi	ገንቢ	mason
genebba - megenbat	ገነባ – መገንባት	to build
genna	ገና	field-hockey; Christmas
genzeb	ገንዘብ	money
yegenzeb minister	የገንዘብ፡ ሚኒስቴር	Ministry of Finance
gered	ገረድ	maid
gerrefe - megref	ገረፈ – መግረፍ	to whip
gerreme - megrem	ገረመ – መግረም	to astonish
geSS	ገጽ	page, face
geTer	ገጠር	uncultivated, underdeveloped
geTTeme - megTem	ገጠመ – መግጠም	to encounter, to come accross, to face, to join, to compose
Torinnet megTem	ጦርነት፡ መግጠም	to fight
gezza - megzat	ገዛ – መግዛት	to buy, to rule
geži / gež	ገዢ/ገዥ	head, chief
gize	ጊዜ	time
beyyegizew	በየጊዜው	often, everytime
gibbi	ግቢ	palace, compound
yegibbi minister	የግቢ፡ ሚኒስቴር	Ministry of the Imperial Court
gibr	ግብር	tax; banquet
gibrinna	ግብርና	agriculture, farming
gibS	ግብጽ	Egypt
gibža	ግብዣ	party, reception, invitation

gidd	ግድ	necessary
giddellem	ግድ፡የለም	never mind
giddeta	ግዴታ	obligation
giddib	ግድብ	dam
gidgidda	ግድግዳ	wall
gilibbaC	ግልባጭ	copy
gilS	ግልጽ	clear, open
begilS	በግልጽ	clearly
gilS mekina	ግልጽ፡መኪና	convertible
gimel	ግመል	camel
gimjabet	ግምጃ፡ቤት	treasury, treasurer; storage
gimmaš	ግማሽ	half
gimmit	ግምት	estimate
gin	ግን	but
ginbar	ግንባር	forehead
ginbot	ግንቦት	September
gind	ግንድ	timber, beam, trunk (of a tree)
ginniññunnet	ግንኙነት	connection, communication, relationship
girge	ግርጌ	bottom, lower part
girik	ግሪክ	Greek
girmawi	ግርማዊ	Majesty (adj.)
girmawinnet	ግርማዊነት	Majesty (n.)
gizat	ግዛት	territory, area
gižži	ግዢ	purchase
gobeññe - megobñet	ጎበኘ – መጎብኘት	to visit
godana	ጎዳና	street avenue
godda - megudat	ጎዳ – መጉዳት	to damage, to harm, to hurt
gojjam	ጎጃም	Gojjam (province)
gojjo	ጎጆ	hut
gomma	ጎማ	tire
gommen	ጎመን	cabbage
gon	ጎን	side

gonlagon	ጎንለጎን	side by side
gorade	ጎራዴ	sword
gorebet	ጎረቤት	neighbor
goremsa	ጎረምሳ	young man, youth
gorf	ጎርፍ	flood
gottete - magottat	ጎተተ — መጎተት	to drag, to pull
gra	ግራ	left
graCCa	ግራጫ	grey
grañ	ግራኝ	left handed
grum	ግሩም	excellent, magnificent
guba'e	ጉባኤ	assembly, confrence
gubbo	ጉቦ	bribe
gubiññit	ጉብኝት	visit
gudat	ጉዳት	harm, damage, loss
guday	ጉዳይ	business, affairs; minus
gudgwad	ጉድጓድ	pit, well
gugs	ጉግስ	an Ethiopian tournament game
gulbet	ጉልበት	knee; strength
gulmasa	ጉልማሳ	youth
gulo	ጉሎ	castor oil seed
gum	ጉም	fog
gumarre	ጉማሬ	hippopotamus
gumruk	ጉምሩክ	custom house
gunC	ጉንጭ	cheek
gunfan	ጉንፋን	cold (ailment)
gurorro	ጉሮሮ	throat
gurša	ጉርሻ	tip, mouthful
guzo	ጉዞ	trip
gwaddañña	ጓደኛ	friend, colleague
gwaro	ጓሮ	yard

h

habt	ሃብት	wealth
habtam	ሃብታም	rich
habtamɪnnet	ሃብታምነት	richness
hadid	ሐዲድ	railroad
hakim	ሐኪም	doctor (MD)
hakimbet / hospital	ሐኪም፡ቤት/ሆስፒታል	hospital
haKK	ሐቅ	truth
halafinnet	ሃላፊነት	responsibility
hamle	ሐምሌ	November
hamus / amus	ሐሙስ/አሙስ	Thursday
harer	ሐረር	Harar (city)
hararge	ሐረርጌ	Hararge (province)
harr	ሐር	silk
hassab / assab	ሃሳብ/አሳብ	thought, idea
hasset	ሃሰት	false; lie
hateta	ሃተታ	detailed account
haTiyat	ኃጢአት	sin
haya	ሃያ	twenty
hayɪK / hayK	ሐይቅ	lake
hayl / hayɪl	ኃይል	strength, power
hayleñña	ኃይለኛ	powerful
hayleññannet	ኃይለኛነት	powerfulness
hayle sɪllase	ኃይለ፡ ሥላሴ	Haile Silassi
haymanot	ሃይማኖት	religion
hazen	ሐዘን	sorrow, distress, mourning
hede-mehed	ሄደ- መሄድ	to go
hɪbret	ሕብረት	collective, unity
hɪdar	ህዳር	March
hɪgg	ሕግ	law, bill, regulations
hɪgg askebbari	ሕግ፡ አስከባሪ	public prosecutor
hɪgg awweTaT	ሕግ፡ አወጣጥ	law making
hɪgge mengɪst	ሕገ፡ መንግሥት	constitution

hıggıgat	ሕግጋት	laws
hıkkımınna	ሕክምና	medıcıne (scıence)
hılm	ሕልም	dream
hımemteñña	ሕመምተኛ	patıent (n.)
hınd	ሕንድ	Indıa
hınSa	ሕንፃ	buıldıng, structure
hıSan	ሕፃን	baby
hıywet	ሕይወት	lıfe
hızb	ሕዝብ	people
yehızb Tena TıbbeKa minister	የሕዝብ፡ ጤና፡ ጥበቃ፡ ሚኒስቴር	Mınıstry of Publıc Health
hod	ሆድ	belly, stomack
hodam	ሆዳም	gourmand
hone-mehon	ሆነ- መሆን	to become
honom	ሆኖም	however
hospıtal / hakimbet	ሆስፒታል/ሐኪም፡ ቤት	hospıtal
hotel / hotelbet	ሆቴል/ሆቴል፡ ቤት	hotel
hulett	ሁለት	two
hulgize	ሁልጊዜ	always
hullu	ሁሉ	all
lehullum	ለሁሉም	ın general, anyway, at any rate
hullum neger	ሁሉም፡ ነገር	everythıng
lehullum neger	ለሁሉም፡ ነገር	anyhow, anyway
huneta / hunate	ሁኔታ/ሁናቴ	sıtuatıon, condıtıons
hwala	ኋላ	behınd
behwala	በኋላ	after

i

ikonomi / ekonomi	ኢኮኖሚ/ኤኮኖሚ	economy
illubabor	ኢሉባቦር	Ilubabor (provınce)
industri	ኢንዱስትሪ	ındustry
ityoPıya	ኢትዮጵያ	Ethıopıa
ityoPıyawi	ኢትዮጵያዊ	Ethıopıan

ı

ıbab	እባብ	snake
ıbakkıwo	እባክዎ	please
ıbd	እብድ	ıdıot, mad, ınsane
ıblət	እብለት	lıe
ıbrayısT	እብራይስጥ	Hebrew
ıda	ዕዳ	debt
ıddıl	ዕድል	chance, luck, opportunıty
ıdgət	ዕድገት	growth
ıdıf	እድፍ	dırt
ıdme	ዕድሜ	age
ıfrət	እፍረት	shame, embarassment
ıgəle	እገሌ	so-and-so
ıgır / ıgr	እግር	foot
ıgrə məngədu	እግረ፡መንገዱ	on hıs way to
ıgrəñña	እግረኛ	pedestrıan, ınfantry
ıgziyabher / ıgzer	እግዚአብሔር/እግዜር	God
ıhıl	እህል	graın, seed
ıhıt / ıt	እህት/እት	sıster
ıhud	እሁድ	Sunday
ıȷȷ	እጅ	hand
ıȷȷ mənsat	እጅ፡መንሳት	to pay respect, to bow
ıȷȷ məsTət	እጅ፡መስጠት	to surrender
ıȷȷəta	እጀታ	handle
ıȷȷıg	እጅግ	very much, too much
ıȷȷıge	እጅጌ	sleeve
ıkkul	እኩል	half; equal
ıkkulə lelıt	እኩለ፡ሌሊት	mıdnıght
ıKa	ዕቃ	thıng
ıKabet	ዕቃ፡ቤት	storage room
ılət	እለት	day
kələtat and Kən	ከለታት፡አንድ፡ቀን	once upon a tıme

ılf	እልፍ	thousands; ınnumerable
ımbi malət	እምቢ፡ማለት	to refuse (to say 'no')
ımbita	እምቢታ	refusal
ımbwa malət	እምቧ፡ማለት	to bellow
ımmete	እሜቴ	madam
ımməbet	እመቤት	lady
ınCət	እንጨት	wood
ımmət	እመት	yes ma'm; ma'm?
ımnət	እምነት	belıef, trust, faıth, confıdence
ınde ↑	እንዴ!	ah!
ındet	እንዴት	how
ındeta	እንዴታ!	certaınly, ındeed
ındə	እንደ	lıke, as
ındəgəna	እንደገና	agaın
ındəmın	እንደምን	how
ındəzzihum	እንደዚሁም	thus, and, so, moreover
ındihum	እንዲሁም	thus
ındiyaw	እንዲያው	gratıs, free of charge
ındiyawım	እንዲያውም	as a matter of fact
ıne	እኔ	I
ıngıda	እንግዳ	newcomer, guest
ıngıda təKəbbay	እንግዳ፡ተቀባይ	hotel receptıonıst
ıngıdiyamma	እንግዲያማ	well then
ıngıdiyass	እንግዲያስ	then
ıngliz	እንግሊዝ	Englısh
ınglizawi	እንግሊዛዊ	Englıshman
ınglīzıñña	እንግሊዝኛ	Englısh (language)
yəngliz agər	የእንግሊዝ፡አገር	England
ınguday	እንጉዳይ	mushroom
ınȷəra	እንጀራ	bread
ınȷi	እንጂ	though, ȷust, except for
ınȷorre	እንጆሬ	raspberrıes

ınkwan	እንኳን	bravo; even
ınKılf	እንቅልፍ	sleep
ınKulal	እንቁላል	egg
ınna	እና	and
ınnante	እናንተ	you (pl.)
ınnat	እናት	mother
ınnatınnet	እናትነት	motherhood
ınneman	እነማን	who, which (pl.)
ınneñña	እነኛ	those (pol.)
ınneññih	እነኚህ	these (pol.)
ınnessu	እነሱ	they
ınnezzih	እነዚህ	these
ınnezziya	እነዚያ	those
ınniya	እኒያ	that (pol.)
ınsıra	እንስራ	pot, jar
ınsısa	እንስሳ	animal
yebet ınsısa	የቤት፡ እንስሳ	domestic animal
ıñña	እኛ	we
ıññih	እኚህ	this (pol.)
ırdata	እርዳታ	help
ırgıT	እርግጥ	true, correct
ırgıTeñña	እርግጠኛ	exact, sure
ırguz	እርጉዝ	pregnant
ırkab	እርካብ	stirrup
ırK	እርቅ	peace
ırmıjja	እርምጃ	progress, step
ırreñña	እረኛ	shepherd
ırsaccew	እርሳቸው	he, she (pol.)
ırsas	እርሳስ	pencil
ırsbers	እርስበርስ	each other
ırsıwo / ıssıwo	እርስዎ / እስዎ	you (pol.)
ırsu / ıssu	እርሱ / እሱ	he

ırswa / ısswa	እርሷ/እሷ	she
ırša	እርሻ	agriculture
yəršа minister	የርሻ፡ሚኒስቴር	Ministry of Agriculture
yərša sıra	የርሻ፡ሥራ	farming
ırTıb	እርጥብ	mist, humid, wet
ırzımət / ırızmət	እርዝመት	lengh
ısat	እሳት	fire
ısırbet	እስር፡ቤት	prison
ıskə	እስከ	until, up to
ıskolaršıp	እስኮላርሽፕ	scholarship
ıslam	እስላም	Islam, Moslem
ısrəñña	እስረኛ	prisoner
ısti	እስቲ	how about, go ahead!
ıšši	እሺ	all right
ıšKdımdım	እሽቅድምድም	race (contest in running)
ıtege	እቴጌ	Empress
ıTa	እጣ	chance, luck, lot
ıTf	ዕጣ	double
ıwınət	እውነት	truth
bəwınətu	በውነቱ	truly, naturally, really
ıwKət	ዕውቀት	knowledge
bəlımıd yətəgeññə ıwKət	በልምድ፡የተገኘ፡ዕውቀት	experience
ıwwır	ዕውር	blind
ıyyandandu	እያንዳንዱ	each one, every one
ızzih	እዚህ	here
ızziya	እዚያ	there

J

ȷanhoy	ጃንሆይ	His Imperial Majesty
ȷəbəna	ጀበና	coffee pot, kettle
ȷəgna	ጀግና	brave, hero
ȷəgnınnət	ጀግንነት	bravery, heroism

jəlba	ጀልባ	boat
jənbər	ጀንበር	sun
jəmmərə-məjəmmər	ጀመረ– መጀመር	to begin
jərba / žərba	ጀርባ /ዠርባ	back
jərmən	ጀርመን	German
jərmənıñña	ጀርመንኛ	German (language)
jərmən agər /yəjərmən agər	ጀርመን፡አገር/የጀርመን፡አገር	Germany
jıb / žıb	ጅብ/ዥብ	hyena
jımla	ጅምላ	total, wholesale
jırat	ጅራት	tail
jografı	ጆግራፊ	geography
joniyya	ጆንያ	sack
joro	ጆሮ	ear

k

kabba	ካባ	cloak
kadə - məkad	ካደ– መካድ	to deny
kahın	ካህን	priest, clergyman
kaluss	ካሉስ	as a matter of fact
karot	ካሮት	carrot
karta	ካርታ	map
katolik	ካቶሊክ	Catholic
kəbbad	ከባድ	heavy
kəbbədə - məkbəd	ከበደ – መክበድ	to be heavy
kəbbərə - məkbər	ከበረ–መክበር	to be rich
kəbəro	ከበሮ	drum
kəbt	ከብት	cattle
kəbt rıbbi	ከብት፡ አርቢ	animal husbandry
kədda - məkdat	ከዳ – መክዳት	to betray, to desert
kəddatəñña	ከዳተኛ	traitor
kəddənə - məkdən	ከደነ – መክደን	to cover
kəfa	ከፋ	Kafa (province)
kəff malət	ከፍ፡ ማለት	to be important

keffa - mekfat	ከፋ - መክፋት	to become bad
keffele - mekfel	ከፈለ - መክፈል	to dıvıde, to pay
keffete - mekfet	ከፈተ - መክፈት	to open
keffıta	ከፍታ	heıght
keffıteňňa	ከፍተኛ	hıgh, elevated, promınent
kelekkele - mekelkel	ከለከለ - መከልከል	to forbıd, to prohıbıt, to prevent
kemmere - mekemmer	ከመረ - መከመር	to pıle up
kenfer	ከንፈር	lıp
kenne	ከነ	wıth, ındludıng
kentu	ከንቱ	vaın
kereTit	ከረጢት	bag, sack
kermo	ከርሞ	next year
kerreme - mekrem	ከረመ - መክረም	to speed the wınter; to spend several days
kesaš	ከሳሽ	plaıntıf
kesel	ከሰል	coal, charcoal
kessa - meksat	ከሳ - መክሳት	to become thın, to lose weıght
kessese - mekses	ከሰሰ - መክሰስ	to accuse
ketema	ከተማ	town, cıty
kettete - mekTet	ከተተ - መክተት	to put ınsıde, to keep, to save
ketto	ከቶ	never
kezzih	ከዚህ	from here
kezziya	ከዚያ	from there
kiray	ኪራይ	rent
kis	ኪስ	pocket
kisara	ኪሳራ	defıcıt
kıbb	ክብ	round
kıbdet	ክብደት	weıght
kıbeb	ክበብ	club, assocıatıon
kıbr	ክብር	honor
kıbrit	ክብሪት	match
kıbur (adȷ.)	ክቡር	Excellency

kɨburɨnnat (n.)	ክቡርነት	Excellency
kɨfat	ክፋት	wickedness, evil
kɨfɨl / kɨfl	ክፍል	room, class, portion, part, department
kɨft	ክፍት	open
kɨfu	ክፉ	mean, bad
kɨfunnet	ክፉነት	meanness
kɨlkɨl	ክልክል	prohibited
kɨmmɨr	ክምር	pile, heap
kɨnd	ክንድ	arm
kɨremt / kremt	ክረምት	winter
kɨrɨkkɨr	ክርክር	argument, dispute
kɨrn	ክርን	elbow
kɨrr	ክር	thread
kok	ኮክ	peach
kokeb	ኮከብ	star
kolej	ኮሌጅ	college
komTaTa	ኮምጣጣ	sour
komTaTe	ኮምጣጤ	vinegar
kopi	ኮፒ	copy
korebta	ኮረብታ	hill
kor̈ɨcca	ኮርቻ	saddle
korra - mekurat	ኮራ - መኩራት	to be proud
